30.00 ብር

# ዜና አይሁድ

## ዮሴፍ ወልደኮርዮን እንደጻፈው

ይህ መፃሐፍ የአዳም ሶስተኛ ትውልድን ከያዘው ሴት ጀምሮ የአበውን ቅደም ተከተል ያስቀምጣል ከሶስቱ የኖህ ልጆች ሲደርስ የያፌትን ልጆች ብቻ በመከተል አድማሱን ያሰፋል ወደ ነገደ እስራኤል ሲደርስ ነገደ እስራኤልን መንደርደሪያ እያደረገ የአሶራውያንን፣የባቢሎናውያንን፣የፋርሶችን፣የዮናናውያንን እና የሮማውያንን የአገዛዝ መፈራረቅ ይተነትናል በመሆኑም መጽሐፉ ለምርምር በር ከፍች ነው፡፡

አዘጋጅ፡- ገብረዮሐንስ ገብረማርያም (M.T)
የካቲቲ 2001 ዓ.ም

www.ethiopianorthodox.org

Beide Mariam Ejigu
Feb 2014

<u>ማውጫ</u>


ምዕራፍ ፩
ከአዳም ልጅ ሴት የጀመረ ታሪክ ........................................ 1
ምዕራፍ ፪
የኤልፋዝ ልጅ ሳፍዋ ታሪክ ............................................ 4
ምዕራፍ ፫
በከይተም ከሳፍዋ በኋላ የነገሡ ነገሥታት ታሪክ .................... 7
ምዕራፍ ፬
የማደይ ንጉሥ ደራ የፋርስ ንጉሥ ኮርሲ ከዮናናውያን ጋር
ጠብና የባቢሎን ንጉሥ በርስዋ ሞት.................................. 12
ምዕራፍ ፭
ከኮርሼ በኋላ የነገሱ ነገሥታት /በፋርስ/አስቴርና መርዶክዮስ
ታሪክ ከአክሶስ ንጉሥ ጋር............................................ 15
ምዕራፍ ፮
የዮናናዊ ፊሊጶስ ልጅ እስክንድር ሜቄዶንያዊ ታሪክ............... 22
ምዕራፍ ፯
የእስክንድር አርአያነት ታሪክ ........................................ 24
ምዕራፍ ፰
እስክንድር ከሞተ በኋላ የአይሁድ ዜና ............................... 38
ምዕራፍ ፱
ሃያ አራቱን መጽሐፍተ ብሉያት የተረጐመ ንጉሥ
ብልማይ ታሪክ........................................................ 41

<u>ክፍል ሁለት</u>

ምዕራፍ ፩
ዜና አንቲያኮስ መቄዶናዊ............................................. 42
ምዕራፍ ፪
የአልአዛር ካህን አሟሟት ታሪክ .................................... 43
ምዕራፍ ፫
አንቲያኮስ የገደላቸው ሰባት ወንድማማቾች ታሪክ................. 44
ምዕራፍ ፬
የዮሐንስ ካን ልጅ መታታን ታሪክ .................................. 49
ምዕራፍ ፭
የመታታን /መታታዩ/ልጅ ይሁዳ ታሪክ............................. 51
ምዕራፍ ፮
የአንቲያኮስ አሟሟት ታሪክ .......................................... 53
ምዕራፍ ፯
ዜና ምህላ.............................................................. 55


www.ethiopianorthodox.org
www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ ፰
የልዮስ ወልደ አፍድር ታሪክ........................................ 56
ምዕራፍ ፱
በሮም የተቀመጡት ነገደ ከይተም ታሪክ............................ 58
ምዕራፍ ፲
ሮማውያን ወደ መታትዩ ልጅ ይሁዳ የፃፉት መጽሐፍ ታሪክ...... 60
ምዕራፍ ፲፩
የአንትያኮስ ልጅ አፍዳር ውሉን የሻረበት ዜና ...................... 61
ምዕራፍ ፲፪
የለልያፓስ ሮማዊ ልጅ መትርያስ መውጣት ዜና.................... 63
ምዕራፍ ፲፫
የይሁዳ መገደል ታሪክ.................................................. 66
ምዕራፍ ፲፬
የማታንን /ማታትዩ/ ልጅ ዮናታን ዜና ............................ 67
ምዕራፍ ፲፭
ዜና ስምኦን ወልደ ማታትዩ............................................ 68
ምዕራፍ ፲፮
ዜና ሕርቃኖስ ወልደ ስምኦን ........................................ 69
ምዕራፍ ፲፯
የአይሁድ መለያየት ዜና ............................................ 73
ምዕራፍ ፲፰
ዜና አርስተቦሎስ.......................................................... 75
ምዕራፍ ፲፱
ዜና እስክንድር ወልደሕርቃኖስ........................................ 78
ምዕራፍ ፳
ዳግም- ዜና- እስክንድር ወልደ ሕርያቆስ ............................ 80
ምዕራፍ ፳፩
ዜና እስክንድራ ንግሥተ አይሁድና የልጆቿ ሕርቃኖስና
አርስተቦሎስ ታሪክ...................................................... 84
ምዕራፍ ፳፪
ዜና አስተሮቦሎስ ወልደ እስክንድር.................................. 86
ምዕራፍ ፳፫
ዜና እንደፌር የሄሮድስ አባት ........................................ 88
ምዕራፍ ፳፬
ዜና ፍምፍዮስ ሮማዊ...................................................... 92
ምዕራፍ ፳፭
ዜና ፍምፍዮስ ሮማዊ...................................................... 98
ምዕራፍ ፳፮
ዜና ክርሶስ ሮማዊ...................................................... 100
ምዕራፍ ፳፯
የቄሣር መንግሥት አጀማመር.......................................... 102
ምዕራፍ ፳፰
የሄሮድስ መነሳት ዜና .................................................. 106
ምዕራፍ ፳፱
ሕርቃኖስ ወደ ቄሣር ስለላከው መልእክት ዜና..................... 109
ምዕራፍ ፴
የመጀመርያው ቄሣር አሟሟት........................................ 111
ምዕራፍ ፴፩
የአርስቶቦሎስ ልጅ አንጢኮስ አነሳስ.............................. 114
ምዕራፍ ፴፪
የአንጦቦስ የፋርሱን ንጉሥ መግደል.............................. 117
ምዕራፍ ፴፫
የሕርቃኖስ ከፋርስ መመለስና አገዳደሉ............................ 120
ምዕራፍ ፴፬
የሄሮድስ የእስክንድርን ልጅ አርስቶቦሎስ የመግደል ታሪክ..... 120
ምዕራፍ ፴፭
የአንጦቦስ ከአውግስጦስ ቄሣር የማፈንገጥ ዜና ................ 127
ምዕራፍ ፴፮
ሄሮድስ እስክንድርንና ሚስቱን እንደገደላቸው የሚናገር ታሪክ.. 132
ምዕራፍ ፴፯
ዜና ሄሮድስ ............................................................. 135
ምዕራፍ ፴፰
ሄሮድስ ልጆቹን እስክንድርንና አስትሮቦሎስን እንደገደላቸው
የሚናገር ታሪክ.......................................................... 140
ምዕራፍ ፴፱
የአንደፌር ወልደ ሄሮድስና የሄሮድስ አሟሟት ታሪክ .......... 148


ክፍል አምስትና ስድስት


ምዕራፍ ፩
የሄሮድስ ልጅ አርከላኦስ ታሪክ.................................... 157
ምዕራፍ ፪
የሄሮድስ ልጅ አንጠሬስ ታሪክ .................................... 159
ምዕራፍ ፫
ዜና አግሪጳስ ወልደ አርስተቦሎስ ወልደሄሮድስ ቀዳማዊ......... 160
ምዕራፍ ፬
ዜና አግሪጳስ ወልደ አርስተቦሎስ ወልደሄሮድስ................... 162
ምዕራፍ ፭
ዜና ወልደ አናፋኒ አልአዛር.......................................... 164


www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

በዚህ በመርዶክዮስ በአስቴርና በአይሁድ ላይ ጥላቻ አደረበት፡፡

ሐማ አማሌቃዊ ነው፣ ሣኦል አማሌቃውያንን አጥፍቶ ነበር፣ የሳኦልን ቂም ለመወጣት ሐማ አይሁድን ለማጥፋት ተነሳ፡፡

ትልቁ እስክንድር የፊሊጶስ ዮናናዊና መቄዶንያዊ ልጅ ነው ፊሊጶስ በነገሠ በሰባት ዓመቱ በሰው እጅ ተገደለ፡፡ የአገዳደሉ ሁኔታ እንዲህ ነው፣ የፊሊጶስ ሚስት ለአመንዝራነት ፋሬስ የተባለው የጦር መሪው ጠይቆ እሺ አሰኘት፣ አስቀድሞ ግን ባልዋ ፊሊጶስ የእስክንድር አባትን ለመግደል ወስኖ አመቺ ጊዜ ይፈልግ ነበር፡፡

ጠላቶች ተነሥተው የፊሊጶስን ግዛት ወረሩ በዚህ ጊዜ ፊሊጶስ ሹማምንቱን በያቅጣጫው ለጦርነት ላካቸው፡ የሃያ ዓመት ወጣት ልጁን እስክንድርንም በሌላ አቅጣጫ ላከው፣ ፋሬስ በዚህ ጊዜ የፊሊጶስ ለብቻው መቅረት ተመለከተ፡፡ ወዳጆቹንም ሰብስቦ ቤተመንግሥቱን አስከበበው፡፡ በዱላም ፊሊጶስን ቀጠቀጠውና ወደቀ ይህን ሰምተው የከተማው ሕዝቦች ተጨነቁ፣ ወድያው እስክንድር ከጦር ሜዳው ሲመለስ የሕዝቡ ዋይታን ሰማ አባቱ እንደተደበደበም አወቀ፡፡ በሩጫ ቢሄድ አባቱ ወድቆ እናቱ በፋሬስ ታሥራ አገኛቸው፣ ወዲያው እስክንድር ፋሬስን ገደለው፡፡ አባቱን ፊሊጶስም ወድያው ሞተ፣ እስክንድርም ነገሠ፡፡

በቤተ መቅደስ ሊቀካህናት አልአዛር ነበር፡፡ አልአዛር ደግ ሰው ነበር፣ ካህኑን አልአዛር ክርሶስ የተባለ ሮማዊ የቤተመቅደስን ንብረት በሙሉ እንዲያስረክበው ጠየቀው፡፡ አልአዛር እስካሁን የሮም ነገሥታት ቤተመቅደስን አከበሩ እንጂ አልዘረፉም አንተ ይህን እንዴት ታደርጋህ አለው፡፡

አልአዛር ሦስት መቶ ግራም ወርቅ ራሴ እሠጣህለሁ አንተ ግን በሥልጣንህ አትዝረፍ አለው እሱ ግን እንቢ ብሎ ያለውን ወርቅ ሁሉ ዘረፈና ፋርስን ለመውጋት ሄደ ግን በፍርሶች ተቸነፈ፡፡

ሮም በሕዝብ በተመረጡ አባላት ትመራ ነበረ፡፡ ተመራጮቹ በነሱ ተመርጦ ያገር መሪ የሚሆነው ሸማግሌ ይባል ነበር፣ የሸማግሌው ሚስት በርግዝና ላይ እያለች ሞተች፣ፅንሷ የአምስት ወር ነበር፡፡

እጅግም ተጨነቀች ትበላው ዘንድ ወሰነች እያየሁት በረሀብ ከሚሞት ራሴ ገድዩ ሥጋውን ልብላው አለች፡፡ ረሀቡ በልጅዋ ላይ እንድትጨክን ገፋፋት፣ እንዲህም አለችው እንደዓይን ብሌን የምሳሳልህ ልጄ ሆይ ዕድሜ አግኝተህ እኔ ሳረጅ በንብረቴ እንደታገዘበት ስሞትም ትቀብረኝ ዘንድ ምኞቴ ነበር፣ ያንተንም ሞት እንደያሰየኝ እማፀን ነበር፡፡

በዚህ መጥፎ አሟሟት ከምትሞት ምነው አስቀድመህ በሞትክ ኑሮ፡፡ ራሴ ቀብሬ ወደ እግዚአብሔር አደራነት አስረክብህ ነበር፡፡ ልጄ አሁን በከባድ ዐፀባ ውስጥ ተይዘናል፡፡ እኔም አንተም ልንሞት ነው አንተ ስትሞት ማንም ቀባሪ የለህም በሜዳው ሬሳህ መውደቁ ነው፡፡ ስለዚህ ገድየህ ከረሀብ እንደታርፍ ወስኛለሁ፣ ገድየም ሥጋህን የትም አልጥለውም እበላሀለሁ በርግዝና የተሸከመችህ ሆዴ መቃብርህ ልትሆን ነው፡፡ እኔም አንተን በልቼ ከረሀብ እድናለሁ ካንተ እጠብቀው የነበረው አንተ ለኔ የምታደርገው መልካም ሁሉ በዚህ ይለወጣል፡፡

እነዚህ ኢየሩሳሌም በጥጦስ ተከባ ለዚህ እንድትበቃ ምክንያት የሆኑ እሥራኤላውያን ይህ ክፉሥራ ታሪካቸውን እንዳበላሸ ይኖራል ካለች በኋላ ልጇን ዘልላ ያዘችውና ጉራዴውን አንስታ አንገቱን ቆረጠችው እሱም ሞተ ወድያው ከሥጋው ለጊዜው የሚበቃትን ቆርጣ በእሳት ጠብሳ በላች የቀረውን አስቀመጠች፡፡

ጢሱን የተመለከቱ ረሃብተኞት በቅፅበት መጡና እየተቆጡ ከበላችው ነገር ተሎ ሥጭን አሏት ከበላሁት እሠጣችሁ አለሁ ተቀመጡ አለቻቸው ማዕድ የሚቀርብበትን ዕቃ አስቀድማ ካዘጋጀች በኋላ የልጇን አስከሬን ከላዩ ላይ ከመረችላቸው፡፡የምወደውን ልጄ በገዛ ራሴ ገድዩ ስለራበኝ ከሥጋው በላሁ እናንተም የኸውላችሁ ብሉ አለቻቸው እነሱም እጅግ ደንግጠው ትተውት ሮጡ፡፡የአይሁድ መከራ እጅግ የከበደው በጥጦስ ወረራ ነው፡፡ አይሁድ በቤተመቅደስ ውስጥ እርስበርሳቸው ተራርደው ቤተመቅደሱ በደም አጥለቀለቁት፡፡

www.ethiopianorthodox.org
www.ethiopianorthodox.org

ወደ ጥጦስ መልዕክት ልከው ፍቀድልንና ካገር እንውጣ አሉት እሱም ካላችሁበት ጥቂት ቆዩ አላቸው ካህኑ ዮሴፍ ወልደኮርዮን ቤተ መቅደስ እንዳትቃጠል ባለው የጥጦስ ባለሟልነት ከሮማውያን ወታሮች መርጦ እንዲጠብቁ አድርጎ ነበር፡፡ ሐናንና ስምኦን ጠባቂዎቹን ወታደሮች ድንገት ደርሰው ገደሉዋቸው ይህን ሁሉ በመጨረሻ ረሀብ ስለፀናባቸው ልብሰመንግሥትን ለብሰው ወደ ጥጦስ ገቡና እጃችንን በፈቃዳችን ሳንተ ሰጠን አሉት እሱም ወዲያው ገደላቸው፡፡

አልዓዛር የተባለው ካህን ከዚህ ሁሉ እልቂት አምልጦ በሌላ ቦታ ተደብቆ ቆየና ጥጦስ መላ ኢየሩሳሌምን ተቆጣጥሮ ሲያበቃ በየጉራንጉሩ የተደበቁትን አይሁድ አድኖ ለመያዝ ከኢየሩሳሌም በወጣ ጊዜ በሮማውያን እጅ መውደቃቸውን ያመኑ አይሁድን እንዲህ አላቸው ለሮማውያን ባሮች ከምትሆኑ ልጆቻችሁንና ሚስቶቻችሁን በሙሉ በገዛ እራሳችሁ አርዳችሁ ጨርሱ አላቸው፡፡ እነርሱም የገዛ ልጆቻቸውንና ሚስቶቻቸውን ጨረሱዋቸው በመጨረሻም ወንዶቹ እርስበርሳቸው ተራርደው አለቁ፡፡

ይህ በአጭሩ የተገለፀው መጽሐፍ ሙሉውን በማንበብ ጠቅላላ ታሪኩን መገንዘብ ይቻላል፡፡

## ምዕራፍ ፩

## ከአዳም ልጅ ሴት የጀመረ ታሪክ

በአካላት ሦስት በሚሆነው አንድ እግዚአብሔር የእርሱን ኃይል መጠጊያ አድርገን ዜና አይሁድን መጻፍ እንጀምራለን፡፡ ይህ መጽሐፍ ከዮሴፍ ወልደ ኮርዮን መጽሐፍ ጋር የሚቀራረብ ሲሆን የህዝበ እስራኤል ማስታወሻ የነገስታቶቻቸው ታሪክ የቤተ መቅደሳቸውን ታሪክ እና ቤተ መቅደስ ከተሰራበት ጀምሮ የተፈጸመውን እንዲሁም የምርኮኞችን ታሪክ በስምንት ክፍል ተከፍሎ በዚህ ይቀርባል፡፡

ጸሃፊው ከዘመን ዘመን የተጻፉትን ታሪኮች እስከ መጨረሻቸው ያለውን እየጠቀሰ ፅፏል፡፡ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን ይቅርታም በሁላችን ላይ ይደር አሜን፡፡

አዳም ሴትን ወለደ ሴት ሄኖስን ወለደ ሄኖስ ቃይናንን ወለደ ቃይናን መላልኤልን ወለደ መላልኤል ያሬድን ወለደ ያሬድ ሄኖክን ወለደ ሄኖክ ማቱሳላን ወለደ ማቱሳላ ላሜህን ወለደ ላሜህ ኖኅን ወለደ ኖኅ ሴምን ያፌትን ካምን ወለደ ያፌት ሆምን ማዓግንና ማዳይን በዋን ዮናልን ያስህንና ሬስን ወለደ፡፡

ሆም እስካርን ረተቅምንና በግርማን ወለደ በዋን አልባልታን በርሴበን ከይተምንና ጸደይ ተምን ወለደ እነዚህ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት የያፌት ለጆችና የልጅ ልጆች ናቸው፡፡ የነበሩበትም ቦታ ይታወሳል በዚህ መሰረት የማደይ ወገኖች ኲራሶን የተባለውን ምድር ያዙ የመዋን ወገኖች ግን ዮናናውያን ናቸው የነሱም ይዞታ መቄዶንያ ይባላል፡፡

የዮባል ወገኖች ደግሞ ሰባኒ ተብለው ቡሳኒ የተባለውን ምድር ይዘዋል ቡሳኒ ሬሳ በተባለው ወንዝ አጠገብ ይገኛል፡፡ የማሱ ወገኖች ከኩሳኒ

www.ethiopianorthodox.org



www.ethiopianorthodox.org

የተባለውን ነገድ ይዘዋል የቴራስ ወገኖች ደግሞ ሮምን የያዙ ናቸው፡፡ በኮበር ወንዝ ተቀምጠዋል ሸክሸሪና ገልሲስ አንድ ነገድ በመሆን በባህር ውስጥ በሚገኙ ደሴቶች ተቀምጠዋል፡፡

አብዛኞቻቸው ፋርሶስ ይባላሉ ራይብ የተባለውንም ምድር ይዘዋል የጸበደኒ ነገዶች ሰብስብ የተባለውን ወንዝ ዙርያ ይዘዋል፡፡ የዚፋኑ ወገኖች ፋሪሱሳ ተብለው ከኡሪ ወንዝ በላይ የሚገኘውን አንጠፋ የተባለውን ምድር ይዘዋል የኡራ ወንዝ ዙሪያም ይዞታቸው ነው የበግርማ ነገዶች ገርባርና ነፍሲቅ የተባሉትን ነገዶች እንዲሁም ሳለን በልጉርን ዝዮኖን ቦጥኮክን ሐምበርን ሐራህርን ወልሚድን አፌፍርንና አሰቡህን አጠቃልለው ባንድ ነገድ ተጠርተዋል እነዚህ ሁሉ ወደ ግራ በኩል ምድርን ይዘዋል፡፡

የይዞታ በታዎቻቸውን ስም ከስማቸው ጋር የተያያዘ ሆነዋል ከመካከላቸው አጥናላባወር በተባሉ ወንዞች መካከል የተቀመጡ አሉ የናብሲቅና የለባርገር ከዲዮኒ ሁድባና ለብሳ በተባሉ ወንዞች አጠገብ ተቀምጠዋል እነሱ አልመልባ በመባልም በተራራዎች ተቀምጠዋል የሰምነንዋ ነገደች የአንብጦልያን ወንዝ ተጠግተው ተቀምጠዋል እስከአሁን ድረስም ከውና ብሰባ በተባሉ ወንዞች ይኖራሉ፡፡

የበርሴስ ነገዶች ወደ ሜቄዶንያ ገብተዋል እስከ ጠርሶስ ወንዝ ድረስም ያለው ቦታ የነሱ ነበር የእስማኤል ልጆች ባሸነፍዋቸው ጊዜ ግን ከጦርሶ ወጥተው ሸሹ፡፡

የከይቶም ወገኖች መኔር ከተባለው ወንዝ በላይ ከሚገኘው ጳባኒያ በተባለው ሃገር ተቀመጡ ይህ ወንዝ ሮምን አቋርጦ የሚፈስ ነው ፀደቲምና በነኩር በተባሉ ነገዶች ከውቅያኖስ ውስጥ በሚገኙት ደሴቶች ሰፍረዋል ይህ ውቅያኖስ ባህር ምድርን በመላ የሚከብ ነው፡፡



የመጽሃፍ ደራሲ /አዘጋጅ/ ‹‹ከጥፋት ውሃ በኋላ ከብዙ ቦታ ተሰባስበው በአንድ ቦታ ተሰብስበው ተቀምጠዋል ቋንቋቸውም አንድ ነበር ነገር ግን እግዚአብሔር ወደ ተለያየ አገር በተናቸው ቋንቋቸውንም ከፋፈለ ቃላታቸውንም ከፋፈለ የተለያዩ ህዝቦችም ሆኑ›› ይላል፡፡ ጸሐፊው በመቀጠልም አግዚአብሔር የአዳምን ልጆች ከከፋፈላቸው በኋላ የከይተም ልጆች ወደ ምድረ አስበኒያ ሄዱ ከበከሮን ወንዝ አጠገብም ኖሩ የአሞፋል ልጆች በበኩላቸው ወደ ምድረ ቦስያ ሄዱ የዮባል ልጆች ደግሞ አገርን ቆረቆሩ /አቀኑ/ ሳባኒያንም በማለትም አገራቸውን ሰየሟት የሰየምዋትም በቅኝዋ ስም ነው ብሏል፡፡

የከይቶም ወገኖች የአባቶቻቸው ወንድማማች የሆኑትን የዮባል ለጆች አማቾች ለመሆን ወደዱ ሴቶች ልጆቻቸውንም ሊያገቧቸው ፈለጉ ነገር ግን የዮባ ልጆች ታበዩባቸው የነሱን ጋብቻ አልፈለጉትም ከጥቂት አመታት በኋላ የዮባል ልጆች አዝመራቸውን ለመሰብሰብ መጡ ሰባኒያንኑ በተባለች አገራቸውም ወንድ አልባ ሆነች ብዙዎች ከከይተም ተሰብስበው ወደ ሃገረ ሰባኒያን ሄዱና ወደ ማህል አገር ገብተው ከልጃ ገረዶች ያገኙዋቸውን ሁሉ ማረኩ በከፍተኛ ተራራ ወደ ሰሩት ቤታቸውም ወሰዱዋቸው፡፡

የዮባል ልጆች ሴቶች ልጆቻቸው እንደ ተማረኩ ባወቁ ጊዜ ይዋጓቸው ዘንድ /የከይተምን ሰዎች/ ወደ ከይተም ሄዱ ነገር ግን አልቻሏቸውም በዚችውም ዓመት ከነሱ ተወገዱ እንደገናም የዮባል ልጆች የከይተመን ልጆች ለመዋጋት ተነሱ በዚህ ጊዜ የከይተምን ልጆች ከነሱ ልጆች የወለዷቸውን ልጆች አሰልፈው ጠበቋቸው የተወለዱትም ልጆች እንዲህ አሏቸው ‹‹የከይተምን ህዝቦች ብትገድሉ እኛን ከእናንተ ሴቶች ልጆች ሴቶች ልጆቻችሁን የምንገድል መሆናችንን እወቁ ስለዚህ የከይተምን ህዝብ በጠላትነት መመልከታችሁን አቁሙ ምህረትንም አድርጉልን›› አልዋቸው፡፡

www.ethiopianorthodox.org

የዮባል ልጆች ይህንን ሲሰሙ ጦርነቱን አቆሙ ከአነሱም ራቁ በሰላምም ወደ ሃገራቸው ተመለሱ፡፡

## ምዕራፍ ፪

## የኤልፋዝ ልጅ ሳፍዋ ታሪክ

ሳፍዋ የኤልፋዝ ልጅ የኤሰ. ልጅ የይስሐቅ ልጅ የአብርሃም ልጅ ነው ሰላም ለሱ ይሁንና ይህ ታሪክ የከይተም ወገኖችንም ይጠቅሳል፡፡

የመጽሐፉ ደራሲ /በዓለ መጽሐፍ/ እንዲህ ይላል ‹‹የያዕቆብ ልጅ ዮሴፍ ገ'ም ወደተባለው ቦታ አባቱ ያዐቆብን ለመቅበር በመጣ ጊዜ የኤሰ. ልጆች አገኙት ጦርነትንም ገጠሙት ዮሴፍ ግን አሸነፋቸው እና የኤልፋዝን ልጅ ሳፍዋን አሰረው ብዙዎችንም የሳፍዋን ተከታዮች ዓገርኮ በእስረኝነት ወደ ግብጽ ወሰዳቸው ወደ አፍራቂያ ንጉሥ አእሳም ወስዶ አስረከባቸው የአፍራቂያው ንጉሥም ዮሴፍን በታላቅ ደስታ ተቀበለው፡፡

በዚሁ ወቅት ፆፁ የሚባል ሰው በምድረ ከይተም ነበር በከይተም ህዝብ ዘንድም ይህ ፆፁ የተባለው ሰው በታላቅነት ይታይ ነበር ይህ ሰው ወንድ ልጅን ሳይተካ /ሳይወልድ/ ሞተ ማህያ የምትባል ሴት ልጅ በቻ ነበረችው ማህያ በተፈጥሮ ውበቷ እጅግ ያማረች እና ቆንጆ ነበረች የአፍራቅውያው ንጉስ አእሳስ አጭቶ እንዲያገባት ላከባት የነነዌው ንጉስ ኖርዮስ በበኩሉ ለራሱ አነዲያገባ ላከባት የከይተም ህዝቦች በዚህ ጊዜ ወደ ነነዌው ንጉሥ ቦርቦስ /ኍርዮስ/ አንተ ለጋብቻ ማህያን ፈልገህ ከመላክህ አስቀድሞ የአፍራቅያ ንጉሥ አእሳስ ለጋብቻ ጠይቋታል አንሰጥህም ብለን ብንከለክለው አገራችንን ያመዘብራል/ያጠፋል/ እኛም ልንቋቋመው አንችልም አንተም ከሱ ጠብ ልታድነን አትችልም በማለት ላኩበት፡፡

በሌላ በኩል የነነዌው ንጉሥ ቦርቦስ /ኍርዮስ/ የፆፁን ልጅ ማህያን ሊያገባ መጠየቁን ለአፍራቅያው ንጉሥ አእሳስ ላኩበት ነገር ግን የነነዌው ንጉሥ ቦርቦስ/ኖርዮስ/ ፈጥኖ ሊዋጋቸው ከነ ሰራዊቱ ወጣባቸው እነሱም የአፍራቅያው ንጉሥ አእሳስን የድረስልን ጥሪ ላኩበት አእሳስም ቦርቦስን ለመዋጋት ተነሳ ሁለቱ በምድረ አስባንያ ተገናኙ በመካከላቸው ከባድ ጦርነት ተካሄደ የመጀመሪያው ድል ግን ለነነዌው ንጉሥ ቦርቦሥ ሆነ ከአፍራቅያው ንጉሥ አእሳስ ብዙዎችን ገደላቸው በሁለተኛው የጦርነት ፍልሚያ ደግሞ እንደገና ድሉ ለአፍራቂያው ንጉሥ ለአእሳስ ሆነ የነነዌው ንጉሥ ቦርቦስን ገደለው ሰራዊቶቹንም ባሮቹ አደረጋቸው የቦርቦስን አስከሬን ወደ ብረት ሳጥን አስገባው የቦርቦስ ወንድም የሆነው የፋሌስ ደግሞ በወርቅ ሳጥን እንዲገባ አደረገ ሁለቱን ቀበራቸው በመቃብራቸው ላይም አዳራሾችን በመንገደኞች እንደሚታይ አድርጎ ሰራ እነዚህ ግንቦች እስከአሁን ድረስ በአልባቡና በሮሚያ መካከል ይገኛሉ፡፡

አሸናፊነቱን ካረጋገጠ በኋላ አእሳስ የፆጹን ልጅ ምሕያን አገባት ቅርጣግና ወደ ተባለውም አገሩ ወስዶ ቤተ መንግሥቱ አስገባት ነገር ግን ጥቂት ግዜ እንደቆየች በከባድ በሽታ ተያዘች ደዌዋም እጅግ በረታ አእሳስ አሉ ከተባሉት ባለ መድኃኒቶች ከህመሟ ይፈውሷት ዘንድ አዘዘ የበሽታዋ ምክንያት ምን እንደሆነ ይነግሩት ዘንድም ጠየቃቸው፡፡

እነሱ ግን እሷ ምንም ምክንያት የላትም ልትታመም የቻለችው የንፋስ ለውጥና ያልተለመደውን ውሃ በመጠጣትዋ ብቻ ነው አገርዋ እያለች እየመነጨ ከሚመጣው ውሃ ትጠጣ እንደነበር ሰምተናል አሉት፡፡

ንጉሡ አእሳስ ከዚያችው እነሱ ከጠቀሷት ምንጭ ውሃ እንዲመጣ አዘዘ ይህንን ውሃ መዘነውና ከሱ አገር ወሃ ለመጠጥ የቀለለ ሆኖ አገኘው ወዲያው ከዚሁ የከይተም አገር የውሃ ምንጭ ቦታ አንስቶ አገሩ አፍራቅያ


www.ethiopianorthodox.org

ድረስ እስከ ቤተ መንግስቱ ቅርጣግና የውሃ መውረጃ ቦይን አስቆፍሮ ሰራ ከሃገረ ከይተምም አፈርንና ድንጋይ አስወስዶ አዳራሽንና የመኝታ ክፍልን ሰራላት።

ይህንን ሁሉ ለማድረግ የተገደደው ምሕያን ስለወደዳት ነው የመንግስቱ ሰዎችንም እጅግ ወደዳቸው በእነዚህ ዘመናት የአፍራቅያ ህዝቦች በየጊዜው በመዘመትየከይተምን ህዝቦች ያስጨንቋቸውና ንብረታቸውንም ይዘርፏቸው ነበር።

የኤልፋዝ ልጅ ሳፍዋን ከነነዌ ህዝቦች ጋር ሆኖ የአፍራቅያን ሕዝቦች አብሮ ለምውጋት ተሰልፎ ነበር የነነዌ ሰዎች ሲሸነፉ ሳፍዋ ወደ ከይተም ሸሽቶ ተቀምጦ ነበር በከይተም ኑሮው አመቻችቶ ለመኖር ጀመረ።

አሰራዋስ ያሁሉ ሲሆን ገና ሕጻን ነበር ሲያድግ ግን ጦረኛ ሆኖ ሰራዊት እየመራ ወደ አፍራቅያ ዘመተ የአፍራቅያ ህዝቦችን ከንጉሣቸው ጋር አሸንፎ በመማረክ ወደ ከይተም አመጣቸው የከይተም ህዝቦች ደግሞ በከባድ ተራራ ላይ መሸጎ የኤልፋዝ ልጅ ሳፍዋን ከመሸጉት ጋር ነበር በተራራም ላይ እያለ ሳፍዋ ምግብ ፍለጋ ተቀሳቀሰና አንድ አንበሳ በሬ ገድሎ እየበላ አገኘው ሳፍዋ በያዘው የጦር መሳሪያ አንበሳውን ገደለው ወደ ከይተምም ተመለሰ። አንበሳ መግደሉንም ለከይተም ህዝቦች ነገራቸው እነሱም አለቃቸው አደረጉት ከፍ ከፍም አደረጉት ምክንያቱም ይህ አንበሳ ከብቶቻቸውን ጨርሶ ከመብላቱም የተነሳ ህዝቡ እጅግ ተቸግረው ነበር እና አንበሳውንም ለመግደል አንድም የደፈረ አልነበረም። ስለዚህ በአንበሳው መገደል ህዝቡ እጅግ ደስ አለው።

ህዝቡ ሳፍዋን ከአንበሳው ጭንቀት ስላዳናቸው ከእለት እለት ሳፍዋንን አከበሩት ምን እንደሚያድርጉለትም ተማከሩ በየአመቱም ፍሪዳን እያረዱ በአል እንዲያደርጉለት ወሰኑ በበዓሉ እለትም እጅ እንዲነሱለት ተስማሙ



‹‹የኖስ›› ብለው ሰየሙት በእነሱ ቋንቋ የኖስ ማለት አንበሳ ማለት ነው። ስለዚህ ሳፍዋን በዚሁ ስም ሰየሙት።

የአፍራቅያ ህዝቦች እንደለመዱት ከይተምን ለመውረር ወደሷ ሄዱ በዚህ ጊዜ ሳፍዋን ሊገጥማቸው ወጣ የከይተም ሰዎች በሱ መሪነት ለጦርነት ተሰለፉ ስለዚህ የአፍራቅያን ህዝቦች አተነፈስዋቸው ከነሱም ብዙዎችን ገደሉ የቀሩት በከባድ ሽሽት ህይወታቸውን አተረፉና ወደ አፍራቅያ ተመልሰው ወደ አገራቸው ገቡ።

የከይተም ህዝቦች ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በአፍሪቅያ ህዝቦች አልተወረሩም እረፍት ሆነላቸው ሰፍዋንም እጅግ አመሰገኑት ከመጠን በላይም አከበሩት ከላያቸውም ላይ አነገሡት የንጉሥነትም ስሙ ‹ዮኖስ› ተባለ /አንበሳ/ አሉት የሚያመልኩትም ኮከብ ‹አቅርቦሰስ› ይባል ነበር ይህ ኮከብ ዘሀልም ይባል ነበር።

ሳፍዋ በከይተም ከነገሠ ጀምሮ እጅግ በረታ የዮባልንም ልጆች በኃይል ማረኩዋቸው አሕዛብንም ሁሉ ድል አደረግዋቸው በአካባቢውም አህጉር ሁሉ ስሙ እጅግ ገነነ የመንግሥቱ አመራርም ተቃናለት። ሳፍዋ አስባንያ ለተባለችው ሀገር የመጀመሪያው ንጉስ ነው ዘመነ መንግስቱ ሃምሳ አምስት ዓመት ይሆናል።

## <u>ምዕራፍ ፫</u>

## <u>በከይተም ከሳፍዋ በኋላ የነገሡ ነገስታት ታሪክ</u>

ሳፍዋ ከሞተ በኋላ ከሱ ቀጥሎ አፎርፎስ ሃምሳ ዓመት በከይተም ነገሠ ከአፎርፎስ ቀጥሎ ፎንቦስ ነገሠ ይህ ንጉስ ልጥርስም ይባላል ይህ ንጉሥ አቅጢኖስ የተባለችውንም ሀገር ደርቦ ለመያዝ ችሎ ነበር ከከዋክብት

www.ethiopianorthodox.org

አቆጣጠር ጋር የተያያዘ ጽሕፈት እሱ ማፍለቅ ጀመረ:: ዙሐል ለተባለውም ጣኦት ትልቅ ግንብ ሠርቷል ብዙ መርከቦችንም ለመስራት ችሎአል:: መርከቦቹም ዙሐል ለተባለው ጣኦት አገልግሎት ይውሉ ነበር::

ይህ ንጉሥ ወደ ቅርጣግና ሄደ አካሄዱም አስዳዊልስን ለመውጋት ነበር አስጻዊልስ የአፍሪቃውያን ንጉሥ አእሳስ ልጅ ነው:: የአስዳዊልስ ልጅ ሶፎኒያን ለማግባት ስለፈለገ ነው አባቷን ሊወጋ የተነሳው:: ያስዳዊልስ አባት አእሳስ በከይተም የነበረችውን የኦፁን ልጅ ማህያን ለመውሰድ እንዳደረገው ጦርነት ያለ ነው::

ሶፎንያም እንደ ማህያ ቆንጆ ነበረች ሶፍንያ ሰባ ዓመት እስኪሞላት ድረስ በቁንጅና የበላይነትን እንደያዘች ቆይታለች:: ብዙዎቹ በእሷ ፍቅር ስለተነደፉ የእሷን ስዕል በልብሳቸው ላይ ያጣብቁት ነበር:: ይህ ንጉሥ ጢኖስ የሚል ድርብ ስምም ነበረው:: ይህ ጢኖስ ሠራዊቱን አስከትሎ መጣና በቅርጣግና ተቀመጠ:: ጦርነትንም ከፍቶ ሀገሪቷን ወጋ አእሳእ ከቆንጆዋ ማህንያ ፍቅር የተነሳ የሠራውን የውሃ ቦይ ቆረጠው የከተማዋን ግማሽ አፈረሰ::

አስዳዊስልም በበኩሉ ጦርነት ሊገጥመው መጣ በመካከላቸው ትልቅ ጦርነት ተካሄደ በጦርነቱ አስዳዊስል ሞተ ለጢኖስ የአስዳዊስልን ወታደሮች ወደ ባርነት አግብቶ ገዛቸው:: ወዲያውም ሶፎኒያን ወደምትገኝበት ከተማ ገብቶ ሶፎኒያስን ወሰዳት ሶፎኒያስ የአስዳዊስል ልጅ ናት አባቷን ገድሎ እሷን ወሰደ ማለት ነው ወደ ከይተምም ወሰዳት:: የጢኖስ ክብር እጅግ ከፍ አለ ለአርባ አምስት ዓመትም ነገሠ ከዚያ ሞተ ከሱ ቀጥሎ አንትያኮስ ነገሠ ለሰላሳ ስምንት ዓመትም በንጉሥነት ተቀመጠ::

ከአንትያኮስ ቀጥሎ ስለኪሉስ ለሃያ ዘጠኝ ዓመት ነገሠ ከሱ ቀጥሎ ለጢናስ 50 ዓመት ነገሠ ከዚያ ሞተ:: ለጢናስ መንሳንና በርነርያ የተባሉት



ሀገሮች በማስገበሩ ይታወቃል:: ዙፍራ ለተባለው ጣኦትም ይህ ንጉሥ ምኩራብን ሰርቷል:: ዙሐል ለተባለው ጣኦት የተሠራውን ምኩራብ ግን አፈረሰው የዚሁ ጣኦትን ካህናትንም በእሳት አቃጥሎ ፈጃቸው:: በእሳት ያቃጠላቸውም እራሱ ለዝኍራ በሠራው ምኩራብ እየሰበሰበ ነው ከዚያ እራሱ ሞተ::

ከሱ በኋላ አንፍአስስ ለአስራ አራት ዓመት ነገሠ ከአንፍአስስ ቀጥሎ ከርፌጦስ ሃያ ስምንት ዓመት ነገሠ ቅዱስ መጽሐፍ እንደሚነግረን የአስርፋስ ንጉሥ በወራሪነት በዘመኑ ተነስቶ ነበር ከከርፌጦስ ቀጥሎ አብቦክስ ሰላሳ ሦስት ዓመት ነገሠ ከአቦክሰስ ቀጥሎ ካልዕ አቦክስ ሃያ ስምንት ዓመት ነገሠ ከካዕል አቦክስ ቀጥሎ አፍስጦስ ሃያ ስድስት ዓመት ነገሠ ከአፍላጦስ ቀጥሎ አፍሮክስ ሰላሳ ሦስት ዓመት ነገሠ ከሱ ቀጥሎ ሮሞሉስ ሰላሳ ስምንት ዓመት ነገሠ ሮሞሉስ በስልጣን ላይ እያለ የእስራኤል ንጉሥ ዳዊት ኤዶምንና ኤርሞንን ድል አደረጋቸው ስፍር ቁጥር የሌላቸው ሰዎችንም ከነዚህ ሀገሮች ገደለ ከሞት የተረፉትም ወደ ሀገረ ከይተም ሸሹ ሸሽተውም የመጡይንም ሮሞሉስ ከባህሩ ጠረፍ ቦታ ሰጣቸው:: እነሱም ከዚሁ ከተማን ቆረቆሩና ከነሱ ጋር ከዳዊት ሸሽቶ ባመለጠው መሪያቸው ስም ‹ደርሶ› ብለው ከተማዋን ሰየምዋት:: የደርሶ የቀድሞ ስምዋ ‹ዱር› ይባል ነበር:: የዚህ ሰው ዘሩ አርማንያ ከኖሩት ነገደ ሐዳድ ነው:: ከጢቂት ጊዜ በኋላ በዚችው በስደተኞቹ ከተማ የጦር መሳሪያን የምታነቃ /የሞት ሰነጥቅ/ ምንጭ ተከስታ ነበር ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን ባህር ዋጣት ደፈናትም::

እነዚህ ዳዊት ያሳደዳቸው ሕዝቦች ሁለተኛ ከተማን ቆርቁረው ነበር እስካሁን የምትታወቀው ግን የመጀመሪያዋና አፎሊ በተባለው ቦታ የተቆረቆረችው ከተማ ናት የአፎሊ ንጉሥ ዳዊት ይወረኛል በማለት ይፈራ

www.ethiopianorthodox.org

ስለነበር ከተማዋን በታላቅ ግንብ አጠረ የከተማዋ ቅፅር በንጉሡ የተሰራው አርባ አምስት ኪሎ ሜትር ይሆናል በዚች ቅፅር የምትገኘውን ከተማ ‹ሮማ› ብሎ ሰየማት ስሙም ሮማ ስለነበር ነው በስሙ የሰየማት ይህ ንጉሥ አንዳንድ ጊዜ ሮማንስ በመባልም ይታወቅ ነበር፡፡ የሮማአስ ሰዎችም ተጠርተውባታል የእሷ ጎረቤቶች ናቸውና እነሱም ሮማውያን ናቸው፡፡

ይህን ታላቅ ግንብ ቢያስገነባም ሮማኖስ ዳዊትን ከመፍራት አልተላቀቀም ነበር መሸተሪ ለተባው ጣኦት ትልቅ ሙክራብ ሰራና ዙሑራ ለተባለው ጣኦት ተሰርቶ የነበረውን ጣኦት አፈረሰው ይህን ሙክራብ የሰራው ለጢኖስ የተባለው ንጉስ ነበር፡፡

ሮፍሎስ ሲሞት ቀጥሎ በማቅዋስ አርባ አንድ ዓመት ነገሠ ከሱ በመቀጠል ተውኪኖስ ለአርባ ዘጠኝ ዓመት፣ ዮልዮስ ሰላሳ ሁለት ዓመት፣ በርኮቦስ ሰላሳ ሰባት ዓመት፣ ለዩኖስ ሰላሳ አራት ዓመት፣ ተርክዮሽ ሰላሳ አምስት ዓመት፣ ነገሡ ተርክዮሽ ከሮማውያን ሴቶች መካከል የሌላ ወንድን ሚስት ስለወደደ በእሷ ምክንያት ተገደለ ተርክዮሽ ሴትዮዋን አስገድዶና ከባልዋ ነጥቆ ከወሰዳት በኋላ ከብስጭት የተነሳ የገዛ ሆድዋን በጩቤ ተርትራ በገዛ ራስዋ ሞተች፡፡

ይህንን የተረዱ አባትዋ ባልዋና ወንድሟ ተርክዮሽን በምኩራቡ መግቢያ ተደብቀው ጠበቁትና ገደሉት ከዚህ የተነሳ የሮም ሰዎች ሲነግሡ አመፀኞች ይሆናሉ፡፡ ስለዚህ ንጉሥ አያስፈልገንም አሉ እንዳያነግሡም ተማማሉ ከመካከላቸው አንድ ተራ ሰው መርጠው ሾሙና ንጉሥ ሳይሉት ሽማግሌ ብለው ሰየሙት፡፡ በሱ የሚመሩም 320 ሰዎችን መረጡ የተመረጡት በስነ ምግባር የተመሰከረላቸው ናቸው፡፡ በዚህም መንግሥትን ሰሩ፡፡



በዚሁ መልክ ሮማውያን ለብዙ ዓመታት ተመርተዋል፡፡ በኋላ ግን የመጀመሪያው ቄሳር ተሾመና በገዛ ራሱ ንጉሥ ነኝ አለ፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ያ የሕዝቡ ምርጫ ተደመሰሰና ለወደፊት እንደምንገልጠው በቅደም ተከተል ቄሳሮች የሮም ነገሥታት ሆኑ ይሁን እንጂ ሽማግሌዎች እየተባሉ በሚመረጡ መሪዎች ለ320 ዓመት ያህል መርተዋል፡፡ በነዚህ ዘመናት ሮማውያንን ለመድፈር የሚነሳ አልነበረም የአካባቢያቸውን ሀገሮች በሙሉ ለመቆጣጠርና ነገስታትን ለማባረር ታላቅ ኃይል አግኝተው ነበር፡፡ በመጨረሻ የተለያዩ ሕዝቦች በሮም መለያየትን አመጡ ዮናናውያንና አልስክንድንዮናውያን በመካከላቸው ጠብ ፈጠሩ ሮማውያን ዮናናውያንን ረዱ አልስክንድዮናውያን ተሸነፉ ይሁን እንጂ አልስክንድዮናውያን በአጭር ጊዜ በረቱ ሮማውያንን በቂም ተነሱባቸው ሮማውያንም ፈርተው ሀገራቸውን በመተው ሜብር ወደ ተባለው ባህር አካባቢ ተሰደዱ ከባህሩም በቦይ ወደ ሮም ውሃን ለቀቁ ሮምም በወንዝ ታጠረች፡፡ አያይዘውም ከተማዋን በብረት አጠርዋት በብረት የታጠረው ቦታ 18 ሜርት ያህላል ጎኑ ደግሞ ሰባ ምዕራፍ ያህላል፡፡

ይህንን ያደረጉበት ምክንያት አካባቢያቸውን የመውረር ጥቃት እንዳይደርስባቸው ይፈሩ ስለነበር ነው፡፡ ናቡከደነጾር የባቢሎኑ ንጉሥ ቤተ መቅደስን እንደ ደመሰሰና እስራኤላውያንን እንደማረከ ሲሰሙ ደግሞ ፍርሃታቸው በረታ መጥቶ እንዳይወራቸው ካለበት ድረስ እጅ መንሻ ላኩለት፡፡ ከሱ ስር መሆናቸውንም ገለፁለት እሱም ደስ ብሎት እንደማይወራቸው ቃል ገባላቸው፡፡ ከዚህም የተነሳ ማደይና ፋስ እስከተከፋፈሉ ድረስ በሰላም ኖሩ፡፡



www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፬

## የማደይ ንጉሥ ደራ የፋርስ ንጉሥ ኮርሲ ከዮናናውያንጋር ጠብና የባቢሎን ንጉሥ ብርዋስደር ሞት

የዚህ መጽሐፍ ባለቤት እንዲህ ይላል ‹የከርዳናውያን ዘመነ መንግስት ሲፈጸም እግዚብሔር የሚፈርድበት ጊዜ መጣ መንግስታቸውንም አጠፋ ነቢያትም እንደገለፁት እግዚአብሔር በነገስታቱ ላይ ተነሳባቸው የፋረሱና የሜዶኑም ተጣሉ እንደገና ሁለቱ ታረቁና የፋርስ ንጉስ ከኒርዲ የሜዶንን ንጉስ ሴት ልጅ አገባ በዚሁም ካርዲዮን የተባለው ንጉስ ለመዋጋት ግንባር ፈጠሩ ይህ ንጉስ ብልጥሳፅር የሚል ድርብ ስም ሲኖረው የናቡከደነፆር የባቢሎን ንጉስ ልጅ ነው ግዛቱም ባቢሎን ነበር።

እሱን ለመውጋት እጅግ ቁጥሩ የበዛ ወታደር አሰልፈው ለጦርነት ተነሱ ብልጣሳፅር /ብልጣሶር/ ሊወጉት መነሳታቸውን ሲሰማ ራሱ ሳይዘምት ወታደር ላከባቸው ሁለቱንም ነገስታት የብልጣሶር ወታደሮች መቱዋቸው ወደ ሀገራቸው ያንድ ቀን ጉዞ ብቻ እስኪቀርም እየተከታተሉ ወጉዋቸው። ብልጣሶር መሸነፋቸው ሲሰማ በአንድ ሺህ አለቆች የሚመራ ብዙ ሰራዊቶችን ላከ።

እነዚህ ሰራዊት በሌሊት ደረሱና ከነሱ ጋር ጦርነት ገጠሙ የሜዳኖንና የፋረሱንም ንጉስ አሸነፋዋቸው ብልጣሶር በድል አድራጊነት ተመለሰ ደስተኛም ሆነ። ሰራዊቶቹንም በመብልና በመጠጥ ብዙ ቀን አስደሰታቸው ከመጠጥ ብዛትም ራሱ ሰከረ መኳንንቱንም በማወደስ ብዙ ለፈለፈ ንግግርንም አበዛ አያቱን ናቡከደነፆርን ከቤተ መቅደስ ያመጣቸውን የወርቅ ፅዋዎች አስመጥቶ ጠጣባቸው እቁባቶቹንና መኳንንቶቹን እንደሱ በቤተ መቅደስ ፅዋ ጠጡ ከስካር ብዛትም የተነሳ ጣዖታቸውን ያመሰግኑ ጀመር



እግዚአብሔር ምስጋና ለሱ ይሁንና በብልጣሶር ላይ ተቆጣ ባደረገውም ድፍረት አዘነበት መልአኩንም ልኮ ከእሱ ፊት ለፊት የእግዚአብሔር ፍርድና ስለ መንግስቱ መውደቅ ነገረው ብልጣሶርም በሰው እጅ መልክ ሲጻፍ አየ የጻፈውም ከግንቡ ላይ ነው እጁ አስደናቂ ብርሃንን ያበራ ነበር።

ብልጣሶር በዚህ ግዜ እጅግ ደነገጠ የተጻፈውም በከነናዊ ፊደል ነው ቋንቋው ደግሞ የዕብራውያን ቋንቋ ነበር ስለተጨነቀም ዳንኤልን አስጠርቶ አስተረጐመው ዳንኤልም የቤተ መቅደስን ንዋየ ቅድሳት ስለደፈርክ እግዚአብሔር ተቆጥቶ መልአኩን ልኮ ያንተን ስህተትና ድቀትህን በጽሑፍ ገለፀልህ እግዚአብሔር መዝኖህ የቀለልህ ሆነህ ተገኝተሃልና አለው።

ብልጣሶር ዳንኤል የነገረውን ሰምቶ እጅግ ደነገጠ ወታደሮቹም ደንግጠው ወደየቤታቸው ሄዱ ብልጣሶር ተነስቶ አልጋው ላይ ተኛ የገዛ አሽከሩም ሌሊት መጥቶ ገደለው እራሱንም ቆርጦ ይዞ ወደ ሜዶኑና ወደ ፋርሱ ነገስታት ሄደ ከመልአኩ የተጻፈውንና ዳንኤል የተረጐመውን አንድ በአንድ ዘርዝሮ ነገራቸው እነርሱም ካሉበት የብልጣሶር ራስ ተቆርጦ ስለመጣላቸው እግዚአብሔርን አመሰገኑት ለከሀሊነቱም አድናቆታቸውን ገለፁ።

ከዚህምየተነሳ የፋርሱ ንጉስ ኵርሽ በኢየሩሳሌም የፈረሰውን ቤተ መቅደስ ለመስራት ተነሳሳ ናቡከደነፆር ከኢየሩሳሌም የማረከውንም ነዋየ ቅድሳት ለመመለስ ወሰነ የተማረኩትም አይሁድ ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ ፈቀደ የፋርሱ ንጉስ ኵርሺና የሜዶኑ ንጉስ ደራ አብረው ወደ ባቢሎን ሄዱ የባቢሎንም ሰዎች ገደሉ ነቢያት በካርድዮን የተናገሩት ትንቢት ተፈፀመ እግዚአብሔር በበደላቸው ብዛት እንደሚያጠፋቸው አስቀድሞ ተንብየዋልና።



www.ethiopianorthodox.org

ከዚያ በኋላ እነዚህ የፋረስና የሜዶን ነገስታት ባቢሎንን ለሁለት ተካፈልዋት የሜዶኑ ንጉስ ደራ ሽምግሎ ስለነበር ቶሎ ሞተ በዚህ ጊዜ የሜዶንና የፋረስ ሕዝቦች ተስማምተው የፋርሱ ንጉሥ ኩርሽ. ሜዶንና ፋረስን እንዲገዛ ወሰኑ ሜዶንና ፋርስም አንድ ሀገር ሆኑ።

ኩርሽ. ሁሉን ካጠቃለለ በአንደኛው ዓመት ወደ ሀገሩ ተመልሶ ናቡከደነፆር ያፈረሰውን ቤተ መቅደስ ለመስራት የሚፈልግ አይሁዳዊ ሊሄድ ይችላል ‹እኔም ኩርሽ. የአምላክ ባርያ ስለሆንኩ ካለኝ የቤተ መንግስት ቤተ መዛግብት ዕቃ ሁሉ ለቤተ መቅደስ ሥራ ሊውል የሚችል ካለ ለዚሁ አውለዋለሁ ባቢሎናውያንን እንዲሸነፉ ኃይል የሰጠኝ እግዚአብሔር ነውና› አለ።

ወንዶች ሁሉ ኩርሽ. የሚለውን ካዳመጡ በኋላ እጅግ ተደሰቱ እግዚአብሔርንም አመሰገኑ ብዙ ሕዝብም ወደ ሀገረ ቤተ መቅደስ /ሀገረ ቀድሽ/ ሄደ ከእነሱ ጋርም እዝራ ካህንና ነህምያ መርድጋይና ኢያሱ ተማርከው የተወሰዱ ምሁራን ሁሉ አብረው ሄዱና የከበረውን የልዑል እግዚአብሔርን ቤት ሰሩ እንደቀድሞውም የውስጡንና የውጭውን አስተካክለው ሰሩት ኩርሽ. ለቤተ መቅደስ አገልግሎት የሚውለውን ሁሉ እንዲያሟላላቸው ጠየቁት ኩርሺም በጥያቄያቸው መሰረት ለቤተ መቅደስ የሚያስፈልገውን ሁሉ አሟላ ሕዝበ እስራኤል የፋርስ መንግስት እስክትወድቅ ድረስ በዚሁ መልካም ነፃነት ለመኖር ቻሉ እግዚብሔር የፋርስን መንግስት አፀና ፋርሶች እጅግ በረቱ የዓለምንም ነገስታት ተቆጣጠሩ ቤተ እግዚአብሔር ተከፈተ ነቢዩ ኢሳይያስ በትንቢቱ እንደገለፀውም ኩርሽ. ለእስራኤል ልጆች መልካምን ስላደረገ እጅግ ረዳው።

የሽብጣ ንጉስ በፋርስ መንግስት ላይ ዐመፀ ነገር ግን ኩርሽ. ዘመተበት ገደለውም ከሀገሩም ሕዝብ ብዙዎቹን ገደለ የሽብጣን ቤተሰቦች ሚስቱንና



ልጆቹንም ገደላቸው የሽብጣም ንጉስ ሚስት ‹ቡሊደሊ› ትባል ነበር ጠንካራ ቤትም ነበራት በእሷ ቤት ብዙዎች ሕይወታቸውን ለማትረፍ ተጠግተው ነበር ነገር ግን ሁሉም የነገስታት ዘሮች ተደመሰሱ ሁሉንም ካጠፋ በኋላ ከአሽከሮቹ መካከል ለዚችው ሀገር ሹሞ ወደ ሀገሩ ተመለሰ።

እቺ የንጉስ ሚስት ቡሊደሊ የልጇን መሞት የንግስትነቷን መቅረት ስተመለከት በቁጭት ከሞት የቀሩትን የባልዋን ወታደሮች ሰብስባ ዲፓ በምትባለው ቦታ እስክትሞት ድረስ በጭካኔ ኩርሺን ጠበቀችው የኩርሺ. ተከታዮች አብዛኛዎቹ እስኪያልፉ ድረስ አደፈጠች ኩርሽ. ወደ ኋላ ቀርቶ አብዛኛውንም ሰራዊት ወደ ፊት በማስቀደም ጉዞ ጀመረ ኩርሺን በግላጭ ከጥቂት ተከታዮቹ ጋር አግኝታ ሁሉንም ገደለቻቸው የፋርሱን ንጉስ ኩርሽ. አንገት ቆርጣ በስልቻ ቋጥራ ደም ሞላችበትና ‹አንተ ኩርስ ደሙን ጠጥተህ ጥገብ› አለችው እንደዚህም አለች ‹አንተ በጭካኔ ሰዎችን ስትፈጅ ምንም አትራራም ምህረትም የለህም› የኩርሺ. ነገር ተፈጸመ ለሞት ያበቃውን ያለ ርህራሄ ሰዎችን መፍጀቱ ነው። ሰውን በጭካኔ መፍጀት ለሰብአዊ ፍጡር አልተፈቀደም እግዚአብሔርን አውቆ መፍራትና ለፍጥረቱም እንደሚያስብ መገዘንብ ለሰው ልጅ ይበጃል ስለዚህ ሁላችሁም በስርዓተ እግዚአብሔር ኑሩ።

## ምዕራፍ ፭

## <u>ከኩርሺ. በኋላ የነገሱ ነገስታት /በፋርስ/</u>

## <u>አስቴርና መርዶክዮስ ታሪክ ከአክሶስ ንጉሥ ጋር</u>

ከኩርሺ. ቀጥሎ ልጁ መኪስ ነገሠ መንግስቱ ሲፀናለትና መንበሩ ሲቀናለት አባቱን የገደለች ቡሊደሊ ወደ አለችበት ሀገር ሄደ ከቤተሰቦቿም ጭምር ነቀላት ለማስታወሻ የሚሆንም ምንም አላስቀረባትም ከዚያ

www.ethiopianorthodox.org



www.ethiopianorthodox.org

በመቀጠል ካባቱን ያፈነገጡ ሁሉ ወደ አሉበት ዘመተ ካባቱ ሞት በኋላም ሁሉንም እያሸነፈ ተቆጣጠራቸው መንግስቱም ፀና ስልጣኑም ፀናለት ስልጣኑም አደገለት ስራውም በረታ አይሁድ ኰርሺን በጣም ይታዘዙለት ነበር ከሱ ቀጥሎም ለእሱ የፋርስ ነገስታትም እንደዚሁ ይታዘዙለት ነበር፡፡

የፋርስ ነገስታትም በበኩላቸው የአይሁድን ፍላጎት ሙሉ በሙሉ ያስተካክሉላቸው ነበር በቤተ መቅደስ ለመስዋዕትና ለሌሎች አስፈላጊዎች ሁሉ ከፋረስ ነገስታት ይሰጣቸው ነበር፡፡ ይህንን የጀመረላቸው ኰርሺ ነው ስለዚህ ፋርሶች ቤተ እግዚአብሔርን እጅግ ያከብሩ ነበር ከቤተ እግዚአብሔርም በረከት ይቀበሉ ነበር በቤተ መቅደስ በበረከት ጊዜም ስማቸው እንዲነሳ ፍላጎት አደረባቸው እስከ ዘመነ እስክንድር ድረስ ይህ ልማድ ቀጥሎ ነበር እስክንድር ከነገሠ በኋላ ግን ያይሁዶች ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ተለወጠ፡፡

የዚሁ ምክንያት ‹እስክንድር ሓማን የተባለውን ሰው ከእነሱ ዘንድ የበላይ አድርጎ ሾመላቸው ለእሱም እንዲሰግዱ አዘዛቸው በዚህ ግዜ ሓማን የአይሁድ ጠላት መሆኑን ታወቀ ሰውየው በዘሩ አማሌቃዊ ነው የእስራኤል ንጉስ በነበረው ሳኦል ዘመን በአማሌቃውያንና በእስራኤላውያን መካከል ከፍተኛ ጥላቻ እንደነበር ይታወሳል ሳኦል ከእግዚአብሔር በተሰጠው ትእዛዝ አማሌቃውያንን ደምስሶአቸዋል ከዚሁ ዘመን ጀምሮ በሁለቱ መካከል የተነሳው ጥላቻ አልበረደም በይበልጥ በብንያም ነገድና በአማሌቃውያን ዘንድ የከረረ ጥላቻ ነበር ምክንያቱም ሳኦል ከነገደ ብንያም ነውና፡፡

በሌላ በኩል ምድረ ጋይ የተባለው የአይሁድ ወገን በአክስሮይስ ቤተ መንግሥት አገልጋይ ሆኖ ነበርና ለሓማን አልሰግድም አሉ ክብርም አልሰጠው አሉ ይህም ምድረ ጋይ ወገኑ ከነገደ ብንያም ነበር ይህ ለብዙ



ዘመናት በታሪክ ብቻ ይታወስ የነበረው ጥላቻ በዚሁ አገረሸ ሓማንም አይሁድን ጨርሶ እስከ ማጥፋት ፈለገ፡፡

ሁለቱ የንጉሥ ባለሟሎች የሆኑ ሰዎች ነበሩ ከላይ የተጠቀሰው አክስሮይስ ሲሆን ዮናናውያን ለማፋቀር ሲሉ ንጉሡን ለመግደል አላማ ነበራቸው በዚሁ ዘመን ዮናናውያን ፋርስን በመውጋት ላይ ነበሩና ምድረ ጋይ /መርዶክዮስ/ የነዚህን የንጉሥ ባለሟሎች ንጉሡን ለመግደል እቅድ ማውጣታቸውን አውቆ ነበር ይህን ተንኰል የአጎቱ ልጅ ለሆነችው አስቴር ነገራት እሷም የአጎቷ ልጅ ምድረ ጋይ /መርዶክዮስ/ የነገራትን ለንጉሡ ነገረች፡፡

እነዚህ ሁለት ሰዎች ንጉሡን አክስሮይስን እንዲነድፉ እባቦችን አዘጋጅተው ነበር ይህንን ተንኰል ሁሉ ምድረ ጋይ /መርዶክዮስ/ ለአስቴር ነግሯቷል እሷም ለንጉሡ ነግራዋለች ንጉሡም እውነት ሆኖ ስላገኘው ሁለቱን ባለሟሎች ገደላቸው አስከሬናቸውም በአደባባይ ሰቅሎ በዚሁ ላይ የመርዶክዮስን አስተዋይነት በንጉሡ የክብር መዝገብ እንዲሰፍር አዘዘ፡፡

ለሓማ ግን ይህ ሁኔታ አስጨነቀው በመርዶክዮስ ላይም ከፍተኛ ቅንአት አደረበት የንጉሡ ባለሟሎች ከማንም በበለጠ የመርዶክዮስ ባለ ምስጢሮችና ፍቅረኞች ሆነዋል ሓማን የአይሁድን ምሳሌ እየፈለገ አይሁድን ንጉሡ የሚጠላበትን መንገድ ይፈላልግ ጀመር በተለያየ መንገድም ሐማን ከሁሉ የበለጠ በንጉሡ ታማኝነቱን አገኘ መርዶክዮስ ደግሞ ሐማን ከአማሌቃዊነት ነገዱ ተነስቶ የሚጠላው መርዶክዮስን ይህንን ያህል የመንግስት ሥልጣን ሲይዝ በመቻሉ እጅግ ተጨነቀ አስክሮስ በንጉሥነት በነበረበት ዘመን ምድር ስትናወጥ ያየበትንም ሕልሙ አስታወሰ ሁለት ትላልቅ እባቦች እርስ በእርሳቸው ሲጣሉ በዚሁ ህልሙ አይቶ ነበር፡፡

www.ethiopianorthodox.org

ከዚህም የተነሳ ታላቅ ጩኸት እንደሆነ በህልሙ ታይቶት ነበር በዚሁ ብዙ ሰዎች ተሰበሰቡ ህዝብን ለማጥፋትና ለክፋት የተዘጋጀ ነበር ዓለም ልትደመሰስ ስለተቃረበች ወደ እግዚአብሔር ትጮኸዘንድ ያድናትም ዘንድ ለምነች ዓለም በጨለማ ተዋጠች በሁለቱም ዝምድና ያለውም ዝምድና ጠነከረ አንዱ ሌላውን ለመዋጥ ይጥር ነበር የተሰበሰበውም ህዝብ ሁለቱን ዘንዶዎች ለማገላገል አልቻለም ዘንዶዎቹ በዚሁ ጠባቸው ብዙ ቆዩ።

እንደገና የውሃ ምንጭ አየ ምንጯም ልትደርቅ ስለተቃረበች ከሷ ጥቂት ውሃ በሁለቱ ዘንዶዎች መካከል ይፈስ ነበር ይህም ጥቂት ውሃ የሁለቱን ዘንዶዎች ጠብ አበረደ ዘንዶዎቹ ታረቁና ምንጩም ብዙ ውሃ ማመንጨቱን ተያያዘው ፀሃይ ወጣ አለም በራ ጨለማም ተወገደ ያች አናሳ የነበረች ቤተሰብም በዝታ ታየች ከዓለም ሰፍኖ የቆየው ፍርሃት እና ድንጋጤ ተወገደ ሰላም እውነትና ርትዕ በዓለም ሰፈነ ይህንን ሁሉ በህልሙ ምድርጋይ/ መርዶክዮስ/ ከአንድ አመት በፊት ታይቶት የነበረ ነው።

መርዶክዮስ ይህነን ራዕዩን አልረሳውም ነበር እስኪተረጎም ብቻ በጽናት ይጠብቀው ነበር በጊዜውም ላባቱ ወንድም ልጅ አስቴር ይህንን ህልሙ ነግሯት ነበር በዚሁም ሃማን በጥላቻ በእሱና በወገኖቹ ላይ በተነሳበት ጊዜ መርዶክዮስ ለአስቴር እንዲህ አላት ‹‹ያ ከዓመታት በፊት አይቼ የነገረኩሽን ህልም አሁን የሚፈጸምበት ጊዜ ደረሰ አሁን ከሁሉ በማስቀደም እግዚአብሔርን ለምኝው ከዚያ አያይዘሽ ወደ ንጉሡ ግቢና ለምኝው ወድቀሽ ተነስተሽም ህዝቦችሽን ለማዳን ተፈራፈጪ›› አላት። ራሱም ምድርጋይ/መርዶክዮስ/ ምህላውን ወደ እግዚአብሔር ተያያዘው ፆመ ፀለየ ወደ እግዚአብሔር ማለደ አመሰገነም።

የመርዶክዮስ ጸሎት እንዲህ የሚል ነበር ‹‹ታላቁ እግዚአብሔር ሆይ ልዑል እግዚአብሔር ሆይ እኔ ለሃማ የአክብሮት ስግደት እንዳልሠገድኩ



አንተ ታውቀዋለህ ነገር ግን ለሱ ያልሰገድኩት አንተን ፈርቼ ነው ያንተንም መንግስት ፈርቼ ነው መስገድ ወዳንተ ብቻ መሆኑን አውቃለሁና ወደ ሌላ ቀርቤ ብሰግድ አንተን አስቆጣለሁ ወዳንተም እቀርብ ዘንድ ከእሱ ራቅሁ ስግደትስ ላንተ ብቻ ይገባል ወዳንተም ጸሎትና አስተብቍኦት ይቀርባል ይህም ባይሆን ኖሮ ለሃማ መስገድን እምቢ ባላልኩ ነበር ለሃማም እየሰገድኩ ወገኖቼ አይሁድ በሰላም እንዲኖሩ ባደረግኩ ነበር የሃማን ፈቃድ ሁሉንም ፈጽሜ የዘመዶቼን ደህንነት ባስጠበቅኩ ነበር የረገጠውንም መሬት በተሳለምኩ ነበር።

ሐማ እኛን ለመደምሰስ መነሳቱን እነሆ አውቄአለሁ ስለዚህ ከዚሁ ከተደቀነብን ጥፋት ታድነን ዘንድ እለምንሃለሁ እሱንም በቆፈረው ጉድጓድ ላይ ጣለው ለባሮችህ ወጥመድ አዘጋጅቷል የሁላችን ዓይን ያንተ ድህንነት ብቻ ይተማመናል ካባቶቻችን ጋር የገባኸውን ቃል ኪዳን አትርሳው በደላችንንም አስበህ ችላ እትበለን በምርኮ ተዋርደናል ያለፈውን ውርደታችንን ተመልከትልን መዋረድና ዝቅ ማለት ለእግዚአብሔር ብቻ ይገባል መርዳትን ትችላለህና እርዳን አድነንም ከመቼም በበለጠ በጭንቀት ላይ ያለነው አሁን ነው ካንተ ሌላ መጠጊያ የለነም ከምንዳቢያችን አድነን በኃይልህም አድነን በጠላታችን ኃይልን ስጠን ምክራቸውንም በትን።

አቤቱ ከአህዛብ ለይተህ የመረጥከው ነውና ለጠላት አሳልፈህ አትስጠው አምላክ የላቸውም ብለህ ጠላቶቻችን አምላካቸው አያድንም እንዳይሉም በጣኦታቸውም እንዳይመኩ አሳፍራቸው እምነታቸውንም ሃሰትን አድርግ በዚህም የአማልክቶቻቸውን ከንቱነት ይረዱ ይህም የሚሆነው የእኛን መዳን ሲረዱ ነው ለእኛ አንተ እንድናመሰግንበት የሰጠኸንንም ኪዳን አታጥፋ ምስጋናህም ከአፋችን አይጓደል አንተ በቃልህ የምትመሰገን ፈጣሪ ነህ በመንፈስህም ትመሰገናለህ።

www.ethiopianorthodox.org

ሃዘናቸንን በደስታ ለውጥ እኛ በዚሁ እናመስግንህና እንባርክህ ዘንድ እንቀድስህም ዘንድ ረድኤትህንም እናይ ዘንድ በእኛ ላይ ስላለው ፀጋ ለበቁ ለበቁዔትና ለመዳን አድርግልን አክሳይሮስ ንጉሥ በሚገዛው አገር ሁሉ ባሉት አህዛብ ሁሉ እንኖር ዘንድ አገሮቹ ሱሳናስቅ ናቸው፡፡

አይሁዶችም ከሐማ የተጀመረውን ተንኮል ስለ ሰሙ ወደ እግዚአብሔር አለቀሱ በፍርሃት እና በመንቀጥቀጥ ወደ እግዚአብሔረ ጮኹ ሃማን ያጠፉላቸው ዘንድም እግዚአብሔርን ለመኑ አስቴርም በበኩሏ ወደ እግዚአብሔር ተማለለች ይህንንም መከራ ፈርታ የንግስትነትን ልብሷን ትታ ሽልማቷንም ጥላ ማቅ ለበሰች ወደ እራስዋም አፈርን ነሰነሰች በፆምና በጸሎት ተጋች እያለቀሰችም በግንባርዋ ተደፋች የክቡርና የልዑል እግዚአብሔርንም ስም ጠራች እንዲህም አለች ‹‹የእስራኤል አምላክ ሆይ የነገስታት ንጉሥ ሆይ የሁሉም መኮንን ሆይ በርያህን እኔን አሸናፊነት ትሰጠኝ ዘንድ ስልጣን ያንተ ነው እኔ ሌላ ረዳት የለኝም፡፡

አቤቱ የመማረክ እድል እንደገጠመኝ አንተ ታውቃለህ ከህፃንነቴ ጀምሮ በምርኮ ነው የኖርኩት በባዕድ አገርም ኖርያለሁ ምርኮኝነት እጅግ አስመረሮኛል ከአባቴ እና እናቴ ጋርም አድክሞኛል ይህ ንጉሥ ያለፈቃዴ ነው ያገባኝ አሁን ከእርሱ ጋር ነኝ ወገኖቼ ካልሆኑ ጋርም እኖራለሁ ባህይማኖት ከማይመስሉኝ ህዝቦች ጋር እንድተባበርም ተገድጃለሁ እኔ ግን እምነቴን አለወጥኩም ዓለምን ሆነ ንግሥትነትን አላሸነፉኝም ከትዕዛዝህም አልወጣሁም፡፡

አቤቱ የእዚህ የእኛ ጠላት ሰው ቦታ የት እንደሆነ አንተ ታውቃለህ እኛንም ለማጥፋት ብዙ ተጋድሎ ማድረጉንም አንተ ታውቃለህ እኔም የራሴንና የወገኖቼን መጥፋት እፈራለሁ በአማለጅነት በፀሎት እለምንሃለሁ ልቤንም እየተቃጠለ ወዳንተ እጮሃለሁ ካንተ ምህረት እሻለሁ ርዳኝ ይቅር



www.ethiopianorthodox.org

በለኝ እኔ ችግረኛ ነኝ ምስኪንም ነኝ ወገኖቼን እንዲጠፉ ፈቅደህ ከሆነ ጥፋታቸው ከማየቴ አስቀድመህ ግደለኝ በዚህ ዓለም እንድኖር ከፈቀድክ ደግሞ ባሮችህን ለጠላት አሳልፈህ አትስጥ አንተ ከነጣቂ አንበሶች አፍ ሰዎችን ታድናለህ በችግራችን ጊዜ ሁሉ አንተ አባቶቻችንን ከመርዳት ወደ ኋላ አላልክም ረድተህናል በዘመናትም ሁሉ አባቶቻችንን ጠብቀሃቸዋል አምላኬ እግዚአብሔር ሆይ መሃሪ አንተ ነህ ሁል ጊዜ ለእኛ የምታደርገውን የምህረት ልማድህን አትተው ደካማዋ በርያህንም አጽናት ድክመቷንም አረጋጋ ወዳንተ ተጠግታለችና ከዚሁ ንጉሥ ባለሟልነትን አግኝቼ ወገኖቼን አድን ዘንድም ልቡን አራራልኝ ወደሱ ለምልጃ ስገባም ጠብቀኝ ልቡናውን ወደኛ ወደ ህዝቦችህ እንዲመልስ አድርገው የነገሥታት ልብ ተለዋዋጭ ነውና›› በማለት ጸለየች፡፡

ለሦስተ ቀን ስትጸልይ ሰንብታ አስቴር የንግሥትነቷን ልብስ ለበሰች ሽልማቷንም አደረገች ከሴቶች ባሮቿም አስከተለችና አንዷ አንዷን እንድትይዝ ሁለተኛዋ በነገስታት ህግ የሚደረገውን መሬት ለመሬት የሚጎተተውል የልብሷን ዘርፍ እንድትይዝ አድርጋ ደስተኛ መሰለች ሃዘንዋንም ደበቀች ንጉሡ ካለበትም ገባች እየፈራችም ከፊቱ ቆመች ንጉሱ ለግዜው ትእዛዙን በመዳፈርዋ ተቆጣት ሳይጠራትም አስቀድማ ገባች መቆጣቱን ስታውቅ እጅግ ደነገጠች ከባሮቿ ዘንድም ተደገፋ በዝምታ ቆየች በልቧ እግዚአብሔርን ትጠራ ነበር ምን ማድረግ እንዳለባትም ታሰላስል ነበር፡፡

እግዚአብሔር የልቧን ሀዘን አይቶ ይቅር አላት ከንጉሡ ዘንድም ባለሟልነትን ሰጣት ንጉሡም ውበትዋን ተመልክቶ ራራላት ቁጣውንም አስወግዶ ወደሱ እንድትቀርብ ፈቀደላት በጣምም ወደዳት ወድያውም ስለ

ወገኖቿ ስለነችው እሱም ልመናዋን ተቀበለ አላሳፈራትም በእጅዋ እግዚአብሔር ሁሉን አስተካከለ።

የአባትዋ ወንድም ልጅ ምድርጋይ/መርዶክያስ/ ከሃዘኑ ተረጋጋ የሃማ አሟሟትና መጥፋት በአስቴር መጽሃፍ ተጽፏል በነብያት መጽሃፍም የተጠቀሰበት ቦታ አለ።

አይሁድ ከዚህ ጊዜ ጀምረው በፋርስ መንግስታት ሥር በመሆን በሰላም ለመኖር ቻሉ ዳግማዊ ደራ የተባለው ንጉሥ በፋርስ እስኪነግስ ድረስም በሰላም ኖሩ ደራ ዳግማዊ ዮናናውያንን አሸንፎ ገዝቶአቸዋል ዮናናውያንም አስክንድር ወልደ ፊሊጶስ እስኪነግሥ ድረስ በፋርሶች እየተገዙ ኖሩ።

እስክንድር ወልደ ፊሊጶስ ግን የፋርሱን ንጉሥ ድል አድርጎ ዮናናውያንን ከፋርስ ከመገዛት ነፃ አወጣቸው ደራንም ከነ ሰራዊቱ አስገዛቸው አስክንድር አለምን ሁሉ ገዝቷል ለፈቀደውም መንግስት እና ኃይልን ለሚሰጥ እግዚአብሔር ክብርና ምስጋና ይሁን።

## ምዕራፍ ፮

## የዮናናዊ የፊሊጶስ ልጅ እስክንድር ሜቄዶንያዊ ታሪክ

የእስክንደር ታሪክ ከፋርሱ ታሪክ ጋርና ከአይሁድ ታሪክ ጋር ተገኘ በሌላ በኩል ደግሞ የዚሁ መጽሐፍ ደራሲ እንዲህ ይላል ‹‹የአስክንድር አባት ፊሊጶስ ከዮናናውያን ነገሥታት በትልቅነቱ የታወቀ ነው ብዙ አገሮችንም እያሸነፈ ፊሊ‹ጶስ እንዲገብርለት አድርጎ ነበር ፊሊጶስ በንጉሰነት የቆየው ግን ለሰባት ዓመት ብቻ ነው ከሰባት ዓመት በኋላ ሞተ ያሟሟቱም ሁኔታ እንደሚከተለው ነው ከበታቾቹ መንግስት ባለስልጣኖች አንዱ የፊሊጶስን ሚስት ወደዳት ይህቺ የእስክንድር እናት ናት እንዲገናኛትም



ተላልኮ እሺ አሰኛት እሷን ለመውሰድ ደግሞ ፊሊጶስን መግደል አሰበኝ አሰ በቀላሉ ለመግደል ስላልተመቸው ጊዜ ለማግኘት ይጠባበቅ ነበር።

በዚህ መካከል መቄዶንያ በሌሎች ንጉሥ ተወረረች የፊሊጶስ ጠላቶች እሷን ወረሩ ፊሊጶስም ባለቆች የሚመሩ ሰራዊቶች ወደውጭ ጠላቶች ላከ እስክንድርም ባንድ በኩል ጦርን መርቶ እንዲዋጋ ላከው በዚህ ጊዜ በከተማው ጥቂት ወታደር ብቻ ቀረው ያየፊሊጶስን ሚስት የወደደና ሊያገባትም እሺ ያሰኛት የመንግሥት ባለ ስልጣን ፋሬስ ይባላል ፊሊጶስን ለመግደል አመቺ ጊዜ ተፈጠረ ወድያውን ወዳጆቹን ይዞ ቤተ መንግስቱን ከበበ በዱላም ፊሊጶስን ቀጠቀጠው ህይወቱን ሥቶ እስኪወድቅም ድረስ አደከመው ነገር ግን ቶሎ አልሞተለትም።

በዚሁ አገር ያሉ ህዘቦች ይህንን ድርጊት ሲሰሙ ደነገጡ እስክንድር ከሄደበት የጦርነት ተልዕኮ በዚህ ጊዜ ተመለሰ ወደ ከተማው ሲጠጋም ጩኸትን ሰማ ሁኔታውንም ላማወቅ ጠየቀ ባባቱም ላይ የደረሰውን አደጋ ነገሩትና በፍጥነት ወደ ቤተ መንግሥት ሲገባ አባቱም መሬት ላይ ተዘርሮ አገኘው ወዲያው እስክንድር ፋሬስን ገደለው ፊሊጶስ የደረሰበት በዱላ የመደብደብ ብዛት እጅግ ከባድ ስለ ነበር ጥቂት ሲያጣጥር ቆይቶ ሞተ።

ወዲያው ግን እስክንድር መንግሥቱን ተረከበና ነገሠ በዚህ እስክንድር የሃያ አመት ልጅ ነበር አስተዋይና ጥበበኛም ሆነ ጥበብን ያስተማረው እውቁ ፈላስፋ አርስጣጣሊስ ነው። የእስክንድርም መልኩ እንዳባቱ ወይም እንደ እናቱ አልነበረም።



www.ethiopianorthodox.org

የአይሁድ አለቆች በዚህ ጊዜ ከአይሁድ ዘር ያልሆኑትን ሴቶች ያገባ ሁሉም ሚስቱን እንዲፈታ አዘው ነበር ከካህኑ ምናሴም በቀር ሌሎቹ በታዘዙት መሰረት ሚስቶቻቸውን ፈተዋል ምናሴ ግን የሰንበለጥን ልጅ የሆነችውን ሚስቱን አልፈታትም ብሏል፡፡ ከዚህም የተነሳ ከክህነት ማዕረጉ አውጥተውት ነበር በዚህም ምክንያት ምናሴ ወደ አማቹ ሀገር ወደ ሰንበለጥ ሄዶ ተቀምጦ ነበር፡፡

የካህኑ ምናሴ በዚሁ መገኘት ምክንያት በማድረግ ሰንበለጥ በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ አምሳያ ከቦታው ቤተ መቅደስ እንዲሰራለት ፈለገ የሱ ቦታ ውርብዚል ይባላል፡፡ ሰንበለጥ ሰዎችን እየሰበሰበ ይህን /ውርብዚል/ የከበረና ልዑል እግዚአብሔር የመረጠው ነው ይላቸው ነበር ምናሴንም ባለበት ካህን ነው አልተሻረም አላቸው እስክንድርም መቅደስ ሲሰራለት ፈቃደኛ ሆነ ነገር ግን በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ያለው ካህን የሚጠላውን እንዳታደርግ ሲል አስጠነቀቀው፡፡

እስክንድር መንገዱን ቀጠለ ሰንበለጥም በውርብዚል መቅደስን ሰራ በዚህም አማቹን ምናሴን ካህን አደረገው ሰንበለጥ ለአይሁዶችም ‹‹ይህ ቦታ እግዚአብሔር እንዲመሰገንበትና ሊባረክበት በሱም ጸሎትና ስግደት እንዲካሄድ መርጦታል ሙሴ በኦሪት ‹በከርከርን በረከቴን እጨምራለሁ› ያለው ይህ ነው›› አላቸው፡፡ ከአይሁድም ብዙዎቹ አባባሉን ተቀበሉት በበዓትና ብጻአታቸውም መባቸውንና አስራታቸውን እየያዙ ወደ ውርብዚል ቤተ መቅደስ መጉረፍ ጀመሩ ወደ ዋናው ቤተ መቅደስ መሄድንም አቆሙ፡፡

ዋናው የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስን ያቃልሉትና በመጥፎ ስም ይጠሩት ጀመር በዚሁ አዲስ ቤተ መቀደስ ብዙ ሀብት ተከማቸ የዚህ ቤተ መቅደስ ካህናትና ተላላኪዎቻቸው እጅግ ከበሩ የኢየሩሳሌምን ቤተ መቅደስ ባዶ አስቀረው የምናሴ ክብርም እጅግ ከፍ አለ ለብዙ ጊዜም በዚሁ ቀጠለ



ሀርቃኖስ የተባለው የስምዖን ልጅ ሊቀ ካህናት እስከሆነበት ዘመን ድረስም ባለበት እንደቀጠለ ታውቆአል፡፡

እስክንድር አሁን ደራን ለመውጋት ወደ ምስራቅ በሄደ ጊዜ በኤፍራጥስ ወንዝ ዙርያ ለጦርነት ተዘጋጀ ደራ መምጣቱን ሲሰማ እንዲህ የሚል ደብዳቤ ወደሱ ጻፈ ከደራ ንጉሠ ነገሥት የሁላችሁም አህዛብ ንጉሥ ወደ መቄዶናዊው እስክንድር እግዚአብሔር ክብሬንና ምስጋናዬን ከፍ አድርጓል በዓለምም ሁሉ የበላይ አድርጎኛል ሁሉንም በእኔ ስልጣን ስር አድርጓል አንተና ወገኖችህ መቄዶናዊው እንዴት ደፍራችሁ እስከ ኤፍራጥስ መጣችሁ ያለኔስ ፈቃድ ልምን ከዚህ ደረሳችሁ፡፡

ይህ ድፍረትህ አይጠቅምህም የኔንም ወዳጆች ልትደፍር አይገባህም ባሮች ጌታቸውን ደጅ እንደሚጠኑ ሁሉ አስቀድመህ የምትፈልገውን እንድሰጥህ በለመንከኝ ነበር ይህ ድርጊትህ አሁንም አይበጅህም ያለኔም ፈቃድ አንዳች ነገር አታድርግ አሁንም በፍጥነት ወደኔ እንድትመጣ አዝዝሃለሁ መዘግየትም የለብህም ትእዛዜን ካልተቀበልክ ግን ገዢነቴ ትቆጣጠርሃለች ትእዛዜን በፍጥነት ተቀብለህ ወደኔ ከመጣህ ግን በደልህን ይቅር እልሃለሁ መለካምም አደርግልሃለሁ፡፡

ደራሲው ደራ በጻፈው ደብዳቤ እስክንድር እንዳልደነገጠ ይገልጻል ነገር ግን እስክንድር ሰራዊቱን አስከትሎ ደራ ወዳለበት ሄደ ደራም ብዙ ሠራዊትን አስከትሎ ተገናኘው በዚህ ጊዜ በመካከላቸው ብዙ ጦርነት ተካሄደ በዚህ እለት ፀሃይ ጨለመ ነጎድጓድም ተሰማ የፋርስ ሰራዊትም አለቁ ደራ ሸሽቶ አመለጠ እስክንድር የደራን እናት ልጁና ሚስቱን አሰራቸው የደራንም ሰራዊት ከነ ንብረታቸው ማረካቸው ደራ ካንድ ቤት ገብቶ ተደበቀ እስክንድር በጦርነቱ ያለቀውን ሰራዊት ለማስቀበር አዘዘ የተገደሉትን ሁሉ አስቀብሮ በዚሁ በፋርስ ጥቂት ሰነበተ ከዚያ የሱ የበታችና የሱ ቀጥሎ



www.ethiopianorthodox.org

ለመውጋትም እንደማይችሉ ተረዱ ስለዚህ እጃቸውን ለእስክንድር ሰጡ ንጉሳቸውን የገዛ ራሳቸው ገደሉት፡፡ እስክንድር ሲደርስ ደራ ወድቆ አገኘው እስትንፋሱ አልወጣችም ነበርና እስክንድር አዘነለት እና አለቀሰለት ከፈረሱ ወርዶ ከወደቀበት አነሳው በእቅፉም አስቀመጠው ህይወቱ እስክታልፍም እያለቀሰ ጠበቀው፡፡

ደራ ከሞተ በኋላ ነገሥታት ሲሞቱ በሚገነዙበት የክብር መግነዝ እንዲገነዝ አዘዘ አስክሬኑንም በሳጥኑ አስገባ፡፡ ከመቃብሩ በፊትም ስለሱ ሃዘን መላ ሰራዊቱን አሰለፈ በያደባባዩም አዞረው የክብር ቀብርም አደረገለት የፋርስ ነገሥታትም ከሚቀበሩበት ልዩ ስፍራ አስቀበረው እስክንድር ደራን የገደሉ ወታደሮችንም ገደላቸው፡፡

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ከፋርስ ባለ ስልጣኖች እስክንድርንየሚቃወም አልነበረም ሁሉም ለእሱ ተገዙ እስክንድር ፋርስን አስገብሮ ወደ ህንድ ለመሄድ ተነሳ የህንድ ንጉሥ ብዙ ዝሆኖችን የተጫኑ ብዙ የህንድ ሰራዊቶቹን በማስከተል ተሰልፎ ጠበቀው የእስክንድር ፈረሶች ዝሆኖችን አይተው ስለማያውቁ ወደኋላ እየበረገጉ ሸሹ፡፡ እስክንድር ዝሆኖችን ከተጫኑ ጠላቶች ተዋግቶ ስለማያውቅ ዝሆኖችን አለመዱምና ለቤተ እግዚአብሔረ በየዓመቱ ብዙ ገንዘብ ይሰጥ ነበር በቤተ መቅደስ ዙርያ ለሰፈሩት ነደያንና ምስኪናን ምግብ ይሰጥ ነበር ለካህናት እና ለሌሎች የቤተ መቅደስ ሰራተኞች ፍላጎታቸውን ያሟላ ነበር ከሱ በፊት የነበሩት የፅርዕ ነገስታት ይሰሩ የነበሩት ደግ ነገር ሁሉ ያከናውን ነበር፡፡

አንድ ደራሲ ከአይሁድ መካከል የሆኑ ክፉዎች ሰዎች ‹‹አልማዝ ዕንቊና ወርቅ በቤተ መቅደስ አለ ይኸውም ተቆጥሮ የማያልቅ ነው ይህ ሁሉ በቤተ መቅደስ ሳይሆን በቤተ መንግሥት ነው መቀበጥ ያበት ብለው



ደገኛውን ንጉሥ ሳርፓፎስ ነገሩት በዚሁም ንጉሡን ሸነገሉት ይህ ንጉሥ መልእክተኛን ወደ ቤተ መቅደስ ላከ፡፡

ሃናንያ የተባለው የቤተ መቅደስ ታላቅ ካህን ከአይሁድ ሽማግሌዎች ጋር በመሆን የንጉሡን መልእክተኛ ተቀበለ ስለ አመጣጡም ጠየቁት ሳርፓፎስ ንጉሥ እሱን የላከበት ምክንያት ዘርዝሮ አስረዳቸው በዚህ ጊዜ ታላቁ ካህን ሃናንያ ለመልእክተኛው እንዲህ አለ ‹‹በቤተ መቅደስ አልማዝ እንቊ ወርቅ የለም ከፋርስ ነገስታት እና ከፅርዕ ነገሥታት የተሰጡ ማስታወሻዎች ብቻ ናቸው በቤተ መቅደስ የሚገኙት የቀረ ገንዘብ ደግሞ ለካህናት ቀለብ ለነዳያን እና ለምስኪናን የሚሰጥ ገንዘብ ብቻ ነው ያለው ይህም ገንዘብ ነገሥታቱ መንግስታቸውን እንዲያጸናላቸው እንዲፀለዩላቸው የሰጡት ገንዘብ ነው፡፡››

ካህኑ ሃናንያ የንጉሡ መልእክተኛ ከቤተ መቅደስ ገንዘብንም ለመውሰድ እንዳይሞክር በእግዚአብሔር ስም አስፈራራው አስጠነቀቀውም መልእክተኛው ግን የካህኑን ሃናንያን ማስፈራራት እንደ ምንም አልቆጠረውም የሱም ተከታዮች ቤተ መዛግብቱን እንዲበረብሩ አዘዛቸው ይህ ሁኔታ በአከባቢው የነበሩት አይሁድ ሁሉ እንዲሰሙት ተደረገ የቤተ መቅደስን ንብረት ወደ ሌላ ማዘዋወር አልቻሉም ሰውየውን ፈርተውታልና ወደ እግዚአብሔር ብቻ ምህላ ያዙ ፆሙ ፀለዩ አለቀሱ ማቅ ለበሱ ከራሳቸው አመድ ነሰነሱ፡፡

በዚህ የምህላ ስርአት ሴት ወንድ ህጻን ሽማግሌ ተብሎ ሳይለያይ ሁሉ ተከፋፈለ ይህን የሚመራው ትልቁ ካህን ሃናንያ ነበር የመጽሃፉ ደራሲ ‹‹መንግስቱን አልአሮድስ የተባለ መልእክተኛ ከተከታዮቹ ጋር ወደ ቤተ መቅደስ ሲገባ ሲሞክር እግዚአብሔር አስደንጋጭ ቃል አሰማው ከሰረገላውም አንስቶ ጣለው ቀጠቀጠውም ተከታዮቹም ከወደቀበት አንስተው



www.ethiopianorthodox.org

ወደ ቤቱ አስገቡት ከዚህ የተነሳ መናገር አቅቶት እንደበቱ እንደተዘጋ ለብዙ ቀናት ቆየ እህልንም መብላት አቃተው ሲቸግራቸው ወገኖቹ ይቅርታ ያደርግለት ዘንድ ለመኑት ሃናንያም ወደ እግዚአብሔር ጸለየ ከበሽታውም ፈወሰው በሕልም እግዚአብሔር የካህኑ ሃናንያ ጸሎት ሰምቶ አድኖኋል እና ወደ ሃናንያን ሄደህ አመስግነው የሚል አየ እሱም ሄዶ ያንን አደረገ ለቤተ እግዚአብሔርም በዙ የገንዘብ ስጦታ አደረገ ለሃናንያም እንደዚሁ አደረገ» ይላል፡፡

እስክንድር የህዝቦችን ምስል ከብረት አሰራና በውስጣቸው እሳት እየጨመረ በሰረገላ በማስጎተት ወደ ህንድ አስጠግቶ የህንድን ዝሆኖች በእሳት አቃጠላቸው ምክንያቱም የህንድ ዝሆኖች እንደነሱ ዝሆኖች እየመሰሉ ተጠግተዋቸዋል እና ከብረት ዝሆኖቹም እየተፈናጠረ የሚወጣው ባሩድ ወታደሮቹንም ጭምር አቃጠላዋቸው በዝሆኖቹ ላይ የተጫኑት ወታደሮች አብዛኞቹ ሲቃጠሉ የቀሩት ሸሹ ከእስክንድር ሰራዊትም ብዙ ስላለቀ ጦርነቱ ለብዙ ጊዜ ቀጠለ፡፡

ግንባር ፈጥረው የህንድ ሰራዊት እስክንድርን በህይወቱ ይዘው ለህንዱ ንጉሥ ለመስጠት ተስማሙ እስክንድር የነሱን አላማ ስላወቀ ወደ ህንዱ ንጉሥ እንዲህ ሲል መልእክት ላከበት ‹‹በመካከላችን የሚደረገው ጦርነት እጅግ ረዘመ ብዙዎቹ ሰራዊቶቻችንም አለቁ ስለዚህ ከሰራዊታችን ተለይተን እኔና አንተ ሁለታችን ብቻ እንድንገናኝ ቃል ኪዳን እንግባ እግዚአብሔር የአሸናፊነት እድል የሰጠውም ሥልጣኑን ይውሰድ›› በዚሁ የህንዱ ንጉሥና እስክንድር ተስማሙ የእስክንድር ቁመት አጭር ነበር የህንዱ ንጉሥ ደግሞ ረጅም እና ግዙፍ ነበር፡፡

በመጨረሻ ሁለቱ ለብቻ ተገናኙ ሁለቱ ብዙ ተደባደቡ ሊሸናነፉ ስላልቻሉ አንተ የገባኸውን ቃል ኪዳን አፈረስክ ይኸውና ረዳቶች መጡልህ



ሲለው የህንዱ ንጉሥ እውነት መስሎት ወደ ኋላ ዞሮ ተመለከተ በዚህ ጊዜ በያዘው ብረት ሆዱ ላይ መትቶ አስክነድር የህንዱን ንጉሥ ገደለው ወድያው እስከንድር ህንድን ተቆጣጠረ አጭር ጊዜም ከዚያው ተቀመጠ ወደ ፋርስም ተመልሶ የፋርስን ጠቢባን መመልከት ጀመረ፡፡የጠቢባኑ ደግነትና እውቀትን አስቀድሞ ሰምቶ ነበርና፡፡

የፋርስ ጠቢባን የእስክነድርን ወደ ነሱ መምጣት ሲሰሙ ‹‹አንተ እኛን ለመውጋት ከመጣህ እኛ ጦርነት አንገጥምህም ንብረታችንንም ብትዘርፍ ዝም ብለን እንመለከትሃለን ጥበባችንን ለመስማት ከፈለክ ያለ ሰራዊት ብቻህን ወደኛ ና የጦር መሳሪያንም አትያዝ በትህትና ብቻ መምጣት አለብህ›› በማለት ወደሱ ላኩ፡፡

የመፅሃፉ ደራሲ እንዲህ ይላል ‹‹ እስክንድር ወደ ነሱ ሲሄድ ራቆታቸውን ነበሩ ልብስ የላቸውም ማደርያም የላቸው በየጥጉና በየ ዛፉ ከመጠጋት በቀር ምንም የሌላቸው ሆነው አገኛቸው ለመጠጥ የቆፈሩዋቸው ጉድጓዶችም ነበርዋቸው ሀገራቸውም አገረ ብጹአን ተብሎ ይጠራ ነበር እስክንድር ይህንን ሲያይ የጥበባቸውን ጥልቀት እና የልባቸውን ንፅህና ተረዳ እስክንድር ከእነሱ አንዱን እንዲህ ሲል ጠየቀው ‹‹ህያዋን ይበዛሉ ወይስ ሙታን? ሰውየው ከባለጸጎች ሙታን ይበዛሉ›› ሲል መለሰለት ድህነትም ከሞት ይቆጠራል በማለት ተናገረው፡፡

እስክንድር ሁለተኛ ‹‹መንግሥታትን ማን ይፈልጋቸዋል›› ሲል ጠየቀው መንግሥትነት ደግሞ ደም ካላፈሰሱ አትቀናም ይህንን የሚያደርግ ሁሉ ደግሞ እግዚአብሔርን የሚፈራ ብቻ ነው፡፡ የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነውና መንግሥትነትስ የእግዚአብሔር ገንዘብ ናት እግዚአብሐር እንደፈቀደ ይሰጣል ይነሳልም›› ሲል መለሰለት ሌላውን ፈላስፋ ከብርሃንና ከጨለማ የቱ ነው የቀደመው ሲል ጠየቀው ፈላስፋውም



www.ethiopianorthodox.org

ጨለማው ይቀድማል ልጅ በናቱ ሆድ በጨለማ ይኖራል ሲወለድ ወደ ብርሃን ይወጣል በማለት መለሰለት ሌላው ፈላስፋ ‹‹እውነተኛው ሰው እግዚአብሔር የማይሰወርበት ነው እግዚአብሔር የእውነት አምላክ ነውና›› አለው ፈላስፋዎቹን ብዙ ነገር ጠየቃቸው እነሱም ብዙ ነገር መለሱለት በመጨረሻ የምትፈልጉትን ሁሉ ጠይቁኝ አላቸው እነሱም ዘላለማዊ ህይወትን ስጠን አሉት እሱም ይህንን መስጠት የኔ ስልጣን አይደለም አላቸው እነሱም ሲመልሱለት አለምን ለማንበርከክ የመትደክመው ለማን ብለህ ነው ማንም ከሞት እንደማይቀር ካወቅህ ለምን ይህን ያህል ትደክማለህ አሉት ካንተ በኋላ ግን ማን እንደሚነግስ አታውቅም አሉት፡፡

እስክንድር የሚከተለውን መልስ ሰጣቸው ‹‹የኋላ ንጉሥ እንደሚሆን የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ነው ነገሥታትን የሚለዋውጣቸው እግዚአብሔር ብቻ ነው ነገሥታትም የእግዚአብሔር መልእክተኛ የሚሆኑበት ጊዜ አለ እሱ ያነሳቸዋል እሱ ይጥላቸዋል መጥፎ አመራር ያለውንና በትክክል የሚያስተዳድረውን እግዚአብሔር ይለየዋል እኔም እግዚአብሔር በሰጠኝ ስልጣን ምስራቁን ምዕራቡን ደቡቡን ለመግዛት ችያለሁ የሁሉንም ንብረት እየሰበሰብኩ የሰበሰብኩትም ንብረት ከኔ በኋላ ለሚመጣው ይሆናል፡፡

ዘላለማዊ ልዑልና ክቡር እግዚአብሔር ፍጥረቱ ላይ ፈረደ እሱንም ተከትለን በዓለም እንድንኖር ፈቅዷል እግዚአብሔር ባይፈቅድ ኖሮ እኛ የዓለም ሰዎች ምንም ባልሰራን ነበር ያሰብነውም ባልተፈጸመልን ነበር ነፍስ የዋህነትንና ርህራሄን ታፈቅራለች ጸጥታና ዝምታ ትወዳለች እኔ የማገኘው ምድርን ነው ነፍስ ጠብንም ትወዳለችወደ መከራ ለመድረስ ጠብና ድካምን ትሻለች ጥፋትም ይደርስባታል እኔ መከራ በጠናብኝ ጊዜ ሞትን እፈልጋለሁ ያመንገድ ግን አይገኝም፡፡



በራሴ ፈቃድ የማደርገው የለኝም ነገር ግን ክቡርና ልዑል እግዚአብሔር ያነሳኛል ይህንንም ለማድረግ ይመራኛል እግዚአብሔር በሰው ልቦና አድሮ ሁሉን ባያደርግ ኖሮ ሰዎችንም ወደ ሚደክሙበት ባይመራቸው ኖሮ መታመንን ድካምን ባይጨምርባቸው ኖሮ ለመትከል እና ለመዝራት ባልተነሳሱ ነበር ብዙ ደክመው የብሱንና ባህሩን እያቋረጡም ባልነገዱም ነበር ይህን ሁሉ ሰዎች ባያከናውኑ ደግሞ ምግባቸውን ባላገኙ ነበር፡፡

ሰዎች በተለያየ የዓለም ስራ ካልተጠመዱ ዓለም ትጠፋለች ሰውንም ታጠፋለች ስለዚህ ሰዎች በዚህ ዓለም በተለያየ ስራ እንዲጠመዱ እግዚአብሔር ፈቀደ ያዳም ልጅ ሁሉ ስራ እንዲሰራ ሰዎች ንብረቱን እንዲያሳምሩ እንዲጠቀሙ በዚህም የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲፈጸም ዓለምም በስርአት እንድትመራ እግዚአብሔር ፈቅዷል፡፡

የመጽሐፉ ደራሲ እስክንድር ከዚህ ላይ የተገለጸው ከፋርስ ፈላስፎች ጋር ከተመላለሰ በኋላ ከነሱ ተለየ ይላል እስክንድር ከእነሱ ከተለየ በኋላ የምድርን ዳርቻ ሁሉ ለማዳረስ ተነሳ ያልታየውንም ክፍለ ዓለም ሁሉ የሰዎችን አኗኗር ለማየት ጉጉት አደረበት በዚህችው ዓለም የተለያየ የአፈጣጠር ባህርይ ያለቸው ፍጡራን ይኖራሉ በማለትም ተናግሯል ሰዎች እስከማይኖሩበት ሃገር ሁሉም ደረሰ በዚሁ አራዊት ብቻ ነበሩ፡፡

እስክንድር ምድረ በዳ የሆነ አገርንም አግኝቷል ወደ ባቢሎን እስኪደርስ ድረስም ጉዞውን አላቋረጠም ብርሃን የሌለበት ድቅድቅ ጨለማ ብቻ የተዋጠና ምንም የፀሃይ ጮራ የማይደርስበት ቦታንም አግኝቷል በዚሁ ለማለፍ አልቻለም ነገር ግን በሌላ አቅጣጫ ዞሮ ወደ ባቢሎን ሲደርስ ችሏል ተአምራትንም አይቷል መንግሥቱም ጸናለት አህዛብ ታዘዙለት ንብረታቸውንም ማረከ የምድር መዛገብትም ተገለጹለት ችሎታውም አደገለት ክብሩም በዛ፡፡



www.ethiopianorthodox.org

ይህ በዚህ እያለ የወታደር አለቃ የሆነ አልጠቂስ ሲገድለው አቀደ ከወይን አቅራቢው ጋርም ተነጋገረ የወታደሩ አለቃ አልጣቂስ ለወይን አቅራቢው ከወይን ጋር ጨምሮ እንዲሰጠው ሰጠው ከዚያ በፊት ወይን አቅራቢውን ተቆጥቶ አበሳጭቶት ነበር ስለዚህ ቂሙን ለመወጣት ከአልጠቂስ ጋር እስክንድርን ለመግደል ወሰነ መርዙንም ከወይን ጋር ጨምሮ ስላጠጣው አስክነድር ሞተ።።

አንጦፌስ የእስክነደርን ሬሳ በረቅ ሳጥን አስገብቶ ከጠቅላላ ሰራዊት ጋር በመሆን ወደ እስክንድሪያ ወሰደው በዚሁም ተቀበረ እስክንድር የጦር መሪ ሆኖ ባባቱ ፊሊጶስ ዘሜቄዶንያ መንግሥት ስር መዋጋት የጀመረው በአሥራ አምሥት አመቱ ነው ንጉሥነትን የተረከበው በሃያ አመቱ ነው ጠቅላላ እድሜው ፴፪ ዓመት ነው እስከሞተበት እለት ድረስ በአሸናፊነት ብቻ ቆይቷል የተወለደውም ግብፃውያን ሙሰር በርሙዳ በሚሉት ወር በዕለተ ረቡእ ጥዋት ነው በግእዝ ወርሃ ሚያዚያ ይባላል የእስክንድር ታሪክ በዮናናውያንና በፋርሶች የተመዘገበ ነው።።

## ምዕራፍ ፰

## እስክንድር ከሞተ በኋላ የአይሁድ ዜና

እስክንድር ከሞተ በኋላ በአይሁድ ላይ በፅርአውያን ብዙ ነገር ተፈጽሟል የመጀመሪያው ታሪክ ከአንትንያኮስ የተፈፀመባቸው ነው የመፅሐፉ ደራሲ እስክንድር እንደሞተ መንግስቱ ለአራት የእስክንድር የቅርብ ባለሟሎች መከፋፈሉን ይገልጻል እነዚህ አራቱ ነገስታት ስር መሰረታቸው ፅርዕ ሆኖ አይሁዶችን በተለያየ መልክ ገዝተዋል።

እነዚህ ከእስክንድር በኋላ የተነሱት ፅርዐውያን ብዙዎቹ አይሁዶችን በክፉ አይን የሚመለከቱ ነበሩ እግዚአብሔር ግን አይሁዶችን ከእነሱ ጥፋት



ጠብቋል ከክፉዎቹ የጽርዕ ነገሥታት የመክስሞናይ ነገዶች በሆኑ ካህናት አማካኝነት አድሮ እግዚአብሔር ከጥፋት አድኗቸዋል የመጽሃፉ ደራሲ እንደመዘገበው ከእስክንድር ቀጥሎ የነገሠው ሳልጥፎር በጣም ደግ ነበር።

ለቤተ እግዚአብሔር በየዓመቱ ብዙ ገንዘብ ይሰጥ ነበር በቤተ-መቅደስ ዙሪያ ለሠፈሩት ነዳያንና ምስኪናንም ምግብ ይሰጥ ነበር ለካህናትና ለሌሎቹ የቤተ-መቅደስ ሠራተኞችም ፍላጐታቸውን ያሟላ ነበር ከሱ በፊት የነበሩ የፅርዕ ነገሥታት ይሰሩት የነበረው ደግ ነገር ሁሉ ያከናውን ነበር።

ከአይሁድ መካከል የሆኑ ክፉዎች ሰዎች ‹‹አልማዝ እንቍና ወርቅ በቤተ መቅድስ አለ ይኸውም ተቆጥሮ የማያልቅ ነው ይህ ሁሉ በቤተ መቀደስ ሳይሆን በቤተ መንግስት ነው መቀመጥ ያለበት›› ብለው ደገኛውን ንጉሥ ሳርፓፎስ ነገሩት በዚሁም ንጉሥን ሸነገሉት ይህ ንጉሥ መልእክተኛን ወደ ቤተ መቅደስ ላከ።

ሃናንያ የተባለው የቤተ መቅደስ ታላቅ ካህን ከአይሁድ ሽማግሌዎች ጋር በመሆን የንጉሡን መልእክተኛ ተቀብለው ስለ አመጣጡም ጠየቁት ሳርፓፍስ ንጉሥ እሱን በላከበት ምክንያት ዘርዝሮ አስረዳቸው በዚህ ጊዜ ካህን ሃናንያ እንዲህ አለው ‹‹በቤተ መቅደስ አልማዝ እንቍና ወርቅ የለም ከፋርስ ነገሥታት እና ከፅርዕ ነገሥታት የተሰጡ ማስታወሻዎች ብቻ ናቸው በቤተ መቅደስ የሚገኙት የተቀረው ገንዘብ ደግሞ ለካህናት ቀለብ ለነደያንና ለምስኪናን የሚሰጥ ገንዘብ ብቻ ነው ያለው ይህም ገንዘብ ነገሥታቱ መንግሥታቸው ይጸናላቸው ዘንድ እንዲፀለይላቸው የሰጡት ነው።።››

ካህኑ ሃናንያ የንጉሡን መልእክተኛ ከቤተ መቅደስ ገንዘብ ለመውሰድ እንዳይሞክርም በእግዚአብሔር ስም አስፈራራው አስጠነቀቀውም መልእክተኛው ግን የካህኑን ሃናንያን ማስፈራራት እንደምንም አልቆጠረውም የሱን ተከታዮች ቤተ መዛግብቱን እንዲበረብሩ አዘዛቸው ይህ



www.ethiopianorthodox.org

እንደሚያጠጣ አብሮ ተቀርፆ ነበር ይቺንም የወርቅ ሳህን ወደ ቤተ መቅደስ በስጦታ ላከት የዚህችም ሳህን ምስጢር ሳያውቁ ሰዎች ለብዙ ጊዜ ኖሩ።

ከመጀመሪያው አንስቶ የተጻፈው ክፍል ቀዳማዊ ከዚህ ላይ ተፈጸመ ቀጥሎ ደግሞ ክፍል ዳግማዊን እንጽፋለን ለእግዚብሔር ክብር ምስጋና ይድረሰው አሜን።

## ክፍል ሁለት

## ምዕራፍ ፩

## ዜና አንቲያኮስ መቄዶናዊ

አንቲያኮስ መቄዶኒያዊ በዮናናውያን ላይ ነግሷል ይህ መጽሐፍ በዘመኑ በአይሁድ ላይ የደረሰውን ይገልፃል ጸሐፊው እንዳስቀመጠው የአንቲያኮስ ቤተ መንግስት መቄዶኒያ ነበር ብልማይ የእስክንድርያው ንጉሥ ሲሞት አንቲያኮስ ግብፃውያንን ወግቶ አሸነፋቸው ግብፅን ጨምሮ በገናናነት ብዙ ሀገሮችን ተቆጣጠረ የፋርስ ነገስታት ጨምሮ አሉ የተባሉ ነገስታት ሁሉ ለእሱ ተገዙ ከዚህም የተነሳ ትዕቢትና ትዝህርት ተሰማው ነገስታት ሁሉ በምስሉ ጣዖታትን እንዲያቆሙ አዘዘ አንቲያኮስ አምላክ እኔ ነኝ አለ ሰዎችም እንዲያመልኩት አዘዘ እንዲያመልኩትና እንዲሰግዱለትም ወታደሮችን በየአቅጣጫው ሰዎችን ላከ ከአይሁድ በቀረም ነገስታት ሁሉ ሊሰግዱለት ፈቃደኛ ሆኑ አይሁድ ግን አንሰግድም በማለት ፀኑ በዚህ ዘመን ከቤተ መቅደስ ሰማይ ላይ ከእሳት ፈረሶች ላይ የተጫኑ እሳታውያን እርስ በእርሳቸው ሲገዳደሉ ታይተው ነበር ይህ ከቤተ መቅደስ አየር ላይ እየታየ ለአርባ ቀናት ቀጥሎ እንደነበር ይነገራል።

በዚህ ቤተ መቅደስ ሦስት መጥፎዎች ካህናት ነበሩ ስማቸውም መባልስ ስምዖንና ኤልፊሞስ ይባላል። ለእያንዳንዳቸው አካይ ከምትባለው



አገር ወዳጆች ነበርዋቸው እነዚህ አማጽያንና መጥፎች ካህናት ወደ ንጉሥ አንቲያኮስ ሄዱ አይሁድ የሱን ትእዛዝ አንቀበልም ብለው ለጣዖት አለመስገዳቸውንም ነገሩት የእነዚህ መጥፎዎችና አላማ ቢሶች ካህና ይህን ደርጊት መፈጸም በዚሁ ሳቢያ በንጉሡ ታውቀው የሱ ቀራቢዎች ለመሆን ነው ስለ ወገኖቻቸው አይሁድ መደምሰስ ግን አልተሰማቸውም።

አንቲያኮስ በድንገት ወደ ቤተ መቅደስ መጥቶ ብዙ አይሁዶችን ገደለ የቀሩትን በባርነት ማረካቸው በህይወት ተርፈው የማምለጥ እድል የገጠማቸው ወደ ጫካው ከቡ ከዚያም ተቀመጡ ለቤተ መቅደስም ከተከታዮቹ ሾመ የተሾመው ፊልፎስ ይባላል ሰንበትን እንዳያከብሩ እንዳይገረዙ ያሳማን ስጋን እንዲበሉና ለጣዖትም እንዲሰግዱ አዘዘ እሺ ያለ በሰላም እንዲኖር እንቢ ያለ እንዲገደልም አዘዘ ፊልፎስ የተባለውን ሁሉ እንዲፈጽሙ ቢያዛቸው አይሁድ እንቢ አሉ እንቢ ያሉትን ገደላቸው የታዘዙትን ደግሞ በሰላም እንዲኖሩ አደረገ ፊልፎስ ከአይሁድ ሴቶች የሆኑ ሁለት ሴቶች ልጆቻቸውን በአንድ ድብቅ ቦታ ደብቀው አገኛቸው ህጻናቱን ከእናቶቻቸው ጡት ጋር አጣብቆ በሰቅላት አስገድሎ በደንጋይ አስወገራቸው እናቶቹ ከህጻናት ልጆቻቸው ጋር በአሰቃቂ አገዳደል ተገደሉ።

## ምዕራፍ ፪

## የአልአዛር ካህን አሟሟት ታሪክ

እነዚህ ከሀዲዎች እና አመፀኞች ካህናት ነገር እየሰሩ ወገኖቻቸውን ማስፈጀቱ ሥራችን ብለው ተያያዙት ከእስክንድሪያ ሊቃውንት አይሁድን በመምራት ብሉይ ኪዳንን ያስተረጎመው ታላቁ ካህን አልአዛር በአንቲያኮስ ጊዜ እጅግ ሸምግሎ ነበር ፊልፎስ ወደሱ አስመጣው የዘጠና አመት ሰው ስለነበር በግድ መጣ ፊልፎስ ‹‹ከቀድሞ ጀምሮ አንተን አውቅሃለሁ ስለዚህ



www.ethiopianorthodox.org

በሰላም የእርጅና ዘመንህን እንድትጨርስ የንጉሥን ትእዛዝ ፈፅም›› አለው አልአዛር ግን እግዚአብሔር ያልወደደውን አላደርግም አለው፡፡

ፊልጶስ ‹‹ራስህ ካረድከው ስጋ ከቤትህ አምጣና ከፊቴ ተመገበው እኔ በዚያን ጊዜ አንተ የማትበላውን ሌላው ሥጋ እበላለሁ በዚህ ጊዜ አንተ የአሳማን ሥጋ እንደበላህ አስመስልብሃለሁ›› በዚህን ጊዜ ከሞት ትድናለህ አለው አልአዛር ግን እኔ ህገ እግዚአብሔርን በመጠበቅ ኑሩ ለባእድ አምልኮ አትንበርከኩ....... እያልኩ ወገኖቼን አይሁድን ስመክራቸው እና ሳስተምራቸው ኖርያለሁ አሁን እኔ እድሜዬ ዘጠና ሆኖ አርጅቻለሁ በድብቅ ለጣዖት ሳልሰግድ በግልፅ ደግሞ ለጣዖት የሰገድኩ የአሳማ ስጋንም የበላሁ በመምሰል ስታያቸው አነሱን መርቼ ከእግዚአብሔር መራቄ ነው ስለዚህ አንተ እኔን በህይወት ለማቆየት አትድከም በሃይማኖቴ ከሞትኩ ለአይሁድ አብነት እሆናለሁ በእግዚአብሔርም ደህንነትን አገኛለሁ›› የሚል መልስ ሰጠው፡፡

ፊልጶስ በዚህ ጊዜ በጣም ተናደደና እንዲያሰቃዩት አዘዘ በመከራው ጊዜ አልአዛር እንዲህ አለ ‹‹አቤቱ እግዚአብሔር ሁሉን የምትችል አንተ ነህ ይህን መከራ ከኔ አስወግድ በአንትያኮስ ትእዛዝ አልሄድኩም ትእዛዝህን ጠብቂያለሁ በሃይማኖትም ፀንቻለሁ መከራንም ሁሉ እንደ ቀላል ነገር ተመለከተኩት ይህ የመከራ ፅናት እንዳያደክመኝ አንተ ቶሎ ውሰደኝ ስህተትንም እንዳልፈጽም ጠብቀኝ›› በሎ ጸለየ፡፡

እግዚአብሔር ልመናውንና ጸሎቱን ሰምቶ ነፍሱን ከዚያው ለየ በሃይማኖቱ እንዲሞት አደረገ አልአዛር በጠቢብነቱና በትእግስቱ ለብዙዎች አይሁዳውያን አርአያ ሆነ አግዚአብሔርም ጸሎቱን ሰምቶ ጠበቀው፡፡



## ምዕራፍ ፫

## አንቲያኮስ የገደላቸው ሰባት ወንድማማቾች ታሪክ

ከአይሁድ ወገኖች ሆነው ነገረ ሠሪዎች የሆኑ ሠዎች ሰባት ወንደማማቾች ወጣቶች ለጣዖት አንሰግድም እንዳሉ ለፊልጶስ ነገሩት ፊልጶስም ሰባቱን ወንድማማቾች ወደ አንትያኮስ ተይዘው እንዲሄዱ አደረገ፡፡ አንቲያኮስ የእነሱን መምጣት ሲሰማ ቃላቃቸው ከፊቱ እንዲቀርብ አዘዘ እሱም ቀረበ አንቲያኮስ ለጣዖት እንዲሰግድ ቢያዘው እምቢ አለ እንዲህም አለ ‹‹ንጉሥ ስለሆንክ ለቤተ መንግሥትህ አንድንገዛ ብታዘን እንገዛለን እንታዘዛለን አንተን ግን አናመልክህም የሚመለከው እግዚአብሔር ብቻ ነው ለፍጡርም አንሰግድም ፍጡርንም አናመለከም›› አለው፡፡

አንቲያኮስ ተቆጣ ከብረት ጋንም በእሳት እንዲነድ አደረገ እጁና እግሩንም እንዲቆረጥ አደረገ እሱንም በዚሁ ገድሎ ሁለተኛውን ወንድሙን አስመጣው በዚህ ጊዜ የንጉሡ ባለሟሎች ግራና ቀኝ ተቀምጠው ነበር ‹‹በወንድምህ ላይ የደረሰው መከራ እንዳይደርስብህ የንጉሡን ትዕዛዝ ተቀበል አሉት፡፡ይህ ወጣት ግን እኔ አግዚአብሔረን ትቼ ለሰው አልሰገድም ከወንድሜ ያላነሰ መከራም አድርስብኝ ካለ በኋላ ወደ ንጉሡ አንቲያኮስ ቀረብ ብሎ አንተ አመጸኛ ከሃዲ ትእቢተኛ ስስታም በስጋችን ላይ ሰልጣን አለህ በነፍሳችን ላይ ግን ስልጣን የለህም ያንተ መከራ ያልፋል የአግዚአብሔረን ጸጋ ተቀብለን የምንሄድበት ቦታ ግን አያልፍም የፈለከውን በእኛ ላይ አድርግ›› አለው፡፡

አንቲያኮስ ወድያው አስገደለው እና ሦስተኛውን ወጣት አስቀርቦ ያለ ፍርሃተና ያለ ድንጋጤ ‹‹አንተ የእግዚአብሔር ጠላት ያንተ ግርማ አያስደነግጠንም በእኛ ላይ አያደረስክ ያለኸውን ያረመኔነት ተግባር



www.ethiopianorthodox.org

በሥልጣንህ የፈጸምከው አይምሰልህ እኛ መከራውን ታግሰን የሱ ሃይል እንዲገለጥ እግዚአብሔር ስለፈለገ ይህን አደረገ እንጂ እኛም አግዚአብሔርን አምነን ሃይማኖታችንን አጽንተን መከራውን እንችላለን›› ሲለው ንጉሡና ተከታዮቹ ተደነቁ ወድያውም አስገደለው፡፡ቀጥለውም አራተኛውን አመጡት ‹‹ለከበረውና ከሁሉ የበላይ የሆነው እግዚአብሔር ህይወታችንና ነብሳችንን እንሰጣለን ወጋችንን ከእሱ እንቀበላለን ምክንያትን በማቅረብ ድህነት በማይገኝበት ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት ቀርበን አንደሰታለን›› በማለትም ከንጉሡ ፊት ተናገረ ንጉሡም አስገደለውና አምስተኛውን ወጣት አስመጥቶ ሲያቆመው አንተ ከሃዲ ንጉሥ እግዚአብሔር የተወን አይምሰልህ አንተ በስጋችን ላይ ስልጣን ሰጠህ ዘላለማዊውን ክብር እኛን ያጎናጽፈናል በእሱ ዘንድ ስልጣናችን ይበዛል አንተም በምትፈፅመው የአረመኔነት ድርጊት ዋጋህን ታገኛለህ የእኛን ፍርድ ለአንተ ዘሮች ይተላለፋል›› አለው እርሱንም አስገድሎ ስድስተኛውን ወጣት አቀረበው ወጣቱ እንደደረሰ ‹‹በልዑልና ክቡር እግዚአብሔር አምናለሁ በደሌንም ይቅር እንዲለኝ ወደሱ እጠጋለሁ ትዕዛዙንም እቀበላለሁ ሃይማኖተ ቢስ ሁነህ የምትፈጽመው ግፍም ይፈርድብሃል ከዓለምም ትነቀላለህ›› ብሎ ሲጨርስ አስገደለው፡፡

ስድስቱን ወንድማማች አስገድሎ ከሁላቸው እጅግ ያነሰውን ህፃን አስቀረበው በዚህ ጊዜ የሚሆነውን ለመመልከት እናቱ አብራ መጣች የልጆቿንም ሬሳዎች አየች ነገር ግን ፍርሃትና ድንጋጤ በሷ ላይ ፈጽሞ አልነበረም የልጆቿ ሬሳዎች በየ ቦታው ተጥለው ነበር ለመጨረሻውና ሰባተኛው ልጇ እንዲህ አለችው ‹‹ልጄ ሆይ እኔ ወላጅ እናታችሁ ከሆንኩ ካሳደግዋችሁም ከሁሉ ሰው የበለጠ ርህራሄ ቢኖረኝም በእናንተ ተግባር የፈራሁት ምንም የለኝም እናንተን ስፀንስ በሆዴ ያለውን አላወቅኩም ከእናንተ እንዳንዱ ብሆን በወደድኩ ነበር፡፡



ነገር ግን ሁሉ ከልዑል እግዚአብሔር ዘንድ ይሆናል ነፍሳችሁንና ስጋችሁን የፈጠረ እሱ ነውና እንደወደደ አድርጎአችሁ ወደዚህ ዓለምም አወጣችሁ ልቦናን ሰጥቶ ከጥፋት ሁሉ ጠበቃችሁ ትእዛዞቹን አስተማራችሁ ሃይማኖቱንና ህጉንም አስጠበቃችሁ ለተወሰነ ጊዜም እንድትመላለሱ /በዓለም/ ፈቀደ ጥንካሬም ሰጥቶ በመከራ እንድትፈተኑ አደረገ እናንተም ስለሱ ፈቃድ መከራውን ታገሳችሁ አንተም በእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ ትገኛለህ እግዚአብሔር በመረጠላችሁ ጎዳናም ቆመህ ትገኛለህ ንጉሣችሁና ፈጣሪያችሁ እሱ ነውና፡፡

እግዚአብሔር ለእናንተ የሚበጀውን ያውቃል እኔ ስለእናንተ የሚጠቅመውን አላውቅም ከወለድኳችሁ ጀምሮ በእናንተ የተደሰትኩበት ቀን የለኝም የተደሰትኩት ዛሬ ብቻ ነው ነፍሳችሁን ለእግዚአብሔር ሰጥታችኋልና ሥጋችሁንና ነፍሳችሁን የፈጠረ እሱ ነውና እናንተ መከራንና ጭንቀን ታገሳችሁ ህገ እግዚአብሔርና ሃይማኖትን ለመጠበቅ ይህንን ፈጸማችሁ ይህን ዓለም የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ሳታፈርሱ ተሰናበታችሁ ለዓመጸኞች አልታዘዛችሁም ብፅዓትና ደስታ ለእናንተ ይገባል እናንተ አሸናፊዎች አናንተ የክብር ወራሾች፡፡››

የመጽሃፉ ደራሲ አንቲያኮስ እቺን ሴት ሲመለከታት ከልጇ ጋር ወጣች እሱ የደነገጠች መስሎት ነበር ስለተገደሉትም ልጆቿ ያዘነች መስሎ ታየው የቀረውንም ሰባተኛው ልጇ እንዳይገድልባት የምትለምነው መሰለው ከመገደል ይድን ዘንድ የንጉሡን ትእዛዝ መፈጸም እንዳለበት ታግባባው ይሆናል በማለተም ገመተ ነገር ግን የሴትዮዋ በጥብአት መጽናት ተመለከተና ራሱ ልጁን ያግባባው ጀመር ይሁንና ልጁን በተለያየ መንገድ ለማግባባት ቢሞክርም በሃይማኖቱ ጸና እንጂ ሲመለስለት አልቻለም፡፡ ልጁን የማግባባቱ ሁኔታ ተስፋ ሲያስቆርጠው ወደናቱ ተመለሰ እንዲህም አላት

www.ethiopianorthodox.org

‹‹አንቺ ሴት ልጆችሽ አልቀው ይህ ብቻ ቀርቶልሻል እሱ ከተገደለ ደግሞ ብቻሽን ቀርተሽ ልጅ አልባ ልትሆኚ ነው ስለዚህ ትዕዛዜን ተቀብሎ በህይወት ይኖርልሽ ዘንድ አስተምሪው›› አላት፡፡

ሴትዮዋ ልጇን ስጠኝና ማንም በሌለበት ለብቻየ ልምከረው አለችው ልጇንም ከእሷ ዘንድ እንዲጠጋ ፈቀደላት ልጇ ሲጠጋት ሳመችው እንዲህም አለቸው ‹‹ልጄ ሆይ ከሁሉ አብልጬ እወድሃለሁ እኔ የምነግርህን ልትሰማኝ ይገባል በሆዴ ተሸክሜሃለሁና ጡቴንም አጥብቼሃለሁ ህገ እግዚአብሔርን ያስተማርኩህ እኔ ነኝ ሃይማኖትንም ከእኔ ተምረሃል እኔ የምነግርህን ለመቀበል ካልፈለክ ሰማይንና ምድርን ተመልከት እግዚአብሔር አምላክህንም አስበው ሁሉን ፈጥሮ ሲያበቃ ከትንሽ ነጠብጣብብ ሰውን ፈጠረ ትዕዛዙን ያከብር ዘንድም መከረው በትንሿ አለም እንዲኖርም አደረገ፡፡

እግዚአብሔር ሰውን በዚች ዓለም ትእዛዙን ያከብር ዘንድ ነው የፈጠረው ከዓለም በሞት ሲለይም ወደ እግዚአብሔር ይሄዳል እግዚአብሔርም መልካም ለሠራ መልካምን ያድለዋል ክፉ ከሰራ ደግሞ ለመከራ ይዳርገዋል ልጄ ሆይ ወደ ማይሞተው እግዚአብሔር ለመድረስ ጥረትህ ይሁን ይህንን ጣያተኛ ንጉሥ አትፍራው ከስሙ ተመልከት ወደልቦነህ አግባው ከግርማውም አትደንግጥ በትእዛዘ እግዚአብሔር ጸንተህ ሙት ወንድሞችህ የተቀበሉትንም ሞት ሙት ከዚያ ወደ ዘላለማዊ ደስታ ትሄዳለህ ለቅጽበተ አይን ጊዜ ያህል እንኳን ልቦናህ ከእግዚአብሔረ አይራቅ፡፡››

ብዙ ስትመክረው ከቆየች በኋላ አንቲያኮስ እናቱ ተእዛዜን እንዲቀበል አግባብታዋለች ብሎ ስለገመተ ልጁን ወደሱ ጠራው ‹‹ከዕብደትህ እንድትመለስና ትእዛዜን አንድትቀበል የመከረችህ የእናትህ ምክር ተቀብለሃል›› ሲል ጠየቀው ልጁ ‹‹ለእግዚአብሔር እንጂ ለአንተ አልታዘዝም



እግዚአብሔርን እንጂ ሌላንም አላመልክም ለጣዖት አልሰግድም ለእሱ ብቻ እሰግዳለሁ እኔ ወደ ወንድሞቼ ለመድረስ እጅግ እቸኩላለሁ አንተ በእኛ ላይ ብትከፋ ክፋቱ ለነብስህ ይተርፋል መልካምን ብታደርግ እንዲሁ ያንተ የኋላ እድል የተበላሸ ይሆናል ስልጣንህ ከእግዚአብሔር እጅ እንድታመልጥ አይረዳህም፡፡ እኛ ሃይማኖትን ከጠበቁ ሰዎች የእግዚአብሔር ቁጣ እንደምታልፍ እናውቃለን እግዚአብሔር በአለም ያለህን ኩነኔ ሊልክብህ ይችላል ወደሱ ከመሄድህም አስቀድሞ መከራ ይደርስብሃል በክፉ ሞትም ትሞታለህ›› በማለት በጥብአት ተሞልቶ መለሰለት የህጻኑን ነገር አዳምጦ ከፈጸመ በኋላ አንቲያኮስ እጅግ ተቆጣ ከወንድሞቹ በባሰና በአሰቃቂ ሁኔታም እንዲገደል አዘዘ እናቱም በሞት ከልጆቿ ጋር እንዲያገናኛት እግዚአብሔርን ለመነችና ወዲያው ሞተች ልጁም ተገደለና እናትና ልጅ አብረው ወደ እግዚአብሔር ሄዱ፡፡ አንቲያኮስ ወደ ቤተ-መቅደስ ተመልሶ ሄደና ትእዛዙን ካልተቀበሉ በቀር አይሁዶችን ጨርሶ እንዲያጠፋ የሾመው ፊሊፎስን አዘዘው በዚሁም ፊሊፎስ እያደነ ብዙ አይሁዶችን ፈጀ፡፡

## ምዕራፍ ፬

## የዮሐንስ ካን ልጅ መታታን ታሪክ

ከክስምና ወገን ለመጀመሪያ ጊዜ የተነሳው መታታን ነው መታታን ወልደዮሐናን ደግ ሰው ነበር ሸሽቶ በአንቲያኮስ ዓረመኔነት ወደ ጫካ ገባ ሰባ ያህሉ አይሁዳውያንም ተከተሉት መታታን በትውልዱ ዩናናዊ ነው በአይሁዳውያን ላይ የደረሰው ግፍ ግን እጅግ አሳዘነው ስለእግዚአብሔርም ቀናኢ ሆነ፡፡

አንቲያኮስ ከቤተ-መቅደስ እርቆ መሄዱን አረጋገጠና በሚስጢር ወደ አይሁድ ሃገር መልእከተኞችን ላከ ስለአይሁድ ድሕነት እንደሚቆረቆርም

አስታወቃቸው አስቀድሞም ለእግዚአብሔር ቀናኢነታቸውን እንዲጠብቁ መከራቸው ብዙዎቹ ወደሱ እንዲሰበሰቡ ከያሉበት ቀሰቀሰ ጉልበት ያለው ሁሉ አንቲያኮስ ለመበቀል እንዲነሳ ጥሪ አደረገ ብዙዎቹ አይሁዶችም ዮናናውያንን ለማሸነፍ መተባበር እንዳለባቸው ተረዱ።

በቤተ-መቅደስ የተሾመው ፊሊፎስ ግን የመታቲያን መነሳትን ስለተረዳ ሊዋጋው ተነሳ በዚሁም ብዙ አይሁዶች ካንድ ዋሻ ውስጥ መደበቃቸውን አወቀና እንዲወጡ አዘዘ አይሁዶቹ ግን ሰንበት ስለሆነ አንንቀሳቀስም አሉ ባሉበትም በጢስ አሳፍኖ ፈጃቸወ ሕፃናት፣ሽማግሌዎች፣ሴቶችና ወንዶች አንድ ላይ በዋሻው አንድ ሺ ሰዎች ሞቱ።

እነዚህን ሰዎች እንዲፈጁ ያደረገ ይሁዲነቱ ክዶ ከዮናናውያን ጋር ያደረ አይሁዳዊ ነው ይህ አይሁዳዊ ዮናናውያን ለማስደሰት አሳማን አርዶ ዮናናውያን ለሠሩት ቤተ-ጣቆት መስዋእት አቀረበ ይህንን ያደረገው መታታን ለማበሳጨት ብሎ ነው። ይህ ሁሉ ሲፈፀም መታታን ቆሞ ይመለከት ነበረና ለሃይማኖቱ ከመቅናቱ የተነሳ ያንን ለጣዖት የሰዋውን አይሁዳዊ በያዘው ሰይፍ መታው ባንድግዜም መትቶ አንገቱን ቆረጠው ከአይሁዳዊው መጥፎ ሰው ጋር የተባበረውንም ባለሥልጣን ቀጥሎ በሰይፍ ቆረጠው።

የሱን ድፍረት የተመለከቱ አይሁድ በፍጥነት ተሰበሰቡና የዮናናውያንን ሠራዊት ገጠሙዋቸው እግዚአብሔርም ያሸናፊነት እድል ለአይሁድ ሰጠ። ብዙዎቹ ዮናናውያንም ተገደሉ የቀሩትም ዮናናውያን ሸሹ መታታን አየተከታተለና በየመውጫው እየጠበቀ ከአይሁድ ጋር በመሆን ብዙዎቹን ዮናናውያንን ፈጀ ከያገሩ የተበታተኑ አይሁድ የመታታንን መነሳት ሰምተው ከየተሰደዱበት እየተመለሱ ከመታታን ጋር ተሰለፉ አይሁዶች እጅግ በዙ።



መታታን የመሞቻው ዕለት ደረሰና አምስቱን ልጆቹን ጠርቶ ‹‹ልጆቼ ሆይ እግዚአብሔርን አምነን ከተነሳን እሱንም ከለመነው ሃይማኖታችንም አፅንተን ወደሱ ከተጠጋን እሱ ከኛ ጋር ይቆማል ስለዚህ እግዚአብሔርን አምናችሁ በጠላቶቻችሁ ላይ ተነሱ ስለዚህ በእግዚአብሔርና ስለሃይማኖቱ ጠላትን ለመዋጋት ተነሱ ለሃይማኖታችሁ እየተዋጋችሁ ብትሞቱ ወደፃድቃን ትሄዳላችሁ ካሸነፋችሁ የእግዚአብሔር ፀጋ ይበዛላችኋል›› በማለት መከራቸው እሱም ሞተ ይሁዳ ልጁም በምትኩ ነገሠ።

## ምዕራፍ ፳

## የመታታን /መታትዮ/ ልጅ ይሁዳ ታሪክ

የማታታን /መታትዩ/ ልጅ ይሁዳ ታሪክ እንደሚከተለው ይቀርባል ከክስምናይ ነገዶች እሱ ሁለተኛው ነው የመፅሐፉ ደራሲ ማታታን /መታትዩ/ ከሞተ በኂላ ልጆቹ ያባታቸውን ትእዛዝ እንዳከበሩ ይገልፃል ይሁዳ ወንድማቸውን መሪ በማድረግ ዮናናውያንን ለመውጋት ዝግጁዎች ሆኑ ፍልፎስ የአይሁድ በይሁዳ መሪነት መነሳት ሰምቶ ብዙ ሰራዊት እንዲወጋቸው ላከ አይሁዶቹ ግን አሸነፉት።

ይሁዳ እጅግ በረታ አንትያኮስ መጀመሪያ መታታን/መታትዩ/ ቀጥሎ ይሁዳ ያደረጉትን እንቅስቃሴ አንትያኮስ ሰማ ዳግመኛም ፋርሶችን ይሁዳ እንዳሸነፈ ሰማ ልጁ አፍድር ይባላል አፍድር በመቄዶንያ ተሹሞ ነበረ ከቤተሰቦቹም ልብስታዎስ የተባለው ሰው እንዲረዳው አደረገ የረዳቱ ስም ‹‹ልብስታዎስ›› ይባላል ልብስታዎስ በአንቲያኮስ ታዞ ከዮናናውያን የታወቁትንና ሰፋቦር፣ ትልምበስና ሄሮድ በመባል የሚታወቁትን መሪዎች አድርጎ አይሁዶችን ከስርመሰረታቸው ነቅለው እንዲያጠፋዋቸው በማዘዝ ላካቸው።



www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር ልመናቸውን ሰምቶ ፍላጎታቸውን ፈጸመላቸው ድንጋይ ላይ እሳት ታየ እንጨቱንና መሥዋእቱንም አቃጠለው።

ይህ እሳት ከመሰዊያው ሳይጠፋ ለብዙ አመታት ኖረ ቤተ-መቅደስም እንደገና አስክትጠፋ ድረስ ሳይቋረጥና ሳይጠፋ እየነደደ ይታይ ነበረ ህዝቦቹም ቤተ-መሰዊያውንም አንዲሰራ ለተከታታይ ሳምንት ቀናት በዓሉን አከበሩ እቺ በዓል በዓለ ህንክ በመባል ትታወቃለች የመጀመርያዋ የበዓል እለት ‹‹ከሰሉ›› በተባለው ወር በሃያ አመስት ቀን የምትከበር ነበረች።

በእነዚህ ስምንት ቀናት ለጸሎት ለምህላ አግዚአብሔርን ለማክበር ህዝበ እስራኤል ባለሟቋረጥ ተሰበሰቡ በአንቲያኮስ ያሳየውንም ሃይል አስታወሱ እነዚህ ስመንት ቀናት በየ ዓመቱ ለእግዚአብሔር ምስጋና የሚቀርብባቸው አንዲሆኑ ወሰኑ በዓሉ ቋሚ ሆኖ ለብዙ ዘመናት ኖሯል።

## ምዕራፍ ፰

## የልዮስ ወልደ አፍርድ ታሪክ

ይህ ልዮስ የአንትያኮስ የልጅ ልጅ የአፍድር ልጅ ነው የአፍድር የጦር መሪ ሆኗል አፍድር /የአንትያኮስ ልጅ የይሁዳ አድራጎት ሰምቶ ሴሊዮስ የተባለው የወንድሙ ልጅ አይሁድን እንዲያጠፉ ላከው ከአይሁድ አገሮች አንዷ የሆነችውን አገር መግቢያ መውጫ በማሳጣት ከበባት አገርዋ ‹‹ቢብ›› ትባላለች የዚችን ከተማ ነዋሪዎች አይሁድ ሲቀላቀሉ ባለመቻላቸው እጅግተቸገሩ በረሀብም ተሰቃዩ።

ይሁዳ ሁኔታውን ሰምቶ ወገኖቹ አይሁድ አንዲጸልዩና እግዚአብሔርን እንዲለምኑ የአሸናፊነትንም ኃይል እግዚአብሔር እንዲሰጣቸው ይማልዱት ዘንድ አዘዛቸው ከፆምና ከጸሎት በኋላም ሰራዊተ አይሁድን አስከትሎ ዮናናውያንን ለመውጋት ሄደ አይሁዶች የዮናናውያን ብዛት ሲመለከቱ ፈሩ



ይሁዳ በዚህ ጊዜ በእሳት ፈረስ ላይ የተቀመጠና ልብሱ እንደ መብረቅ የሚያንጸባርቅ ሆኖ አየው ሰውየው በእጁ ጦርን ይዟል።

ይህ መልአክ ወደ ዮናናውያን አቅጣጫ ያመለክት ነበር ሲመታቸውም ሲዘጋጅ አየው ይህ መልአክ ዮናናውያንን ለማጥፋት የመጣ መሆኑንና እግዚአብሔር ዘንድ የተላከ መሆኑን አወቀ በዚሁም ልቦናው ተጥናና በሙሉ እምነትም በሌሊት ተነስቶ በይሁዳ መሪነት ዮናናውያንን ገጠማቸው ከያሉበት እንደ ቅጠል ረፈረፏቸው ብዙዎቹ ዮናናውያን ተገደሉ።

በዮናናውያን ላይ እግዚአብሔር ፍርሃትንና ድንጋጤን አሳደረ ከሞት የተረፉት ሁሉ የትም በረሩ። መሪያቸውም ሲሲዮስ ይሁዳን መማፀን ጀመረ ከይሁዳ ጋርም ሰላምን ለመመስረት ፈለገ ዮናናውያን እስከ መጨረሻው አይሁድን በጠላትነት እንዳይመለከቱ ሃይማኖታቸውንም እንደሚያከብሩና እንደሚጠብቁ እንደሚያደርግ ለይሁዳ ገለጸለት። ይሁዳም አንተን እኛን እንድትዋጋ የላከህን የአንቲያኮስን ለጅ አፍድር በዚህ ከተስማማ እኔም ለሠላም እገዛለሁ ሲል መለሰለት።

ሲሳዮስ ስምምነቱን አንዲደግፍ ወደ አፍድር ደብዳቤ ጻፈ በደብዳቤው ውስጥ የአይሁድ ጽናትና ጥንካሬ ገለፀ በጦርነቱም የዮናናውያን ወታሮች እንደተፈጁም ጨምሮ ፃፈ አፍድር ደብዳቤውን ሲመለከት እጅግ ተደሰተ የጀመረውን የሰላም ጎደናም በይበልጥ እንዲቀጥልበትና ህጋቸውንም ሆነ ሃይማኖታቸውን አንደሚያከብርላቸው በወራሪነትም የሚነሳባቸው እንደሌለ ቃል እንዲገባላቸው አብልጦ ሲያበረታታው የመልስ ደብዳቤ ጻፈለት።

በሌላ በኩል ይህ የአንቲያኮስ ልጅ አፍድር ወደ አይሁድና ወደ ሲቃነ ካህናት በመልእክተኛው ሊሳስ በኩል ከነሱ ጋር የሰላም መድረክ መመሥረቱን ዘርዝሮ ገለጸለት በሁለቱም ወገኖች ሰላም ተመሰረተና አይሁዶች በሰላምና በጤና መኖር ጀመሩ ሕዝበ አይሁድ



www.ethiopianorthodox.org

የቅርጣና ህዝቦች ወደአቢባን መልእክት ልከው በችግር ላይ ወድቀን ተከበናል የከተማችን መጥፋትና የኛ እልቂት ይጠብቀናል። እኛ ሣቅያንና ሠራዊቱን ለመውጋት አንችልም የቀረን በሩን ከፍተን ከተማዋን ለጠላት ማስረከብ ብቻ ነው አሉት።

አቢባል መልእክቱን ሲሰማ ከሮማውያን በምርኮ የያዛቸውን ሰዎች ሰብስቦ ገደላቸውና ከሮም ተመልሶ በመርከብ በመሳፈር ወደ አፍራቅያ አገሩ ተመለሰ ሳቅያንም አገኘውና ለጦር አመቺ የሆነውን ቦታ ሁሉ ተቆጣጥሮ ስለያዘ አቢባልን ጦርነት ገጠመው አቢባልም ተሸንፎ ወደ ግብፅ ሸሸ ሳቅያግን ተከታትሎ ያዘው ወደ አፍራቅያም ይዞት ተመለሰ በአፍራቅያም አቢባልን ገደለውና አፍራቅያን ግዛቱ አደረጋት።

የሮማውያን መንግት ገናናነት የጀመረው ከዚሁ ጀምሮነው የሮም መንግስት ከአለም ሁሉ የበላይነትንም ያዘ በዘመኑ ሮማውያንን የሚስተካከል ማንም አልነበረም።

## ምዕራፍ ፲

## ሮማውያን ወደ መታትዩ ልጅ ይሁዳ የፃፉት መፅሐፍ ታሪክ

ሮማውያንን ከ፴ሺ የበታች ሹማንምት ጋር በመሆን ያስተዳድር የነበረው ሽማግሌ እስራኤልን ይመራ ከነበረው የመታትዩ ልጅ ይሁዳ ዘንድ መፅሐፍን ልኳል መፅሐፉ የሚከተለውን መልእክት ይዟል ‹‹ይሁዳ ሆይ ሰላምታ ላንተ ይሁን እናንተ ሕዝበ እስራኤል አሸናፊዎችን መሆናችሁንም ሰምተናል በዚሁም ተደስተናል ስለዚህ ከኛ ከሮማውያን ጋር ወዳጅነትን እንድትመሰርቱ ፍላጎታችን ነው›፡



ከፅርዑ ንጉስ አንትያኮስ ጋር ወዳችነትን እንደመሠረታችሁ ሰምተናል ከሱ እኛ እንሻላችሁአለን እነዚህ ፅርዐውያን በናንተላይ ግፍ ፈፅመዋል አንትያኮስ ራሱ በናንተ ላይ የፈፀመው ግፍ ብዙ ነው ወግቷቹኋል ግፍ ፈፅሞባቹኋል እኛ መነሻችንን አንፆኪያ አድርገን ፅርዓውያንን ለመውጋት ተዘጋጅተናል አኛ አሁን የናንተን ማንነት ለማወቅ እንፈልጋለን ከኛ ጋር ከተሰለፋችሁ ተሰለፉ ከፅርዓውያን ጋር ነው የምንሆነው የምትሉ ከሆነ ደግሞ አስታውቁ።

ይህ ከዚህ በላይ የተዘረዘረው መልእክት ከሮም አረጋዊ መሪና ከ፴ውሺ የበታች ሹማሙምንቶቹ‹‹የጦርነት መሪ ለሆንከው ይሁዳና ለሁላቸው አይሁድ እኛ ሮማውያን ከኛጋር ተሰልፋእሁ እንድትወዳጁ ፈለግን በኛላይ የየብስም ይሁን የባህር ጦርነት ቢነሳ እንድትረዱን እንፈልጋለን እኛም በናንተላይ ጠላት ቢነሳ ከናንተጋር ተሰልፈን እንወጋዋለን እኛን የሚወጋ ጠላት ሲነሳ ይሁዳ ከነሠራዊቱ ጋር ከኛ ጋር ይሰለፋል በአይሁድ ላይ ጠላት ቢነሳም ሮማውያን ከናንተጋር ተሰልፈን አንወጋዋለን አኛ ሮማውያን በጻፍነው የመልእክት መፅሐፍ የመልእክት መልስ ከናተ ዘንድ እንሻለን እኔ የሮም መሪ አረጋዊና 30የበታች ሹማምት ይህንፃፍን››።

## ምዕራፍ ፲፩

## የአንትያኮስ ልጅ አፍዳር ውሉን የሻረበት ዜና

አፍድር ያንቲያኮስ ልጅ የአይሁድን ኃያልነት ሲሰማ የይሁዳን ከሮማውያን ጋር መወዳጀት ሲሰማ በጣም ተበሳጨ እጅግም ከፋው አስቀድሞ ከይሁዳ ጋርም ወዳጅነት መስርቶ ነበርና ወዳጅነቱን አፈረሰ



www.ethiopianorthodox.org

ያባቱን ወንድም ልሳአለን ከብዙ ሰራዊት ጋር አይሁድን እንዲወጋ ላከው በፅርዓዊው በልሳል መሪነት ቤተ እግዚአብሔርን ከበብዋት::

ይሁዳ የጽርዓውያን በወራሪነት መምጣትን ሰማ ወገኖቹንም ሰበሰበ የአይሁድ ሽማግሌዎችንም ሰብስቦ ወደጸምና ፀሎት ገባ ለእግዚአብሔርም መባ አስገቡ ከፆሙና ከጸለዩ በኋላ ዮናናውያንን ለመውጋት ተነሱ እግዚአብሔር ስለ ረዳቸው ከዮናናውያን ብዙ ገደሉ የቀሩት ዮናናውያን ሸሹ የወገኖቹ ድል መመታትና መደምሰስ አፍድር ሰማ ነገር ግን ነገሩን አላመነም በሌላ በኩል ሮማዊ ዱስማስ ወልደ ሰልፓፎስ መቄዶንያን ለመውረር የተነሳበት ጊዜ ስለ ነበር በጣም ተጨነቀ::

ይሁዳ ከአፍድር ጋር ሰላምን ለመመስረት ወደደ የአፍድር የአባቱ የወንድም ልጅ ልስአስን አፍድርና ይሁዳ ተገናኝተው በመካከላቸው ሰላምን መሰረቱ ዕርአውያን ይሁዳን እስከ መጨረሻው በጦርነት እንደማይፈልጉ ቃል ኪዳን ገቡ አፍድር ለቤተ መቅደስ ብዙ ገንዘብ ሰጠ እየሩሳሌምን ጎብኝቶ ወደ ሜቄዶንያ ተመለሰ ይሁዳ ደግሞ ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ ከእግዚአብሔር ለተደረገለት መህረትና ከጦርነትም ስለ ዳነ ለእግዚአብሔር ምስጋናን አቀረበ ለህዝብም መልካም አደረገ::

የመጽሃፉ ደራሲ እንደሚተርከው ‹‹ከአይሁድ ወገኖች ሆነው ለአንቲያኮስ በነገረ ሰሪነት ቀራቢዎች በመሆን ህዝበ አይሁድን ካስፈጁ ሦስት መጥፎ ሰዎች አንዱ የሆነው ቢላኦስ ነው እንደገና ወደ አፍድር /ያንቲያኮስ ልጅ/ ሄዶ አይሁድን እንዲያጠፋ ስለ መከረው ነው አፍድር ቀደም ብለው በሁለቱ በአይሁድና በአፍድር የተመሰረተውን ቃል ኪዳን እንዲፈርስ ያደረገው:: በኋላ ግን ቃል ኪዳኑን በማፍረሱ አፍድር እጅግ ተፀፀተ::



ያ ክፉ ከሦስት የአይሁድ ወገኖች ሆነው በነገረ ሰሪነት ወገኖቻቸውን አይሁድ ለማጥፋት ከሚዳርጉ አንዱ ቢላሶን የአፍድር መፀፀትን ሲሰማ እጅግ ደነገጠ አፍድር ለስህተት የዳረገውን ቢላሶን እጅና እግሩን አሰረው ወደ ከፍታማም ቦታም አስወጣው ከዚያውም ወደ ምድር ወረወረውና ሞተ እኩይ ሞትን ሞተ እግዚአብሔር ለውርደትና ለመከራ ዳረገው::

## ምዕራፍ ፲፪

## የለልያፓስ ሮማዊ ልጅ መትርያስ መውጣት ዜና

አፍድር ከመታታዩ ልጅ ይሁዳ ጋር ሰላምን መስርቶ ወደ ሜቄዶንያ ሲመለስ የአፍርፖስ ሮማዊ ልጅ ማትሪያስ መጣበት /ከሮምያ ተነስቶ/ አመጣው ብዙ ሰራዊትን በማስከተል አፍድርን ለመውጋት ነው:: አፍድር ማትርያስን ሊቋቋመው ስላልቻለ ተሸንፎ ሸሸ የአፍድር የአባት ወንድም ልስአስ ግን ማትያስን ተዋጋው አሸንፎም ገደለው ከዚያ ወደ አንጾኪያ ሄዶ ተቀመጠ ከአይሁድ ካህናት ሶስት ነገረ ሰሪዎች ከአንቲያኮስ ጀምረው የተነሱት መኖራቸው ተደጋግሞ ተገልጿል ከነዚህ ክፉዎች ካህናት አንዱ በአፍድር ተገድሏል ሁለተኛው ካህን ድምትርያኖስን አገኘውና እያለቀሰ ‹‹ይሁዳንና መሰሎቹ ከኛ ከአይሁዳውያን መካከል በግፍ ገድለዋል ከቤት ንብረታችንም አስወጥተውናል ይህን ያደረጉት ሃይማኖታቸውን ስለተውን ነው የናንተን ሃይማኖት በመከተላችን ሊያጠፉን ተነስትዋል

አሁን ንጉስ ሆይ እኛን እንድትረዳንና በሰላም እንድንኖር እንድታደርግልን›› እያለ ነገር ሰራባቸው ብዙ ነገርንም ተናግሮ ድምትርያኖስ ለበቀል እንዲነሳና እንዲወጋቸው የሚገፋፋ ሁኔታ በዙ የማስመሰል ተንኮለን ተናገረ:: ድምትርያኖስ የበታች ባለስልጣኑን ቢፋቦርን ይሁዳን እንዲይዘው ወደ ቤተ መቅደስ ላከው:: ወደ ቤተ መቅደስ ሳይጠጋ ከሩቅ ሆኖ ቢፋቦር

www.ethiopianorthodox.org

ምስጢሩን ሳይገልጥ ለሠላም የመጣ በመምሰል ይሁዳ መጥቶ እንዲገናኘው ላከበት ይሁዳ ቢፋቦርን በክብር ለመቀበል ብዙ ሰራዊትን አስከትሎ ወጣ የክብርና የደስታንም አቀባበል እንዲያደርግለት ተዘጋጀ።

ቢፋቦር በዚህ ጊዜ በይሁዳ ላይ የመያዝም ሆነ የበላይነት ሳያሳይ ቀረ ነገሩ ግራ የሚያጋባ ሆኖበታልና በተቃራኒው መንገድ ሁለቱ ይሁዳና ቢፋበር ተገናኝተው ሃሳብ ለሃሳብ ተለዋወጡ ቢባፎር ከይሁዳ ጋር ወደ ቤተ-መቅደስ ገባ በይሁዳና በቢባፎር መካከል ፍቅር እጅግ ፀና።

ያ መስተዋድይ ካህን ስሙ አልቂሞስ ይባላል አልቂሞስ የሁለቱን በፍቅርና በሰላም መጠመድ ሲሰማ መስተዋድይነቱ ከንቱ እንደሆነ ተረዳ ወደ አንፆኪያም ተመልሶ ንጉስ ድምትርያኖስን አገኘው መስተዋድይነቱንም በበለጠ ቀጠለበት አይሁድን ለማጥፋት ሆን ብሎ በምቀኝነት ተነሳ ቢባፎር ላንተ የማይታዘዝ ነው ከዳሀል በመሆኑም ይሁዳን ሲይዘውና ወደ አንተ አምጥቶ ለፍርድ እንዲቀርብ ማድረጉን ፈፅሞ ትቷል›› በማለት የረከሰውን አላማው ለማስፈፀም ጀመረ ።

ደምትርያኖስ የመስተዋድይ አልቂሞስ ነገርን ሰምቶ በሄደበት ይሁዳን ይዞ ወዳለበት አንጾኪያ አስሮ እንዲያመጣው ካላመጣው ግን ግርፋት እንደሚጠብቀው ላከበት መልእክቱ ከቢባፎር ዘንድ ከመድረሱ አስቀድሞ ወደ ይሁዳ ደረሰ ይህንም ተቃዋሚዎች ባካባቢው የተነሱበት አስመስሎ ከነሱ ጋር ጦርነትን ልገጥም ነው በሚል ምክንያት ካገር ወጣ ሰባስጥያ ከተባለችውም ሃገር ተቀመጠ ቢባፎር ግን ይህንን ሁሉ አላወቀም ነበር የድምትሪያኖስ ደብዳቤ ሲደርሰው ግን ይሁዳን ይይዘው ዘንድ ፈለገው ሆኖም አላገኘውም የሄደበትንም ቦታ አላወቀውም ነበርና በቤተ-መቅደስ ውስጥ የተደበቀ መሰለው ካህናቱንም ይሁዳ ከኔ ዘንድ አምጡልኝ አላቸው።ካህናቱ ከኛ ዘንድ ይሁዳ የለም ያለበትንም ቦታ አናውቅም



አሉት።በዚህ ጊዜ ቢባፎር እጅግ ተቆጣ እጅግ ብሥጭትና ንዴትንም የተቀላቀለበት ተግሳጽ በካህናቱ ላይ አዘነበ ቤተ-እግዚአብሄር ላይና በነሱ ላይም ምራቁን ተፋባቸው በቤተ-መቅስ ክልል ውስጥ ብዙ የተለያየ አገልግሎት የሚካሄድባቸው ቤቶች ነበሩ እነዚህ ቤቶች በወታደሮቹ እንዲበረበሩ አደረገ በዚህ ጊዜ በአይሁድ ዘንድ ብዙ ሀዘንና መከራ ደረሰ ይሁዳ ካለበት ሀገረ ሰበስጥያ ሁኖ በወገኖቹ አይሁድ እየደረሰ ያለውን መከራ ሰማና ‹‹እኔን ለማግኘት በወገኖቼ ላይ ግፍ አትፈጽም እኔ በቤተ-መቅደስ ዙሪያ የለሁም ከራቀ ቦታ ላይ ነው ያለሁት ከፈለክ ከዚያ ውጣና ከዚያ ውጪ ከሆነ ቦታ እንገናኝ›› ሲል ላከበት።

ቢባፎር ይሁዳን ለመገናኘት ሰራዊቱን አስከትሎ ወጣ ከክህደቱም የተነሳ በእግዚአብሔር ማህሪና ሁሉን ቻይ ላይም ስድቡን ያወርደው ነበር የእግዚአብሔርን ሃይማኖትና ቤተ-መቅድስንም ይሰድብ ነበር ህዝበ እስራኤልንም ያቃልላቸውና ይሰድባቸው ነበረ ይሁዳም የሱን ስድብ ሰምቶ ልቦናው በፍቅረ እግዚአብሔር ተቃጠለ ወደ እግዚአብሔርም ተማሕኖው እያቀረበ እግዚአብሓርን ጠራ እንዲህም አለ ‹‹አቤቱ አንተ የሰናክሬምን ሰራዊት ደምስሰሃል የሱ ሰራዊት ብዙ ነበር የሰናክሬም ሠራዊት ወደ ቤተመቅደስ እንደማይገባም በነቢያት አስቀድመህ ተናግረሃል አሁንም ይህንን ከሐዲ ጠላት ትደመስሰው ዘንድ እለምንሃለሁ አንተና መቅደስህንም ሰድቧልና ሃይማኖትህንም ለውጧልና በሱ ላይ መዓትህን አፍጥን መቅሰፍትህንም ፈጥነህ አውርድለት›› በማለት ጸለየ።

ከዚያ ይሁዳና ቢባፎር ተገናኙ ጦርነትንም ገጥሞ ገደለው ከሠራዊቱም አብዛኞቹ ተገደሉ ከሞት የተረፉት ሸሹ አይሁዶቹም ካያሉበት ወጥተው ከየደረሱበት የቢባፎርን ወታደሮች ገደሉዋቸው ይሁዳና ተከታዮቹም በታላቅ ደስታ ወደ ቤተመቅደስ ተመለሱ ስላደረገላቸውም



www.ethiopianorthodox.org

ምህረት አግዚአብሔርን አመስገኑት እቺ ዕለት የደስታና የነፃነት ቀን ሁና በየዓመቱም እንድትከበርም ይሁዳ ወሰነ።

ቀኗን እያስታወሱ ሕዝበአይሁዳ በየዓመቱ በቤተ መቅደስ በመገኘት እዚአብሔርን ሲያመሰግኑት ኖሩ ይህ ዕለት ሕዳር አስራ ሦሥት ቀን ነበር የሚውለው። ይሁዳ የቢባሮርን ራስ ካስቀመጠበት መካነምሥዋዕ እንዲያመጡት አዘዘ። እግዚአብሔርንና ቤተ መቅደስን በሰደበበት ቦታ ላይም ሰቀለው ይህም ቦታ ከቤተ መቅደስ አቅጣጫ ስለሚገኝየቢባሮር በር ብሎ ሰየመው።

## ምዕራፍ ፲፫

## የይሁዳ መገደል ታሪክ

ቢባሮር ተገድሎ ይሁዳ ወደ ቤተ መቅደስ የተመለሰበት ዕለት ለሁለተኛ ጊዜ በመረከብላይ እያለ ኒፊሮስ የሚባል ከሮም ታላላቅ ባለስልጣኖች አንዱ የሆነው ከብዙ ሠራዊት ጋር መጣ የሠራዊቱ ብዛት ሦስት እልፍ ያህላል አመጣጡ ይሁዳን ለመውጋት ነው። ይሁዳ በዚህ ጊዜ ከሦስት ሺ ሠራዊት ጋር ‹‹ለልሣን›› በምትባል አገር ይገኝ ነበር ሦስቱ ሺ የይሁዳ ወታደሮች ፈረሰኞች ነበሩ ስለዚህ የሮማዊው ኒፊሮስን መምጣት ሲሰሙ በፈረሳቸው እየጋለቡ ሸሹ ከይሁዳ ጋር የቀሩት ሦስት መቶ ሰዎች ብቻ ነበሩ። ስምዖንና ዮሐዮንስ የተባሉት ወንድሞቹም አብረውት ነበር እነዚ የይሁዳ ወንድሞች ነፊሮስን ለመውጋት ተነሱ ሮማዊው ነፊሮስ ግን በሁለት አቅጣጫ ጦርነት ገጠማቸው በሱ ከሚመሩ ሰራዊቶቹ ጋር ነፊሮስ እነይሁዳን ገጠማቸው ጦርነት የተከፈተበት ቦታ አዝዲድ ይባላል ሁለተኛው የነፊሮስ ሰራዊት በባለስልጣኖቹ እየተመራ በሌላ አቅጣጫ መኖሩን አላወቀም ነበር ይህ ሠራዊት የመሸገበት ቦታ ዴፖ ይባላል በዚህ ጊዜ



ከወድያና ወዲህ ይሁዳ ተከበበ ብዙ ጦርነትም ተካሄደ ይሁዳ በዚሁ ጦርነት ሞተ ወንድሞቹ ስምዖንና ዮሐንስም ከማታንን /ማታትዩ/ መቃብር ጎድን ቀበሩት ከወገኖቹ እስራኤላውያን ጋር በመሆንም ብዙ ቀን አለቀሱለት የይሁዳ ዘመነ መንግስት ሰባት አመት ነው ከሱ በመቀጠልም ውንድሙ ዮናታን ነገሰ።

## ምዕራፍ ፲፬

## የማታንን /ማታትዩ/ ልጅ ዮናታን ዜና

የይሁዳና የዮናታን አባት ማታንን /ማታትዩ/ ነገድ ከከስምናይ ነገድ ነው ይሁዳ በጦርሜዳ ሲገደል ዮናታን ወደ ዮርዳኖስ ሄደ ሮማዊው ነፊሮስ ሲከታተለው ዮርዳኖስን ተሻግሮ ወደ ሌላ ቦታ ሄደ ሻብዕ ወደ ተባለው ጫካ ውስጥም ገባ ሠራዊቶቹም በዚሁ ተጠጋጉ የነፊሮስ ወታደሮች የዮናታንን ወታደሮች እጅግ አስጨነቁ።

ተከበው መንቀሻቀሻ ከማጣታቸው የተነሳ በለሊት ወጥተው መልሰው የነፊሮስን ወታደሮች ከበቡዋቸው እግዚአብሔርም በነፊሮስ ወታደሮች ላይ ፍርሃትን አሳደረ ከዮናታን ወታደሮችምለማምለጥ ሸሹ ነፊሮስም አብሮ ሸሸ ዮናታንም ተከታትሎ ያዘው ሊገድለውም ወደደ ነፊሮስ ግን እንዳይገድለው ተማፀነው ደግሞም እስከመጨረሻው ድረስ እንዳይጣላው ማለለት።

የተማረኩት የሱ ሰራዊትንም እንዲለቅለትና ነፃ እንዲያወጣቸው ለመነው እሱም እንዳለው አደረገ እሱንም ሆነ ወታደሮቹን በነፃ አሰናበታቸው ነፌሮስ ከወታደሮቹ ጋር እንደገና ወደ ሮም ተመለሰ ዮናታን ደግሞ ብዙ ሳይቄይ በህመም ሞተ ከሱ ቀጥሎም ወንድሙ ስምዖን ተሾመ።



www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፲፭

## ዜና ስምዖን ወልደ ማታትዩ

ስምዖን ወልደመታትዩ ከክስምናይ መሳፍንት ልጆች አራተኛው ነው፡፡ የመታትዩ ልጅ ስምዖን በተሾመ ጊዜ የይሁዳ ሰራዊት ሁሉ ተሰብስቦ ይሁዳ ከሞተ በኋላ ለይሁዳ መንግሥት እንታዘዘም በማለት አፈንግጠው የቆዩት ሁሉ እንዲታዘዙ አድርጓል ለወገኖቹ አይሁድ ፍትህ የሰፈነበት አስተዳደር እንዲኖራቸው አድርጓል፡፡

መቀመጫው በአንፆኪያ ያደረገው የሶፍሊያፎስ ልጅ ደምትሪያስ ስምዖንን ለመውጋት ሰራዊት ላከበት ስምዖን ሰራዊቱን በሁለት አቅጣጫ እንዲመሽጉ አደረገ ሁለተኛው ክፍል በልጁ የሚመራ ሆኖ ሁለተኛው ምድብ በሱ የሚመራ ነበር ስምዖን የድምትሪያስን ወታደሮች አሸነፋቸው ጦርነቱ ሲፋፋም በሌላ በኩል በልጁ መሪነት የተሰለፈው ሰራዊት የድምትርያኖስ ሠራዊት ወጋው ድምትርያኖስ ተሸንፎ ሸሸ ሠራዊቱም አብዛኛው በጦርነቱ አለቀ ድምትርያኖስ አይሁድን ለመውጋት ዳግም አልተመለሰም በስምዖን ዘመን አይሁድ ሰላም አገኙ ስምዖን በሰላም አይሁድን ለስምንት ዓመት መራቸው፡፡

‹‹ብልማይ›› የተባለውን አማቹ በማዕድ ጊዜ ድንገት ተነስቶ ስምዖንን ሚስቱንና ሴት ልጁን ገደላቸው ከስምዖን ቀጥሎ ልጁ ሕርቃኖስ ተሾመ ዮሐንስ የሚል ድርብ ስምም ነበረው ይህ ዮሐንስ አባቱ በሹመት ላይ እያለ ሃይለኛ የነበረውን ሕርቃኖስ የተባውን ሰው ስለገደለ ነው አባቱ ስምዖን በተገደለው ሰው ሕርቀኖስ ብሎ የሰየመው በዚህ ስም ይጠራ የነበረው ሕርቃኖስ እጅግን ሃይለኛ ስለነበረ ነው፡፡



## ምዕራፍ ፲፮

## ዜና ሕርቃኖስ ወልደ ስምዖን

ሕርቃኖስ ከክስምናይ መሳፍንት ልጆች አምስተኛ መስፍን ነው ብልማይ የፈፀመውን በደል ሕርቃኖስ አወቀ የብልማይ እና እህቱን ያዘቻው ብልማይ ግን አስቀድሞ ሸሸ ወደጋዛም ሸሽቶ ሄደ ሕርቃኖስ ግን ሊገድለው ተከተለው ሆኖም የገዛ ነዋሪዎቹ ተከላከሉለት እንዳይገለውም ከለከሉት ብልማይ እንደገና ከጋዛ ዳኩን በተባለው ቦታ ተቀመጠ፡፡

ሕርቃኖስ ተመልሶ ወደ ቤተ መቅደስ ገባ ያባቱን ሹመት ያዘ ያባቱም ሠራዊት አደራጅቶ ወደ ብልማይ ዘመተ ብልማይ የስምዖንን ሴት ልጅ ያገባ ነበር፡፡ ሕርቃኖስ ብልማይ ያለበትን ቅፅር ሠብሮ በመግባት ብልማይን ሊይዘው ሞከረ ብልማይ ከመፍራት የተነሳ የሕርቃኖስን እናትና ወንድሞችን በቅፅሩ ላይ አስቀመጣቸው፡፡

የሕርቃኖስ እናት በዚህ ጊዜ ይህን የአባትህን ገዳይ ልትምረው አይገባም አለችው ሊገድለውም በመዘጋጀት ላይ እያለ በዓለ መፀለት ደረሰ ሕርቃኖስም በዓሉን ለማክበር ወደ ቤተ መቅደስ ሄደ ብልማይ አመቺ ጊዜ ስላገኘ የሕርቃኖስን እናትና ወንድሞቹን ገድሎ ወደ ሌላ አገር ሸሽቶ ሄደ፡፡

በዚህ ጊዜ ምትርያስ የአልፓፎስ ልጅ ወታደሮቹን ስለገደለበት ስምዖንን ሊበቀለው ተነሳ የስምዖንን መገደል ሲሰማ ባለበት ወደ ቤተ መቅደስ ሄደ፡፡ አይሁድንም ሊወጋ ተነሳ ምትርያስ የሮምን ስልጣን ከያዘ በዚሁ ጊዜ አራት አመት ሆኖት ነበር ሕርቃኖስ ደግሞ ገና አንድ ዓመቱ ነበር ሕርቃኖስ ምትርያስን ባክህ በዓለ መፀለትን በማበር ላይ ስለሆንኩ ጦርነትን ከመቀስቀስ ተጠብቀህ ጠብቀን ለእግዚአብሔር ምስጋና በማቅረብ ላይ ነኝና በማለት ለምትርያኖስ ላከበት፡፡

www.ethiopianorthodox.org



www.ethiopianorthodox.org

ምትርያኖስም እሺ አለ እንዲህ አለ ‹‹እኔም የበዓሉን ተካፋይ እሆን ዘንድ ቀንዱ በወርቅ የተለበጠ በሬን ለቤተ እግዚአብሔር ለመስጠት ፈቅጃለሁ›› አስቀድሞ ለቤተ እግዚአብሔር ከወርቅና ከብር የተሰሩትን ግህኖች አእምሮን የሚመስጥ መልካም ሽቶ ከብዙ ገንዘብ ጋር ለቤተ እግዚአብሔር ላከ ካህናቱም የምትሪያስን ሥጦታ ተቀብለው ወደ ቤተ መቅደስ አስገቡት።

ካህናትና ሕርቃኖስ የምትሪያስን ስጦታ ሲመለከቱ ከሱ ጋር ሰላምን ለመመስረት ተስማሙና በሕርቃኖስና በሱ መካከል ሰላም ይሆን ዘንድ ቢጠይቁት ለመታረቅ ፈቃደኛ ሆነ ወደ ቤተ መቅደስ ከተማም ሲገባ ከአይሁድ ሽማግሌዎች በመሆን ሕርቃኖስ አቀባበል አደረገለት ሕርቃኖስ ለምትርያስ ክብር ታላቅ የምሳ ግብዣ አደረገ ሦስት መቶ ወቄት ወርቅም በስጦታ ሰጠው እየተደጋገፉ ለመኖርም በመካላቸው ቃል ኪዳን መሠረቱ።

ታሪክ ጸሐፊዎች ወርቁ ከነገሥታት መቃብር ላይ ይገኝ እንደነበር ይተርካሉ ከዳዊት ጀምሮ ከዚያ ወዲህ በቤተ መቅደስ ቤተ መዛገበት ውስጥ የነገሥታት መቃብር ባንዱ ነው በቤተ መዛገብት እጅግ የበዛ ወርቅ ይገኝ ነበር ሕርቃኖስ በዚሁ ጥቂቱን ለመቀነስ ለምትሪያስ ሰጠ ቀደም ሲል ምትሪያስ አፍርሶት የነበረውን የቤተ መቅደስ ቅፅር ሕርቃኖስ ጠገነው።

ፋርሶች በሮማውያን ሥር ይገዙ ነበር በዚሁ ጊዜ ግን ፋርሶች አሻፈረኝ ብለው አፈነገጡ ለሮማውያንም አንገዛም አሉ ምትሪያስ ፋርሶችን ለመውጋት ሲነሳ ሕርቃኖስም በገባው ቃል ኪዳን መሠረት ሊረዳው ሠራዊቱን አስከትሎ አብሮት ወደ ፋርስ ዘመተ ሁለቱም ፋርሶችን በመውጋት አንበረከክዋቸው ብዙ ወታደርንም ገደሉባቸው።

ምትሪያስ ጦርነት በተካሄደበት ቦታ ሆኖ በሀገረ ፋርስ ማስታወሻ ይሆነው ዘንድ ግንብን ሰራ ምትርያስ የፋርሱን ንጉስ ለመያዝ ወደ ማህል



አገር ገሰገሰ ሕርቃኖስ ሰንበትን ለማክበር ወደኋላ ቀረ ሲንቀሳቀስም አልፈቀደም ምትሪያስ ብቻው ሄዶ የፋርሱን ንጉሥ ጦርነት ገጠመው ምትርያስም በዚህ ጦርነት ሞተ አብዛኛው ሠራዊትም በጦርነቱ አለቀ።

ሕርቃኖስ የምትሪያስን መሞት ሲሰማ ወደ ኋላ ተመለሰ ሻም በተባለው ቦታም አደረ እግረመንገዱንም ሐገረ ሀለብን ኀበኘ ከዚችውም አገር ግብርን ሰበሰበ ወደ ቤተ-መቅደስም ተመለሰ እንደገና ወደ ሳምራውያን አገር ወረደ ናብሎስ ወደ ተባለችው ከተማ ገባ የካህኑ ምናሴ አማች ሳንበለጥ በእስክንድር ፈቃድ የሠራውንም ቤተ-መቅደስ አፈረሰ ሳንበለጥ ሳምራዊ ነው ይህ ቤተ-መቅደስ ከተሰራ በሁለት መቶ አመት ፈረሰ የዚሁ ቤተ-መቅደስ ካህናትንም ገደላቸው።

ከዚያ ተነስቶ ሕርቃኖስ ሀገረ ኤዶም ሄደ ደብረ ሹራ ከተባለው ቦታም ደርሶ ከሕዝቡ ብዙዎቹን ገደለ ሰዎቹ ግን አትጨርሰን እኛ በሰላም ለመኖር እንፈልጋለን አሉት ግብር እንዲገብሩለት ና ህገ ኦሪትንም እንዲጠብቁ አዘዛቸው እነሱም ግብር ገበሩለት ህገ ኦሪትንም ተቀብለው እስከ ቤተ-መቅደስ መፍረስ ድረስ ቆዩ ሕርቃኖስ አይሁዶችን በጠላትነት የሚመለከቱትን ያካባቢ አገሮች ሁሉ አሸነፈ መንግስቱ ከተረጋጋችም በኋላ ወደ ሮም አለቃ ከበታች ሹማምንቱ መርጦ ላከ በሱና በሮሙ አለቃ መካከልንም ከምትሪያስ ጋር የገባውን ቃል ኪዳን እንደገና እንዲያድሱ በመልእክተኞቹ ደብዳቤ ላከ። የሮማውያን አለቃ የሕርቃኖስን መልእክተኖች በታላቅ አክብሮት ተቀበላቸው የሱ የበላይ ሆኖና በህዝብ ተመርጦ ሮምን ከሚያስተዳድረውንም አረጋዊ የሰላም መልስ ተላከለት የመልሱ ደብዳቤም ሙሉ ቃል እንዲህ ይላል።

‹‹ለታላቁ የአይሁድ ንጉሥ ሕርቃኖስና ለሦስት መቶ ያንተ የበታች ሹማምንት ሰላም ላንተ ይሁን ወደኛ የላከው መፅሃፍ ደርሶናል እኛም



www.ethiopianorthodox.org

እንበበነዋል በፍሬ ነገሩ እጅግ ተደስተናል ስለ ዝናህም ካንተ መልእክተኛ ተረድተናል እሱንና የተልእኮ ጓደኞቹን ታላቅ አክብሮት ሰጥተናቸዋል ያንተን ፍቃድ ለመፈፀም በሙሉ ልብ ተነሳስተናል ይህንንም ያንተን መልእክተኞች ለማክበር ስንል ፃፍንልህ።

ያኛውም ያገር ሽማግሌ /አረጋዊ/ እንዳተ ሦስት መቶ ሃያ የበታች ሹማምንት አሉት እነዚህ ሁሉ ወዳንተ ሰላምታ ያቀርባሉ ያስተዳደራችንና ህዝባን ምንነት የሚገልፁ ዝርዝር ታሪክ በመልክተኞቹ አማካኝነት ልከንልሃል

የታሪክ ምሁራን ከሮም የመንግሥት ባለሥልጣኖች በተጻፈው ደብዳቤ ንጉስ ስለተባለ በዚሁ ንጉሥ መባል አለብኝ ብሎ ሕርቃኖስ በንጉሥነት ተጠራ›› ይላሉ ሕርቀኖስ የአይሁድ ንጉሥ ነኝ አለ። ከዚያ በፊት ግን ከብዙ ዘመናት ጀምሮ ካህኑ ነበር በታላቅነት የሚጠራው የአይሁድ ንጉስ ነኝ ማለቱን ሲረዱ አይሁድ ተሰብስበው በመዓረገ መንግስትና በማዕረገ ክህነት ሾሙት።

ቤተ-መቅደስ ደግሞ ከተሰራ አንስቶ ከህርቃኖስ በቀር በቤተ-መቅደስ ሌላ አልተሾመም ህርቃኖስ የክህነቱንና የንጉስነቱን ስያሜ ካገኘ በኋላ በሃገረ ሳምር ውስጥ ወደ ምትገኘውና ሰባስጢያ ተብላ ወደ ምትጠራ ክፍል ሄደ ወደ ማህልም ገብቶ ብሁ ሰዎችን ገደለ ብዙ ጥፋትንም አደረሰባት ከዚያ ጀምሮ ህርቃኖስ እጅግ ገነነ አይሁድም በዘመኑ በሰላምና በፀጥታ ለመኖር ቻሉ።



## ምዕራፍ ፲፯

## የአይሁድ መለያየት ዜና

በዚህ ዘመን አይሁድ ለሦስት ተከፈሉ አንዱ ክፍል ፈሪሳዊ ተባለ የዚህ ትርጉሙ የተጫኑ ማለት ነው ሁለተኛው ክፍል የሰዱቃውያን ክፍል ተባለ እነዚህ ከሳዶቅ ወገኖች ናቸው ሦስተኛው ክፍል የእልግብሰዲሞ ወገን ተባለ የዚሁ ትርጉም ሕፉያን ማለት ነው እነዚህ ሦስተኛውን ክፍል የያዙ ወገኖች ለሃይማኖት የሚያገለግሉ ናቸው ሰዱቃውያን እነሱን ስለሚጠሉ በመካከላቸው ፀብ ስላለ በሶዱቃውያን የተጠሉት ምእትዝላ የተባሉት ናቸው ሕርቃኖስ ከምእትዝላ ወገን ነበር ቆይቶ ግን ወደ ሶዱቃውያን ወገንገባ ምእትዝላዎችንም ጠላቸው ይህ ይታወቅ ዘንድ ሕርቃኖስ ለታላላቅ ሹማምንቱ ታላቅ የምሳ ግብዣ አደረገና በዚሁም ሥልጣን ላይ የነበሩት የምእትዝላ ነገዶች ስለሆኑ አብሮአቸው ሕርቃኖስ የግብዣው ተካፋይ ሆነ ምእትዝላዎች ጠቢባን ነበሩና ሕርቃኖስ ‹‹ከዛሬ ጀምሮ ከእናንተ ደቀ መዛሙርት እንዳንዱ ሆኛለሁ የናንተንም ምክር እቀበላለሁ እንጂ አልሽርም ከኔ ዘንድ ስሕተትን ስትመለከቱም ምከሩኝ ከስሕተትም መልሱኝ እውነትንም ግለፁልኝ ይህን ማድረግ ለናንተ ይገባልና እኔ እናንተን የሚያስቆጣ አላደርግም›› አላቸው።

እነሱም ንጉሥ ሆይ አንተ ደግነህና ከስህተት እግዚአብሔር ያድንህ እግዚአብሔርም ምስጋናን ንጉሥነትንና ክህነትን ሰብስቦ ሰጥቶኃልና አሉት።

ከነሱ ውስጥ አልአዛር የሚባል ሚስጢር አዋቂ ሰው ነበር ሰውየው በጣም ምክር አዋቂ ሰው ነበር ለሕርቅያኖስም ‹‹እነሆ እንድመክርህና ከስህተትህም እንድንጠብቅህ አዘዝሽናል። የእኛን ምክር ለመቀበል ፈቃደኛ ከሆንክ ንጉሥነት ይበቃሃል ክህነት ይቅርብህ ንጉሥ ሆነህ ሲቀ ካህናት



www.ethiopianorthodox.org

ልትሆን አይገባህምና እናትህ በአንቲያኮስ ግዜ የተማረከች ናት አንተን ከመፅነሷ አስቀድሞ ተማርካለች የምርኮኛ ልጅ ሊቀ ካህናት ሊሆን አይችልም ወደ ቅድስተ ቅዱሳንንም አይገባም አለው በዚህ ጊዜ የእልምትዝላ ወገኖች ዝም አሉ ይላል መፅሃፍ የእነሱ አባባል እውነት ነውና።

ሕርቃኖስ በዚሁ ተቆጣ ደስታውም ወደ ሀዘን ተለወጠ በዚሁ ከሰዶቃውያን ወገን የሆነ አንድ ከበርቴ ነበር ስሙ ዮናታን ይባላል ይህ ሰው የምእትዝላ ወገኖች አንተን ከልብ እንደሚወዱህ በዚሁ ተረዳ እኔ እንደማይወዱህ ገልጨልህ ነበር አሁን የእኔ ነገር እውነት ሆነ አንተ ምትእዛሎች ቢወዱህ ኖሮ አልአዛር በድፍረት እንዲናገርህ ባልፈቀዱለትም ነበር›› አለው።

ሕርቃኖስ ነገደ ምእትዝላ በአልአዛር ላይ የሚገባውን ነገር በመናገሩ እንዲፈርዱበት አዘዛቸው። ሕርቃኖስ ምእትዝላዎች በአልአዛር ላይ የሞት ፍርድን እንዲፈርዱበት ፈልጎ ነበር። እነርሱ ግን አርባ ጅራፍ እንዲገርፉት ብቻ ፈረዱ። በዚህ ምክንያ ሕርቃኖስ ወደ ሰዱቃውያን ሃይማኖት ገባ በምእተዝላዎች ላይ ከባድ ጥላቻ አደረበት የነሱን ትምህርት እንዳይቀበለም ማንም ሰው በአዋጅ ተከለከለ ትእዛዙን ያልተቀበሉትንም አብዛኞቹን ገደላቸው። አብዛኞቹ አይሁዶች የምእትዝላ መንገድ የሚከተሉ ነበሩ ስለዚህ በአይሁዶች ላይ መከራ ፀና።

ከዚህ በፊት አይሁድ ሕርቃኖስን ይወዱት ነበር። የከስምና ነገዶች የሱን ነገዶች ናቸው። እነዚህ ነገዶች በአይሁድ ዘንድ የተወደዱ ስለነበሩና ሕርቃኖስም የነሱ ነገድ በመሆኑ አይሁድ ይወዱት ነበር ከምእትዝላ ቡድን አባልነቱን ወደ ሰዱቃውያ ቡድን ከገባ ጀምሮ ሕርቃኖስ የምእትዝላ ቡድን ከሆኑ አይሁዶች አብዛኞቹን ገደላቸው በሃይማኖት የተለያዩት አይሁዶች



እርስበርሳቸው እንዲጣሉ ሆን ብሎ ራሱ የጠብ መሪ ሆነ በየጊዜው በአይሁዶች ዘንድ የ ርስበርስ መተላለቅ ሰፈነ።

አይሁድ ሕርቃኖስን እጅግ ጠሉት መላቤተሰቡም ተጠላ አንጢጎስ አስተሮቦሎስና እስክንድር የተባሉ ልጆች ነበሩት ሕርቃኖስ አንጢጎስን ይወደው ነበር። እስክንድርን ግን ይጠላው ነበር እስክንድር ከእርሱ እርቆ በደብረ ገሊላ እንዲኖር አደረገ የሚወደውንም የሱን ሥልጣን እንዲወርስለት እግዚአብሔርን ለመነ ነገር ግን ከሱ በኋላ እስክንድር እንደሚነግሥ በሕልሙ ምልክትን አየ ሐዘን ተሰማው ሕልሙን ግን ለማንም አልነገረም እግዚአብሔር የወደደውን ያድርግ ብሎ በትእግስት ጊዜውን ጠበቀ አርባራት ዓመት በሥልጣን ላይ ቈይቶ ሞተ ከሱ ቀጥሎ ግን አስተሮቦሉስ ልጁ ሥልጣኑን ተረከበ።

## ምዕራፍ ፲፰

## ዜና አርስተቦሎስ

አርስተቦሎስ ከክስምናይ ነገዶች መኳንንት ስድስተኛ ነው በስም ደግሞ ከነዚህ መኳንንት ንጉሥ ተብሎ መሰየም ሁለተኛ ነው አርስተቦሎስ በነገሠ ጊዜ ትዕቢት ተሰማው ከኔ በላይ ማንም የለም ብሎ በመታበይም ትልቅ የራስ ወርቅ በራሱ ላይ አደረገ የካህናትን የራስ ወርቅን ግን እጅግ አቃለለው ወንድሙን እስክንድር አሰረው እናቱንም እስክንድርን ስለ ምትወድ አሰራት ወንድሙንና የመጀመሪያውን ልጅ የሆነውን አንጢጎስን ደግሞ የጦር መሪ አድርጎ ሾመው።

አርስቶቦሎስ ለሱ አንገዛም ያሉትን አሕዛብ እንዲወጋ ወንድሙን አንጢጎስን ላከው አንጢጎስም ብዙዎችን አስገብሮ ተመለሰ ወደ ሀገረ ቈጅሽም መጣ አርስቶብሎስ ንጉሥ እጅግ ታሞ ጠበቀው መታመሙንም

www.ethiopianorthodox.org

ሲሰማ ወደሱ ከመሄድ ይልቅ ወደ ቤተ መቅደስ ሄደ በአሸናፊነት እንዲፈፅም ላደረገው ልዑልና ክቡር እግዚአብሔር ምስጋና አቀረበ ባለበትም ለወንድሙ ፊውሰ ስጋ ከእግዚአብሐር ለመነ፡፡

ጊዜው እንደ አጋጣሚ ሆኖ በዓለመፀለት ሆኖ አይሁድ ወደ ቤተ መቅደስ ተሰበሰቡ አንጢጎስ የወርቅ ቀበቶን በወገቡ ላይ ታጥቆ ነበር በቤተ መቅደስ ከወዲያ ወዲህ እየተንቀሳቀሰ ከተሸለመው የመኳንንት ልብስ ጋር ሲመለከቱት አይሁድ እጅግ ቁመናንና ደምግባቱን ወደዱት አንድ አረጋዊ ስሉህን ከሚባሉ ቡድኖች የሆነ አንጢጎስን ሲመለከተውና ሰዎችም ሲያደንቁት አየና ለተማሪው የዚህን ወጣት ጥፋት ከማየቴ አስቀድሞ ብሞት ምንኛ መልካም ነበር እነሆ በሴጥሮን ሲገደል መሆኑን ተገለፀልኝ›› አለው ሴጥሮን በባህር ዳርቻ የምትገኝ ክፍል ስትሆን የጥፋት ቦታ መሆንዋ ከዚያ በፊትም የታወቀች ናት እቺ የመርከቦች መቆምያ ስትሆን ከፍተኛ የማስተናገጃ አዳራሽም ነበራት፡፡

ተማሪው ይህን ነገር እንዴት ሊሆን ይችላል ሴጥሮስን እኮ ከቄድሽ በጣም ርቃ ነው የምትገኘው ከዚያስ መቼ ሄዶነው አንጢጎስ ሊገደል የሚችለው ሲል መለሰለት አረጋዊ መምህሩ ደገኛ ነበር እንዲህም የሚል መልስ ለተማሪው ሰጠው ‹‹ይህ ማለቴን እንደማይሆንና እንደውሸት አድርገህ አትቍጠረው ልጄ ሆይ አንጢጎስ ከዘመቻው ወደ ቤተ መቅደስ በመምጣቱና ንጉሡን አርሰተቦሎስን አስቀድሞ ባለማግኘቱ ነገረ ሰሪዎች አጣልተውታል ወንድምህ አንጢጎስ ሊገድልህ ይፈልጋ ስለዚህ ነው አንተን ማግኘቱን ትቶ ወደ መቅደስ የሄደው ከዚያም ሰዎችን ወደሱ ሊስብ ነው እሱና ተከታዮቹ በሽልማት አሸብርቀው በቤተ መቅደስ እየተዝናኑ ይገኛሉ በሀና መታመምህን ስለሰማም በጦር መሳርያ እየታጀበ ይገኛል›› አሉት አስትሮቦሎስም የጦር መሣርያን ታጥቀው በየበሩ በመጠበቅ እንዲገድሉት



አዘዘ እንደገና ሐሳቡን ለወጠና የጦር መሳሪያውን ገፈው ወደሱ እንዲያመጡት አዘዘ፡፡

የንጉሡ የአርስቶቦሎስ ሚስት አንጢጎስን እጅግ ትጠላው ነበር እንዲገደልም ትፈልግ ነበር፡፡ ስለዚህ የባልዋ የንጉሡ አርስተቦሎስን መልእክት ለውጣ አንጢጎስን እንዲጠራ ለሚላከው መልእክተኛ የተሸለመውን ሽልማት እንደተሸለመ ለንጉሡ እንዲታየው እንዲነግርላት አደረገች አሸናፊነትህንሰምቼ ስለተደሰትኩ በለበስከው የአሸናፊነት የማዕረግ ልብስ እንዳይህ እጅግ ጓጉቼ አለሁና ፈጥነህ ወደኔ ‹‹ና›› በማለት ንጉሥ አርስቶቦሎስ እንዲጠራው አስመስላም ላከችበት፡፡

መልእክተኛውም የአርስቶቦሎስ ሚስት እንደነገረችው ለአንጢጎስ ካለበት ድረስ ሄዶ ነገረው አንጢጎስም ምንም ሳይጠራጠር በደስታ ወደ ንጉሡ አርስቶቦሎስ ሄደ ከለበሰውም ከወርቅ ሽልማት አንዲትንም ሳይቀንስ ለብሶ ነበር አርስቶብሎስ በሲጥሮን አዳራሽ አምሳል የተሰራ በጦር መሣርያ የታጨቀ ስሙም ማሕፊደ ሲጥሮስ ተብሎ የተሰየመ ነበረው ቀደም ብለን እንደገለፅነው ከባሕር ወደብ /ከቤተ መቅደስ ርቆበሚገኘው/ ማሕፊደ ሲጥሮን የሚባል እንደነበር ገልፀናል፡፡

ወደ ማሕፋደ ሲጥሮን /አርስቶቦሎስ ወደ ሰራው/ የተጠጋ ሁሉ እንዲገደል አረስቶቦሎስ አስቀድሞ አውጇል ምክንያቱም የጦር መሳርያ ማከማቻና የምስጢር ቦታ ነውና ማሕፊደ ሲጥሮን በምስጢርና በቅርብ ስለተሰራ ብዙዎች አያውቁትም ነበር በዚህ በሲጥሮን አዳራሽ በኩል አንጢጎስ ብቅ ሲል የአርስቶብሎስ ታማኝ ወታደሮች በቅፅበት ደርሰው በጎራዴ ቆራርጠው ጣሉት፡፡

ያ አረጋዊ መምህር በማሕፊደ ሲጥሮን አንጢጎስ ይገደላል ብሎ የተነበየው ትንቢት ተፈፀመ ንጉስ አርስተቦሎስ የወንድሙ አንጢጎስን



www.ethiopianorthodox.org

መገደል ሲሰማ በተንኰልና በእጅ አዙር ምቀኝነት መገደሉን ተረድቶ ሉሉ ብሶ አለቀሰ ደረቱንም በእጁ ደበደበ ከበሽታውም ገና በማገገም ላይ ነበር ስለዚህ ሰውነቱ እጅግ ተጎሳቆለ ከበሽታው ላይ የወንድሙ ሞት ሐዘን ተጨምሮበታልና፡፡

በአፉም ደም ተፋ ባሮቹ ያረጋጉት ዘንድ ጣሩ እሱ ግን የወንድሙ በግፍ መገደል ከአንጀቱ ላይ ገብቶ ተጨማሪ ከባድ ህመም ሆነበት ደሙ በአፉ መፍሰሱን ቀጠለ፡፡ሰዎቹ ከአፉ ከሚፈሰው ደም ወደ ብልሐተኛ ሰው ወስደው እንዲያሳዩትና መድሐኒት እንዲፈለግለት እንዲነግሩት ተነሱ ደሙን በሙዳይ አሰቀምጠው ለመልእክተኛ ሰጡት መልአክተኛው አንጢጎስ በተገደለበት ቦታ በኩል ለማለፍ ሲራመድ አንጢጎስ በተገደለበት ለማለፍ ሄደ የአንጢጎስ ደም ገና አልደረቀም ነበርና መልእክተኛው ሲንሸራተት የአርስቶቦሎስ ደም ከያዘው ሙዳይ አምልጦ ፈሰሰ የንጉሡ ባለሟሎች በመልእክተኛው ላይ ጮኹበት አርስቶቦሎስም አወቀ የተመሰገንክ በትክክል የምትፈርድ የዓመፀኛንም ደም አፍሳሽነት የምትመለከት አለ በልብ በሽታም ተይዞ በዓዕረሞት ላይ ተይዞ ነበር ለጥቂት ጊዜም እየተጨነቀ ቈየ ሕዝቡ ሁሉም በአንጢጎስ በሕብረት አለቀሱለት ጠላቶቻቸውንም ያቸንፍላቸው ስለነበር ሐዘናቸው ጠነከረ ደግነቱም ብዙ ነበረ አርስቶቦሎስም ወድያው ሞተ ከሱ በኋላም ወንድሙ እስክንድር ነገሰ የሕርቃኖስ ሕልምም በዚህ እውነትነቱ ታወቀ፡፡

## ምዕራፍ ፲፱

## ዜና እስክንድር ወልደ ሕርቃኖስ

ከክስምናይ ነገዶች መሳፍንት እስክንድር በስድስተኛ ቁጥር ይቀመጣል በንጉሥነት በመጠራት ደግሞ ሦስተኛው ነው አርስቶቦሎስ እንደሞተ



ወታደሮቹ በፍጥነት እስክንድርን ከታሰረበት አወጡት እስክንድር በአርስተቦሎስ ሞት ምክንያት የአካ ሰዎች እንዳፈነገጡ ሰማ እስክንድር በፍጥነት ወደ አካ ሄዶ ከበባት፡፡

የአካ ሰዎች የግብፁ ንግሥት ከሆነችው ቀልብሥጥራ ልጅን ጢሩ በእስክንድር ለመጠጋት እንዲታደጋቸው ላኩበት ለሱም እንደሚገዙ ገለፁለት ጢሩ ከናቱ ሸሽቶ በቆጵሮስ ነበር የሚኖረው ጢሩ ከቆጵሮስ ተነስቶና አሥር ወታደሮቹን አስከትሎ አካን የሚያስተዳድረውን ሰው ለመርዳት መርከብ ተሳፍሮ ጉዞውን ቀጠለ የጢሩን መምጣት ሲሰማ እስክንድር ወደአካን መርከቡን ትቶ ተመለሰ፡፡

የግብፅዋ ንግሥት ልጅ ጢሩ /ጢሩዋ/ እንደመጣ ሲረዱ የአካ ሕዝቦች እንደገና ሐሳባቸውን ለውጠው ላንተ አንገዛም ወደ ሀገራችን አትግባብን አሉት ጢሩ /ጢሩዋ/ ከነበረበት ቆጵሮስ ሠራዊቱን አሰልፎ እንዲመጣ ያደረጉት የታወቀውን የነሱ አስተዳዳሪ የነበረውን ሰው በመላክ ነው ለሱም እንደሚገዙትም ቃል ገብተው ነበር ነገር ግን ዋሹት በአካ አለቃም ለጢሩ /ጢሩዋ/ ብዙ ገንዘብ ተሰጥቶት ነበር በዚሁ ጢሩ /ጢሩዋ/የአካን ሰዎች ተቃውሞ ሳይቀበል ጥሶ ገባና አካን ተቈጣጠራት ቀጥሎ ወደ ቤተ መቅደስ ለመዝመት ተነሳ እስክንድር የጢሩ /ጢሩዋ/ ወደ እሱ ለዘመቻ መነሳት ሲያውቅ ወደ ግብፅዋ ንግሥት ቅልብሥራ ‹አንቺን ክዶ ወደ ቆጵሮስ የኰበለለው ልጅ በአካባያችን ይገኛል አንቺና እኔ ሁነን በመተባበር እንክበበው በዚህ ጊዜ ተሸንፎ ባንቺ እጅ ላይ ይወድቃል› ሲል ላከባት፡፡

ጢሩ የእስክንድር ከናቱ ቅልብሥጥራ ጋር በመልእክት መገናኘት ሲሰማ ወደ ገሊላ ገብቶ ብዙ ሰዎችን ገደለ ብዙዎችንም ማረከ እስክንድርንም ለመውጋት መንገዱን ቀጠለ በዮርዳኖስም ሰልፉን አሳመረ እስክንድርም ይህን ሰምቶ ሠራዊቱን አሰልፎ ሊዋጋው ከቤተ መቅደስ ተነሳ



www.ethiopianorthodox.org

ስድስት ሺ ወታደርንም አስከትሎ ነበር ብዙ ትዝሕርትንና መታበይንም አሳየ፡፡

ወደ ዮርዳኖስ ሄዶ እስክንድር ጢሩን /ጢሩዋን/ ጦርነት ገጠመውና ውጊያው ተፋፋመ ጢሩዋም እስክንድርን አቸነፈው ከሠራዊቱም ብዙዎቹን ገደላቸው ይህ ውድቀት የደረሰበት በልዑልና ክቡር እግዚብሔር መመካቱን ትቶ በጉልበቱ ስለተማመነ ነው የጢሩ /ጢሩዋ/ እናት የሆነችው የግብፅ ንግሥት ቅልብሥጥራ ትቷት የኰበለለውን ልጇ እስክንድር በላከላት መሰረት ትፈልገው ዘንድ ወጣች፡፡

ጢሩ(ጢፊዋ)የናቱ የግብፅ ንግሥት የሆነችው ቅልብጥሥራን መምጣት ሲሰማ ፈርቶ ወደቆጵሮስ ተመለሰ ቅልብስጥራ በበኩልዋ የጢሩ (ጢሩዋ) ፈርቶ ወደቆጵሮስ መመለሱን ስትሰማ ወደግብፅ ተመለሰች በሁለተኛው ዓመት እስክንድር ወደ ጋዛ ሄደና አመዘበራት ከነዋሪዎቹም አብዛኞቹን ገደለ የጋዛ ሕዝቦች ጢሩን (ጢሪዋን) ረድተው ነበርና ጣዖታቸውንም ደመሰሰ የጣዎት ካህናቶችንም ፈጃቸውይህንንሁሉ ፈፅሞ ወደቤተመቅደሱ ተመለሰ ዳግም ክፍል መፅሐፍ ከዚህ ላይ ተፈፀመ፡፡

## ምዕራፍ ፳

## ዳግም-ዜና -እስክንድር ወልደሕርቃኖስ

ወልደ ሕርቅያኖስ እስክንድር በዓለመፀለት ሲደርስ ወደ ቤተ-መቅደስ ገባ በካህናት ልማድም ወደ መሠዊውያው ቦታ ወጣ በዚሁ እለት አይሁዶች የዘንባባ ዝንጣፊን በመያዝ የመዝፈን ባህል ነበራቸው በህጋቸውና በባህላቸውም መሰረት መዝፈን ጀመሩ ከዚህ የዘንባባዝንጣፊ ይዘው በቤተ-መቅደስ ውስጥ ከሚዘፍኑ መካከል አንዱ በያዘው የዘንባባ ዝንጣፊ የንጉሱን ፊት መታው፡፡



በዚህ ጊዜ የንጉሱ ባለሟሎች ተቆጡ እንዲህም አሉ «እናንት የምእትዝላ ወገኖች ይህን ያህል እንዴት ደፈራቹ ንጉሱንስ እንዴት ልትመቱ ሞከራችሁ የሱን ክብር ተዳፍራችኋል በንጉስነቱም አላከበራችሁትም» አይሁዶቹ ግን እኛ የበአሉን ክብር በተመለከተ ዘፈን እንጂ ንጉሡን ለመድፈር ብለን የፈፀምነው ነገር የለም ድርጊቱ ባለማወቅ ተፈፅሟል አባቶቻችን ያቆዩን ባህልም ልንተው አይገባንም" አሉ፡፡

እስክንድርና ባለሟሎቹ ግን ይህን የማስተባበል ንግግር አልተቀበሉትም የምእትዝላን ቡድኖች አጥብቀው ይጠሉአቸው ነበርና የምእትዝላ ቡድኖች እስክንድርና ባለሟሎቹ የማስተባበል ንግግራቸውን ስላልተቀበሏቸው በእስክነድርና ባለሟሎቹላይ የድፍረት ቃልን መሰንዘር ጀመሩ፡፡እስክንድር የምእትዝላን ቡድኖች እንዲገድሉአቸው ባለሟሎቹን አዘዘ በዚችው ዕለት የምእትዝላን ፓርቲ ከሆኑት አይሁዶች መካከል ስድስትሺ ተገደሉ፡፡

እስክንድር በዓለመፀለት ካለፈ በኋላ መካነምስዋሉን ከተራ ሰዎች መቆያየሚለይና መካነም ስዋሉን የሚከልል ግንብ ሠራ ወደ መካነም ሥዋሉም ከካህናትና ታላላቅ ባለስልጣኖች በቀር ማንም እንዳይጠጋ አወጀ በምእትዝላና በሰዶቃውያን ፓርቲዎች መካከል ጥላቻው እየጠነከረ ሄደ እስክንድር የምእትዝላ ቡድኖችን ትቶ ሰዱቃውያንንይደግፍና ይረዳ ጀመረ፡፡ በመካከላቸውም ጥላቻ እንደበረታና እንደተጣሉ ለሰባት ዓመት ያህል ቆዩ በዚህ መካከልም አምሳ ሺ የምእትዝላ ወገኖች ተገድለዋል፡፡

እስክንድር የተቀጣጠለውን ጥላቻ ለማስቀረትና ሰላም ለማስፈን ሞከረ ነገርግን እንደጎሳ መቃጨት ሆኖ ብዙ ደም ስለፈሰሰ ሲረጋጋለት አልቻለም የምእትዝላ ቡድኖች ቂሚና ጥላቻው እያመረቀዘባቸው ስለቀጠለ ወደ ሮሙ ገዥምትርያስ ወልደስልፓዎስ እርዳታን ለመጠየቅ ሄዱ



www.ethiopianorthodox.org

እስክንድርንም እንድያስወግድላቸው ለመኑት ምትርያሰ ዳግማዊ አንተያከስም ይባላል።

አብዛኖቹ አይሁዶች የምእትዝላን ፓርቲ አባሎች ስለነበሩ የሮሙ ገዝ ምትርያስ እስክንድር ወልደሕርቃኖስን ለመውጋት ሲመጣ ባለበሌለ ኃይላቸውና ንበረታቸው ሁሉ ከሱጋር ተሰለፋ ናብሎስ በተባለው ቦታም ተሠለፈና እሰክንድር ወልደሕርዋኖስ ጦርነት ገጠመው በዚህ አስክንድር ተቸነፈ ምትርያስ ብዙዎቹን የእስክንድር ተከታዮችንአይሁዶች ገደላቸው።

እስክንድር ሸሽቶ ወዳንድ ተራራ ወጣ ከሞት የተረፉትንም የሱ ተከታዮች አይሁድ ወዳለበት ተከተሉት ምትርያስም የደገፋ አይሁዶች ወደ ተደበቀበት ተራራ መጡ ምትርያስን እየከዱ ወደእስክንድር ገቡ ከሱጋር ምትርያስን ለመውጋት ተገለበጡ እስክንድር ደግሞ ምትርያስን ጦርነት ገጠመው በዚህ ጊዜ ምትርያስ ተቸነፈ ወዳገሩ በሽሽትና በውርዴት ተመለሰ።

ምትርያስን ከምእትዝላዎች ጋር ካባረረ በኋላ ወድያው እስከንድር ምእዝላዎችን ለምን ምትርያስን

ደገፋቹሁ ብሎ ገደላቸው ብዙዎቹ ከምእትዝላ ቡድን የሆኑ አይሁድ ተገደሉ ከነሱምቡድን አባሎች እስክንድር ሰድስት ሺ ያህሉ ታላላቆች ወደቤተመቅደስ ወሰዶ ዕቁባቶቹና ሴቶች ባሮቹን በግራና በቀኝ አስቀምጦ በከፍተኛቦታ በመቀመጥ መጠጥ እየጠጣ ስድስት የምእትዝላ ቡድን አባሎች አይሁድ ከፊቱ እንዲገደሉ አዘዘ እነሱም ተገደሉና ከፊቱ እንዲንጠለጠሉ አደረገ።

እስክንድር ወልደሕርቃኖስ በአምባገነንነት ሁሉንም አቸነፈና ይገዛ ጀመር ወደ ድሞትርያስም ዘምቶ ጦርነት ገጥሞ ገደለውና ወደ ቤተመቅደስቅ ድምጥርያስን ለመውጋት ከሄደ በሦስተኛው ነው የተመለሰው



የሚጠሉትን አይሁዶች በሙሉ አንበረከካቸው እጅግም የገነነ ሆነ ከጊዜ በኋላ ግን በየአራት ቀን የሚያገረሽ የኩፍኝ በሽታ ያዘው ለሦስት ዓመትም በህመም ኖረ ስጋውም መነመነ።

እሱ ከሚገዛቸው አገሮች መካከል ህመሙን ሰምተው አመፁ እሱም በከባድ ሕመም ተይዞ እያለ ሊወጋቸው ሄደ ሴት ባሮቹና እስክንድራ የተባለች ሚስቱንም አስከተለ የዘመተባትንም አገር ከበባት ወደ ማሃል አገርም ከመግባቱ በፊት ግን በሽታ ፀናበት ይንቀጠቀጥም ጀመር ሚስቱ እስክንድራ መታመሙን አይታ አለቀሰች እንዲህም አለች የምትእዝላው ቡድን የሆኑ አይሁድ አንተን ይጠሉሃል እኔ ደካማ ሴት ልጆችህ ለዓቅመ አዳም ያልደረሱ ሕፃናት እነሱን ተቋቁመን ልንኖር አንችልም ምን ትመክረኛለህ ።

እስክንድር እንዲህ አላት ‹‹እኔ ከምትኩ ሞቴን ደብቂ በሕይወቴ ያለሁም አስመስሉ በዚችህም አገር ተቀመጭ አንቺም እየገዛሻት ኑሪ ከዚህም በኋላ ወደ ቤ-ተመቅደስ ተመለሺ በድብቅም ተሸከሚኝ የምትእዝላ ታላላቆችና አለቆቻቸው ጠርተሽ አክብሪያቸው ከነሱ ጋርም ሰላምን መስርቺ ከዚያም በኋላ እሱ እናንተን በድኋል አስከሬኑን የፈለጋችሁትን ታደርጉ ዘንድ ልስጣችሁ እኔን የፈለጋችሁትን ፈፅሙብኝ በያቸው እግዚአብሔርን ስለሚፈሩም አይበቀሉሽም የምትእዝላ ቡድኖች በውስጥም በውጭም ታዋቂነት አላቸው አንቺም ሊያነግሱሽ ይችላሉ እንዲህ እያልሽ ከቆይሽ ከልጆችሽ ለንጉስነት የደረሰ ይገኛል››አላትና ሞተ እስክንድራ እስክንድር በነገራት መሠረት መሞቱን ደበቀች አገሩንም ገዛች ቆይታም ወደ ቤተ-መቅደስ ተመለሰች የምእትዝላ ቡድን አባላት ከሆኑት አለቆችም ዋና ዋናዎቹን ጠርታ እስክድር እንደመከራት አደረገች እሺ አልዋት



www.ethiopianorthodox.org

የደረሰባቸውንም ግፍ ዘረዘሩላት ይህ ሁሉ ሲሆን የእስክንድርን መሞት አልገለፀችም በመጨረሻ ግን መሞቱን ገሃድ አወጣች።

እስክንድር ወልደሕርቃኖስ በክብር ነገስታት በተቀበሩበት እንዲቀበር አደረጉ እነሱም ከመላ ማሕበረ አይሁድ ጋር ተማክረው እስክንድራን አነገስዋት የምእትዝላ ቡድን አይሁድ አባሎች አይሁድ ባልዋ እስክንድር የፈፀመባቸውን ግፍ በመርሳት በአስተዳደርዋ ይረድዋት ጀመር የእስክንድር ወልደሕርቅያኖስ ዘመነ መንግስት ሃያ ሰባት ዓመት ነው ሁለት ልጆችንም ወልዷል ስማቸውም ሕርቅያኖስና አርስቶበሎስ ይባላል።

## ምዕራፍ ፳፩

## ዜና እስክንድራ ንግሥተ አይሁድና የልጆቿ ሕርቃኖስና አርስቶቦሎስ-ታሪክ

እስክንድራ መንግስትነቱን ካደላደለች በኂላ የምትእዝላን ቡድን አለቆች አይሁድ ሰበሰበች የነበራቸውንም ስልጣን መለሰችላቸው እጅግም አከበረቻቸው ከነሱወገን የታሠረውንም ሁሉ ፈታች በሕርቃኖስና በእስክንድር አገር ተባርሮ የተሰደደውንም አይሁዳዊ ሁሉ ወደአገሩ መለሰች ሰዱቃውያንንም ትታ ምእትዝላዎችን ተከተለች ደገፈቻቸውም።

ልጆቿ ሕርቃኖስና አርስቶቦሎስ ባደጉ ጊዜ ሕርቃኖስን ሊቀ ካህናትነት ሾመችው እሱ ትሑት ርኅሩህና ታጋሽ ነበርና አርስቶቦሎስን ደግሞ የጦር መሪ አድርጋ ሾመችው እሱ ብርቱና ደምግባቱ የተዋበ ነበርና የምትእዝላ ቡድኖችም ሹመቱን ተቀበሉ እስክንድር ይገዛቸው የነበሩትን አገሮችም ፀጥ ለጥ ብለው ተገዙላት በያመቱም ይገብሩላት ነበር።

መንግስቷ ፀና ትእዛዟንም ሁሉ ተቀበሉ የምእትዝላ አለቆች ወደሷ ገቡና‹‹ሰዱቃውያን እስክንድርን እየገፋፉ ከወገኖቻችን ባንድ ጊዜ ስምንት ሺ እንዳስገደሉና እንደሰቀሉ አንቺ ታውቂያለሽ ስለዚህ ፍቀጂልንና የተገደሉትን ወገኖቻችን ደም ለመበቀል ከሰዶቃውያንወንዶችን እንግደል›› አሉዋት እስክንድራም የወደዳችሁትን አድርጉ አለቻቸው።

የምእትዝላ ቡድን የሆኑት እነዚህ አይሁዶች የሰዱቃውያንን አለቃ ካለበት ሄደው ገደሉት ከዚያም አያይዘው ከሰዱቃውያን ብዙዎቹን ገደሉሰዱቃውያን ጊዜ እንደከዳቸው አውቀው ወደ እስክንድራ ተሰበሰቡ ልጇ አርስቶቦሎስም አብሮአቸው ነበር በዚህ ጊዜ ለእስክንድራ እኛ እስክንድር ካገሩ አልፎ ሌሎቹንም እንዲያስገብር ረድተነዋል ያን ያህል ታላቅ ንጉስ ሲሆን የቻለው የኛን ረዳትነት ይዞ ነውአሁን በከባድ መከራ ላይ እንገኛለን ይህን ሁሉ ነገር አንቺ እንዴት አታስቢም ጠላቶቻችንን አነሳሽብን በኛ ኋይም እጃቸውን ዘረጉብን የፈለጉትንም ሁሉ በኛ ላይ ፈፀሙብን እነሱ የእስክንድር ጠላቶች ናቸውና እኛ ግን ወዳጆቹ ነበርን ይህ ሁሉ ብታስታውሺ ኖሮ ለኛ ታላቅ ውለታ በዋልሽልን ነበር በኛ ድጋፍ አህዛብን ሁሉ አስገበራችሁ አህዛብ የኛን መዋረድ ሲሰሙ ደስ ይላቸዋል መንግስታችሁንም ለመቀማት ሊነሱባችሁ ይችላሉ አንቺንም ሲወጉሽ ይነሱብሻል በኋላ የሚመጣብሽን አታውቂም እኛ ግን አንክድሽም ከትእዛዝሽም አንወጣም የምትእዝላው ቡድኖች እንደበጎች ያርዱን ዘንድ ግን አንፈቅድም ለመከላከልም ሃይል አለን ከቻልሽ እነሱን አስታግሽልን ካልሆነ ደግሞ ካገር እንወጣና እንሰደድ ዘንድ ፍቀጅልን የወገኖቻችንን እልቂት ቁመን አንይ›› በማለት ከፊቷ ቀርበው እጅግ አለቀሱ እስክንድራም ከነሱ ጋር አለቀሰች።

ልጇ አስተርቦሎስም ሰዶቃውያንን ደገፈ ብዙም ስለነሱ ድጋፍ ዘረዘረ በዚህም ምክንያት እስክንድራ ግራ ተጋባች ስለዚህ አማካሪዎች ሴቶች ነበርዋትና ሰዶቃውያኑንካገር እንዲወጡ ታደርግ ዘንድ መከርዋት


www.ethiopianorthodox.org

ሰዱቃውያንም ካገረ ቤተ-መቅደስ ይወጡ ዘንድ ፈቀደች እንዲህም አለቻቸው «ከእልሞትእገዛላዎች\ምትእገዛላዎች ጋር ለመኖር አትችሉም እናንተ አስቀድማችሁ በነሱ ላይ ግፍ ፈፅማችኋልና በናንተና በነሱ መካከል የማይታረቅ ጥላቻ አለ»።

እስክንድራ ሰዱቃውያን ከቤተ-መቅደስ ቢወጡ ባገሩ ሰላም ይመሰረታል ብላ ታምን ነበረ በዚህም ሰዱቃውያን ካገር ወጡ ሰዱቃውያን ሲወጡ ታላላቅ የሰራዊቱ አለቆችም አብረው ወጥተዋል የዚህ ውሳኔ በስራላይ መዋል የእስክንድራ ትልቁ ድካምዋ ነበር በሰላም ይታዘዝዋት የነበሩ ሁሉ እየከበለሉ ሰዱቃውያን ወደ አሉበት ሁሉ እየሄዱ ተደባለቁ ባልዋ ከሞተ ጀምሮ ታላቅ ድጋፍ ያደርጉ የነበሩ ሁሉ መክዳት ጀመሩ ለልጆችዋ ሕርቃኖስና አርስቶሮቦሎስ የእርስ ብእርስ ጦርነት መጋጠም ምክንያት ሆነ።

እስክንድራ ለዘጠኝ ዓመት በስልጣን ላይ ቆይታ ሞተች እድሜዋም 73 ዓመት ነው። እስክንድራ ደምግባትዋ ያማረ ሃይማኖተኛ ነበረች ከመሰናክልና ከዳሕፅም የተጠበቀች ነበረች በሰዱቃውያንም ላይ ከፈፀመችው ስህተት ሌላ የፈፀመችው ስህተት የለም። ከእስክንድራ ቀጥሎ ልጇ አስትሮቦሎስ ነገሰ።

## ምዕራፍ ፳፪

## ዜና አስትሮቦሉስ ወልደ እስክንድር

አስተሮቦሎስ ከደቂቀ ክስምናይ መሳፍንት ስምንተኛው ነው በንጉስነት በመጠራት ደግሞ አራተኛ ነው አርስትሮቦሎስ የእስክንድራን በፀና መታመም ሲመለከት በሌሊት ወጥቶ ከቤተ-መቅደስ ሄደ ሰዱቃውያን



ወዳሉበት ሄዶ የናቱን በፀና መታመም ነገራቸውና ከጕድኑ እንዲሰለፉ በነሱ ረዳትነት ስልጣነ መንግስቱን እንዲያይዝ እንዲረዱት ጠየቃቸው።

እነሱም ጥያቄውን በደስታ ተቀበሉ ወሬውንም ወደ እናቱ እስክንድራ ደረሰ እስክንድራ የአርስቶቦሎስ ሚስትና ልጆቹ እንዲታሰሩ አደረገች የአርስቶቦሎስ እንቅስቃሴ በሰዱቃውያን ድጋፍ እየበረታ ሄደ እርሱን እንዲረዱትም ወደሱ መለሳቸው ከሊባኖስና ከገሊላ ተራሮች እየተነሱም ወደ እሱ ተሰበሰቡ ከሌሎችክፍሎች ያሉትም ወደሱ መጡ የሱ ሠራዊት እጅግ በዛ ጦርነትንም አካሄደ ወንድሙ ሕርቃኖስን ጦርነት ገጠመው ።

የምትእዘላው ቡድኖች ይህን ሰምተው እጅግ ፈሩ በዚህ መካከል እስክንድራ ሞተች አርስቶቦሎስ ወደ ዮርዳኖስ ሄደ ለጦርነትም ተዘጋጀ ህርቃኖስ ደጋፊዎቹን የምትእዘላው ቡድኖች አሰልፎ ሄደና ከዚያ ጦርነትን ገጠሙ ሕረቃኖስ ተሸንፎ ወደ ቤተ-መቅድስ ሸሸ አርስቶቦሎስ ተከተለውና ቤተ-መቅደስን ከበባት የከተማውንም ቅፅር እንዲያፈርሱ ወታደሮቹን አዘዘ።

በዚህ ጊዜ ከከባድ ፈተና ላይ የወደቁ የቤተ-መቅደስ ካህናትና የአይሁድ ሽማግሌዎች ወጥተው በአርስቶቦሎስ እግር ወደቁ ከወንድሙ ጋር እንዲታረቅም ለመኑት አርስቶቦሎስም ልመናቸውን ሰማና ከወንድሙ ሕርቃኖስ ጋር ታረቀና አርስቶቦሎስ ንጉስ ሆነ ሕርቃኖስ ደግሞ ሊቀ ካህናት ሆነ ሕዝቡ ምሕላ አደረጉና ለጥቂት ግዜ ሰላም ሆነ ጥቂት ቆይቶ ግን ሕርቃኖስንና አርስቶቦሎስን አንደፌር የተባለው ሰው አጣላቸውና ጠቡ አገረሸ።



www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፳፫

## ዜና አንደፌር የሄሮድስ አባት

አንደፌር አይሁዳዊ ሲሆን ከካህኑ እዝራ ጋር ከባቢሎን ከተመለሱ አይሁዶች ነው ነገዱ እንደፌር ሰውን የማቃለል ጠባይ ነበረው በተፈጥረው ክፉ በመጥፎ ተንኮል የተተበተበ ነው በመሬትና በገንዘብ የከበረ ነበር በእንስሳትም የከበረ ነበር ይህን ሰው የሕርቃኖስ ልጅ እስክንድር ሮምን እንዲቆጣጠርለት ሹሞት ነበር።

አንደፌር የተሾመባት አገር ከሮም ተገንጥላ የአይሁድ ግዛት የሆነችውን ደብረ ሹራህ ትባል ነበር አንደፌር ለብዙ ዓመታት ደብረሹራሕን እየገዛ ቆይቷል የኤዶም ተወላጅ የሆነችውን ሴት አገባ አራት ልጆችንም ከሷ ወልዷል ስማቸው ፌሰሉ ሄሮደስ ፍርድና ዮሴፍ ይባላል አምስተኛዋ ሴት ስተሆን «ሰሎሞንት» ትባላለች።

አይሁድ የኤዶም ትውልድ እንጂ ከእሥራኤል ምንም ትውልድ የለውም ይሉታል ይክስማይ ነገዶች ከሆኑት ካህናት አንዱ ካህን አንደፌርን በባርነት ተቀብሎት ነበረ እስክንድር ወልደሕርቃኖስ ሲሞትና እስክንድራ ስትነግስአንፌር ከሹመት ተሻረ በሀገረ ቆድሽም ያለ ሹመት ተቀመጠ ለሁለቱ ወንድማማቾች አርሰቶቦሎስና ሕርቃኖስ በየግላቸው የቅርብ ወዳጅ ይመስላቸው ነበር ሲያጣላቸው ግን ተንኮል ይሠራ ነበር አርስቶቦሎስን ለማስወገድም ጥረትን አካሄደ።

በሊቀ ካህናትነት ሥልጣን ያለውን ሕርቃኖስ «ወንድምህ አርሰቶቦሎስ ሊገልህ ተዘጋጅቷል አንተ በህይወት እያለህ መንግስቱ እንደምት ፀናለት አያምንምና አንተን አምፆ ንጉስ እንደሆነ ህዝቡ አያውቁምና በእውቀትም አንተ ከሱ ትሻላልህ አመቺ ጊዜ ብቻ ይጠብቃል



ስለዚህ ለህይወትህ ተጠንቀቅአመቺ ገዜ ካገኘ አንተን ከመግደል ወደ ኋላ አይልም» አለው ሕርቃኖስ የአንድፌርን ምክር አልተቀበለውም አንደፌር ግን አየደጋገመ ይህን የሐሰት ምክር ይመክረው ነበር በመጨረሻ አልቀበለው ሲለው ብዙ ገንዘብ በመስጠት ሌሎች ሰዎች ይህን የማስመሰል ተልእኮ ለሊቀካህናቱ ሕርቃኖስ እየደጋገሙ እንዲነግሩ በማደረግ ሕርቃኖስ እንዲጠራጠርና እንዲሰጋ አደረጉ።

አንደፌር አርስቶቦሎስ ወንድምህ እስኪገድልህ ድረስ ካለህበት ሁነህ ከምትጠብቅ ወደ ምዕራቡ ንጉስ ሄደህ ተጠጋና በሰላምኑር አለው አንደፌር ይህን ካለ በኋላ ወደምዕራቡ ንጉስ ዘንድ ሄዶ ሊቀ ካህናት ሕርቃኖስ የንጉስነትን ስልጣን ከያዘው ወንድሙ አርስቶቦሎስ ጋር በሰላም ለመኖር ስላልቻለ ወደአንተ በጥገኝነት ይመጣልና ተቀበለው አለው ንጉሱም ሕርቃኖስን ተቀብሎ ለማስጠጋት ደስተኛ ሆነ።

ይህንን ካከናወነ በኋላ ወደ ቤተ-መቅደስ ተመለሰ የምዕራቡ ንጉሥ ሀሪማ ይባላል ሀሪማ ሕርቃኖስን ለማስጠጋት ፍቃደኛ መሆኑን ለሕርቃኖስ ነገረው አንደፌር በሌሊት አሾልኮ ሕርቃኖስን ወደምዕራቡ ንጉስ ሀሪማ ወሰደው አብረውም ከዚያ ጥቂት ቆዩ ከዚያ አያይዞ አንደፌር አርሰቶቦሎስን ሀሪማ ይወጋው ዘንድ ወተወተው ሕርቃኖስም እንደሚረዳው ገለፀለት።

ሀሪማ ግን በዚህ አልስማማም አለ ከዚያ በፊት እስክንድር ወልደሕርቃኖስ ሀሪማን ሦስት ጊዜ ጦርነት ገጥሞ ብዙ ወታደሮችን ፈጅቶበታልና በዚህ ሊቀበለው አልቻለም አንደፌር በእኩይ የመሠረይነት ተግባሩ ለሃሪማ እንዲህ አለው«አርስቶቦሎስ በአይሁዶች ተጠልቷል የነሱ ፍላጎት ሕርቃኖስ እንዲነግስላቸው ነው አለው» በዚህ ግዜ የምዕራቡ ንጉስ ሀሪማ እውነት መሰለውና እሺ አለው።



www.ethiopianorthodox.org

ሀሪማ ለሕርቃኖስ አርስቶቦሉስ ተወግዶ እሱ ሲነግስ እስክንድር ወልደሕርቃኖስ ማርኮ የወሰደበትን ንብረት እንዲመልስለት ቃል አስገባው ወዲያው ሀሪማ ከሕርቃኖስ ጋር አርስቶቦሉስን ለመውጋት ብዙ ሰራዊት አስከትሎ ሄዶ ጦርነት ሲጀመር አብዛኞቹ የአርስቶቦሉስ ወታደሮች አርስቶቦሉስን እየከዱ ወደሕርቅያኖስ ተጨመሩ ከአርስቶቦሉስ ጋር የቀረው ሰራዊት ጥቂት ሆነ።

አርስቶቦሉስ ከጥቂት ሰራዊትጋር ብቻውን መቅረቱን ሲመለከት በሌሊት ሸሽቶ ወደ ቤተ-መቅደስ ተጠጋ ወዲያው ሕርቅያኖስና የምዕራቡ ንጉሥ ሀሪማ ወደ ሀገረ አይሁድ ገቡ ከነዋሪዎች አይሁድ ብዙዎቹ አይሁድ አርቶቦሉስን ስለደገፉ ሁለት ቀን ሙሉ ጦርነት ተካሄደ በዚህም ጦርነት ብዙዎቹ ወደ ግብፅ ተሠደዱ ይህ በዚህ እንዳለ የቂጣ በዓል ደረስ ካህናተ አይሁድ ለሕርቃኖስ ሠራዊቶች ‹‹በዓለናኦት እንደደረሰ ታውቃላችሁ ለመስዋዕት የሚታረዱ እንስሳት የሉንም ይህ በዓል እግዚአብሔር የሰራው በዓል ነው እናንተ እግዚአብሔርን ፍሩት ህጉንም አትጣሱ ይህንንም ለማድረግ አትከልክሉን›› አሉዋቸው።

ሀሪማና ሕርቃኖስ ይህን የአይሁድ አባባል ሳይቀበሉ ብዙ ገንዘብ ስጡንና እንመለስ አሉ ገንዘቡንም አርስቶቦሉስ አሰባስቦ ሰጣቸው እነሱም ቤተ-መቅደስን መክበብ አቆሙ።ይሁን እንጂ የቤተ-መቅደስ አይሁድ እግዚአብሔርን ስላስቀየሙ በረሃብ ቀጣቸው በረሃብም ብዙዎቹ ሞቱ።

በዘመኑ ሐና የሚባል ሽማግሌ ሰው ነበረበያምና በፀሎትም እግዚአብሔርን ይለምን ነበር ቅድስናውም በሁሉ ዘንድ ታውቆ ነበር ከሕርቃኖስ ጋር የወገኑ አይሁድ አገኙትና የነሱ ወታደሮች ወዳሉበት ወሰዱት እንዲህም አሉት ‹‹አንተ የእግዚአብሔር አገልጋይ እንደሆንክ



ታውቋል ስለዚህ አርስቶቦሉስን ርገምልን እሱን የሚከተሉትንም ርገማቸው በነሱ ላይ አሸናፊነትን እንዲሰጠንም እግዚአብሔርን ለምንልን››

ሽማግሌው ሰው ግን እንዲህ ሲል መለሰላቸው ‹‹አርስቶቦሉስንና ተከታዮቹን ሆነእናንተን ልረግም አይገባኝም ሁላችሁ የእግዚአብሔር ህዝቦች ናችሁና ከአርስቶቦሉስ ጋር የወገኑትም የእግዚአብሔር ካህናት ናቸው ነገር ግን ለነሱም ሆነ ለናንተ ልፀልይ ይገባኛል›› እነሱ ግን አጥብቀው እንዲረግምላቸው ወተወቱት እሱ ግን በእንቢተኛነቱ ፀና እሺ አላላቸውም በመጨረሻም ሊገሉት ፈለጉ።

በዚህ ጊዜ እጆቹን ወደሰማይ አነሳ‹‹እግዚአብሔር ሆይ አንተ ብቻ ትልቅ ነህ ፍጥረታትንም ፈጠርክ ፍጡሮችህንም አንተ ትገዛቸዋለህ አንተ ወደፈቀድከውም ልባቸውነ ትመልሳለህ በሕዝቦችህ ዘንድ ሰላምን ትመሰርት ዘንድ እለምንሃለሁ የካህናትህንም ልብ ትመልስ ዘንድና ትእዛዝህንም ወደመልካም ነገር ትምልስ ዘንድ እያንዳንዳቸውም እንዲጠፉፉ አትፍቀድላቸው መልካምን ለማድረግ ርዳቸው እንጂ ከመካከላቸውም ክፉትንና ጥላቻን አርቅ አንተንም ለማወቅ ይመለሱ ዘንድ አፍቅራቸው ወዳንተም ይቅረቡ››

ይህ አረጋዊ ይህን ሁሉ ፀለየ እነጂ የሕርቃኖስንና መሰሎቹን ጥያቄ ተቀብሎ አርስቶቦሉስንና የሱን ተከታዮች ካህናት ለመርገም ፈቀደኛ እንዳልሆነ አይተው ገደሉት እግዚአብሔር ድገሞ ጭካኔያቸውን አይቶ ካሉበት በወባ በሽታ እንዲለከፉ አደረገ በበሽታውም ብዙዎቹ አለቁ።



www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፳፩

## ዜና ፍምፍዮስ ሮማዊ

በዚሁ ዘመነ ፍምፍዮስ ሮማዊ የሠራዊት አለቃ ሆኖ አርመንን፣ ደማስቆንና ሌሎችን ለማስገበር ተነሳ ከታላላቅ ባለሥልጣኖቹ አንዱንና ስክሮስ የተባለውን ወደደማስቆ ላከው ስክሮስ ደማስቆንአስገብሮ እንደገና ሐለብ የተባለውን አስገበረ ሌሎችንም ያካባቢው አገሮች በሙሉ ለሮም መንግስት እንዲገብሩ አደረገ በውጥረት ላይ የነበረው አርስቶቦሎስ የስክሮስን ዝና ሲሰማ በመላላክ ወንድሙ ሕርቃኖስ በዓመፅ ስለተነሳበት እንዲረዳው ጠየቀው ብዙ ገንዘብንም ላከለት ሕርቃኖስ በበኩሉ ወንድሙ አርስቶቦሎስን ለማንበርከክ ርዳታ እንዲያደርግለት ለመነው ሁለቱ በየፊናቸው እረዳታ ስለጠየቁት ስክሮስ ለሁለቱም እምቢ አላቸው ቀጥሎም ሕርቃኖስን ለመርዳት የሚገኘውን የምዕራቡ ንጉስ ሀሪማ ጣልቃ ገብቶ ሕርቃኖስን መርዳቱን እንዲያቆምና ወደአገሩም እንዲመለስ ደብዳቤ ፃፈለት አልመለስም ካለግን ሠራዊቱን ልኮ እንደሚደመስሰው አስጠነቀቀው።

የስክሮስ ደብዳቤ እንደደረሰው ሃሪማ ወዲያው ወዳገሩ ተመለሰ ሕርቃኖስና ነገረ ሰሪው ተንኮለኛ አንደፌር አብረውት ተመለሱ በሌላ ደግሞ አሬፎስ የሚባል የሮማውያን አለቃ ወደደማስቆ ስለመጣ አስተሮቦሎስ ብዙ ገፀበረከት በወርቅ ከተሰሩ ሁለት ጋሻዎት ጋር እንደላከለት በጠቅላላ አምስት መቶ ባድራ የሚመዝን እንደላከለት አንድ በድራ መቶልጥር እንደሚመዝን ይህንንም ያደረገው ሕርቃኖስን እንዲቋቋምለት ብሎ አንደሆነ ተፅፋል።

ይህ ሁለተኛ የሆነው ተጨማሪ ታሪክ ሕርቃኖስም ከወንድሙ አስትሮቦሎስ ጋር በሚያደርገው ትግል ይረዳው ዘንድ ወዳጁ አንደፌርን ወደሱ \ወደ አንዳፌር\ እንደላከለትም ፍምፍዮስም አስትሮቦሎስን ለመርዳት



ፈቃደኛ እንደሆነና ከሕርቃኖስ መልእክተኞች የአስትሮቦሎስ መልእክተኞች ቀድመው ወደ ፍልፍዮስ እንደደረሱ ይገልፅና አንዳፌር በምሥጢር ለፍምፍዮስ ‹‹ከአስትሮቦሎስ የተላከውን ስጦታ አትቀበል አስተሮቦሎስ አይሁድን ሊይዝ አይችልም ሕረቃኖስ ግን ሊቀካህናት ስለሆነ ሊይዛቸው ይችላል እነሱም ይታዘዙለታል አይሁድ ላንተ ከታዘዙ ደግሞ ላንተ ታላቅ ዝናን ያተርፋል ይህ ድል ካንተ በፊት በሮም በነገሡትነገስታት አልታየምእና የሕርቃኖስን ትእዛዝ የሚተላለፍ አይሁዳዊ ከቶ አይገኝም ስላለው ፍምፍዮስ እሺ እንዳለው ተገልጿል።

የዚሁ የሁለተኛው ታሪክ የአንደፌርን የማግባቢያ ተንኮል ሰምቶ ስለተደሰተ አስተሮቦሎስ የሚደግፌው እየመሰለው እንዲታለል አድርግልኝ ሕርቅያኖስን ልረዳው ተነስቻለሁ እኔ እንድማላምነው እሱም እንዳይጠረጥረኝ ግን አድርግ ከነቃብኝ ግን የሱን ደጋፊዎች አይሁድ አሰልፎ ይገጥመኝና እናልቃለን እኔ ሕርቃኖስን ለመርዳት መነሳቴ ነው ወደ ቤተ-መቅደስም ለመድረስ እነሳለሁ ከዚያ ስደርስም አንተ የምትወደውን ሁሉ አደርጋለሁ ካሁን ጀምሮ ግን ለኛ ለሮማውያን እንድትገብሩ ቃልኪዳን ግባልኝ›› እንዳለው ያትትና ፍምፍዮስ ወደ አስትሮቦሎስ ወደኔ ና የሚል እንደላከለት ይገልፃል።

ፅሑፉ ሐተታውን በመቀጠል ‹‹አንደፌር ተመልሶ ወደሕርቃኖስ ሄደና ስለሱ ከፍምፍዮስ ጋር ስምምነት እንደመሰረተ ገልፆለት ፍምፍዮስን ለመገናኘት ሁለቱ አንደፌርና ሕርቃኖስ ብዙ ሰራዊትን አስከትለው ወደ ደማስቆ እንደሄዱና የአይሁድ ታላላቆችም አብረው እንደተጓዙ ያትታል አስተሮቦሎስም እንደሄደና በሌላ አቅጣጫ ወደፍምፍዮስስለደረሰ ከዚያ ሲገናኙ ችለዋል እንደ ዳገመኛው ታሪክ አባባል ሕርቃኖስን ተከትለው የሄዱ የአይሁድ ሽማግሌዎች በኛና በአስትሮቦሎስ መካከል ፍርድህን ስጥ



www.ethiopianorthodox.org

አርስቶቦሎስ በድሎናልና በሕጋችን መሠረት ሀርቃኖስ ታላቅ ስለሆነ ሊነግሥ ይገባል እሱ ደግ ነው አርስቶቦሎስ ግን ክፉ ነው ብዙ ሰውን ገድሏል ገንዘባቸውንም ዘርፎ አጣላቸው እኛንም አጣላን በማለት አንድ ሺ ሽማግሌዎችን ለምስክርነት አቆመ።››

አርስቶቦሎስ ‹‹ በአርግጥ ወንድሜ በእድሜ ይበልጠኛል ነገር ግን ከበታቾቻችን የነበሩ አህዛብ ባመፁብን ጊዜ ወንድሜ መንግሥትን ሊመራ እንደማይችል አረጋገጥኩ ጠላቶቻችንም እንዳያጠፉን ፈራሁ በዚህ መሰረት መንግሥትነትን ለመያዝ ተገደድኩ በሥርዓትም መራህዋት ጠላቶቻችንም አንበረከኩ። ከጠላት ሊሰነዘርብን የነበረውም ጥቃት ተወግዶ በሰላም ለመኖር ሞከርን አባታችን ከመሞቱ በፊት ይህን ይመኝ ነበር። አባቴ ሁናቴዬን አይቶር ንጉሥ መሆን እንደሚገባኝ ተናግሯል። ለእናቴ እስክንድራም የዚህን አደራ ሰጥቷት ነበር›› አለና ከአይሁዶች ብዙ ምስክሮችን አቀረበ።

አርስቶቦሎስ ለምስክርነት ያቀረባቸው የአይሁድ ወጣቶች ከመሆናቸውም በላይ በልብስና በልዩ ልዩ ጌጥ የተዋቡ ነበሩ የሮሙ ንጉሥ ፍምፍዮስ የነዚህን ወጣቶች ደምግባት አለበሳቸውና የተሻለውን ከእንቍ ከወርቅና ከአልማዝ የተሠራውን አይቶ እጅግ ተደነቀ። አይሁድ በሱ ሥር መሆን እንዳለባቸውም በሕሊናው ወሰነ ስለዚህ ‹‹ወደ ቤተ መቅደስ ሄጄ ሁኔታንው ካላጠናሁ ፍርድ ልሰጥ አልችልም ሙሉ ፍርድን እሰጥ ዘንድ ወደ ቤተ መቅደስ መሄድ አለብኝ›› አላቸው።

ፍምፍዮስ ከደማስቆ ተነስቶ ወደ ቤተ መቅደስ ሄደ አንዴፌር በዚህ ጊዜ አርስቶቦሎስ ተዋግቶ ወዳሸነፋቸው አገሮች ሄደና ፍምፍዮስን በጥሩ አቀባበል እንዲቀበሉት መከራቸው አርስቶቦሎስ የፈፀመባቸውን ግፍ ለፍምፍዮስ ዘርዝረው እንዲነግሩ ገፋፋቸው አርስቶብሎስ በወረራቸው ጊዜ የተዘረፉትንም ንብረታቸውን መጠየቅ እንዳለባቸውም አጥብቆ አነሳሳቸው።



ፍምፍዮስ ያስገበራቸውን ህዝቦች አቀባበል ያደርጉለት ዘንድ በፅሑፍ እንዲያዛቸው አስትሮቦሉስን አዘዘው አስትሮቦሉስም የታዘዘውን አደረገ ህዝቡም ተሰልፈው መጡና በሱ ላይ ተቃውሞ አሰሙ አስትሮቦሎስ ፍምፍዮስን ስለጠረጠረ በፍጥነት ሸሽቶ በቤተ መቅደስ ተጠጋ ፍምፍዮስ ተጠግቶት ሲዘምት በኢያሪኮ አደረ። ከዚያም ወደ ቤተ መቅደስ ተጠጋና አደረ።

ፍምፍዮስ በኢያሪኮ ያደረበት ምክንያት ኢያሪኮ እጅጉን የህይወት መአዛ ሎሚ ፅጌሬዳና ሌላችም የመልካም መአዛ ተክሎች የሚገኙባት ስለነበረችና በዚችም የሚበቅሉ የመልካም መአዛ ሽቶዎች በሌላ ፈዕመው ሊገኙ የማይችሉ ስለነበሩ ነው። ብዙ የአለም ነገሥታት ከኢያሪኮ እየወሰዱ ይህንን ተክል ወዳገራቸው ወስደው ለመትከል ቢሞክሩም ሊበቅልላቸው አልቻለም ነበር። በግብፅ ብቻ ይህ የሽቶ ተክል ሊበቅል ችሎ ነበር።ዕፀ በለስን ጨምሮ ሌሎች የመልካም ሽቶ ተክሎች ቤተ መቅደስ ዳግም እስከትጠፋ ድረስ በመልካም ሁኔታ እየበዛ በኢያሪኮ ይገኝ ነበር ቤተ መቅደስ ዳግም ስትጠፋ ግን ደረቀና ጨርሶ ጠፋ በግብፅ የፀደቀውም ሽቶ እስከዚሁ ድረስ ቆይቶ ጠፋ።

ፍምፍዮስ ከኢያሪኮ ወደ ቤተ መቅደስ ሄደ አስትሮቦሎስ ወጥቶ በፍርሃትና በድንጋጤ ተቀበለው እሱም ይቅርታ አደረገለት ወንድሜ በመንግሥቴ ላይ ስላመፀብኝ እንዲታዘዘኝ አድርግልኝ ክብሬንም ጠብቅልኝ ካልሆነ ጠላቶቼ ይዘብቱብኛል ከውርዴት አድነኝ እኔም የፈለግኸውን እሰጥሃለሁ አለው።

ፍምፍዮስ ‹‹ በል በቤተ መቅደስ የተከማቸውን ንብረት ሁሉ አስረክበኝ ወርቁን ብሩንና ገንዘቡን በሙሉ ሥጠኝ እኔም በቆጵሮስ



www.ethiopianorthodox.org

የሚገኘውን ምኩራብ አልሽምትሪ በመባል ታውቆ የሮምያ አምላክ የሆነውን አስረክበዋለሁ እኔም የጠቅከውን እፈፅምልሃለሁ ››ሲል መለሰለት፡፡

አርስቶቦሎስ በቤተ መቅደስ ያለውን ሁሉ ያንተ ነው የሚያመጣልህን ሰው ላክ እንጂ ሲል መለሰለት ፍምፍዮስም የቤተ መቅደስን እቃ እንዲያመጣለት ከአለቆቹ አንዱን ላከ የቤተ መቅደስ እቃ እንዳለ ይዞ ለመውጣት ሲሞክር ካሕናትና ሕዝቡ ከለከሉት ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከአስትሮቦሎስ ሰራዊት ጋር ጦርነት ተካሄደ የሕርቃኖስ ሰራዊት አመቺ ጊዜ ስላገኙ ብዙ ሕዝብን ገደሉ ፍምፍዮስ ይህን ስለተረዳ ካገሩ በር ቆመ ሠራዊቱንም ተከትሎ ነበር፡፡

ሕዝበ አይሁድ በሩን ከፈቱለትና ገብቶ የንጉሡን ድንኳን ያዛት ቀጥሎም ቤተ መቅደስ ለመግባት ወደ ቤተ መቅደስ ሄደ ነገር ግን መግባት አልቻለም ካህናት የቤተ መቅደስን በር ዘግተው አናስገባም አሉት ፍምፍዮስ ወታደሮቹን እንዲወግዋቸው ላከባቸው ይህ የሆነው ተሙን በተባለው ወር ነበር፡፡ የፆም ወራት እስኪገባ ጦርነቱ ቀጠለ የሰባት አስር ፆም ሲደርስ ካህናት እጅ መንሻ ወደ ቤተ መቅደስ አስገቡ ከጦርነት የተነሳም እጅግ ደክመው ነበር፡፡

በዚህ ጊዜ ፍምፍዮስ በየ ቅፅሩ ባለሹል ብረት እንዲተክሉ አዘዘ በዚህም የሮም ወታደሮች ቅጥሩን ጥሰው ወደ ቤተ መቅደስ ገቡና ብዙ ህዝብን ጨፈጨፉ ካህናት ግን ያ ሁሉ መከራ እየደረሰ የቤተ መቅደስ አገልግሎታቸውን አላቋረጡም ነበር፡፡ የልቡና ፍርሃት ሳይደርስባቸው ዕጣንን አጠኑ ማሳረጉንም ተያያዙት የሕግ መልእክታትንም በጥብዓት እንፈጽም በማለትም እርስ በራሳቸው ተፅናኑ እስክንሞት ድረስም የእግዚአብሔርን ተልእኮ በማከናወን እንጠባበቅ አሉ፡፡ ጠላቶቻቸው ሊገድሉዋቸው ሲመጡ እያዩ ዝም ብለው ተልእኮዋቸውን ማከናወን



ተያያዙት ከመካከላቸው አንዱ ሲገደል አብሮት ያለው ሌላው ካህን መንፈሳዊውን ተልእኮ ያከናውናል አንድ አንድ እያሉ ምንም የመሸሽ መልክ ሳያሳዩ ብዙዎች ካህናት በሮማውያን ወታደሮች ተገደሉ፡፡ ደማቸውም ከደመ መስዋእት ጋር ተደባለቀ ለእግዚአብሔር ትእዛዝ እያሉም ተገደሉ፡፡

የሮሙም ንጉሥ ፍምፍዮስ የቤተ መቅደስን ስነ ህንፃ ሲመለከት እጅግ ተደነቀ በልቡ ግን ድንጋጤ አደረበት የንዋየ ቅድሳትን ማኖርያና አሠራራቸውንም አይቶ እጅግ ገረመው ከነሱ ግን አንዲት እንኳ አልወሰደም ከሞት የተረፉትንም ካህናት ጠርቶ በታረዱት ካህናት ደም የተጥለቀለቀውን ቤተ መቅደስ እንዲያፀዱ የተገደሉትንም ካህናት አስክሬን እንዲቀብሩና የተለመደውን መንፈሳዊ ስርዓታቸውን ሳያቋርጡ እንዲቀጥሉ አዘዛቸው፡፡

ይህን ትእዛዝ አስተላልፎ ፍምፍዮስ ከቤተ መቅደስ ወጥቶ ወደ አገሩ ሄደና ህርቃኖስ በአይሁድ ላይ ነገሠ፡፡ አርስቶቦሎስ ግን ፍምፍዮስ እንዳሰረው ታስሮ ቀረ ከብዙ ተከታዮቹ ደግሞ ከፊሎቹ ተገደሉ ሕርቃኖስ የአይሁድ በአህዛብ መገዛትን አስወገደ በአህዛብ የተወሰደው ግዛታቸውንም መለሰ አይሁድ ግን በየ አመቱ ለሮማውያን ግብር እንዲያስገቡ ወሰነ፡፡

ፍምፍዮስ ከቤተ መቅደስ ከመውጣቱ አስቀድሞ ነገረሠሪውን አንደፈርና ህርቃኖስን እንዳይከዱት ቃል ኪዳን አስገባቸው አርስቶቦሎስን ግን እንዲታሰር ከሁለት ልጆቹ ጋር ወደ ሮም ወሰደው፡፡ ሦስተኛው ልጁ እስክንድር ግን ሸሽቶ ስላመለጠ በፍምፍዮስ አልተያዘም ነበርና ሳይወሰድ ተደበቆ ቀረ ፍምፍዮስ ከቤተ መቅደስ ሲወጣ የሱን ወኪል ሰክሮስ የሚባል ትቶ ሄደ፡፡

ሕርቃኖስ አንደፈሬና ሰክሮስ ተስማምተው አይሁድን ይመሩ ጀመር ፍምፍዮስምን ለማስደሰት የሱን ትእዛዝ ለማስፈፀም ወደ ምዕራብ ሄዱ ከሮም መንግሥት ጋርም በመስማማት ለመቀጠል ወሰኑ የአስትሮቦሎስ ልጅ



www.ethiopianorthodox.org

እስክንድር የሀርቃኖስ ከነስክሮስ ጋር ወደ ምዕራብ ሄዱ ከሮም መንግስት ጋርም በመስማማት ለመቀጠል ወሰኑ የአስትሮቦሎስ ልጅ እስክንድር የሀርቃኖስ ከነሰክሮስ ጋር ወደ ምዕራብ መሄድ ሲሰማ ከተደበቀበት ሮጦ ወደ ቤተ መቅደስ ገባ አይሁድም በደስታ ተቀበሉት ወድያውም አነገሱት ፍምፍዮስ ያፈረሰውን የቤተ መቅደስ ቅፅር ወድያው አሰራው።

ብዙዎቹ አይሁዶች ባጭር ጊዜ ውስጥ ወደሱ ተሰበሰቡ ሀርቃኖስ ከእንደፊሬና ስክሮስ ጋር ከሄደበት የምዕራብ ክፍል ቢመለስ እስክንድር ለጦርነት ተዘጋጅቶ ጠበቀውና ብዙዎቹን የሱን ተከታዮች ገድሎ አባረረው።

## ምዕራፍ ፳፫

## ዜና ፍምፍዮስ ሮማዊ

ከሮማውያን ከፍተኛ ባለ ስልጣኖች አንዱ የሆነው ከስብያኖስ ከሮማውያን ተነስቶ አርመንን ለመጎብኘት መጣ ባለበትም የአርስቶቦሎስ ልጅ እስክንድር ቤተ መቅደስን እንደያዘ ሰማና ሲዋጋው ወደ ሀገረ ቆድሽ ሄደ ሕርቃኖስ አንፌርና ሰክሮስም እሱን ተከትለው እስክንድርን ለመውጋት ወደ ቤተ መቅደስ /ሀገረቄድሽ/ ሄዱ አስክንደርም ጦርነትን ገጥሞ በጦርነቱ ሜዳ ሕርቃኖስን አንደፌርንና ስክሮስን ማረካቸው ከስብያኖስ ግን ቀስ በቀስ ብርታትን አግኝቶ ሀገረ ቁድሽን ከበባት በዚሁ ወቅት የእስክንድር አባት አስትሮ ቦሎስ በበኩሉ ሀገረ ቁድሽን ከበባት በዚሁ ወቅት የእስክንድር አባትአስትሮ ቦሎስ ከሮም እስር ቤት አምልጦ ያፈተለከበት ጊዜ ነበር። እስክንድር ወደ አስብያኖስ በሰላማዊ መንገድ መጣ በሰላምም እርቅ እንዲመሰረት አግባባው ወድያው ግን አንቲፎስ ከተባለው ሰው ጋር አስትሮቦሎስ ወደ አገረ አይሁድ ደረሰ ብዙዎቹንም አሸነፋቸው ተከታዮቹም



ብዙዎቹን ገደላቸው። አርስቶቦሎስም ተማረከና እንደገና ተይዞ ወደ ሮም ተወሰደ የቄሳሮች መንግሥት እስኪመሰርት ድረስም እንደታሰረ ኖረ።

ሮም ከብዙ ዘመን ጀምሮ በተመረጡ ያገር ሽማግሌዎች ትመራ እንደነበረ አስቀድሞ ተገልጿል። በመጨረሻ ግን አመባገነን ቄሳር ነገሠ የተመረጠውንም ሽማግሌ ከነ ተከታዮቹ ገድሎ ከስልጣን አባረረና ራሱ ነገሠ። ይህ የሮም የመጀመሪያው ቄሳር ፍምፍዮስ አስትሮቦሎስን እንዳሰረው ስላወቀ ከእስር ፈታው በመልካም ዓይን ተመልክቶ ታላቅ ሥልጣን ሰጠው።

ሁለት ታላላቅ ባለ ሥልጣኖች የሱ የበታች ሹማምንት እንዲሆኑ በማድረግም አርማንያንና ሀገረ አይሁድን እንዲገዛ ፈቀደለት መቶ ሺ ሁለት መቶ ወታደሮችም የእሱ ሰራዊት እንዲሆኑ አደረገ የአርመንና የአይሁድ አገሮች ከፍምፍዮስ ትእዛዝ ወጥተው ለሱ/ለቄሣር/ ብቻ እንዲገዙ ያደርግ ዘንድም አዘዘው በደማስቆ የተቀመጠውንም ፍምፍዮስ ለማስወገድ ሕዝበ አርማንያና ህዝበ አይሁድ እንዲተባበሩት እንዲያደርግ አርስተቦሎስን አዘዘው።

ነገረ ሠሪው አንደፌር በታላቅ ኃይል የአርስቶቦሎስን መምጣት ሲሰማ ከሱ ጋር የሚግባባበትን መንገድ ፍለጋ ከቤተ መቅደስ ታላላቅ ሰዎችንም ጠርቶ አርስቶቦሎስን ከሩቅ በታላቅ ክብር እንዲቀበሉት አዘዛቸው።እኛ ካንተ ወገን የሆን የቤተ መቅደስ ሰዎች ነን በማለትም ወደ አርስቶቦሎስ እንዲጠጉ መከራቸው አንድ ተንኮለኛንም አዘጋጅቶ ወደ አርማንያን ላከበት።

አርስቶቦሎስ ከሀገረ ቆድሽ ለመጡ መልእክተኞች ታላቅ አቀባበል አደረገላቸው እነዚህ ተንኮለኞች አርስቶብሎስን እንዴት መርዝ እንደሚያጠጡት ሆኔታዎችን ወዳጆች በመምሰል ሲያመቻቹ ሰነበቱ በመጨረሻም መርዙን ከምግብ ጋር አስጨምረው በማብላት ገደሉት



www.ethiopianorthodox.org

በአርማንያ መቶ ተቀበረ በሥልጣንና በእስር አርስቶቦሎስ ሦስት ዓመት ከመንፈቅ ቈይቷል በጣም ጠንካራና አስተዋይ ሰው ነበር ቄሳር ከመንገሡ በፊት ተመርጦ ከተሾሞው አረጋዊ /በሮምያ/ የተወለዱ ልጆች አስትሮቦሎስ ጋር ስለነበሩ እናታቸው ወደ ሀገረ ቈድሽ እንዲልካቸው ስለለመነችውወደ ቤተ መቅደስ ልኳቸው ነበር።

ክስምናይ የግብፅ ሕዝቦች ንጉሣቸውን አንታዘዝም እንዳሉትና ለሮም መንግሥት አንገብርም እንዳሉ ሰማ የግብፁ ንጉሥ ብልማይ ይባል ነበር ነገረሰሪው እንደፈረን አስከትሎ ክስምናይ ወደ ሮም ዘመተና ወጋቸው ብዙ ወታደሮችንም ገደለባቸው ብልማይንም ወደ መንግሥቱ መለሰው።

የግብፅ ሁከት አበቃለት ክስምናይ ይህን ፈፅሞ ወደ ሀገረ ቈድሽ ተመለሰ ክስምናይ የሮም ባለሥልጣን ነው። ሕርቃኖስ ወንድሙ ስለሞተለት የአይሁድ ንጉሥ ሆነ እጅግም በረታ እንደፈረንም በክብር ቦታ ላይ አስቀመጠው ከጥቂት ጊዜ በኋላም ወደሮም ተመለሰ።

## <u>ምዕራፍ ፷፮</u>

## <u>ዜና ክርሶስ ሮማዊ</u>

ክስብያኖስ ወደሮም ሲመለስ ፋርሶች በሮማውያን ከመገዛት አፈነገጡ ክርሶስም ከሮም ተዋግቶ እንዲመልሳቸው ተነሳ ክርሶስ ብዙ ሠራዊትን በማስከተል ወደ ፋርስ ገሠገሠ ወደ ፋርስ ከመሄድ ይልቅ ወደ ቤተ መቅደስ ሄደና ወደ ቤተ እግዚአብሔርም ገብቶ በቤተ መቅደስ ያለውን ንብረት በሙሉ እንዲያስረክቡት ካህናትን ጠየቃቸው።

በወቅቱ ከካህናት መካከል አንድ አልአዛር የሚባል ደግ ካህን ነበር። ይህ ካህን ክርሶስን እንዲህ አለው። "ብዙ ነገሥታት ለቤተ መቅደስ ስጦታን ሰጥተዋል የወሰዱት ነገር ግን የለም አንተ ይህን ለመውሰድ እንዴት ተነሳሳህ



ፍምፍዮስ ክስብያኖስና ሌሎች ምንም የወሰዱት የለም።" ክርሶስ ግን "የማስቀረው ነገር አይኖርም ሁሉን እወስዳለሁ" ሲል መለሰለት ይህ ደግ አልአዛር ካህን እንዲህ አለው "አንድ ምናን ሁለት ሺህ መክሊት ነው ስለዚህ ሦስት መቶ ምናን እሰጥሃለሁ የቤተ መቅደስን ንብረት ግን አትውሰድ"

ክርሶስ በዚሁ ተስማማ በቤተ መቅደስ ከሌሎች ነገሥታት በስጦታ የተሰጠ የወርቅ ጣዖት ነበር አሠራሩ ደስ ይላል በጣም ጥበበኛ የሆነ ሰው የሠራው ነውና ከቤተ መዛግብት አንዱን ክፍል ሞልቶት ነበር ሦስት መቶ ምናንም ይመዝን ነበር። የዚህን ጣዖት መኖር ከአልአዛር በቀር ከካህናት መካከል የሚያውቀው አልነበረም ስለዚህ ይህን ከወርቅ የተሠራ ጣዖትን ለክርሶስ ሰጠው።

ክርሶስ ግን ይህን ከወርቅ የተሠራ ጣዖት በእጁ ካስገባ በኋላ ቃል ኪዳኑን አፈረሰ ያለውን የቤተ መቅደስንም ንብረት ሁሉ በሥልጣኑ መዘበረ። ቤተ መቅደስ ዳግም ከተሠራ ጀምሮ የተከማቸው የቤተ መቅደስን ንብረት በሙሉ አንዲት ሳያስቀር ጠራረገው አይሁድ የሌሎችን አገሮች መንግሥታት በወረሩ ቁጥር ያከማቹትን ሁሉ ወሰደ። አንድ በድል አስር ሺህ ብር ማለት ነው። ከቤተ መቅደስ የተወሰደው ንብረት ሁለት ሺህ በድልን ይመጥናል።

አይሁድ እየማረኩ ከሰበሰቡት ንብረት ሌላ በሥእለት ግለሰቦች የሰጡት አለ ነገሥታትም በፈቃዳቸው ብዙ ንብረትን አስረክበዋል። አይሁድ የሚያስገብሩዋቸው አህዛብም በግብር መልክ ለቤተ መቅደስ እጅ መንሻ ያበረክቱ ነበር። ክርሶስ ይህን የቤተ መቅደስን ንብረት ዘርፎ ወደፋርስ ጉዞውን ቀጠለ ጦርነትም ገጠማቸው እነሱ ግን አቸነፉት እንጂ አልተበገሩለትም በፋርሶች ጦርነት ብዙ ወታደሮች አለቁበት ከቤተ መቅደስ የዘረፈውን ንብረት ጨምሮ ያለውን ሁሉ ማረኩበት እሱንም ለማሳደድ ባደረጉት ክትትል አርማንያን ተቈጣጠሩ በመቀጠልም ብዙዎች ሌሎች የሮም ግዛቶች ወሰዱ



www.ethiopianorthodox.org

የሮም ባሥልጣኖች ሁኔታው ስላሰጋቸው ክስሎፌ በተባለው የጦር መሪ የሚመራ ብዙ ጦር ሠራዊት ፋርሶችን እንዲከላከል ላኩ፡፡ አርማንያን ጨምሮ በፋርሶች የተያዙትን የሮም ግዛቶች በሙሉ አስመለሰ፡፡

ክስሎፌ ከዚሁ በመቀጠል ወደ ሀገረ ቂድሽ ሄደ፡፡ ሕርቃኖስና እንደፈር ከወገኖቻቸው አይሁድ ጋር እየተዋጉም አገኛቸው፡፡ እሱ አስታርቆ በስምምነት እንዲኖሩ አደረገ ባለበትም ወደ ፋርስ ሄደና ፋርሶች በሮማውያን ሥር ሁነው እንዲገብሩላቸው አደረገ ወደ ምሥራቅም ሄደ፡፡

የቅድስት ድንግል ማርያም አባት ኢያቄም በዚሁ ዘመን ተወለደ የኢያቄም አባት ዮና የሚልኪ ልጅ የሌዊ ልጅ ሲሆን ሌዊ ማታትዩንና ቅሥራን ወለደ ማታትዩ ኤሊን ወለደ ቅሥራ የማታትዩ አባት ነው፡፡ ማታትይ ደግሞ የኢያቄም አባት ነው፡፡ ኢያቄም የእግዝእትነ ማርያም አባት ነው፡፡ የዮሴፍ ልደት እንደሚከተለው ነው የማታትዩ ልጅ ኤሊ በሞተ ጊዜ የሱን ሚስት የያዕቆብ አባት ለወንድሙ ዘር ያቆምለት ዘንድ ከኤሊ ሚስት ልጅን ወለደ ስሙም ዮሴፍ አሉት ዮሴፍ በሥጋ የያዕቆብ ልጅ ነው በኦሪት ህግ ግን የኤሊ ልጅ ነው፡፡

## ምዕራፍ ፳፯

## የቄሣር መንግሥት አጀማመር

የቄሣር መንግሥትነት፡- ሮምን ቄሣር ለመግዛት እንዴት እንደቻለ ከሮም ግዛቶች ሁሉ ረበናትን ማሳደዱ የሚገልፅ ታሪክ በዚህ ተገልጿል፡፡ ሦስት መቶ ሃያ የሮም ባለሥልጣኖች በተመረጠው የሮም ሽማግሌ ሥር ነበሩ፡፡፡ በሕዝብ የተመረጠው ሽማግሌ ሚስት በመውለጃዋ ጊዜ ሞተች ልጁ በሆድዋ እያለ ስለሞተች ሙታ እያለ ልጁ ሆድዋ ይንቀሳቀስ ነበር፡፡ ስለዚህ ብልሐተኞች የሞተችውን ሴት ሆድ ቀደው ሕፃኑን አወጡት ጤናማም ሆኖ ወጣ፡፡



ልጁ አደገ "ብሉባስ" የሚል ስያሜም ተሰጠው ይህን ስያሜ የሰጡት ከዓመቱ በአምስተኛው ወር ስለተወለደ ነው፡፡ እንደገና የአወላለዱን ታሪክ ለማስታወስ ቄሣር አሉት፡፡ ቄሣር ማለት በነሱ ቋንቋ የሚቀድ የሚሰነጥቅ ማለት ነው፡፡ ቄሣር ሲያድግ እጅግ በረታ የፀናም ሆነ፡፡ በወቅቱ የሮማውያን ግዛቶች በሆኑት የምዕራብና የምሥራቅ ግዛቶች የግዛት መፈረካከስ ሰፊነ አገሮቹ ለሮም አንገዛም እያሉ አሻፈረኝ ማለትን አበዙ፡፡

ቄሣርን ያንድ ክፍለ ጦር መሪ በማድረግ ሮማውያን ወደ ምዕራብ ላኩት እሱም በሄደበት ድልን ተቀዳጀ ለሮም መንግሥት እንዲገብሩም አደረገ በታላቅ የአርበኝነት ክብርም ወደ ሮም ተመለሰ ሲመለስም ልቡ ደነደነ መንግሥትንትንም ፈለገ ንጉሥ እንዲሉትም የሮምን ሕዝቦች ጠየቃቸው በዚህ ጊዜ እነዚያ በሕቦቹ የተመረጠው የሮም ሽማግሌ አስተዳዳሪ ሦስት መቶ ሃያ የበታች ሹማምንቶች ለሽማግሌው አባቶቻችን ንጉሥ እንዳይኖር በማለት ተማምለዋል የዚህም ምክንያቱ "በረክዮስ" የተባለው ንጉሥ በፈፀመው ወንጌል ምክንያት ነው፡፡

ህግ ሠርተውም በዘመናቸውና ከነሱ በኋላም ፀንቶ እንዲኖር ስለወሰኑ እስከ ዘመናችን በሕዝቡ በሚመረጡ አፈጋውያን ስንመራ ኑረናል አሁንም አለን አርበኞችም ብዙ ያመፁ አገሮችን አስገብረው ሲመለሱ አንግሱን ብለው አያውቁም ፍምፍዮስ ወደ ምሥራቅ አገሮች ዘምቶ ሁለት ነገሥታትን በማቸነፍ በሮም ሥር ሲያንበረክክ ኑሯል በዚህም ታላቅና ክቡር ነው፡፡ አንግሱኝ በማለት ግን አልጠየቀም፡፡ እጅግ በርትተው የነበሩትን አይሁድ በሮም ሥር ያስገዛ ፍምፍዮስ ነው፡፡

ስለዚህ ቄሣር ንጉሥ በሉኝ በማለቱ አንጠላውም ነገር ግን "እኛ ከአባቶቻችን የወረስነው አንድ ህግ አለ ይኸውም በሕዝብ የተመረጠ ሽማግሌን



www.ethiopianorthodox.org

መሪ ከማድረግ በቀር ንጉሥ በሀገራችን እንዳይኖረን የሚል ህግ ስለተቀመጠ ነው" ብለን መልስ እንስጠው ተባባሉ፡፡

ቄሣር ግን አባባላቸውን ፈጽሞ አልተቀበለም ወድያው ብዙ ተከታይ ስላገኘ በሕዝቡ የተመረጠውን ያገር መሪና ሦስት መቶ ሃያዎቹን መማክርት ገደላቸው በገዛ ጉልበቱና በአምባገነንነቱም ንጉሥ ነኝ አለ የሮም መንግሥት የበታች ሁኖ ግብፁን ያስተዳድር የነበረው መሪ "ሎፍምዮስ" ይበላል ለሮም መንግሥት አልገብርም ማለትን ስለጀመረም ቄሣር ወደግብፅ ሄዶ በመውጋት አቸነፈው ገደለውም ግብንፅም በሥሩ አደረገ የሮምንም ግዛት ሁሉ ተቆጣጣረ ወደ አርማንያም ዘመተ አርማንያንም ከመደምሰሱ አስቀድሞ የአርማንያው ንጉሥ በሥርህ ነኝ ብሎ ተንበረከከለት የአርማንያው ንጉሥ ስም "ምትራዳብ" ይባል ነበር፡፡

ቄሣር ምትራዳብን ወደ ግብፅ ሄዶ የቀድሞው ሮማዊ ባለሥልጣን ፍምፍዮስ የበታች ሹማምንት በግብፅ ይገኙ ስለነበር እንዲጠራቸው አዘዘው ምትራዳብ በቄሣር በታዘዘው መሠረት ጉዞውን ወደ ግብፅ ቀጠለ፡፡ "አስታህ" ከተባለችው አገርም ደረሰ ፍምፍዮስ በቄሣር ከተገደሉት ታላላቅ የሮም በለሥልጣኖች ዋናው ነው፡፡ የአይሁድ ንጉሥ ሕርቃኖስ ደግሞ በፍምፍዮስ ድጋፍ ነው ሥልጣን ላይ የወጣው ስለዚህ የቄሣር ወደ አርመን መምጣት ሕርቃኖስን አስደነገጠው፡፡

ሕርቃኖስ አስቀድሞ ከቄሣር ጋር ሰላምን መመሥረት ስለመረጠ አንደፌርን ከብዙ ሠራዊት ጋር ወደአርማንያ ቄሣርን እንዲገናኝ ላከው አንደፌርና ምትራዳብ በመንገድ በአስቀሎና ተገናኙና አንደፌር ወደ ቄሣር መሄዱን ትቶ ከምትራዳብ ጋር ወደግብፅ ተጓዘ ምትራዳብ በተናጠል ግብፃውያንን ለመውጋት ቢሞክር ግብፃውያን አቸነፉት ነገር ግን አንደፌር ረዳውና አቸነፋቸው፡፡ ነገር ግን ግብፃውያን ቢያንበረክኩም አንፌሬዝ በጦርነቱ



ክፉኛ ቈሰለ፡፡ ምትራዳብ አንፌሬዝን በጣም አከበረው ውለታው እንዲታወቅም ወደ ቄሣር ፃፈለት ቄሣርም ስለ አንደፌር ምትራዳብ የፃፈውን ሲያነብ እጅግ ደስ አለው በጣምም አንደፌርን አወደሰው ወደሱም እንዲመጣ ቄሣር አንደፌርን ጠራው ከምትራዳብ በመሆን ተመለሱና ቄሣርን በደማስቆ አገኙት፡፡ ቄሣር አንደፌርን እጅግ አከበረው ታላቅ ተስፋንም ሰጠው፡፡ ወዲያው ግን የአርስተቦሎስ የሕርቃኖስ ወንድም ልጅ አንደፌር በነገረሠሪነት መግባቱ በአርስተቦሎስ ላይ የፈፀመውን ግፍ ለቄሣር ዘረዘረ ይህ የአርስተቦሎስ ልጅ ሊጢአስ ይባላል፡፡ ሕርቃኖስንም አጋለጠው ሕርቃኖስና አንደፌር አርስቶቦሎስን ግፍ ፈጽመውበታል፡፡

ቄሣር ፍምፍዮስን እጅግ ይጠላዋል የአርስተበሎስ ልጅ ሊጢአስ በዚህ ጊዜ አባቱ አርስተበሎስ ፍምፍዮስን ሊወጋ ሲነሳ ሕርቃኖስና አንደፌር ፍምፍዮስን በመደገፍ አስገድለውታል በማለት ለቄሣሩ ነገረ፡፡ በዚህ ጊዜ አንደፌር እንዲህ ሲል መለሰ "ፍምፍዮስ አይሁድን ስላስገበረ ለሮም መንግሥት ክብር ስል አፈቀርኩት ስለዚህ ለቄሣር ብየ በግብፅ የፈፀምኩትን ውለታ ብቻ ይታይልኝ፡፡ "በማለት በግብፅ የቈሰለውን ራሱን እጆቹን ሌላውን አካላቱ ገልጦ ለቄሣር አሳየ፡፡ እኔ ለፍምፍዮስ ብዬ የትም ዘመቻ አልሄድኩም ላንተ ለቄሣር ግን በጦር ግንባር ሕይወቴን ሰጥቼ በፅኑዕ ቈሰልኩ" አለም ቄሣር የአንደፌርን ንግግር ሲሰማ እጅግም ተደነቀ እንዲህ ሲል አመሰገነው "አንተ በአይሁድ ዜና ሰላማዊ መሆንህን በሚወዱህ ሁሉም የተመሰገንክ እንደሆንክ በእውነት ተገለፀ ለፅናትህም በአካላትህ የሚታዩ ቁስሎች ምስክሮች ናቸው፡፡ እኔን ማክበርህንና መውደድህን ፅናትህንም ጭምር የሚገልፁና የሚመሰክሩ ናቸውና እነሆ ከምወዳቸው ታማኞቸ ሁሉ የበላይ በማድረግ ሾሜሃለሁ፡፡



www.ethiopianorthodox.org

እኔ ወደምሥራቅ ለዘመቻ እሄዳለሁና የጦር መሪ ሁነህ ከኔ ጋር ትዘምታለህ የምሄደው ፋርሶችን ለማስገበር ነው። ስመለስም ከኔ ጋር ትመለሳለህ ከዚያ በኋላ የሚያምርህን ሥልጣን ይዘህ ወዳገርህ ትመለሳለህ።"

ቄሣር ፋርስን ወግቶ ለማስገበር ወደዚሁ ሄደ አንደፌርም አብሮት ሄደ የአንደፌር ጀግንነት በዚህ ጊዜ ታውቆ በቄሣር ዘንድ አንደፌር "ፅኑ ትሑትና ታጋሽ መልካም ስነ ምግባር ያለው ከቄሣርም በላይ ሞያ ያለው" ተብሎ ተወደሰ ክብርንና በዕልንም ጨመረለት ቄሣር ከፋርስ ወዳገሩ ወደምድረ ይሁዳ እንዲመለስ አሰናበተው ቄሣር ወደሮም ተመለሰ አንደፌር ደግሞ ወደምድረ ይሁዳ ተመለሰ።

በአንደፌር ድካምና ከቄሣር ጋር ባገኘው ማለሚልነት ሕርቃኖስ በሰላም የአይሁድ ንጉሥ ሆኖ እንዲቀጥል ረዳው የቤተ መቅደስም ንጉሥ መሆኑን በግልጽ አወጀ ህርቃኖስ በአስተዳደር የተመሰገነ ሆነ። ሩሕሩህ የማይጨክን ፀጥታንና ዝምታን የሚወድ እየተባለም በአይሁድ ዘንድ ተነገረለት ይህን ሁሉ ለማግኘ የቻለው በአንደፌር ድካምና ጥረት ነው።

## ምዕራፍ ፳፫

## የሄሮድስ መነሳት ዜና

ሄሮድስ የአንደፌር ልጅ ነው ሕርቃኖስ የአንደፌርን ምክርና ጭምትነት ተመልክቶ እሱንና ልጆቹን በገባዔ ሾማቸው አንዱን የአንደፌር ልጅ ፋሲሎስን የቤተ መቅደስ ተቆጣጣሪ አድርጎ ሾመው ሁለተኛው ልጁ ሄሮድስን ደግሞ የመስፍንነት መዓረግ ሰጠው።

ሄሮድስ በመስፍንነት የተሾመበት ቦታ ገሊላ ነው። ሄሮድስ የገሊላ መስፍን ሆኖ ሲሾም የአስራ አምስት አመት ልጅ ነበር። የአንደፌር ልጆች በፖለቲካ የበላይነትን ስለያዙ የሕዝቡን ስሜት ሳቡ። የህርቃኖስ ሥልጣን ግን



የአሻንጉሊት ያህል ተንሳፈፈ በወቅቱ ሕዝቅያስ በመባል የሚታወቅ ቀሳጢ ሰው ነበር የመንግሥት ሰዎችን ወደሱ ሰበሰበ የሚሰበስባቸው የመንግሥት ሰዎች ወደአርማንያ እየሄዱ ዘረፋ እንዲያካሄዱ ሰዎቹም እንዲገድሉና የተዘረፈውንም እንዲያካፍሉት ይመክራቸው ነበር።

ሕዝቅያስን ከመጥፎ ድርጊቱ እንዲቆጠብ አድርግልኝ የቄሣርን ፈቃድ ምን እንደሆነ አንተ ታውቃለህ ሕዝቅያስንና ወገኖቹ በአርማንያ የፈፀሙትን ጥፋት አንተ ታውቃለህ ከዚህ ቀሣጢ ሰው ታሳርፈኝ ዘንድ እለምንሃለሁ ንጉሥ ቄሣርም ይህን የቀሣጢውን ድርጊት አይቀበለውም ስለዚህ የህዝቅያስን አድራጎት ካስቀረህ ቄሣሩ ደስ ይለዋል። እኛም ያንተን ውለታ አናስቀርም"

የሚል ደብዳቤ ለሄሮድስ ተጻፈለት።

ሄሮድስ ደብዳቤውን አነበበና ከገሊላ ተነስቶ ወደአርማንያ መንገዱን ቀጠለ። ሄሮድስ አርማንያን ሲያመዘብር ቆይቶ ሲመለስ ሕዝቀያስን በመንገድ አገኘው። በመክበብም ያዘውና ሕዝቅያስን ገደለው ህዝቅያስን እየተከተሉ ይዘርፉ የነበሩትንም ገደላቸው።የቄሣር የበታች ሹም ለሆነው ስፍኖስም ይህን ፃፈለት (በፅሑፍ ገለፀለት) ስንፎስም የሄሮድስን አድራጎት ስላስደሰተው የገንዘብ ስጦታ ላከለት ሌሎቹ የሮም ሹማምንትም እንዲሁ ላኩለት ስፍኖስ ሄሮድስን አወደሰው።

የሄሮድስ ነገር በዚሁ መሠረት እየተያያዘና እየተስፋፋ ሄደ ተከታዮቹም በዙ አይሁድ የሕዝቅያስን መገደል ሲሰሙ እጅግ ታወኩ ወደንጉሡ ሕርቃኖስም ተሰበሰቡ እስከ መቼ ድረስ አንደፌርን ትታገሰዋለህ እሱና ልጆቹ ሁሉንም ነገር በእጃቸው አስገብተው የበላይነትን እስኪይዙ አንተ ዝም ብለህ ትመለከታለህ ስም ብቻ ተሸክመሃል እንጂ ሥልጣንህስ ከተወሰደ ቆይቷል አንደፌር ባንተ ገንዘብ ወደሮም ነገሥታት እየተጠጋና እየተወዳጀ ታወቀበት ልጁ ፋሲሎስ የቤተ መቀደስ ተቆጣጣሪ ሆኖ ያላንተ ትእዛዝ



www.ethiopianorthodox.org

የፈለገውን ያደርጋል ልጁ ሄሮድስ ደግሞ አህዛብን በኛ ስም ሲያስገብር የኖረውን ሕዝቅያስን ቄሣሮችን ለማስደሰት ብሎ ገደለው በተለይ የአርመን ሕዝቦችን ለማስደሰት ብሎ ይህንን አደረገ ከአርመኖችም ገንዘብንና ሌላም እጅመንሻ ለመቀበል ይፈልጋል ሄሮድስን በነፍስ ገዳይነት ለፍርድ ልታቀርበው ይገባል" በማለት ከገሠፁት በኋላ ሕዝቅያስ ሲገደል አብረው የተገደሉትን ወንጆች እናቶች ከሱ ፊት አቀረቡ የተገደሉት ወንዶች ሚስቶችንም አቀረቡለት። ሕርቃኖስ ወዲያ ወዲህ በሚንቀሳቀስበት ሁሉ በንዝሕላልነቱ ብዛት አይሁድ እየጮሁ በጣም አስጨነቁት ሄሮድስ ስለፈፀመጣቸውንም በደል አለቀሱበት ከሱም ከአምባገነንነት ግዛት እንዲያላቅቃቸው ተማፀኑት።

ሕርቃኖስ የሚያደርገውን አጥቶ በጣም ተቸገረና ሄሮድስ ወደ ሀገረ ቄድሽ እንዲመጣ ደብዳቤ ፃፈለት ሄሮድስም ብዙ ሠራዊትን አስከትሎ ረበናተ አይሁድ ወደሚፈርዱበት አደባባይ መጣ በዚህ ጊዜ ሄሮድስ ጢሙን እጅግ አሳምሮ እጅግ ያማረ ልብስንም ለብሶ ሰይፍንም ታጥቆ መጣ የተከተሉት ወታደሮች ደግሞ ነፍስ ወከፍ የጦር መሣሪያ ይዘው ነበር።

ሕርቃኖስ በበኩሉ ወታደሮቹን አሰከትሎ ወደአደባባዩ መጣ ረበናት የሄሮድስን አኳኋን ሲመለከቱ በሱ ላይ አንዳችም ከመፍረድ ተቆጠቡ እጅግ ፈርተውታልና እሱን በመክሰስ ወደ ህርቃኖስ ብዙ ሲዘበዝቡ የነበሩት ሁሉ ወደኋላቸው ገሸሽ አሉ አንዲት ቃልንም ለመተንፈስ አልደፈሩም ቀድሞ በሄሮድስ ላይ ብዙ ይለፈልፍ የነበረ ሁሉ አንደበቱ ተዘጋ። ሸማግሌዎቹ /የአሁድ ሽማግሌዎች/ ግን ትክክለኛውን ፍርድ ለመፍረድ ጀመሩ። ይሁን እንጂ አያያዙ መልካም እንዳልሆነ የተረዳ ሕርቃኖስ ነገሩ በይደር እንዲታለፍ ሽማግሊዎቹን ጠየቀ ነገሩም በማግሥቱ ተዘርዝሮ መታየት አለበት አለ።

ከረበናት መካከል ያንዱ መምህር /ረቢ/ ተማሪ ሰማይ የሚባል ከዚሁ ነበርና እሱም ታወከ። "ለሽማግሌዎች" ወደ ፍርድ አደባባይ የሚመጣ ሁሉና



የነፍስ ገዳይነት ክስ የቀረበበት ሁሉ ጥቁር ለብሶ ይመጣ ነበር ጠጉሩንም ሳይቀባ በፍርሐትና በድንጋጤ ይመጣ ነበር። ይህ ወጣት የሆነው ሄሮድስ ግን ከዚሁ በተለየ አኳኋን መጣ ወንጀለኛ በወንጀል ተከሶ ሲቀርብ የመፀፀቱን ስሜት የሚገልፅ ልብስንም አልለበሰም ነገር ግን እሱና ሠራዊቱ ለጦርነት ብቻ ተዘጋጅተው መጡ። ይህንን ያደረገበት ምክንያት የፍርዱን አደባባይና ፈራጆቹን ስለናቃቸውና ሆን ብሎ ስላቃለላቸው ነው።

በሱ ላይ አንዳች ፍርድ ቢፈረድ የፈረደበትን አካል ወድያው ለመበቀል ተዘጋጅቶ ነው የመጣው እናንተ ፈራጆች ሆይ ህገ ወጥ አለባበስን ለብሶ ከፊታችሁ ሲቀርብ ሳትቈጡና ሳትቃወሙት መቀረታችሁን አደንቃለሁ። ይህ ሄሮድስ ውሎ አድሮ የናንተ ንጉሥ መሆኑ አይቀርለትም በዛን ጊዜ እንደፈለገው ይፈርዳል የናንተንም ደም ያፈሳል። ንብረታችሁንም ይዘርፋል ህርቃኖስ ከመፍራቱ የተነሳ ፍርዱ በይደር እንዲታለፍ አደረገ ነገር ግን ሕርቃኖስ በሄሮድስ እጅ መገደሉና መንግሥቱም በሄሮድስ መወሰዱ አይቀርለትም" አለ። ህርቃኖስ የሰማይን ንግግር ሰምቶ ወደቤቱ ተመለሰ ባደባባዩ ላይ የተሰበሰቡት ሽማግሌዎች ረበናትና ሌሎቹም ህርቃኖስን ተከትለው ሄዱ በዚችው ሌሊት ሄሮድስ ከገሊላ ወጥቶ ወደ አርማንያ ሄዶ በዝያ ከነበረው የቄሣር ወኪል ፍምፍዮስ ጋር ተገናኘ ፍምፍዮስም ሄሮድስን በታላቅ ክብር ተቀበለው ከነበረበት የገሊላ ሹመትም ሌላ መላ ሀገረ አይሁድን እንዲገዛ ሥልጣን ሠጠው።

## ምዕራፍ ፳፱

## ሕርቃኖስ ወደቄሣር ስለላከው መልእክት ዜና

ሕርቃኖስ ወደቄሣር የፃፈው መልእክት የሕርቃኖስ የቃል ኪዳን መጽሐፍ ተብሎ ተሰይሟል። ይህን የቃል ኪዳን መጽሐፍ ሕርቃኖስ በራሱ



www.ethiopianorthodox.org

መልእክተኞች አማካይነት ። ወደቄሣር ላከው የሕርቃኖስ መልእክተኞች ይህን የሕርቃኖስ የቃል ኪዳን መጽሐፍን ይዘው ወደሮም ተጓዙ መልእክቱን ወደ ቄሣር የላከው ቄሣር ቃልኪዳን እንዲያድስለት ነው።

የህርቃኖስ መልእክተኞች ሮም ሲደርሱ ቄሣር በደስታ ተቀብሎ መልካም መስተንግዶ አደረገላቸው ለጊዜውም እንደ ቤተ መንግሥት ሰዎች እንዲሆኑ ፈቀደላቸው ፍላጎታቸውንም ሁሉ አሟላላቸው ለሕርቃኖስ የቃል ኪዳን መልእክት መልስም እንዲህ ሲል ፃፈ "ከቄሣር ንጉሠ ነገሥት በዓሩአዳ ለምትኖሩ የሮም መንግሥት ተወካዮች ሰላም ለናንተ ይሁን የእስክንድር ልጅ ሕርቃኖስ መጽሐፍ ከኔ ዘንድ ደረሳለች የዚችው የመልእክት መጽሐፍ ከኔ ዘንድ መድረስም አስደስቶኛል።"

እሱና የሕዝቦቹ እኔን መውደዳቸው የሙሉ ሮምንም ሕዝብ ማክበራቸውን እናገራለሁ። ሕርቃኖስ ከአይሁድ ፈሪሳውያን ወገን የሆነውን አንደፌር በጣም ይወደዋል። አንደፌር ደግሞ ከወዳጁ ምትራዳብ ጋር በመሆን ግብፃውያንን አቸንፎ በኔ ሥር እንዲሆኑ ያደረገ ጥሩ የኔ ታማኝ ነው። ወዳጁን ምትራዳብን በግብፅ ከገጠመው ከባድ ጦርነት ከመሞት ያተረፈው አንደፌር ነው።

እኔ ፋርስን ለማስገበር በተጓዝኩ ጊዜም አብሮኝ ሄዶ አንድም ሳይቀር አገሮች ሁሉ ለኔ እንዲገዙ አድርጓል አሁን ከመርከብ ማቆሚያ ወደቦች የሚገኘው ቀረጥ ከጋዛ ጀምሮ እስከፀይዳ ካለው ሁሉ ተሰብስቦ ለቤተ እግዚአብሔር ያስረክቡ ከነሱ የሚሰበሰበው ሃያ ሺህ ገንዘብም ከስንዴ ጋር በየዓመቱ ለቤተ መቅደስ ይሰጥ።

ሎደቅያስና አካባቢው በአይሁድ ንጉሥ እጅ የተያዘውም አገር ሁሉ እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ድረስ ያለው ሁሉና የክስምናይ ልጆች የሚኖሩበት አገር ሁሉ ... ይህ ሁሉ ለሕርቃኖስ ወልደ እስክንድር ይመለስ ሕርቃኖስ



የአይሁድ ንጉሥ ሲሆን የተጠቀሰው አገር ሁሉ አባቶቹ በኃይላቸው ወደራሳቸው አስገብተውት ነበር።

ፍምፍዮስ ከአስትሮቦሉስና ሕርቃኖስ እጅ ለመውሰድ ብዙ ደክሞ በቃል ለኔም እንዲመጣ አድርጓል። ከዛሬ ጀምሮ ግን ያ ሁሉ ተጠቃልሎ ለንጉሥ ሕርቃኖስ እንዲሆን ሰጥቻለሁ። ዛሬ ለሕርቃኖስ የሠጠሁት እስከ ዘለዓለም የሱ ተከታዮች ለሆኑ ሁሉ እንዲፀና ወስኛለሁ ይህን ህግ በሮም የሚነግሱ ሁሉ ያክብሩት ይህን ህግ የጣሰና የሻረ የተደፋፈረ እግዚአብሔር ይፋረደዋል። ርግማንም ይሁንበት ባገሩም እንዲሁ "ይህን መጽሐፈ ኪዳን /የውል መጽሐፍ/ ያነበበ ሁሉ በብረት ሰሌዳ ይጻፍ በዮናናውያንና በሮማውያ ቋንቋም ጽፋችሁ ሁሉ እንዲያነበው በግንብና በየአደባባዩ ይሰቀል። ዮቤስ የተባለው ጣዖት በሚመለክበት አልሞሻር በተባለው የአምልኮ ጣዖትም ቦታ ይሰቀል። ይህ ከሆነ ለሕርቃኖስና ለአይሁድ የተሰጠ ህግ መሆኑ ይታወቃል።"

## ምዕራፍ ፴

## የመጀመርያው ቄሣር አሟማት

## ዜናና የአንደፌር አሟሟት

ቄሣር ሁሉ ተንበረከከልኝ ብሎ ተዝናና። ዕረፍትም አደረገ። በድንገትም ያልጠረጠራቸው ሁለት ሰዎች ስክሮስና አብሳይሮስ ገደሉት እነዚህ ከታላላቅ የመንግሥት ባለሥልጣኖች የሚመደቡ ነበሩ። የፍምፍዮስም ወዳጆች ነበሩ። ስክሮስ ወዲያው ብዙ ሠራዊትን ሰበሰበና በረታ ነገር ግን ቄሣሩን ከግብረአበሩ ጋር ስለገደለ ለሕይወቱ ስለሚፈራ በሮም ለመቀመጥ አልፈለገም ነገር ግን ባሕርን ተሻግሮ ሄደና እስያን ገዛ።

ስክሮስ ወደ ሀገረ አይሁድ ሄዶ አይሁድን 70 በድራ ወርቅን እንዲሰጡት አስገደዳቸው አንደፌር በዚህ ጊዜ የቤተ መቅደስ ተቆጣጣሪ



www.ethiopianorthodox.org

በሆነው ልጁና በሄሮድስ ልጅ ይህን መጠኑ እጅግ የበዛ ገንዘብን ከመላ የአይሁድ ግዛት ማሰባሰብ ጀመረ የተሰበሰበውንም ገንዘብ ከአንደፌር እጅ ተቀበለና ወደ መቄዶንያ ሄዶ ተቀመጠ የአይሁድ አለቆች አንደፌርን እንዲገድል በሚሥጢር ላኩበት ነገር ግን ለመግደል አልተሳካለትም። ቀስ በቀስ ጠጅ አሳላፊውን በገንዘብ ገዛው አንደፌርንም የሚገድልበት መርዝ ሰጠው ጠጅ አሳላፊውም በመጠጥ ጨምሮ መርዙን ለአንደፌር ሰጠውና ወዲያው ሞተ። አንደፌር የህርቃኖስን ወንድም አርስተቦሎስን በመርዝ አስገድሎታል እሱም በመርዝ በመገደል ዋጋውን አገኘ እግዚአብሔር በእንደዚህ አኳኋን ሥልጣኑን ያሳያል።

ሕርቃኖስ የአንደፌር በመርዝ አሟሟት ፊፅሞ አላወቀም ያ በመርዝ አንደፌርን የገደለ ሰው ሚልክያስ ይባላል። ሄሮድስ ያባቱን በመርዝ መገደል ሲሰማ ከገሊላ የአባቱን ደም ለመበቀል ወደ ቤተ መቅደስ ሄደ ቤተ መቅደስን እንዲቈጣጠር የተሾመው ወንድሙ ፍሲሉ ግን ብጥብጥ እንዳይነሳ ስለሰጋ መግባት ከለከለው። ይህ በዚህ እንዳለ ለኪሳኦስ የተባለው ሰው በአባቱ አንደፌር ላይ ያደረገውን ድርጊት ለፍሲሉ ነገረው ፍሲሉ ሚክያስን እንዲገድለው መከረው። ይሁንና ሊገድለው አልደፈረም።

በአንደፌር መገደል የማቱ ቄሣር ወንድም ልጅ ለኪዎስ እንዳለበት ተሰምቷልና። ክብርያኖስና አንጥቦበስ ብዙ ሠራዊትን አስከትለው ወደ መቄዳንያ በመዝመት የመጀመርያውን ቄሣር ከአብሳይሮስ ጋር በመሆን በድንገት ገድሎ መቀመጫውን በመቄዶንያ ያደረገውን ሰርክስ ገደሉት ክብርያኖስ የመጀመሪያው ቄሣር ወንድም ሲሆን አውግስጦስ ተብሎ የሮም ንጉሥ ሆነ በሥልጣንም እጅግ ከፍ አለ። እንደገና የአባቱን ወንድም ቄሣርን ለማስተወስ ዳግማዊ ቄሣር ተባለ። የቀጠሉት የሮም ነገሥታት ሁለቱን ቄሣርና አውግሥጦስ ደርበው መጠሪያ እያደረጉዋቸው ኖሩ።



በአውግስጦስ ሁለተኛው ቄሣር ዘመን ምስጋና ለሱ ይሁንና ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተወለደ። ህርቃኖስ የአይሁድ ንጉሥ ኪስቃል ሙቶ አውግስጦስ እንደነገሠ ሲሰማ ብዙ እጅ መንሻን አስይዞ መልእክተኞችን ወደሱ ላከ ከእጅመንሻው መካከል ከዕንቍ የተሠራ የራስ ወርቅ ነበር። ካለፈው ቄሣር ጋር የነበረውን የቃል ኪዳን ስምምነትንም እንዲያድስለት በጻፈው ደብዳቤ ለመነው በያገሩ ተበታትነውና ተማርከው የሚገኙትንም አይሁዶች ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ ነፃነትን ይሰጣቸው ዘንድ አሳሰበው።

አውግሥጦስ ስጣታውን ተቀብሎ ተደሰተ መልእክተኞቹንም በክብር አስተናገዳቸውና ሕርቃኖስ ለጠየቀው ሁሉ በጎ ምላሽ እንደሚሰጥ አስታወቀ እንዲህ የሚል የመልስ ደብደቤም ጻፈለት። “ከንጉሠ ነገሥት አውግስጣስና ከአንጥቦበስ የሠራዊት አለቃ ወደ አይሁድ ንጉሥ ሕርቃኖስ የተፃፈ ሰላም ላንተ ይሁን ያንተን መልእክት አንብበን ደስ አለን በደብዳቤህ የዘረዘርከውን ሁሉ ለመፈጸም በሙሉ ልብ ተስማምተናል ከሕንድ ጀምሮ እስከ ውቅያኖስ እስከ ምዕራብም ድረስ ባለው ግዛታችን ቃል ኪዳንህ እንዲታደስ ተስማምተናል።

ዓማጺውን ከነውሴ ቄሣርን በመድፈሩና በመግደሉ የሚበቀለው አጥቶ ቆይቶ ነበር እግዚአብሔር ኃይል ስለሰጠን ግን አቸነፍነው ገደልነውም የሱ ተከታዮች ዓመፀኞችንም እንዲደበቁ አደረግን ሀገረ እስያንም ነፃ አወጣን በሱ ጭካኔ ብዙዎች ለመከራ ተጋልጠው ነበር። ሕርቃኖስ የአይሁድ ንጉሥ ሆይ አንተና በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ያሉ ካህናት ስጦታችሁን ከፍ አድርጉ አውግስጦስ ቄሣር ብዙ ዕድሜ እንዲያገኝም እግዚአብሔርን ለምኑ በያገሩ የሚገኙ አይሁዶች ያለአንዳች ቅድመ ሁኔታ በነፃ እንዲለቀቁ እኔና አንጥቦቦስ የሠራዊት አለቃ ትእዛዝ አስተላልፈናል።”



www.ethiopianorthodox.org

አውግስጣስ በገባው ቃል መሠረት የአይሁድን ግዛት የያዙም ሆነ አይሁድን ማርከው የወሰዱ ሁሉ ምንም ሳያስቀሩ እንዲመልሱ አወጀ ከሱ በፊት የነበረው ቄሳር ለአይሁድ የገባውንም ቃል ኪዳን በበለጠ እንዲያከብሩ አዘዘ በአርማንያ የሚገኘው የሠራዊቱ አለቃ አንጥቦቦስም ይህንን እንዲያስፈፅም አዘዘ "ቅልብሥጥራ" የምትባል የግብፅ ንግሥት ወደ አንጥቦቦስ የሠራዊት አለቃ ሄዳችና አገባችው ቅልብስጥራ በመሠርይነት ድርጊቷም ከሷ ትእዛዝ እንዳይወጣ አደረገችው። በዚህ ጊዜ አለቆች ወደ ሊቀ ሠራዊት አንጥቦቦስ ሄዱ የሄሮድስንም ዓመፀኛነት ነገሩት አንጥቦቦስ ሄሮድስንና ወንድሙን ይወዳቸው ነበር። ስለዚህ እነዚህን ሄሮድስን የከሰሱ የአይሁድ ሽማግሌዎች ገደላቸው ሄሮድስንና ወንድሙን ደግሞ እጅግ ከፍ ከፍ አደረጋቸው በታላቅ ክብርም ወደ ቦታቸው ሸኛቸው ወደ ቤተ መቅደስም ሸኛቸው አንጥቦቦስ ባለበት ፋርሶችን ለማስገበር ሄደ።

## ምዕራፍ ፴፩

## የአርስቶቦሎስ ልጅ አንጢኮስ አነሳስ

አውግስጦስና አንጥቦቦስ ፋርስን አስገብረው ከተመለሱ በኋላ አንጢኮስ ወደ ፋርስ ንጉሥ ሄደና ባንድ ሺህ በድሪ የሚመዘን ወርቅና ሰባት መቶ ጋሻ ከአይሁድ ወስጄ እሰጥሃለሁና ካባቴ ወንድም ሕርቃኖስ ቀምተህ መንግሥትነትን ስጠኝ አለው። ሄሮድስንና ፊሲሉንም እንዲገድላቸው ጠየቀው። ፊሲሉ የሄሮድስ ወንድም እንደሆነ ይታወቃል። የፋርስ ንጉሥም በአንጢኮስ ጥያቄ ተስማማ ወድያውም የፋርሱ ንጉሥ ብዙ ሠራዊትን አስከትሎ ተነሳና የሮም ግዛት የሆነችውን አርማንያን ወረረ። ከዚያ የሚገኙትንም ሮማውያን ገደለ። የሱ ተወካዮችን አርማንያን ተቆጣጠሩና ከዚያ ተነስቶ ባለበት ወደቤተ መቅደስ ለመዝመት ተንቀሳቀሰ።



የገዞው ዓላማ በአንጢኮስ አሳሳቢነት የአይሁድ ንጉሥ የሆነውን ሕርቃኖስን ለመግደል ነው። ሕርቃኖስን ብቻ ሳይሆን ወንድማማቹን ሄሮድስንና ፊሲሉንም ለመግደል ነው የገዞው ዓላማ። ከዚያ በኋላ መንግሥቱን አጠቃልሎ ለአንጢኮስ ለማስረከብ የፋርሱ ንጉሥን ሰላማዊ በመምሰል ያለጦርነት ወደ ሕርቃኖስ ላከ /ወደ ቤተ መቅደስ/ ገዙአቸውም ሰላማውያን በመምሰል ነበር አንጢኮስ ወደ ቤተ መቅደስ ገብቼ ለመፀለይ እፈልጋለሁ ሲል አይሁዶች ጠረጠሩትና እንዳይገባ ከለከሉት እሱ ግን ለተንኮል እንዳልመጣ ማለላቸው። ሄሮድስና ወንድሙም በጥርጣሬ ከሩቅ ሁኔታውን ይከታተሉ ነበር አንጢኮስና የፋርሱ ንጉሥ ተከታይ ወደ ቤተ መቅደስ ገቡና ሰውን መግደል ጀመሩ ሄሮድስና ወንድሙ ፈጥነው በገሊላ መሸጉ ሕርቃኖስም በሌላ በኩል መከላከሉን ጀምረ።

የፋርሱ ነጉሥ ተወካይ ነገሩ እንዳልተሳካለት ተረድቶ በስሕተት ስዎችን እንደገደለ በማስመሰል አቅጣጫውን ለውጦ ለአይሁድ መልካም ሥራን ለመስራት ጀመረ ሄሮድስን የፋሲልንና ሕርቃኖስን በሰላማዊ መንገድ ተገናኝቶ በፈፀመው ስሕተት ይቅርታ እንዲጠይቃቸው ጠራቸው ሄሮደስ በጥርጣሬ ስለተመለከተው ጥሪውን አልተቀበለም ወደሱም አልመጣም ሕርቃኖስና ፊሲሉ ግን ምንም እንኳ ከጥርጣሬ ነፃ ባይሆኑም ጥሪውን አክብረው ወደሱ መጡ።

ይህ የፋርስ ንጉሥ ተወካይ የሕርቃኖስንና የሄሮድስ ወንድም ፋሲለስን አከበራቸው የፍቅር መንፈስም በከፍተኛ ሁኔታ አሳየ ይዞአቸውም ወደ አርማንያ ተመለሰ እንደደረሰም እንዲታሰሩ አደረገ በብስጭት ፊሲል ሙቶ አደረ ሕርቃኖስም አሰረው አንጦቦስን ደግሞ ሊቀካህናትነትን እንዳይሾም ጆሮውን ቆረጠው።



www.ethiopianorthodox.org

ሕርቃኖስን በእስር ይዞ ወደሀገሩ ተመለሰ ሀገሩ እንደደረሰ ሕርቃኖስን ከእስር እንዲፈታ አደረገ መልካም አያያዝንም አደረገለት እንጢጎስን ደግሞ በአይሁድ ላይ ይነግሥ ዘንድ የራሱን ባለሥልጣን ረዳት ሰጥቶ ላከው ገሊላንና ቤተመቅደስን አንድ ላይ አጣምሮ ሄሮድስ መግዛት ጀምሮ ነበር የአንጢኮስ ከፋርሱ ረዳት ጋር መመለስ ሲሰማ ግን በጣምራ ሚስቱንና ልጆቹንም ወደደብረ ሹራህ ላከ ወንድሙ የአንደፌር ልጅ ዮሴፍ በደብረ ሹራህ ይኖር ነበርና ቅልአ በምትባል ክፍልም እያኖረ አስፈላጊውን ሁሉ እንዲያሟላላቸው ወንድሙ ዮሴፍን አዘዘው ከዚያ በኋላ ወደሮም ለመጓዝ ወደግብፅ ሄደ የግብፅዋ ንግሥትም እጅግ አከበረችው ብዙ ገንዘብንም ሰጠችው እቺ ቀደም ሲል የጠቀስናት ቅልብሥራ ናት መርከቦችንና ተከታዮች ሰዎችንም መደበችለት ከግብፅም በመርከብ ሮም ደረሰ ወዳጁ አንጥቦቦስንም አገኘው በክብርም ተቀብሎ ወደአውግሥጦስ ቄሣር አስገባው የፋርስ ንጉሥ ከአንጢኮስ ጋር በመሆን የፈፀመውንም ሁሉ ሄሮድስ ለአውግሥጦስ ዘርዝሮ ገለፀ።

አውግሥጦስ በዚህ ጊዜ እጅግ አከበረው ራስ ወርቅም ተደርጎለት በሮም ሕዝብ ሁሉ ንጉሥ መሆኑ እንዲታወቅ አዋጅ አስነገረ አንጥቦቦስና አውግሥጦስም በመካከላቸው በማስቀመጥ ከአደባባይ አውጥተው ለሕዝቡ አስተዋወቁት ከአደባባይ መልስ በታላቅ ክብር ወደ ጦር መሪው አንጥቦቦስ ቤት ወሰዱት አንጦቦቦስም ታላቅ ግብዣ አደረገላቸው የሮም መንግሥት ባለሥልጣኖችም የግብዣው ተካፋዮች ሆኑ፡

አውግሥጦስ የሄሮድስን ባለሟልነት በታላቅ ቃልኪዳን እንዲፀና ወሰነ ስለሄሮድስ የገባውም ቃልኪዳን ክብረት ሰሌዳ እንዲፃፍ አደረገ አንጦቦቦስ ወደ ፋርስ ለመዝመት ተነሳ ሄሮድስም ከሱ ጋር ጉዞ ጀመረ። አንጾኪያ ሲደረስ አንጥቦቦስ ብዙ ሰራዊት አስከተለና ወደፋርስ ጉዞውን ቀጠለ ሄሮድስም በበኩሉ



የቀረውን ሠራዊት አስከትሎ አንጢኮስ ወደሚገኝበት ሀገረሹም ሄደ /ሊወጋው/ አንጢኮስ የሄሮድስ መምጣት ሲሰማ ወደደብረሹራህ ሄደ። ወደደብረሹራህ የሄደበት ምክንያት የሄሮድስን ቤተሰቦችንና ወንድሙን ዮሴፍን ለመያዝ ነው። አንጢኮስ እንዳሰበው አደረገ የሄሮድስን ሚስት ልጆችንና ወንድሙን ያዛቸው በውሃጥምም ለመከራ ዳረጋቸው ዮሴፍ፡ ሕይወቱን ለማትረፍ ይሸሽ ጀመር የሄሮድስን ቤተሰቦች ከሞት ለመታደግ ወታደሮች አንጢኮስን ለመጋፈጥ ሞከሩ ይህ በዚህ እያለ ሌሊቱን ሐይለኛ ዝናብ ዘነበ ወንዙ ሜዳውና ኩሬው ሁሉ በውሃ ተጥለቀለቀ አንጢጎስም የሄሮድስ ቤተሰቦች ካሉበት ራቀ ።

ሄሮድስም የቤተሰቦቹን በአንጢኮስ ቁጥጥር ሥር መዋል ሰምቶ ወዳሉበት ሀገረሹራህ ሄደ እንጢኮስንም አገኘውና ጦርነት ገጠመው የሄሮድም /የሄሮድስ ወንድም / በሌላ በኩል እንዳያመልጥ መንገድ ዘጋበት ከግራቀኝም በመሆን ብዙ ሠራዊት ገደሉበት በዚህ ጊዜ አንጢጎስ ሸሽቶ ወደ ቤተመቅደስ ሄደና ተማሕፀኖውን ቀጠለ ሄሮድም ተከታተለውና ቤተመቅደስን ከበባት አንጢኮስ ለሮም ወታደሮች ብዙ ገንዘብን ሰጠ ከሄሮድስ እጅ እንዲያድኑትም ተማፀናቸው እነሱም ሄሮድስን ለመውጋት ሞከሩ ነገር ግን አይሁዶች ከሄሮድስ ጋር ስለተሰለፉ በገንዘብ የተገዙ የሮም ወታደሮች ምንም ሊረዱት አልቻሉም

## ምዕራፍ ፴፪

## አንጦቦቦስ የፋርሱን ንጉሥ ገደለው

የአውግሥጦስ ቄሣር የጦርመሪ የሆነው አንጦቦቦስ ወደፋርስ ሄደና የፋርሱን ንጉሥ ገደለው ባለበትም የፋርስ ንጉሥ ሆነ ጥቂትም ፋርስን እየተቆጣጠረ ቆይቶ የፋርስ ሕዝብ ለሮም መንግሥት እንዲገብር አድርጎ

www.ethiopianorthodox.org

ወደሮም ሲመለስ የኤፍራጥስን ወንዝ ተሻገረ ሄሮድስ የአንጠቦቦስን መመለስ ሲሰማ ወንድሙ ዮሴፍ አንጢጎስን በዚያ ከሚገኙ የሮም ወታደሮች ጋር በመተባበር እንዲወጋው መመርያ ሰጥቶ አንጠቦቦስን ለመገናኘት ወደሮም ሄደ፡፡

ሄሮድስ አንጠቦቦስን እንኳን ደህና ተመለስክ ካለው በኋላ አንጢኮስን ለመውጋት እንዲተባበረው ለመነው አንጠቦቦስም የሄሮድስን ጥያቄ በሰላም ተቀብሎ ባንድ አለቃ የሚመራ ብዙ ሠራዊትን አዘዘለት ወዳገሩ ሲመለስም የአርመን ሰዎች እርዳታና ድጋፍ እንዲያደርጉለት ደብዳቤ ጻፈላቸው ሄሮድስ የግብፅ ንግሥት የአንጦቦቦስ ሚስት ስለሆነች ባለቤት በመርከብ ወደ ግብፅ ሄደ፡፡ ባለቤትም አንጦቦቦስ እንዲረዳው ከሰጠው የጦር መሪ ጋርና ከሮማውያን ወታደሮች ጋር ወደ ቤተ መቅደስ ሄደ፡፡

ሄሮድስ ደማስቆ ሲደርስ አንጢኮስ በዚያ የሚኖሩትን የሮም ወታደሮች አስተባብሮ ወንድሙ ዮሴፍን ተዋግቶ እንዳቸነፈውና ብዙ የሄሮድስ ወታደሮችንም እንደገደለ ወንድሙ ዮሴፍንም እንደገደለው ሰማ አንጢኮስ የዮሴፍን አንገት ቆርጦ ለብዙ ገንዘብ ሸጠው የገዛው ሰው ግን ቀበረው፡፡

ሄሮድስን እንዲረዳ ከአንጥቦቦስ የታዘዘው ሲሳር ይህን ድርጊት ሲሰማ በጣም ተናደደ መቶ ሃያ ሺህ ወታደሮችንም አስከትሎ አንጢኮስን ለመውጋት ተዘጋጀ አንጢኮስ ፋፋስ የሚባል የጦር መሪ ነበረው ሁለቱ አንጠቦቦስን ጦርነት ሲገጥሙት በምድረ ገሊላ ጠበቁት፡፡ በመካከላቸው ጦርነት ተከፈተና አንጢኮስ ተቸንፎ ሸሸ የሱ የጦር መሪ ግን በርትቶ ተዋጋ ግን በጦርነቱ ፋፋስ ተገደለ፡፡ ብዙ ሠራዊቱም አለቀ፡፡

ፍሩዳ የፋፋስን አንገት ቆረጠ ወደ ሄሮድስም ወሰደው ፍሩዳ የሄሮድስ ወንድም ነው፡፡ ሄሮድስ ግን እንዲቀብሩት አዘዘ ከአንጠቦቦስ የተላከው ሲሳርና ሄሮድስ በመሆን አብረው ወደ ቤተ መቅደስ ሄዱ አንጢኮስም በዚያ መሽጎ



ጠበቃቸውና ውጊያ ሆነ ጦርነቱ ባጭሩ የሚያባራ አልሆነም የቤተ መቅደስ ጠባቂዎች የማይቻሉ ሆኑ፡፡

በሌሊት የቤተ መቅደስ ጠባቂዎች የሄሮድስ ወታደሮች በመሰላል ወጥተው ከተኙበት ገደሉዋቸው ሄሮድስና ሲሳርም ወደ ቤተ መቅደስ ቅፅር በቀላሉ ለመግባት ቻሉ የሮም ወታደሮችም አብረው ወደ ቦታው ገቡ፡፡ ሄሮድስ ለሲሳር ብዙ ገንዘብን ሰጠው የሮም ወታደሮች ከአይሁድ የዘረፉትን ንብረት ግን እንዲመልሱ ያደርግ ዘንድ ሲሳርን ጠየቀው እነሱም መለሱ ሲሣር ለቤተ እግዚአብሔር ብዙ ስጦታዎችን አበረከተ እግዚአብሔር እንዳይቀየመው ፈርቷልና፡፡

ተሙዝ በተባለው ወር ወደ ሀገረ ቁድሽ ገባ በዚሁ ወር በአሥራ ሰባት ቀን ነው የገባው ዕለቱ የፆም ዕለት ነበር፡፡ አንጢጎስን ከተደበቀበት ለመያዝ አዘዘ አግኝቶም አሠረው ወደ ምድረ ግብፅም ወሰደው፡፡ የአውግሥጦስ ቄሣር ዋና የጦር መሪ የሆነው አንጠቦቦስ የግብፅን ንግሥት አግብቶ በግብፅ ይገኝ ነበርና ሄሮድስም በበኩሉ ብዙ ገፀበረከት ይዞ ወደ አንጥቦቦስ ሄዶ አስረከበና አንጢጎስን ተይዞ አያለ እንዲገድልለት ለመነው አንጦቦቦስም በሄሮድስ ጥያቄ አንጢጎስን ገደለው፡፡

ሄሮድስ ከነገሠ በዚህ ጊዜ ሦስት ዓመት ሁኖት ነበር የአንጥቦቦስም የጦር መሪ መሆን 3ኛው ዓመት ነበር አንጢጎስን ካስገደለ ጀምሮ ሄሮድስ ተቀናቃኝ ሳይኖረው በሰላም ይገዛ ጀመረ አይሁዶችን በኃይል ገዛቸው የሱን የበላይነት አሜን ብሎ ለተቀበለው አይሁዳዊ ግን ደህና ነበር፡፡ እሱን የሚቃወም አይሁዳዊ ሁሉ እያደነ ገደለው ንብረቱንም ዘረፈ ከአይሁድ ጋር የሚመጣጠኑ አህዛብ ሁሉም ከበታቹ አስገባ፡፡ የአይሁድ የበታቾች እንዲሆኑም አደረገ ብዙ ግብር ስለሚያስገብርም ሀብት በዛለት መንግሥቱም ተቃናለት አህዛብ ብዙ ግብር ያመጡለት ነበርና፡፡



www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፴፫

## የሕርቃኖስ ከፋርስ መመለስና አገዳደሉ

አስቀድመን የሕርቃኖስ ወደፋርስ መወሰድ መግለፃችን ይታወሳል የፋርስ ንጉሥ ዕራቅ ወደተባለው ሀገር ወሰደው ከወሰደው በኋላ ግን በኢራቅ ከሚኖሩ ወገኖቹ አይሁድ ጋር እንዲኖር ፈቀደለት ፍላጎቱንም አሟላለት በኢራቅ የሚኖሩ አይሁድ ሕርቃኖስን በመልካም ሁኔታ ይዘውት እያለ ሄሮድስ ለፋርሱ ንጉሥ "ሕርቃኖስ እኔ አንዳባት ሆኖ ያሳደገኝ ባለውለታዬ ነው እሱን ይቀናቀን የነበረውን የወንድሙን ልጅ አንጤዕስን አስገድየዋለሁ ስለዚህ ሕርቃኖን በእንክብካቤ እንዳኖረው ወደኔ ላክልኝ በማለት ለፋርሱ ንጉሥ ፃፈለት ፁሑፍንም በማስረዘም ሕርቃኖስን በፍጥነት ካላክልኝ አንተን አስገድዶ እንዲያስጠኝ የሮምን ንጉሥ እማፀናለሁ" አለ።

ሄሮድስ ከደብዳቤው ጋር ለፋርሱ ንጉሥ ብዙ ገፀበረከትን ልኪል የፋርሱ ንጉሥ ሕርቃኖስን "አንተን እንድልክለት ጠይቋል እኔ ወደሀገርህ ለመሄድ ከፈቀድክ አልከለክልህም ነገር ግን ባትሄድ ይሻልሃል ምክንያቱም በመልካም ይዞታ እንደሚያኖርህ ቢጻፍም በእጁ ገብብትህለት እንዲገድልህ ስለፈለገ ነው ያንተ በዚህ መኖር ዕረፍት ስለነሳው ብቻ ምክንያት አቀረበ ሄሮድስ ክፉ መሠርይ ሰው ነው በጥርጣሬ ልትመለከተው ይገባሃል እንጂ አትመነው" በማለት አነጋገረው።

በኢራቅ የሚኖሩ አይሁድ ረበናትም ተሰበሰቡና ሕርቃኖስን ሄሮድስ ካህን አደርገዋለሁ በማለት አንተን ለመውሰድ ተስገብግቧል ካህን እንዳትሆን ከአንጢኮስ ጋር የፈፀምከው ስሕተት ያግድሃል በጣም ዕድሜህ እየገፋ ሄዷል አንተ ካሁን ቀደም ውለታ ስለዋልኩለት ውለታዬን ይመልሳል የማለት ግምት ይኖርህ ይሆናል ነገር ግን ስዎች ለተደረገላቸው ውለታ ሥልጣናቸው



እንዲረሱት ያስገድድቸዋል በአመባገነንነት የሚኖሩበትን ዘዴ ብቻ ያነፈንፉሉ ሥልጣን ሰውን ይለውጠዋል የገባውንም ቃል ኪዳን ጨርሶ እንዲስርዝ የገፋፋዋል አንተ ከኛ ጋር በክብር እየኖርክ ነው ወደቤተ መቅደስ ብትሄድ የሚጠብቅህን አታውቅም ሄሮድስ እየገዛህ ከምትሞት ከኛ ዘንድ ተቀመጥ " በማለት መከሩት

ሕርቃኖስ የፋርሱን ንጉሥ ማስጠንቀቂያና የረበናትን ማሳሰቢያ አልተቀበለም ከቤተእግዚአብሔር ርቂ መኖሩን አልወደድኩትም የማለት መልስ ሰጣቸውውና ከኢራቅ /ዕራቅ/ ተነስቶ ወደ ቤተመቅደስ ሄደ ወደ ቤተመቅደስ ሲደርስም ሄሮድስ ተቀበለው ክብሩንም ከፍ አደረገለት በየአደባባዩም ክብሩን ገለጠለት በማወደስ በቀላሉ ሄሮድስ የሕርቃኖስን ስም የሚያነሳ ሆነ በልቦናው ግን ሊገድለው ያደባ ነበር።

የሕርቃኖስ ልጅ እስክንድራና ልጇ የሄሮድስ ሚስት ማርያም ምሥጢሩን ያውቁ ስለነበር ወደሕርቃኖስ ልከው የሄሮድስን ደባ ከገለፁለት በኋላ ወደሌላ እንዲሄድ ነገሩት ለጊዜውም ከቤተ መቅደስ ባልራቀ ቦታ እንዲጠበቅ የምስጢር ሰዎችን ላኩለት ሄሮድስ ወንድሙን ስለገደለበት የሚጠላውን አይሁዳዊ ሕርቃኖስ ተወዳጅ ይህንንም ሰው ወደምዕራብ ንጉሥ ሕርቃኖስ ለመሄድ ይችል ዘንድ እንዲያመቻችለትም ለመነው።

ይህ አይሁዳዊ ጋር ግንባር መፍጠሩን ከሰማ እንዳይገድለው ፈራ በሌላ በኩል ደግሞ በሕርቃኖስ ሰበብ ከሀገር ለመውጣት ፈለገ ሰውየው ሌላ ዘዴ ፈጠረና ባንተና በምዕራቡ ንጉሥ የወዳጅነት ቃልኪዳን እንዲኖር ለንጉሱ መልእክት እንድሰጥ ላከኝ አለው ሄሮድስም ደስ አለው የምሰጥህን የመልእክት ደብዳቤ ለምዕራቡ ንጉሥ ውሰድና መልሱንም ይዘህልኝ ተመለስ አለው።

ይህ ሰው የሄሮድስን የመልእክት ደብዳቤና የሕርቃያኖስ ደብዳቤ ይዞ ወደንጉሡ ምዕራብ ሄደ ከሕርቃኖስ በኩል የተፃፈው ደብዳቤ ሄሮድስ ሊገድለኝ



www.ethiopianorthodox.org

ፊፅሞ የተከለከለ ነው። ህጋችንን እንድንደፍር አይገባንም እንዲህ ሹመት የሚወጣ የሚወርድ አይደለም አለው ለአንጠቦቦስም ይህንኑ ቃል ፃፈ።

አንጠቦቦስ ወደቤተ መቅደስ መጥቶ በነበረ ጊዜ ማርያምንና ወንድማ አርስቶቦሎስን አይቶአቸው ስለነበር መልእክተኛውና አርስተቦሎስ በሁለቱ ደምግባት እጅግ ይደነቁ ነበር ይህ መልእክተኛ ለእስክንድራ እንዲህ አላት የሁለቱ ልጆችሽን ሥእል ስጭኝ እኔም ለንጉሡ ልስጠው ከዚያ ወዲያ አንጦቦቦስ የፈለግሽውን ሁሉ ያደርግልሻል።

እስክንድራ መልእክተኛው የነገራትን አደረገች ልጇ አስትሮቦሎስ እንዲሾምላት በጣም ጓጉታለችና የአስትሮቦለስን ሥእል ሲመለከት አንጦበቦስ እጅግ ተደነቀ አርስተቦሎስን ወደሱ እንዲልክለትም አንጦቦብስ ወደ ሄሮድስ ላከ በፍጥነት ካልላከው ግን እንደሚጣሉ አስጠነቀቀው። ይህ መልእክት ሲደርሰው ሄሮድስ ደነገጠና ሊቀ ካህናትነተን የሾመው ሰው አውርዶ አርስተቦሎስን ሊቀ ካህናት አደረገው።

ይህን አከናውኖ ሄሮድስ ወደ አንጠቦቦስ እንዲህ ሲል ጻፈ. "እኔ ካሁን ቀደም አስትርቦሎስን ሊቀ ካህናትነት ያልሾምኩት የካህናትን ህግ እንዳላበላሽ በማሰብ ነው አሁን ግን ትእዛዝህን ለማክበር ሹሜዋለሁ ወዳንተ እንዳልከው ግን ሊቀ ካህናትነት የተሾመ ሰው ከቤተ መቅደስ ርቆ የትም እንዲሄድ አይፈቀድለትም ንጉሥ የትም እንዲንቀሳቀስ ይፈቀድለታል ሊቀ ካህናት ግን ከቤተ መቅደስ ወጥቶ የትም እንዲሄድ አይፈቀድለትም የቤተ እግዚአብሔር ተልእኮ ማከናወን ብቻ ነው ተግባሩ ወዳንተ እንዲመጣ ካስገደድኩት አይሁድ በሙሉ ይታወካሉ።"

አንጠቦቦስ የሄሮድስን ደብዳቤ ደርሶት ካነበበ በኋላ ዝም አለ ስለአርስተቦሎስ ወደሱ መምጣት በዚሁ ዘጋ። አርስተቦሎስ በዚህ ጊዜ የአሥራ ሰባት ዓመት ነው ። በአይሁድ ህግ እውነትም ክህነት የዕድሜልክ ሥልጣን



ነበር ይህን ህግ ለመጀመርያ ጊዜ የሻረ አንትያኮስ ነው አፌምፎስ ደገመ ካህንን መሻር ደግሞ እንደገና አፌምፎስ አንጢኮስ በነውረኝነት አካለ ጉደሎ ተብሎ ሊቀ ካዓናትነትን ከመሾም እንዲቀር ጆሮውን /የአንጢኮስን ጆሮ ቆረጠ/ ሦስተኛው /በካህን መሻር/ ደግሞ ሄሮድስ ነው የታወቀው ይኸውም አንጠቦቦስን በመፍራት መጀመሪያ የሾመውን ሽሮ አንትሮቦሎስን ሹሚልና።

ሄሮድስ የአማቱን እስክንድራና የሚስቱን ማርያም ቂም በዚሁ ይቀራል የማለት ግምት አደረው ምንጊዜም ቢሆን እስክንድራን ሰዎች እንዳታነሳሳበት ሄሮድስ ይፈራት ነበር። እሷም ሳታውቅ የምትለውን ሁሉ በየዕለቱ የሚያቀብለውን ጆሮ ጠቢ ከላይዋ ላይ አቁሞ ነበር።

እስክንድራ ወደ ግብፅዋ ንግሥት ቅልብስራ ልጇን አርስተቦሎስን ድጋፍ እንድታደርግለት ደብዳቤ ፃፈችላት ቅልብሥጥራ በበኩልዋ ከሀገረ ቁድሽ እንደምንም ወጥታ ወደ ግብፅ እንድትመጣ የምክር ደብዳቤ ጻፈችላት የምትመጣባቸውንም ታንኳዎች ከብዙ ዕጻቢዎች ጋር ላከችላት እስክንድራን ለመውሰድ የመጡ ታንኳዎች ሐይፋ በተባለው ወደብ ተሰለፉ እስክንድራም እንድትመጣ ጠሩዋት። እሷም ለመውጣት አልቻለችም። እሷና አርስተቦሎስ በሬሳ ሳጥን ውስጥ ገብተው መውጣት ጀመሩ ነገር ግን ያ ጆሮ ጠቢ ሆኔታውን ለሄሮድስ ነገረው ሳጥኑ ሲከፈት ሁለቱም እያንዳንዳቸው በሁለት የሬሣ ሣጥን ተገኙ ሄሮድስ እጅግ ተቆጣ ስለፈፀሙትም ስህተት ወቀሳቸው ነገርግን ይቅርታ አደረገላቸውና ወደቤታቸው መለሳቸው ከዚያ አያይዞ በዐለመፀለት ደረሰ በዚሁም ምክንያት ሰዎች ወደቤተመቅደስ ተሰበሰቡ በየብቻቸውም ቆሙ የአስራ ሰባቱ ዓመት ወጣት አርስቶበሎስ የሊቀ ካህናቱን ልብስ ለብሶ ወደ ቅድስተ ቅዱሳት ገባ ሕዝበ አይሁድ ከመልከመልካም የተፈጥሮ ውበቱ ጋር የሊቀካህናቱን ልብስ ለብሶ ሲያዩት ደስ አላቸው እጅግም ወደዱት።



www.ethiopianorthodox.org

ይህ ነገር ግን ለሄሮድስ የሚዋጥለት አልሆነም አርስተቦሎስ ከሊቀካህናትነት አልፎ ወደንጉሠነት እንዳይሸጋገርበት ከባድ ቅንዓት አሳደረበት በዐለመፀለት ሲያልቅ የእሥራኤል ነገሥታት በኢያሪኮ ወደሚገኘው የአትክልት ቦታ የመጡጣት ባህል ነበራቸው በዚሁም ለጥቂት ቀናት ይሰነብቱ ነበር።

ይህንን ልማድ መነሻ አድርጎ ሄሮድስ ወደተጠቀሰው የአትክልት ቦታ ወጣ የአትክልት ቦታው በጣም ደስ ይላል ሄሮድስ በዚህ በነበረበት ጊዜ አርስቶቦሎስም በሊቀ ካህናትነቱ አብሮት ከዚሁ ነበር የንጉሥ ቤተሰቦችና ወዳጆቹም ከዚሁ ነበሩ ሄሮድስ አርስቶቦሎስን ከጉድኑ አስቀመጠውና የቀሩትን ተከታዮቹ እንደየደረጃቸው አስቀመጣቸው የምሳም ግብዣ በዚሁ ተደረገና በልተው ጠጥተው ሁሉም ተደሰቱ።

በዚሁ ፀሐይ በርትቶ ቀትር ሲሆን በየአትክልቱ ማሕል ሄሮድስ መዘዋወር ጀመረ። ከየአቅጣጫው የሚጉርፈውም የውሃ ምንጭ ይመለከት ነበር። አርስተቦሎስም አብሮት ነበር። የንጉሡ ተከታዮች ባሮች በውሃው ለመታጠብ ይሽቀዳደሙ ነበር። በዚህ ጊዜ ሄሮድስ በምስጢር ለባሮቹ “ከእናንተ ጋር እንዲዋኝ አርስተቦሎስን ጥሩት አብሮ በመዋኘት እያለም እንዳይነቃባችሁ እየዘፈናችሁና እየቀለዳችሁ ወደታች በማስጠም ግደሉት መሞቱን ሳታረጋግጡ አትተውት” አላቸው። እነሱም እንዳላቸው አደረጉና የገዛራሱ ዋና ሳይችል ቀርቶ እንደሞተ አስመስለው ሬሣውን አወጡ።

ሕዝበ አይሁድ በሱ መሞት እጅግ አለቀሱ እጅግም አዘኑ ሄሮድስም አርስተቦሎስን በማስገደሉ እየተፀፀተ አለቀሰ። ከአሥራ ሰባት ዓመት ምንም ሳይጨምር አርስተቦሎስ ሞተ ሄሮድስ በታላቅ ክብር አስቀበረው በሊቀ ካህናትነት ላንድ ዓመት ሙሉ አልቆየም እስክንድራ ሄሮድስን በዚህ እንደገና ጠላችው የሷ ልጅ የሄሮድስ ሚስት ማርያምም ጠላችው።



የሄሮድስ እናት ኤዶማዊት ናት ሚስቱ ማርያም በዚሁ ትውልዷ ታሽሟጥጣት ነበር። ይህንንም እናቱ ለሄሮድስ ትነግረው ነበር ሄሮድስ ግን ከእናቱ የሚነገረውን የማርያም አሽሟጣጭነት በዝምታ ያልፈው ነበር። ሄሮድስ ግን ማርያምን እጅግ ይወዳት ነበርና ማርያም ግን ነጋም ጠባምየሄሮድስን እናትና እህቱን ከመሣለቅ አልፋ ኤዶማውያን በመሆናቸው ትሰድባቸው ነበር። እያደረ ጠቡ ከረረ የሄሮድስ እህት ተንኰለኛ ነበረች ወደፊት እንደምንገልፀውም ብዙ የተንኰል ተግባር ፈፀመች።

## ምዕራፍ ፴፫

## የአንጠቦስ ከአውግስጦስ ቄሣር የማፈንገጥ ዜና

ቅልስጥራ ተንኰለኛ ከመሆንዋም ሌላ በሽልማት የመዋቡን ነገር ታውቅበት ነበር። ከዚያም ላይ የምትቀባቸው የሽቶ ዓይነቶች ወደር የማይገኝላቸው ነበሩ ታላቅ በዕድሜ የገፉች ሴት ሁና እያለም ገና ለግላጋ ወጣት እየመሰለች ትታይ ነበር የሷን ያህል በተሟላ ሁኔታ ተስተካክላ የምትታይ ሴት የትም አልነበረችም። አንጦቦስን ካገባቹም ጀምሮ ህሊናውን ለወጠችው ወደፈለገችውም አቅጣጫ ታሽከረክረው ጀመር። በሷም ምክር እየተመራ በሮም መንግሥት ሥር የነበሩትን የብዙ አገሮች ነገሥታት እየገደለ ንብረታቸውን ይዘርፍ ጀመር።

በግፍ ነገሥታቱን ይገድልና ንብረታቸውን ይዘርፋል ሚስቶቻቸውንና ልጆቻቸውን በባርነት ያሰቃያል በዚህም አንጠቦስን ብዙዎች ጠሉት ይህ ነገር እስከ አውግስጦስ ቄሣር ተሰማ አውግስጦስም ድርጊቱን አወገዘ እጅግም ጠላው። ቅልብሥጥራ አንጠቦስን የአይሁድን ንጉሥ ሄሮድስን ይገድለው ዘንድ መከረችው። እሱ ግን የሄሮድስ በአውግስጦስ ቄሣር ዘንድ ባለሚል መሆንን ስለሚያቅ አልገደለውም አውግስጦስ ቄሣርን እንዲክድም መከረችው።



www.ethiopianorthodox.org

አንጠቦብስ በቅልብጥራ ሚስቱ ተመርቶ አውግስጦስን ካደው ሊወጋውም ተዘጋጀ ሄሮድስም ከሱ ጋር ተሰልፎ አውግሥጦስ ቄሣርን ለመውጋት እንዲነሳ አዘዘው፡፡ ሄሮድስ የአንጠቦቦስን ትእዛዝ ተቀብሎ አውግሥጦስን ለመውጋት አብሮት ለመዝመት አስቀድሞ ወደ ግብፅ ሄደ፡፡ በዚህ ጊዜ አንጠቦቦስ ለሄሮድስ እኔና አንተ አብረን አገርን ጥለን ከሄድን የምንገዛቸው የአህዛብ ነገሥታት ሊከዱን ይችላሉ የአህዛብ ነገሥታት አንተን እንደሚፈሩህ አውቃለው፡፡ ስለዚህ አንተ የሁለታችንን ግዛት እየጠበቅህ ብትቆይ ይሻላል ዓረቦች ከወዲሁ አንታዘዝም ማለት ጀምረዋል፡፡ አንተ ወደነሱ ሂድና አንብርክካቸው" አለው፡፡

ይህን ለሄሮድስ ነግሮ አንጠቦቦስ አውግሥጦስን ለመውጋት ወደ ሮም ገሰገሰ ሄሮድስ በበኩሉ ዓረቦች ወደሚኖሩበት ሀገረሻም ሄደ ቅልብስጥራ ሄሮድስን አትወደውም ነበር፡፡ የሱንም መንግሥት ደርቦ ለመውሰድ ትፈልግ ስለነበር ሊሞትላት ትፈልግ ነበር፡፡ የሌሎችን አገሮች መንግሥታት በሥርዋ ነበሩና የሄሮድስንም ግዛት እንደዚሁ ለማድረግ ትመኝ ነበር፡፡

የሕርቃኖስ ለጅ እስክንድራ ሄሮድስን በቻለችው ሁሉ እንድታስገድልላት በምሥጢር ዘወትር ትመፀናት ነበር፡፡ አንጠቦቦስ እንዳዘዘው ሄሮድስ ዓረቦችን ለመውጋት ከመሄዱ አስቀድሞ ወደ ሀገረ ቈድሽ ተመለሰ ከዚያም ተልእኮውን ለማከናወን ወደ ዓረቦች ጉዞውን ቀጠለ ቅልብስጥራ "አሳውር" በመባል የሚታወቅ የሷ ባለሟል ከሄሮድስ ጋር አብሮ እንዲዘምት ላከችው ብዙ ሠራዊትንም አስከትሏል፡፡ ሄሮድስን ለመረዳት የሚሄድንም አስመሰለችው፡፡ ነገር ግን ከዓረቦች ጋር ጦርነቱ ሲጋጋም አጋፍጦት ወደ ኋላ በመሸሸትና በተቃራኒው ዓረቦችን በመርዳት ሄሮድስ እንዲገደል ያደርግ ዘንድ መከረችው፡፡ የቅልብሥጥራ መልእክተኛ አሳውር ባደረገውም ተንኰል ብዙ የሄሮድስ ተከታዮች አይሁዶች አለቁ ይሁንና አሳውር አልተሳካለትም



ከአይሁድና ከአሣውር ተከታዮች ወታደሮች በእልፍ የሚቆጠሩ ረገፉ እንጂ ሄሮድስ አልተነካም ወደሀገረ ቆድሽ ተመለሰ እንጂ፡፡

በዚሁ ወር በብዙ ቦታ ብዙ የምድር መናወጥ ተከሰቷል በአግሪጳ ዘመን ካልሆነ ይህን የመሰለ የከፋ የምድር መናወጥ በምድር አልታየም ብዙ ሕዝብ በምድር መናወጡ አልቋል ሄሮድስና አይሁድ ሁሉ በምድር መናወጡ እጅግ ደንግጠው ነበር፡፡ ከዚህም የተነሳ ሄሮድስ ከአይሁድ ጋር በመመካከር ከአህዛብ ሁሉ ሰላምን መመሥረት አለብኝ አለ ከምዕራቡ ንጉሥ በቀርም አሕዛብ ሁሉ ከሄሮድስ ጋር ሰላምን መሠረቱ የምዕራቡ ንጉሥ ግን ከሄሮድስ ጋር ብዙ ደም ስለተቃባ አልታረቅም አለ ለሰላም ተልእኮ ከሄሮድስ የተላኩትንም መልእክተኞች ከማስተናገድ ፈንታ ገደላቸው፡፡

ሄሮድስ የመልእክተኞቹን መገደል ሰማና ሕዝበ አይሁድን ሰብስቦ የምዕራቡ ንጉሥ ለሰላም የተላኩትን መልእክተኞቻችንን ገደለ በመልካም ፈንታ ክፉን ከፈለን አሕዛብ እንዳይዘብቱብን ልንተወው አይገባም ይህን የሰማ ሁሉ ሊሰድበን ይችላል፡፡ እናንተ ስለእግዚአብሔር ሃይማኖት ከአህዛብ ጋር ያልተዋጋችሁበት ጊዜ የለም አሁንም ስለ እግዚአብሔር ብላችሁ የምታካሄዱትን ጦርነት መቀጠል አለባችሁ በዚህም ድርጊታችሁ ከወገኖቻችሁ ተሳልቆን ታስወግዱላችሁ የመሬት መናወጥ እንኳ ተነስቶ ወገኖቻችሁን አልገደለም አህዛብን ገደለ እንጂ የእግዚአብሔርን ጠላቶች ማጥፋት የናንተ ኃላፊነት ነው ዓረቦች ከግብፃዊቱ ንግሥት ተመሣጥረዋል፤ እግዚአብሔር አላጠፋንም አሁንም እግዚአብሔርን አምናችሁ ለጦርነት ተዘጋጁ ሳይማርኩዋችሁ ማርኩ እንደቀደሙት አባቶቻችሁም በርቱ..." አላቸው፡፡

የሄሮድስን ዲስኩር ሲሰሙ የአይሁድ ወንዶች በስሜት ለጦርነት ተነሱ ለሄሮድስም ከእግዚአብሔር አጋዥነት ጋር ወደኋላ እንደማይሉ ቃልገቡለት እሱም አወደሳቸው ለእግዚአብሔርም ብዙ መባ እንዲያስገቡ



www.ethiopianorthodox.org

ካደረገ በኋላ ለጦርነት ወደ ምዕራብ ሄደ ከምዕራብ ሰዎች ብዙዎችን ገደለ ብዙዎች ከጦርነቱ እየሸሹ በየቤታቸው ተደበቁ ሄሮድስም አምስት ቀን ሙሉ ከቦ መውጫ መግቢያ አሳጣቸው በውሃ ጥማትም ሲያልቁ ሆነ።

ወደሄሮድስ በመልእክተኞቻቸው ብዙ ገንዘብን ልከው ውሃን መጠጣት ይችሉ ዘንድ መውጣት መግባት እንዲፈቅድላቸው ለመኑት ሄሮድስ ግን ነገራቸውን አልተቀበለም ሥጦታቸውንም አልተቀበለም ውሃ ጥማቱ ሲጠናባቸው እየተዋጋን እንለቅ ብለው በቁራጥነት ለመዋጋት ከየተደበቁበት ወጡ። ሄሮድስም ከነሱ ገድሎ አቸነፋቸው ባገራቸውም ከባድ ጥፋትን አደረሰ። የቀሩት ሠጥ ለጥ ብለው ለሱ ተገዙ በየዓመቱም እንዲገብሩለት ቃል አስገብቶ ወደ ቤተ መቅደስ ተመለሰ ከዚሁ ጊዜ ጀምረው የምዕራብ አገሮች ለሱ የሚገዙ ሆኑ።

አንጠቦቦስ አውግሥጦስን ለመውጋት ወደሮም ሄደና ጦርነት ገጠሙ አውግሥጦስ ተዘጋጅቶ ስለጠበቀው አቸነፈው ብዙ ሠራዊቱንም አስፈጅቶ በውርደት ከሮም ተመለሰ። ሄሮድስ የአንጠቦቦስ ተቸንፎ መመለስ ባወቀ ጊዜ ሊቀበለው ፈጥኖ ተነሳ። እሱ የሚያዛቸውን ሁሉ እንዲፈፅሙም ተከታዮቹን ነገራቸው እህቱንና እናቱን ፍሩዳ በተባለው ወንድሙ አማካይነት ደብረ ሹራህ ውስጥ ወደምትገኘው ቀንዓ ላካቸው እስክንድራንና ሚስቱን ማርያምን ደግሞ እስክንድሮባ ወደ ተባለው አገር ላካቸው ከነሱ ጋር የእህቱን ባል ዮሴፍንና ሲማን ላካቸው። እነዚህ ሁለቱ ወንዶች እስክንድራንና ማርያምን በመንገድ እንዲገድሉዋቸው አዘዛቸው።

በዚህ ጊዜ አንጥቦቦስን ለመቀበል አስመስሎ ወደ ግብፅ ሄደና ብዙ ገፀ በረከትን ይዞ ባለበት ወደ ሮም ሄደ አውግሥጦስ የሄሮድስና የአንጥቦቦስን ወዳጅነት ያውቀ ስለነበር ሄሮድስ እንደደረሰ አውግሥጦስ የራስወርቁን እንዳይፋት አዘዘ ከአውግሠጦስም ፊት ቁሞ ሄሮድስ በመፍራትና



በመንቀጥቀጥ ሰገደ አንተ አቸናፊና የሁሉ የበላይ ንጉሠ ነገሥት ቄሣር ሆይ በኔ ላይ ልትቆጣ ይገባሃል። እኔ አንጠቦቦስን የወደድኩበት ምክንያት አሁን ከራሴ ያወረድከው የራስ ወርቅን ያቀዳጀኝ እሱ ስለሆነ ነው ሁልጊዜ ስለሚረዳኝም እኔም ረድቸዋለሁ ይህንንም በማድረጌ ጥፋተኛኝና ይቅርታ አድርግልኝ አንተን ለመውጋት ሲመጣ ግን አልተከተልኩትም ባንተ ላይም እጄን አላነሳሁም አንተን የከዱ ዓረቦችን እወጋ ነበር እንጂ በዚሁም ብዙ ደክምኩ የአንጠቦቦስ አንተን መክዳትና ሊወጋህ መነሳትም በጣም አሳዝኖኛል።

አንተን ከምከዳና የአንጠቦቦስን ምክር ከምሰማ መሞትን እመርጣለሁ አንጠቦቦስን ለዚህ ሁሉ ክህደት ያበቃችው ቅልብሥጥራናት የሷን ነገር በመቀበል ለክህደትና ለመደምሰስ የደረሰ ይመስለኛል ንጉሡ ሆይ የራስ ወርቄን ከራሴ ብታስነሳም ስላንተ ያለኝ ክብርና አድናቆት አይቀነስም በሕይወት እንድኖር ከፈቀድክልኝ መላ ሕይወቴ ላንተ ከመገዛት አልርቅም ፍቅርህንም እጠብቃለሁ.." በማለት ብዙ የማስመሰል ንግግርን ቀባጠረ።

አውግሥጦስ ገና ከሩቅ ሲያየው "ግደሉት" ብሎ ነበር ቆይቶ ግን በንግግሩ ተማርኮ ሐሳቡን ለወጠ። እጅግም አከበረው። እንዲህም አለው "አንጦቦቦስ ስለካደ ዋጋውን ከፍለነዋል አንተ ግን ከኛ ፍቅር እንዳልተለየህ በቃልህ ስለገለፅክ ተደስተናል የመሠርይዋ ቅልብስራን ምክር በመስማቱ ነው አንጦቦቦስ የካደው አንተ ግን ለወደፊትም ጠላታችንን እንደምታቸንፍልን እናምናለን።"

ወድያውም የተገፈፈውን የራስወርቁ መልሶ ደፋለትና የላቀ ክብርና ሞገስ ሰጠው ወድያው አውግሥጦስ ቄሣር ወደግብፅ ሄደ ሄሮድስም ተከትሎት ወደዚያ ሄዱ የግብፅዋን ንግሥትንም ገደላት አንጥቦቦስ የሰጣትንም ንብረት ሁሉ ለሄሮድስ አስረከበው ይህንንም አከናውኖ አውግሥጦስ ወደ ሮም ሲመለስ ሄሮድስ ደግሞ ወደ ቤተ መቅደስ ተመለሰ።



www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፵፮

## ሄሮድስ እስክንድሮንና ሚስቱን እንደገደላቸው የሚናገር ዜና

ቀደም ብሎ በተገለፀው መሠረት ሄሮድስ ወደ ሮም ለመሄድ ሲነሳ በሁለት ሰዎች አማካይነት ወደ ሌላ ወስደው እንዲገድሉዋቸው እንደተመሣጠረ ገልፀናል አስትሮቦሎስና ማርያም የእስክንድራ ልጆች ሲሆኑ እንዲሁም ሀርቃኖስ የእስክንድራ አባት ሆኖ ሳለ ሀርቃኖስንና አስትሮቦሎስን ሄሮድስ በማስገደሉ ሁለቱ እናትና ልጅ (እስክንድራና ማርያም) አጥብቀው ስለሚጠሉት ለዚህ መብቃታቸውን ተደጋግሞ ተገልጿል። ዮሴፍንና ሶለሜን እስክንድራንና ማርያምን እንዲገድሉዋቸው ቃል ያስገባቸው ራሱ ሄሮድስ በሮም ተገድሎ የሰሙ እንደሆን ነበር ሲያስገድላቸው እንደነበረም እስክንድራና ማርያም ስለደረሱበት በሱ ላይ ያላቸው ጥላቻ እጅግ ተበራከተ ከሮም ሲመለስ እነሱም ወደ ተወለዱበት ቦታ ተመለሱ።

ከዛን ሰዓት ጀምሮ ሁለቱን እናትና ልጅ አመቺ ጊዜ እየጠበቀ በአፉ ግን እጅግ የተለሳለሰ አኳኋን ያሳያቸው ነበር። በማርያምና በሄሮድስ እህት መካከልም ነገሩ እየከረረ መጣ። ማርያም የሄሮድስን እህት በስድብ አዋከበቻት እሷም ወደ ንጉሡ ቀርባ ከሰሰቻት ያላለችውንም ነገር ከዚያም በላይ ለሄሮድስ "አንተ ወደ ሮም በሄድክ ጊዝ የኔ ባል የሆነው ዮሴፍ ማርያምን ተገናኝቷታል" አለችው ሄሮድስ ግን አባባልዋን አልተቀበለም ምክንያቱም በሌላ ድርቅናዋ እንጂ ማርያም ምንም እንኳ ወደር የማይገኝላት ቆንጆ ብትሆንም የአመንዝራነት ጠባይ እንዳልነበራት ያውቅ ነበርና ከዚህም ሌላ በሰበቡ እዲገደልላት ትፈቅድ እንደነበር ያውቅ ነበርና።



ሄሮድስ ሚስቱን ማርያምን እኔ ባንቺ ፍቅር የተጠመድኩ ነኝ አንቺ ግን ከቶውንም አትወጅኝም ስለኔ የሰማሽው እስኪ ግልፅ አድርገሽ ንገሪኝ እያለ ይወተውታት ጀመር በዚህ ጊዜ ሌላውን ትታ "አንተ እኔን ከወደድክ ለምን ዮሴፍንና ሰሎሜን እንዲገድሉኝ አዘዝካቸው ወዳጁ የሚገድል ሰው አይተህ ታውቃለህን" አለችው በዚህ ጊዜ ሄሮድስ "የእህቴ ባል ባይገናኛት ኑሮ ይህን ምሥጢር ባልገለፀላትም ነበር" ማለትን በሕሊናው ቀረፀ።

ወድያው በቁጣ ብድግ ብሎ ሄደ ከዚሁም ጊዜ ሄሮድስ ማርያምን እስከመጨረሻው ጠላት ምሥጢሩንም ከሷ ደበቀ የሄሮድስ እህትም ማርያምን በዮሴፍ እንደጠረጠራት አውቃ እጅግ ተደሰተች የሄሮድስንም ተላላኪዎች እየጠራች ያለ የሌለ ውሸት ሁሉ እየነገረች በሷ ላይ እንዲያሳብቁ በመንገር ዓላማዋን ለማስፈፀም ሩጫዋን ቀጠለችበት እንዲዋሹላትም ብዙ ገንዘብ ትሰጣቸው ነበር። ለነገር አቀባይዋም መርዝ ሰጥታ ለሄሮድስ አሳየው በምግብ ጨምሬ እንዳበላህ ማርያም ሰጠችኝ" በለው አለችው። እሱም ይህንን አደረገ።

ሄሮድስ በዚህ እጅግ ተናደደና "ከበደለኞች ላንዱ በምግብ ጨምራችሁ አብሉት ሞት ለተፈረደበት ስጡት" አለ ማርያምንም ፈራጆች እስኪሰበሰቡ ድረስ እሥር ቤት አስገባት። በዚህ ጊዜ የሄሮድስ እህት ነገሩ እንዳይጓተት ፈለገች ፈራጆች ነገሩን ሲመረምሩት የማርያም ንፅሕና እንዳይገለጥ የሷንም ጉድ እንዳይታወቅ እጅግ ደነገጠች ወይም ደግሞ ሳይውል ሳያድር ማርያም እንድትገደል ወተወተች ሰዎችንም ይዛ ወደ ሄሮድስ ገባችና "ሄሮድስ አሁኑኑ ማርያምን ካልገደልካት የገዛ ባሮችህም ሆኑ ቤተሰቦችዋ እየወደቁ እየተነሱና አቤት እያሉ እንዳትገድላት ይማልዱሃል እንዳትጨክንባትም ያዳክሙሃል አለችው አብረዋት የመጡት መስተዋድያንም በበኩላቸው ተሳዳቢ ዘማዊትና ሥነ ሥርዓት የሌላት ናት አሁኑኑ ትገደል በማለት አዋከቡት በዚህ ጊዜ እሷን ለናንተ አሳልፌ ሰጥቻለሁና የፈለጋችሁትን ፈፅሙባት አላቸው



www.ethiopianorthodox.org

ወድያው ማርያም ባሰቃቂ ሁኔታ ታሥራ ወደምትገኝበት ቦታ ሄዱ ሲገሉዋትም ከከተማ ውጭ ወሰዱዋት የሄሮድስ እህት በመንገድ ጠብቀው እንዲዘብቱባት ብዙ ሴቶችን ሰብስባ ጠበቀቻት አንቺ ዘማዊት አመንዝራ እያሉም ፊፅሞ ባላደረገችው ሰደቧት እሷ ግን ቀን ጥሎአታል ዝም አለቻቸው ለማንም መልስ አልሰጠችም። ፊቷም አልከፋትም ህሊናዋም አልታወከም ፍፁም ፍርሐት አልታየባትም እንደ ወገኖቿ ነገደ ክስምናይን በጥብዓት ታየች እንጂ የነሱ ነገዶች ለሞት ሲወሰዱ ፍርሃትን አያሳዩምና።

ያለፍርሃትም አንገቷን አመቻችታ ሰጠቻቸውና ቁረጧት እቺ ወደር የማይገኝላትና ልበ ሙሉ ውበትን የተላበሰች ቈንጆ ይህን ዓለም ተሰናበተችው በዘመኑ በመልክ የሚወዳደራት ማንም አልነበረም። ከመልካም ደምግባቷ በተጨማሪ አንደበተ ርቱዕ የማትዋሽና አድርባይነትን የማታውቅ ነበረች ሕሊናዋ ንፁሕ ሃይማኖቷ የቀና ሰውን በስድብ የማታስቀይም ነበረች።

ለትዕቢተኛ ግን ራስን ዝቅ ማድረግ አትወድም ነበር. ከዚህም የተነሳ ሄሮድስንና ቤተሰቡን በሚፈፅሙት አረሜናዊ ተግባር ትዘልፋቸው ትገሥፃቸውና ታብጠለጥላቸው ነበር። ሄሮድስ ማርያምን አስገድሎ አልተደሰተም ተፀፀተ እንጂ በልቡም ድንጋጤ አደረበት ከባድ የሥጋ ደዌም አደረበት ሊሞትም ቀርቦ ነበረ።

ሄሮድስ በዘዴ እሱን ለማስገደል እንደምትፈልግ (እስክንድራ) ያውቅ ስለነበር በትእዛዝ ካለችበት አስገደላት ማርያም ከሄሮድስ ሁለት ልጆችን ወልዳለች ሁለቱንም እስክንድርና አርስተቦሎስ በማለት ነው የሰየመቻቸው እናታቸው ስትገደል እነዚህ ልጆች በሮም ነበሩ አባታቸው ሄሮድስ የሮማውያንን ፅሑፍና ቋንቋ እንዲማሩ ወደዚህ ልኳቸዋል።



## ምዕራፍ ፴፮

## ዜና ሄሮድስ

ሄሮድስ በሐሰት የሱን ሚስት ማርያምን ተገናኝቷል ብሎ ስለጠረጠረና ማርያምን ለማስጠላትና ለማስገደል ስትል እህቱ ባልዋ ዮሴፍ ማርያምን እንዳማገጠ ስለነገረችው ሄሮድስ ዮሴፍን ገድሎ እህቱን ከርስስ ለተባለው ኤዶማዊ አጋባት ወደ ኤዶምም ሹሞ ላከው ኤዶማውያን በዚሁ ዘመን ይገረዙና የኦሪትን ህግ ያከብሩ ነበር። ይህን እንዲያደርጉ ቀዳማዊ ንጉሥ ሕርቃኖስ አስገድዶአቸዋል።

ሄሮድስ የኦሪትን ህግ ከጠበቁና ከተገረዙ ጣዖትን ማምለክ እንዲተው እንዲመክራቸው አዘዘው ከርስስ ግን የሄሮድስን እህት በመጥፎ ጠባይዋ ጠላት ሄሮድስንም ከዳው የሄሮድስ እህት ከከርስስ እንዲያፋታት ሄሮድስን ለመነችው። አይሁድ በሦስት ቡድን በተከፈሉ ጊዜ ክስምናይን የተባሉ ቡድኖች ሦስተኛውን ክፍል መያዛቸው ይታወቃል። የክስምናይን ቡድን ደጋፊዎች በሄሮድስ ከመገደል እያመለጡ ከርስስ በሚገዛው አባቢ ይደርሱና እሱም በሮም ግዛት እንዲደበቁ በማድረግ ለአሥራ ሁለት ዓመት አስቀመጣቸው።

የሄሮድስ እህት የነገደ ክስምናይን በዚያ መኖር ለሄሮድስ ነገረችው ሄሮድስም በግድ አስመጥቶ ገደላቸው። የእህቱ ባል ከርስስንም ገደለው ከዚህም በመነሳት በክስምናይን ፓርቲ የተጠሩ የአይሁድ ወገኖች አንድም ሳያስቀር ፈጃቸው ሄሮድስን የሚቃወም ሁሉ እየታደነ ተገደለ የልቡንም አደረሰ። ሄሮድስ ብዙ ከኦሪት ህግ እንዲሻር አደረገ ቤተ መቅደስን ግን በጥሩ ሁኔታ ገነባ የራሱንና እያቸነፈ የገደላቸውን ነገሥታት ሥእልንም በቤተ መቅደስ ግንብ ላይ አስቀረፀ የቤተ መቅደሱንም ግቢ እጅግ ሰፊ እንዲሆን



www.ethiopianorthodox.org

አደረገ በቤተ መቅደሱም ግቢ ሠረገላን እየጐተቱ ፈረሶች የሚያሽቀዳድሙበትን ሜዳ ሠራ እንደ እስታድየም ያለ ማለት ነው፡፡

በቤተ መቅደስ ዙርያ የአውሬዎች ፓርክ አዘጋጀ የሴት አንበሳንም ከፓርኩ ውስጥ አኖረና አንበሳዋ እየተለቀቀች ሰዎችን እንድትገድል ያደርግ ነበር፡፡ እሷን ያቸነፈ ሰው ብዙ ገንዘብ እሠጠዋለሁ አለ የአይሁድ ደጋግ ሰዎች በዚህ ሁሉ ድርጊቱ ሄሮድስን አይወዱትም ነበር፡፡ ብዙዎች በዘዴ ሄሮድስን ለመግደል ሞክረው እግዚአብሔር ለቅጣት ያመጣው አምባገነን ንጉሥ በመሆኑ አልተሳካላቸውም፡፡ እሱን ለመግደል ሲያሴሩ ባሉት ጆሮ ጠቢዎች አማካይነት ይደርስባቸዋልና ይፈጃቸዋል፡፡

ብዙዎች እንደሚሉት መልኩን ለውጦ ራሱ በሰዎች መካከል እየተገኘ በመሰለል ወዳጁንና ጠላቱ ይለይ ነበር፡፡ ከዚህም የተነሳ በአይሁድ መካከል ሰላም ያለው ሕይወትን ለመኖር አይቻልም ነበር፡፡ እሱ የሚደግፉትው ከአይሁድ ፓርቲዎችም ነበሩ የአልሞትእዝላ የሐሴልና የከስማይን ቡድኖች በጣም ስለሚወዳቸው ያከብራቸው ነበር፡፡ በነሱ ድጋፍ ሊነግሥ ችሏልና ከረበናት መካከልም አልሱላሃ የባሉትን ቡድኖች ያከብር ነበር፡፡

ከነዚህ የረበናት ቡድን ውስጥ ምናሄም የሚባል ደግና ብልሐተኛ ነበረ ሄሮድስ በሕፃንነቱ ወደ መምህራኑ ለመማር በሄደ ጊዜ "ምናሄም ለወደፊት እንደሚነግሥ አውቆ ንጉሥ ሆይ ህያው ሁን" አለው እየተባለ የሚነገር ታሪክ አለ ለጊዜው እየተሳለቁበት መስሎት ተቈጥቶ ነበር ምናሄንም ሰድቦታል ምናሄ ለምን ሰደብከኝ ብሎ ገረፈው እንደገናም ወዳጄ ሆይ እግዚአብሔር ነግሥሃል የኔን ግርፋትና ንግርት ግን አትርሳት ንጉሥ ሁነህ ብዙ ክፉ ሥራ ልትሠራ ነው፡፡ የምነግርህን ብቻ ልብ ብለህ አስተውለው፡፡

እኔ ግን ንጉሥ ስትሆን ክፉውን እየተውክ መልካምን እንድትሰራ እመክርሃለሁ፡፡ እኔ ምክሬን እንደማትቀበል ከወዲሁ እረዳለሁ ለክፋት ብቻ



www.ethiopianorthodox.org

ትተጋለህ ብሎት ምናሄም ከሱ ተለየ ሄሮድስም ለምን መታኝ ብሎ እያለቀሰ ሄደ ይላል ታሪኩ፡፡

ሄሮድስ አድጎ ይህን የምናሄን ትንቢት አስታወሰ በዚህ ጊዜ ምናሄ በጣም ሽምግሎ ነበር ሄሮድስ ምናሄን እኔ እንደምነግሥ ትንቢት ተናግረሃል አሁን ደግሞ በንጉሥነት ስንት ዓመት እንደምቆይ ንገረኝ አለው ምናሄ ግን ዝም አለ ቶሎ እንደሚያበቃ ያውቅ ነበርና ሄሮድስ መልሶ መልሶ ምናሄን ቢጠይቀው አልመልስልህ ቢለው ካሁን ወዲያ አሥር ዓመት ያህል እነግሣለሁን አለው ምናሄም በዚህ ጊዜ አሥርም ሃያም ሊሆን ይችላል ብሎ መሰሰለት ብዙ አቆያለሁ ብሎም ተስፋ አደረገ ሀገረሣምርን ሄሮድስ አቅንቶአታል ሳብስጥያ የሚል ስያሜም ሰጣት በዚችም ለአውግሥጦስ ቄሣር አዳራሽ ሠራ፡፡

የቂሣርያንም ከተማ ቆረቆረና በዚችውም ጥሩ ግንብ ሠራ ሄሮድስ ብዙ ከተሞችን ቆርቁሯል ብዙ ግንብንም ሠርቷል፡፡ በዚህም ተወድሷል ሄሮድስ ሌላ የተወደሰበትም ምክንያት አለው በ13ኛው ዘመነ መንግሥቱ በመላ ምድረ ይሁዳ ረሀብ ሆነ በአህዛብ አገሮችም እንዲሁ በሱ ግዛት ሥር ያለ ሁሉ በረሃብ ተጐዳ በአንፃሩ ግብፅ ውስጥ ጥጋብ ነበር፡፡ ከቤተ መዛግብቱ የተከማቸውን ገንዘብ አውጥቶ በመርከቦች እህልን ገዝቶ (ከግብፅ) ሕዝቡን በረሃብ ከመሞት ታድጓል ወደ አውግሥጦስ ቄሣርም ደብዳቤ ጽፎ ሕዝብ ስለተራበ እህል እንዲልክለት ስለጠየቀ አውግሥጦስ ቄሣር ለተራቡት ሁሉ ከሮምና ከግብፅ በየብስ በግመሎች በባህር በመርከቦች ባፋጣኝ እህል እንዲደርስ አዟል፡፡ ገንዘብ ያለው ሰው እህሉን መገዛት ያለበት በጥጋብ ጊዜ በነበረው ዋጋ እንዲሆንም ትእዛዝ አስተላልፏል፡፡

ባለታሪኮች ይህን ሲዘረዝሩ ብዙ እንጀራ እያስጋገረ ደካሞችን በመመገብ እንዲጠሩ ያደረግ ነበር ማየት የተሳናቸውና እጅ እግር የሌላቸው

ሕንፀቱ ዘወሀቦ ሄሮድስ ልኩዕ ውስተ መፅሐፈ አይሁድ ወዜናሆሙ"\ የዚህ መጽሐፍ አዘጋጅም ሕንፃው ተጀምሮ እስኪጨረስ ስምንት ዓመት እንደወሰደ መዝግቧል በመጀመሪያ የመቅደሱ አጀማመር ዓመት ዝናም አልዘነመም ይህም ሥራው እንዳይሰናከል የእግዝአብሔር ፈቃድ እንደሆነ ያሳያል።

የመቅደሱ ሥራ ተከናውኖ እንዳለቀ ሄሮድስ መባ እንዲገባ አዘዘ ስለራሱና ስለሕዝብ ሁሉ ኃጢአትም የሥርየት መሥዋእት እንዲሰዋ አዘዘ እቺንም ቤተ መቅደስ ሠርቶ ሄሮድስ የፈፀመባት ዓመት የደስታ ዓመት እንድትሆን አወጀ ዓመቱንም ሙሉ ሕዝቡ በእግዚብሔር ምስጋናና አክብሮት በመንፈሳዊ ደስታ አሳለፉዋት።

## ምዕራፍ ፴፰

## ሄሮድስ ልጆቹን እስክንድርንና አስትሮቦሎስን ገደለ

ሄሮድስ ልጆቹን እስክንድርንና አስትሮቦሎስን ለትመህርት ወደ ሮም ልኳቸው በሮም የሮማውያንን ጥበብ በመማር ላይ ነበሩ። እናታቸው ማርያምን እንደገደለ ስለሰሙ እጅግ ታወኩ ከሮም ወደ ቤተ መቅደስም ተመልሰው መጡ አባታቸው ሄሮድስ ባገኙትም የአባትነትን ክብር ሳይሰጡት ቀሩ በናታቸው በሱ መገደል እጅግ አዝነዋልና። ሄሮድስ ረሲስ የምትባል ሚስት ነበረችው ከሱም አንድ ወንድ ልጅን ወልዳ ነበር። የልጁ ስም አንደፌር ተባለ። ከሁሉ አብልጦ ማርያምን ስለወደደ ረሲስንና ልጅዋን አንደፌርን ከቤቱ አስወጥቶ አባረራቸው የማርያምን ልጆች እስክንድርንና አርስተቦሎስንም እጅግ ይወዳቸው ነበር። ማርያምን በገደለና ልጆቿንም በነቀፈ ጊዜ ግን ረሲስንና ልጇአንደፌርን ወደቤቱ መለሳቸው አንደፌርን ከሱ ቀጥሎ ባለው ሥለጣን ላይ ሾመው ሙሉ ሥልጣኑንም ሰጠው።



አንደፌር እነዚህ የማርያም ልጆች እስክንድርና አርስተቦሎስ ከሄሮድስ በኋላ ሥልጣን ይቀናቀኑኛል በማለት ሠጋ ማርያም ከታላላቅ ካህናት ወገን ስለሆነች የሷ ልጆች በአይሁድ ዘንድ ታላቅ ተቀባይነት እንዳላቸውም ያውቃል ረሲስ ግን ምንም እንኳ የአይሁድ ተወላጅ ብትሆንም ከነገደ መንግሥት ወይም ከነገደ ካህናት ወገን ተውልድ የላትም ስለዚህ ረሲስ ሄሮድስ በሕይወት እያለ እስክንድርንና አርሰተቦሎስን እንዲያስወግድላት ልጇን እንዲያከብርላት ስትወተውተው እሷም በበኩልዋ ሁለቱን ለማስገደል ምክንያት ትፈልግ ነበር።

አንደፌር ለሄሮድስ እንዲህ የሚል የስብቀት ቃል ነገረው። "ካባታችን ሄሮድስ በበለጠ አገርን መምራት እንችላለን እሱ ለንጉሥነት ብቃት የለውም የኛ እናት ከሁሉ ስለምትበልጥ መንግሥቱ ለኛ መሆኑ አያጠራጥርም" ይላሉ ከዚህም አልፈው አንተን ለመግደል በማሴር ላይ ናቸው እናታቸውንም ስለገደልክ ሊበቀሉህ ያደባሉ።

አንደፌር በዚህ ብቻ አልተገታም ሰዎችን በጥቅማጥቅም እየገዛ ለሄሮድስ በእነእስክንድር ላይ ለሞት የሚያደርሰውን ሁሉ ስብቀት ያቀርብ ጀመር ሰጊዜው ሁለቱንም እስክንድርንና አርስተቦሎስን ከቤቱ እንዲርቁ አደረገ። በዚህ ማህል ሄሮድስ ወደአውግሥጦስ ቄሣር እጅ ለመንሳት በሄደ ጊዜ እስክንድርን አስከትሎት ሄደ። የገዛ ልጁንም "እኔን በናቱ ቂም ሊገድለኝ ይፈልጋል" በማለት ወደ አውግሥጦስ ቄሣር ከሰሰው \እስክንድርን\።

አውግሥጦስ ቄሣር እስክንድርን "ለምን እስኪከስህ ድረስ አባትህን ታስቀይመዋለህ" አለው እስክንድር እኔ በእናቴ ሞት ላይ ነው ሐዘኔ ያስሐጢአት ተገድላለችና እንስሳት እንኳ ከናታቸው ሲለዩ ያዝናሉ በዚሁ መንገድ ስትመለከተው እናቴ እንደናፈቀችኝ ስትለየኝና አገዳደልዋም በግፍ መፈፀሙን ሳውቅ እንዴት አላዝን ሊገድለኝ ይፈልጋል ማለቱ ግን በእግዚአብሔር ፊት ፍፁም ሐሰት ነው እግዝአብሔር አባትህንና እናትህን

www.ethiopianorthodox.org

በአንድነት አክብር ይላል። እኔም በዚሁ ነው የምመራው አባቴን ለማጥፋት አላማ የለኝም በፍርድ ቀን ከፊቱ እቈማለሁና ወንድሜ አንደፌር ግን እናቴን እንደገደልካት እኛምን ባንተ እጅ እንድትገድለን ይጥራል" አለ።

በእስክንድር ንግግር ከአውግሥጦስ ጀምሮ ያሉት ሁሉ አለቀሱ ወድያው አውግሥጦስ ቄሣር እስክንድርንና ወንድሙ አርስተቦሎስን የነገረ ሠሪዎችን ስብቀት መስማት አቁም ወደ ቀድሞ ሥራቸው እንዲመልሳቸው ሄሮድስን አዘዘው እስክንድርንም ያባቱን እግር እንዲስም አዘዘው እሱም ሳመ ሄሮድስንም ልጁን እስክንድርን አቅፎ እንዲስመው አዘዘው እሱም ሣመው። ከዚህ በማያያዝም ከዚያ በኋላ ሄሮድስ አርሰተቦሎስንና እስክንድር ልጆቹን ዳግም እንዳይጠላቸው በግፍ የተገደለችው እናታቸው ሃዘንንም እንዲያስረሳቸው መሐላ አስማለው ባለበትም ሄሮድስ በሮም ጥቂት ቀናት ሰነበተና ወደ ቤተ መቅደስ ተመለሰ።

የታሪኩ ምሑር እንደሚገልፀው ሄሮድስ ቤተ መቅደስ እንደደረሰ ወዳጆቹንና ረበናተ አይሁድን ሰበሰበ ሦስቱ ልጆቹም በስብሰባው እንዲገኙ አደረገ እንዲህም አለ "የክብርና ልዕል እግዚአብሐረ ቤት የኛን መንግሥት ከፍ እንድትል አደረገ (ሦስቱ የሄሮድስ ልጆች የተባሉት እስክንድር አርስተብሎስና አንደፌር ናቸው) ስለዚህ ለሦስቱ ልጆቼ እንዳካፍላት ወደድኩ የማካፍላቸውም እኩል አድርጌ ነው ላንዱ ትንሽ ለሌላው ትልቅ አላደርግም እናንተ የዚህ ስብሰባ ተካፋዮችም በዚሁ ድጋፍ ስጡኝ እናንተም ወዳጆቼ ሁሉ በቀና መንገድ ታዘዙዋቸው እንጂ ችግር አትፍጠሩባቸው ደስ ይበላችሁ ነገር በመካከላቸውም ጥላቻን አትፍጠሩ አሳዛኝ ነገርንም አትንገሩዋቸው። ነገር ልብን ያውካልና የባሕርን ውሃ ነፋስ እንደሚያውከው የሰውን ልብ ነገር ያውከዋል።

እነሱ ባሉበት መጠጥን አታብዙ ጨዋታንም ከነሱ ጋር አታብዙ የጨዋታና የቀልድ ብዛት የነሱን ምሥጢር ያባክናል የነሱን ነገር ስትሰሙ ደግሞ ያንዱን ለሌላው እየወሰዳችሁ ለመንገር ትገደዳላችሁ ያንዱን ለሌላው ስታሳብቁ ለጥፋታችሁ ምክንያት መንስኤ ሊሆን ይችላል ለነሱ መጥፋትም ምክንያት ይሆናል።"ቀጥሎ ወደ ሦስቱ ልጆቹ ፊቱን አዞረና "የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ጠብቁ ይህን ካደረጋችሁ ዘመናችሁ ይበዛል ኑሮአችሁም የተቃና ይሆናል በዚህ ዓለምም ሆነ በሚመጣው ዓለም ብዕልንና ፀጋን ታገኛላችሁ" ብሎ እያንዳንዳቸውን እያቀፈ ሳማቸው።

የዚህ ታሪክ ፀሐፊ እንደገለፀው የሄሮድስ አባባል በልጆቹ ዘንድ መልካም ሁኔታን የፈጠረ አልነበረም። እንደሚታወቀው ሄሮድስ ከራሱ ቀጥሎ አንደፎርን በሁሉዘንድ የበላይ አድርጎ ሹሞት ነበር አሁን ግን ሊቀነስበት ሆነ በመሆኑም ከባድ ሐዘን ተሰማው። እስክንድርና አርስተቦሎስ በበኩላቸው አንደፌር ከነሱ ጋር በትክክል ሥልጣንን ለመጋራት ዝግጁ እንዳልሆነ ይረዱ ነበር።

አንደፌር በአፉ መልካምን እየተናገረ በወንድሞቹ ላይ ነገርን ከመጠንጠን አላረፈም ነበር። ሲያገኛቸው ትህትናን የተላበሰ በመምሰል የክብርና የወንድማማችነት ቃል ያሰማቸው ነበር። በልቡ ግን ሁለቱን ለመግደል መንገድን ያዘጋጅ ነበር። በሐሰትና በስብቀት በመስተዋድይነትም የተካኑ ሰወችን አዘጋጅቶ ሐሰቱን እውነት በማስመሰል ከሄሮድስ ጋር እንዲያጣሉዋቸው ወደ ሄሮድስ ላከባቸው። ሄሮድስ ግን የነገረሰሪዎቹን ስብቀት ሰምቶ እነዚህን ልጆች ከማፍቀር አልቀነሰም። አንደፌር ፍሩዳ የተባለውን ያባታቸው ወንድምና ያባታቸውን እህት ሰሎሚት በሽንገላ መንገድ እንዲጠመዱ አደረገ እነዚህ ሴትና ወንድ እስክንድርና አርስተቦሎስ አንተን

www.ethiopianorthodox.org

ሲጠይቀው አንተ የኔን ሴት ባሪያ ቀምተህ ስለወሰድክብኝ ይህንን አደረግሁ አለ። ሄሮድስ በዚህ ጊዜ አርከላኦስን "ላንተ ስል የወንድሜን ስህተት በይቅርታ አልፌዋለሁ። አንድ የጤና ባለሙያ በሽተኛውን እስኪድን ድረስ መውጣት መውረዱን እንደማያቆምሁሉ አንተም በኔ ላይ የተነሳው ሠው ሠራሽ በሽታ ለመፈወስ ብዙ ደከምክ" በማለት አመሰገነው።

ሄሮድስ የታሠሩትን ልጆቹ እስክንድርንና አርስተቦሎስን እንዲፈቱዋቸው አዘዘ ለአርከላኦስም ብዙ ገንዘብ ሰጠው ሌሎች ታላላቅ ሰዎችም ለአርከላኦስ የገንዘብ ስጦት እንዲያደርጉ አዘዘ እነሱም የታዘዙትን አደረጉ አርከላኦስ ወደ ሀገሩ ሲመለስ ሄሮድስ እስከ ሩቅ መንገድ ተጉዞ ሸኘውና ለአሸኛኘት ከሄሮድስ ጋር የወጣ ሁሉ ሄሮድስን ተከትሎ በመመለስ ወደየቤቱ ገባ።

አንደፌር አባቱ ሄሮድስ እነ እስክንድር ይቅርታ አድርጎ ከእሥር እንደፈታቸው አወቀና አዘነ። ሳይውል ሳያድርም የመሠርይነት ተግባሩን ቀጠለበት ብዙ ገንዘብን ሰጥቶ ዳግም እነሱን ለማጥፋት የተዘጋጀ ነገረ ሠሪን አዘጋጀ። ይህም ነገረሰሪ ወጥቶ ወርዶ የሄሮድስን ሐሳብ በማስቀየር ዳግም ለእሥር አበቃቸው። ነገሩን የተመለከቱ ሰዎች እጅግ ደነገጡ የተቃውሞ ቃልን ለማሰማት ግን በፍፁም አልቻሉም።

አንድ አረጋዊ ሰው ከሠራዊት መካከል ነበረ የዚህ ዓረጋዊ ልጅ የሄሮድስ ልጅ እስክንድር ወዳጅ ነበር ይህ አረጋዊ የነ እስክንድርን በስቃይ ጊዜያቸውን ማሳለፍ እጅግ አሳዘነው። በተለይም ዳግም ሲታሠሩ ከማዘኑ የተነሳ የራስ ምታት ተነሳበት እንደሌሎችም ሐዘኑን ሊታገሰው አልቻለም ከንጉሡ ዘንድም የመቅረብ መብት ነበረው ከሠራዊት መካከል በመሆንም በከፍተኛ ድምፅ "ኡኡ" አለ እየጮኸም "እውነት ተገደለች ሐሰት ሰፈነች ፍትሕ ከዓለም ራቀች..." አለ።

ለሄሮድስ ደግሞ "አቤቱ ጠላቱን የሚወድ ወዳጁን የሚጠላ ንጉሥ የት አለ ሄሮድስ ሆይ አእምሮህ የት ሄደ ምክርህና ጥበብህስ የት ገባ የጠላቶችህን ወሬ ትቀበላለህ እነሱ አንተን እያታለሉ ልጆችህን ሊያስገድሉህ ነው በኋላም አንተ ብቻህ ስትቀር ይገድሉሃል" አለ።

የእስክንድርና የአርስተቦሎስ ጠላቶች ግን "ሄሮድስ ሆይ ይህ አረጋዊ እየጮኸ ያለው አንተን ስለወደደ አይደለም ልጆችህንም አይወዳቸውም ነገር ግን በልቡ ስለሚጠላህ በሰበቡ ጥላቻውን ለመወጣት ነው። እየጮኸ ያለው ልብ እንደሌለህም ይገምታል እሱ ቀንደኛ ጠላትህ እንጂ ወዳጅህ አይደለም ነገር ግን አንተን ለማስገደል ይህ አረጋዊ ከጠላቶችህ ብዙ ገንዘብን ተቀብሏል" በማለት ሄሮድስን በማስመሰል አዋከቡት። ሄሮድስም በነሱ ተገፋፍቶ አረጋዊውን ሰው በፍጥነት ይዘው ባሰቃቂ ሁኔታ ይገድሉት ዘንድ አዘዘ መዛይን የተባለውም የሠራዊት አለቃ አብረው ነገር ስለሠሩበት ሁለቱ ተይዘው እንዲገደሉ አዘዘ ያ የአረጋዊው ልጅና የእስክንድር ወዳጅም አብሮ እንዲሰቃይ በሄሮድስ ተወሰነበት መዛይንና አረጋዊው ለምርመራ እንዲናገሩ ብዙ ሲቀጠቀጡ ትንፍሽ አላሉም ወጣቱ የሽማግሌው ልጅ ግን ስቃዩ ስለፀናበት ነገረ ሠሪዎቹ የሚሉት እውነት እንደሆነ ለፈለፈ ይህን ለመቀባጠር የተገደደው ከስቃዩ ለመዳን ብሎነው አባቱንም በዚሁ ከሞት የሚተርፍለት መሰለው ግን ምንም አልተጠቀመም አባቱን መዛይንንና ወጣቱን እንዲገደሉ ሄሮድስ ስላዘዘ ወዲያው ተገደሉ።

እስክንድርንና አስትሮቦሎስን ዳግም ሰብስጥያ ወደተባለው ቦታ አስወሰዳቸው በዚሁም አስገደላቸው በድናቸውም ተሰቀለ ለእስክንድር ሁለት ልጆች ሲኖሩት እስክንድርና ብርገን ይባሉ ነበር እናታቸው የክፍቦር ንጉሥ አርከላኦስ ልጅ ናት አስትሮቦሎስ በበኩሉ አስትሮቦሎስ አግሪጳና ሄሮድስ



www.ethiopianorthodox.org

የሚባሉ ልጆች ነበሩት አግሪጳ ከአንደፌር ቀጥሎ ንጉሥ ሁኗል። ይህ በአያቱ ስም ሄሮድስ የተባለው የአርስተቦሎስ ልጅም ሁለት ልጆችን ትቷል።

## ምዕራፍ ፴፱

## የአንደፌር ወልደ ሄሮድስና የሄሮድስ አሟሟት ዜና

እስክንድርና አርስተቦሎስ (የሄሮድስ ልጆች) በተገደሉ ጊዜ ወንድማቸው አንደፌር እጅግ ተደሰተ የተመኘውንም አገኘ ሕዝቡ ግን አንደፌርን እጅግ ጠላው አንደፌር ግን በዚህ እኩይ ተግባሩ ብቻ አልተገታም የነሱንም ልጆች ለማጥፋት ፈለገ። ሄሮድስ የገዛ ልጆቹን በግፍ ከገደላቸው በኋላ በሐሰት ተሞርኩዞ እንደገደላቸው ተረዳና እጅግ ተፀፀተ። ስለዚህ የአርስተቦሎስንና የእስክንድርን ልጆች አቀረባቸው አኗኗራቸውም አሳመረ።

ሄሮድስ የቤተ መንግሥቱን ትላላቅ ባለሥልጣኖች ሰብስቦ "እኔ ነፍሴን በነፍሴ አቁስያታለሁ ልጆቼን ገደልኩ ልቅሶዬ ሐዘኔና ትካዜዬ የከፋ ነው ከዚያም ላይ በዕድሜ ስለገፋሁ ልሞት ቀርቤአለሁ የሐሰትን ቃል በመስማት ብቻ ልጆቼን ገደልኳቸው የነሱ በግፍ መገደል እሳት ሆኖ ህሊናየን አቃጠለው የነሱን ልጆች በታላቅ ርሕራሄና እንክብካቤ መያዝ አለብኝ እነሱ ገና ትንሾች ናቸው ባባቶቻቸው ምትክ እኔ ከፍተኛ ዋጋ ልከፍላቸው ይገባኛል" አላቸው።

ወንድሙን ፍሩዳ "ያንተን ሴት ለእስክንድር ልጅ ብርጋን እንዳባት ትሆነው ዘንድ ላጋባው ፈቀድኩ" አለው አንደፌርን ተንኰለኛውን ልጁ ደግሞ ትሆነው ዘንድ ያንተን ሴት ልጅ ለወንድምህ አርስተቦሎስ ልጅ እንዳባት ትሆነው ዘንድ እንድታጋባው እፈልጋለሁ አለው። በዚህ ጊዜ ለሄሮድስ ፍሩዳና አንደፌር እንዳባት ትሆነው ዘንድ እንድታጋባው እፈልጋለሁ አለው። በዚህ ጊዜ ለሄሮድስ ፍሩዳና አንደፌር ሄሮድስን ለመቃወም አልቻሉም። ስለዚህ እሺ አሉት በልባቸው ግን እጅግ ቅር ተሰኙ ሄሮድስ ደግሞ በህጋቸው መሠረት ነገሩን አመነበት።

በስብሰባው የተገኙት ባለስልጣኖች ደግሞ በሄሮድስ ድርጊት ተደሰቱ ሄሮድስ እነሱን በምስክርነት አስቀምጦአቸዋልና። በናቱ ብርገን ወልደ እስክንድር የክፍየር ንጉሥ አርከላኦስ የልጅ ልጅ ነው። ስለዚህ ብርገን የአያቱን ድጋፍ አግኝቶ ጉድ እንዳያፈላበት ነገረ ሰሪው ፍሩዳ ፈራ። ንጉሥ አርከላኦስ በለመደው የቅጥፈት ሥራ ሄሮድስ የጀመረውን የጋብቻ ሂደት አቅጣጫ እንዲያስለውጥ ፉሩዳ መከረው በመሠርይነት ተግባሩም የተባለውን ጋብቻ አስለወጠ በዚህ እያለ ሄሮድስ ያንን መሠርይ ልጁ አንደፌርን ቃል ኪዳኑን እንዲያሳድስለት ወደ አውግሥጦስ ቄሣር ወደ ሮም ላከው። ሄሮድስ ወንድሙ ፍሩዳ የሱን ሞት እንደሚመኝ ስማ ከቤቱም አራቀው ደግሞ እንዳይገባም ከለከለው።

ፍሩዳ በፀናታመመ ወንደሙን ሄሮድስም ከመሞቱ አስቀድሞ እንዲያየው ላከበት ሄሮድስም በርኅራሄ ተጠመደና ሲያየው ሄደ በዓዕረ ሞት ተይዞ ሲመለከትም አለቀሰለት ካባታቸው ሞት በኋላ እንደሚረዳቸው ልጆቹንና ቤተሰቦቹን አፅናናቸው ፍሩዳ ሞተ ሄሮድስም በወንድሙ ሞት አዘነ ባባቶቹ መቃብርም ቀበረው። ፍሩዳ እንደሞተ ፍሩዳ በሱ ላይ ነገር ሲያውጠነጥን እንደነበር ለሄሮድስ ጥቆማ ደረሰው። ሄሮድስ ይህን ነገር ለማጣራት የፍሩዳን ሴትና ወንዶች ባሮችን አስሮመረመራቸው እነሱም አንደፌርና ፍሩዳ በቤት እየተገናኙ በሱ ላይ ሲመክሩበት ሌሊቱን ሙሉ ያድሩ እንደነበር ገለፀለት ወደ አንደፌር እናት ረሲስም ይሰበሰቡ እንደነበር ገለፀለት።

ከባሮቹ አንዱ "ከእለታት ባንዱ ቀን ይህ ሄሮድስ ሰው በላ አውሬ ነው ከአውሬም በላይ ነው አውሬ ልጆቹን አይበላም ይህ ግን ልጆቹን በላ ሚስቱንም በላ እኛንም ለመግደል ወደኋላ አይልም ሳይቀድመን በሆነ ዘዴ ተጠቅመን እንግደለው ይህን ካላደረግን እኛን መግደሉ አይቀሬ ነው እሱን ከገደልን በኋላ እነዚያን እያስጠጋቸው ያሉት የልጅ ልጆቹን ደግሞ

www.ethiopianorthodox.org

በማለትም የድፍረት ቃል አስተጋቡ። አርኬላኦስም ገና ከመንገሱ ብዙ ተቃዋሚዎችን ገደለ።

በዚህ ጊዜ ከሕዝበ አይሁድ ተመርጠው ወደ ሮም ሄዱና ለአውግስጦስ ቄሣር "አረመኔው ሄሮድስ ሰዎችን በመግደል ብቻ ሳይሆን ብዙ የአረመኔነት ድርጊት ሲፈጽምብን ኑሮ ቢሞትልን የሱ ልጅ አርኬላኦስ በስልጣኑ አንተ ሳትፈቅድለት ነግሦ ተቃዋሚዎቹን መግደል ተያይዞታል ብዙዎችንም ገድሏል። እንደህጉ ከሆነ ራሱ ንጉሥ ነኝ ከማለት ያንተን ፈቃድ መጠየቅ ነበረበት ነገር ግን ይህን አላደረገም" በማለት አርኬላኦስን ከሰሱት። እሱን እንዳያነግሥባቸውም አጥብቀው ለመኑት። ከአይሁድ ወገን ያልሆነ ከተከታዮቹ ሮማውያን እንዲሾምላቸውም አውግስጦስ ቄሣርን ለመኑት።

አርኬላኦስ በበኩሉ ወደሮም ያባቱ ፀሐፊ የነበረውን ኒቆሎስ አስከትሎ ወደ አውግስጦስ ቄሣር ሄደ። ኒቆሎስ የአይሁዶቹን አቤቱታ ለማኮላሸት ለአውግስጦስ ቄሣር "እነዚህ አርኬላኦስን ለመክሰስ የመጡ አይሁድ ወገናቸውን አርኬላኦስ እንዲገዛቸው ጠልተው አይደለም የሮምን መንግሥት ለመክዳት ስለፈለጉ ነው እንጂ አለ። ከቄሣር የበታች ሽማምንት ዘንድም የአርኬላኦስን ንጉሥነት እንዲረጋገጥ ብዙ ደከሙ ንጉሥነቱንም አፀደቀለት።

አርኬላኦስ ከከሳሾቹ ይልቅ ተቀባይነት በማግኘት ወደ አገሩ ተመለሰ አውግስጦስ ቄሣር ንጉሥነቱን አፅድቆ ላከው አይሁድን ያላንዳች ተቃዋሚ እንደፈለገ ቀጥቅጦ ገዛቸው ብዙ መከራንም አደረሰባቸው የወንድሙን እስክንድር ሚስትን አገባት እቺ ሴት ወደ አርኬላኦስ በተወሰደችበት ሌሊት በሕልሟ ባልዋ እስክንድር ሲቆጣ ታያት ልትጠጋው ብትሞክርም ራቃት ከኔ በኋላ ጋብቻ አይጠቅምሽም እኔን ሐፍረትንና ውርደትን እንዳለበሽኝ ተረጂ በማለት ብዙ ዛተባት እሷም በድንጋጤ ከእንቅልፏ ነቃች ያየችውንም ሕልም



ለሰዎች ተናገረች አርኬላኦስ በወሰዳት በሁለተኛው ቀንም ሞቱች አርኬላኦስ በበኩሉ በሕልሙ ካንድ ግንድ እጅግ የሚያማምሩ የሽቶ ዘለላዎችን አየ ትልቅ በሬም መጥቶ ሽቶቹን በላቸው። ይህንን ለሕልም ፈካሪዎች ነገራቸው ሕልም ተርጓሚዎችም ሰባቱ የሽቶ ዘለላዎች ሰባት ዓመት ናቸው ለሰባት ዓመት ትነግሣለህ ሰባቱን የሽቶ ዘለላዎችን የበላ ትልቁ በሬ ደግሞ ቄሣር ነው። ከሰባት ዓመት በኋላ ቄሣር መንግሥትህን ይወስዳል በዚችውም ዓመት ከመንግሥትህ ትወገዳለህ" አሉት። ከጥቂት ዓመታት በኋላ ከአውግስጦስ ቄሣር መልእክተኞች አንዱ ከፍተኛ ባለሥልጣን ወደ ቤተ መቅደስ መጣ አርኬላኦስንም ይዞ አስረው ወደ ሮምም ወሰደው። ከእሥር እንዳለ ሞተ። ከሱ ቀጥሎ ወንድሙ አንጠሬስ ነገሠ።

## ምዕራፍ ፳፪

## የቀዳማዊ ሄሮድስ ልጅ አንጠሬስ ታሪክ

አንጠሬስን ያነገሠው አውግሥጦስ ቄሣር ነው። አርኬላኦስ ታሥሮ ወደ ሮም እንደተወሰደ በዚያው ሞተ አውግስጦስ ቄሣር አንጠሬስን አንግሦ እንዳባቱ ሄሮድስ አለው አንጠሬስ እንዳባቱና እንደወንድሙ አርኬላኦስ ክፉ ገዢ ሆነ አመንዝራም ሆነ ወንድሙ ፊሊጶስ በሕይወት እያለ ሚስቱን ሄሮድያዳን ቀማው ሁለት የወንድሙን ሚስት በመቀማቱ የአይሁድ ታላላቅ ሰዎች ቢቃወሙት ገደላቸው በዚሁ ምክንያት ብዙዎች ተገድለዋል የካህኑ ዘካርያስ ልጅ ዮሐንስንም ገድሎታል። ወንድምህ በሕይወት እያለ ሚስቱን ልትቀማው አይገባም በማለት ዘልፎታልና ከፊሊጶስ ሚስት አንጠሬስ ሁለት ልጆችን ወልዷል።



www.ethiopianorthodox.org

ለአይሁድ ጥምቀትን ያስተማረ ዮሐንስ ነው:: አይሁድ ዮሐንስን "ይሕያ" ይሉታል ክርስቲያኖች ደግሞ ዮሐንስ ይሉታል:: በሄሮድስ ልጅ አንጠሬስ ዘመነ መንግሥት አውግሥጦስ ቄሣር ሞተ ጢባርዮስ ቄሣርም ነገሠ ጢባርዮስ ቄሣር ክፉ ንጉሥ ሆነ:: በሱ ዘመን ብዙ ክፉ ነገር ታየ ሰዎች ወደሱ እንዲሰግዱ አዘዘ እንዲያመልኩትም አዘዘ አይሁድ አንሰግድልህም ስላሉ ብዙዎች አይሁዶችን ገደለ:: አይሁድ በዓመፀኝነት ተባብረው አንጠሬስን ከቤተ መንግሥት አባረሩት እነሱ እንደጠሉት አውቆ ጢባርዮስ ቄሣር ይዞ አንድሎስ በተባለው ቦታ አሠረው በዚያውም ሞተ:: አንጠሬስ ኀልሳዊ ሄሮድስ በመሆን አይሁድን ሃያ አንድ ዓመት ገዝቶአቸዋል:: ከሱ ቀጥሎ የሱ ወንድም የአርስጦቦሎስ ልጅ አግሪጳ ነገሠ::

## ምዕራፍ ፫

## ዜና አግሪጳ ወልደ አርስጦቦሎስ ወልደ ሄሮድስ ቀዳማዊ

በዘመነ አግሪጳ ወልደ አርስጦቦሎስ፣ ጢባርዮስ ቄሣር ሞተና በምትኩ ኔሮን ቄሣር ነገሠ ከሱ በፊት እንደሱ ክፉ ቄሣር አልነገሰም እሱ አራተኛ ቄሣር ነው:: ሰዎች ሁሉ አምላክ እንዲሉት አዘዘ ሲምሉም በስሙ እንዲምሉ አዘዘ በስሙም የሚመለክበት ቤተ መቅደስ በሱ ግዛት ሁሉ እንዲታነፅ ወሰነ ቊርባን በየመቅደሱ በስሙ መፈፀም አለበት አለ::

አሕዛብ ሁሉ በሱ ትእዛዝ ተመሩ የሱን ትእዛዝ አንቀበልም ያሉት አይሁድ ብቻ ናቸው አይሁድ አፌሎ የተባለውን ሰው ወደሱ ላኩ አፌሎ አስተዋይና ብልሐተኛ ነበር ኔሮን ቄሣር አፌሎን ለምን አንታዘዝም ትሉኛላችሁ አለው አፌሎ በበኩሉ አምላክ የምንለው እግዚአብሔር እንጂ ሰውን አምላክ አንልም የምንምለውም በእግዚአብሔር ስም ብቻ ነው መቅደስንም ለእግዚአብሔር ብቻ እንሠራለን ቊርባንንም ለሱ እናቀርባለን እንጂ ከአምላካችን ትእዛዝ አንወጣም::" አለው::

ኔሮን እጅግ ተቆጣ (በአፌሎ ላይ) ብዙ የአይሁድ መልእክተኞችን አስከትሎ ነበር የሄደው ወደ ኔሮን እንዲቀርብ የተፈቀደለት ግን እሱ ብቻ ነው:: ከኔሮን የወረደበትን የስድብ ውርጅብኝ ከውጭ ለሚጠብቁት አይሁድ ነገራቸው አሁን እሱ በኛ ላይ ቁጣውን ሲያነድብን ነው:: "እኛ እግዚአብሔርን በጾምና በፀሎት እንለምነው:: ከዚሁ ከተደቀነብን መከራም ያወጣን ዘንድ እንማፀነው" አላቸውም በመላ ምድረ ሮም ያሉት አይሁድ ከያሉበት ሁነው በልቅሶ በፆምና በጸሎት ረድኤተ እግዚአብሔርን እንዲጠይቁ መልእክት አስተላለፈላቸው እነሱም ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ጸለዩ ከኔሮን ቄሣር እጅ እንዲያድናቸውም እግዚአብሔርን ለመኑ::

በሦስተኛው ቀን አይሁድ የሮምን ሕዝብ አስተባብረው ተነሱና ኔሮን ቄሣርን ከበቡት በሰይፍም አንገቱን ቆረጡት አካላቱን በሙሉ ቆራርጠው ጣሉ:: በመይዳ ላይም የአካላቱን ቁርጥራጭ ስለጣሉ ውሾች በሉት በመቃብር አልተቀበረም እግዚአብሔር ቁጣውን በሱ ላይ አሳይቷልና ከሱ ቀጥሎ ቀላውዴዎስ ቄሣር ነገሠና አፌሎ በሰላም ወዳገሩ እንዲመለስ አደረገ አፌሎና ተከታዮቹ እየተደሰቱ ወደ ቤተ መቅደስ ተመለሱ ኔሮን ቄሣር እንዲመለክባቸው የተሠሩትን የጣዖት ቤቶች በሙሉ እንዲፈርሱ ቀላውዴዎስ ቄሣር አዘዘ::

የአይሁድ ንጉሥ አግሪጳም በመልካም አመራር ይኖር ነበር ሆኖም ቀላውዴዎስ ቄሣርንም እያከበረውና እየታዘዘው ኖረ:: ለሃያ ሦስት ዓመት


www.ethiopianorthodox.org

በዚህ ዘመን የነበረው ይህ ኔሮን ዳግማዊ ነው ጴጥሮስንና ጳውሎስ በዚህ ዘመን የነበረው ይህ ኔሮን ዳግማዊ ነው ጴጥሮስንና ጳውሎስ

በዚህ ዘመን የነበረው ይህ ኔሮን ዳግማዊ ነው ጴጥሮስንና ጳውሎስ ሐዋርያትን የገደላቸው ኔሮን የአቅሎዱስ ልጅ ይባላል። በኔሮን አሥራ ሦስተኛ ዓመተ መንግሥት ዮሐንስ ወንጌላዊ ወንጌሉን ፃፈ። በዚህ ጊዜ መድሐኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ካረገ ፴ ዓመት ሁኖት ነበር የመጀመርያው አግሪጳ እንደ አያቱ አረሜናዊ ሄሮድስ ተባለ የዮሐንስን ወንድም ያዕቆብን ያስገደለው አግሪጳ ዳግማዊ ተብሎ የተሾመው ነው። በዚሁ ዳግማዊ አግሪጳ ፊት ቅዱስ ጳውሎስ ተከሶ ቀሟል።

## ምዕራፍ ፰

## ዜና ወልደ አናፋኒ አልአዛር

የሮምን መንግሥት አናውቅም ለማለት አልአዛር የመጀመሪያው ነው። ከአርበኞችም አንዱ ነው። ከአልዓዛር ጋር ለሮም መንግሥት አንገዛም በማለታቸው ቤተ መቅደስ እንድትደመሰስ ምክንያቶች ሁነዋል። ብዙ ሕዝብም ተደምስሷል። እንደሚነገረው አናኒ የሚባል ካህን ነበር አልአዛር የሚባል ልጅም ነበረው አልአዛር ብርቱ ከመሆኑም በላይ ሽፍታ ነበር። ብዙ ሽፍቶችንም አሰባሰበ ብዙ ክፉ ሰዎችም ወደሱ ተሰባሰቡና ወደ አርመን ሄደው የባለፀጎችን ንብረት ቤት እየሠረሠሩ ይሠርቁ ነበር።

መንገደኛ ሲያገኙም ይዘርፉት ነበር። ሲዘርፉ ሀብታም ድሐ አይሉም ያገኙትን ሁሉ ይዘርፋሉ እንጂ ይህንን እየፈፀሙም ወዳገራቸው ይመለሱ ነበር። እየተመላለሱም በመዝረፍ አርመንን አመዘበሩዋት ወገኖቻቸውንም አይሁድ በውንብድናቸው አስጨንቀዋቸው ዘረፋው ሲጠናባቸው የአርመን ሕዝቦች ወደ ሮሙ ሹም ፊልፎስ አቤት አሉ ፊልፎስም በረቀቀ ዘዴ

አልኣዛርን ያዘው አሥሮም ወደሮም ወሰደው የሱን ተከታዮች ገደላቸው አልአዛር ግን በሮም ለጥቂት ጊዚያት ታሥሮ ተለቀቀ ወደቤተ መቅደስም ተመለሰ አግረደስ ደግሞ ወደሮም ሄዶ ኔሮንን ለመገናኘት ፋስገ ሄዶም አግሪጳስ ቤተመቅደስን ትቶ ኀዞው ሲጀምር በሮማውያንና በአይሁድ መካከል ከባድ ጠብ ተነሳ።

የጠቡ መነሻ ፊልፎስ የሮሙ ባለሥልጣን በአይሁዶች ላይ ብዙ ግፍ ስለፈፀመ ነበር አይሁድ ግን አንድነት ግንባር ፈጥረው ፊልፎስን አቸነፉት እሱ ተሸንፎ ሲሸሽ በቤተመቅደስ ዙርያ የተገኙ ብዙ ሮማውያን ተገደሉ የቀሩትን ሮማውያን ከቤተመቅደስ አሳደዱዋቸው ፊልፎስ ሸሽቶ ወደ ግብፅ ሄደና አግሪጳስ በመርከብ ተሳፍሮ ወደሮም ለመሄድ ሲዘጋጅ ደርሶበት ወደሮም መሄዱን አቋርጦ ወደቤተመቅደስ እንዲመለስ አዘዘው።

አግሪጳስ ወደ-ቤተመቅደስ ለመመለስ ሲነሳ ፊልፎስ ከአልኣዛር ድርጊት ጀምሮ በቤተመቅደስ የተፈፀመውን ሁሉ ለአግሪጳስ ገለፀለት ከአግሪጳስ ጋር ብዙ ከፍተኞች የሮም ወታደሮች ነበሩ ወደቤተመቅደስ ሲመለስ አይሁድ በደስታ ተቀበሉት አግሪጳስ ከፊልፎስ ጋር ምን እንዳጣላቸው ጠየቃቸው እነሱም የፈፀመባቸውን ግፍ ገለፁለትና ከዛሬ ጀምሮ ለሮማውያን አንገዛም አሉት አግሪጳስ በዚህ ጊዜ አዘነ ግራ ገብቶትም እጅግተጨነቀ ከሮማውያን ተገገርነት ማፈንገጡ እንደማያዋጣቸውና ሮማውያን ሊደመስሱዋቸው እንደሚችሉም ተረዳ።

አብረውት ያሉትን የሮም መንግሥት ወታደራዊ ባለሥልጣኖች ተስፋ እንዳይቈርጡ አግሪጳስ አፅናናቸው አይሁዶችንም በየመዓርጋቸው እንዲሰበሰቡ አደረገ ምክንያቱም አንድ ላይ ከሰበሰባቸው ብዙ ደም ከሮማውያን ጋር ስለተፋሰሱ ሊረጋጉለት አልቻሉምና ነገር ግን ለየብቻ ከሰበሰባቸው በኋላ እንዲህ አላቸው «ወንድሞቼ ስሙኝ በርጋታም አዳምጡኝ በፀጥታ



www.ethiopianorthodox.org

እነዚህ የአስብስያኖስን መምጣት የሰሙ አስቀድመው መጥተው በዮርዳኖስ ወደምትገኘው ፍብረዳ የገቡ የሐናን ተከታዮች የአስብስያኖስን መምጣት ሲሰሙ ሸሽተው ወደጫካ ገቡ ከዚያውም ተቀመጡ።

አስብያኖስ የነሱን ሸሽቶ ጫካ መግባት ሲሰማ ሠራዊቶቹን ላከባቸው የተላኩትም ሠራዊቶቹ የሐናንን ተከታዮች ከገቡበት ገብተው አገኙዋቸው ጦርነትንም በመክፈት አብዛኞቹን ገደሉ የቀሩት የትም ሸሹ እነዚህ የአስብስያኖስ ሠራዊት ሲመለሱ ወደቤተመቅደስ የሚመጡትን አይሁድ አገኙ ና ገደሉዋቸው አንድ መቶ ሺ ሦስት መቶ አይሁድ በዚሁ ተገደሉ የቀሩትን አይሁዶች ከነ ሕይወታቸው በሙላት ላይ ወደነበረው የዮርዳኖስ ወንዝ ወረወሩዋቸው። ብዙዎች አይሁድ በዚህ አለቁ።

አስብአያኖስ ገዛውን ወደሮም አቀና «ደግዳ» ወደተባለው ቦታም ደረሰ ቀጥሎ ስብስጥያ ደረሰ ራሱ ያፈረሰውንም የከተማዋ ቅዕር እንዲሠራ አዘዘ ወደ ቤተመቅደስ ለመዝመትም ዝግጅት አደረገ ቂሣርያም ደረሰ ብዙ ሠራዊትንም ሰበሰበ በቤተመቅደስ ዙርያ የተቀሰቀሰው ጦርነት አላባራም ነበር ሐናን ያለዕረፍት ሕዝቡን በመግደል ሴቶቹን በመማረክና ንብረትን በመዝረፍ ላይ ነበር።

## ምዕራፍ ፱

## የስሞዖን ታሪክ

ሐናንና አስብያኖስ በየግላቸው ቤተመቅደስንና አይሁድን ደምስሰው በነበሩበት ወቅት ስምዖን የሚባል ሰው ተነሳ ይህም ስንዖን የለየት አረሜናዊ ክፉ ሰው ነበር የሐናን ፈለግ ተከትሎ አይሁዶችን መፍጀቱ ተያያዘው አናኒ ካህን ይህን እኩይ ሰው ካገር አባረረው ይሁን እንጂ በሄደበት አገር መሰል ወንበዴዎችን አሰባሰበ ሁለት መቶ ሺ ወንበዴዎች ወደሱ ተሰበሰበ።



የቤተመቅደስ ሰዎች ሁኔታውን ሰምተው ወዳለበት ወታደሮችን ላኩበት ነገር ግን አብዛኞቹን ገድሎ የቀሩትን አባረራቸው ወደቤተመቅደስም ተመልሶ የሕዝበ አይሁድን አዝመራ አቃጠለ በሀገረ መቅደስ የነበረችውን ሚስቱ ካገር እንድትወጣ ላከባት ሐናን ስምዖንን ለመውጋት ተነሳ ነገር ግን ሊቃወመው እንዳልቻለ ተረድቶ በሌላ አቅጣጫ ተመለሰ የስምዖን ሚስት ወንዶችንና ሴቶችን ባሮችዋ አስከትላ ወደባልዋ ለመድረስ ጉዞ ስትጀምር ሐናን ከመንገድ መልሶ በሀገረ ቤተመቅደስ ባለው ቤቱ እንድትቀመጥ አደረገ።

ስምዖን የሐናንን ድርጊት ሰምቶ የሐናንን ቤተሰቦች እጃቸውን ቆርጦ ወደ ሐናን ላካቸው እንዲህም አለው «ሚስቴን ካልላክልኝ በአቸናፊነት ወደ ቤተመቅደስ እመጣና የነዋሪዎችን ሁሉ እጅ እንደዚሁ አቀርጣለሁ» በዚህ ጊዜ የሀገረ መቅደስ ነዋሪዎች እጅግ ደነገጡ ሐናን በፍጥነት ሚስቱን ላከለትና ሀገረ ቤተመቅደስን ማጥፍቱ ለጊዜው አቆመ ነዋሪዎቹም ላጭር ጊዜ ዕረፍት አገኙ።

ስምዖን ወደ ኤዶም ሄዶ ነዋሪዎቹንም አሳደደ ንብረታቸውንም ዘረፈ ይህን ካደረገ በኋላ ባለበት ወደ ሀገረ መቅደስ መጣ ሀገረ መቅደስ በሐናንና በስምዖን አማካይነት ሰላም አጥታ ታወከች ካገር ውጭ ስምዖን ያገኘውን አይሁዳዊ ይገድላል ንብረቱንም ይዘርፋል ባገር ውስጥ ደግሞ ሐናን ሰውን ይጨፈጭፋል ንብረትንም ይዘርፋል ሀገረ መቅደስ በውስጥም በውጭም ተወጠረች።

የቤተመቅደስ ነዋሪዎች ቢቸግራቸው ሐናን እንዲያስወግድላቸው ወደስምዖን ላኩ ጭንቀቱና ዕልቂቱ በዝቶባቸዋልና ስምዖን ሐናን ካስወገድኩ ለኔ እንድትገዙ ቃል ግቡልኝ እኔም ክፉ ላለማድረግ ቃል እገባለሁ አላቸው እነሱም እሱ በተናገረው መሠረት ቃል ገቡለት ወድያው ወደማህል አገር ገብቶ ከሐናን ጋር ጦርነትን ገጠመ ሐናን ግን ሊሸነፍለት አልቻለም የሁለቱ ጦርነት በሕዝቡ ዘንድ የማይያቋርጥ ጦርነት ተቀሰቀሰ የገባውም ቃል ኪዳን ሽሮ

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፲

# የጥጦስ ወደ ቤተመቅደስ መምጣት ታሪክ

ጥጦስ የአስብያኖስ ልጅ ነው ካባቱ ቤተ መቅደስን እንዲያጠፋ አስቀድሞ መመርያ ተሠጥቶታል:: ተልእኮውን አከናውኖ ወዳባቱ ወደሮም ለመድረስ እጅግ ተቻኩሏል:: ስለዚህ ከቂሣርያ ተነስቶ ባሎ በተባለው ቦታ ሠፈረ ከዘያም ተነስቶ ሰባት መቶ ፈረሰኞችን በማስከተል ወደቤተ መቅደስ ሄደ አካሄዱ የቤተመቅድስን ቅዕር ግንብ ለመሰለል ነበር ለሕዝቡ ሰላምንና ፀጥታን ለማስከበር መምጣቱን አስነገረ ወዳገሩም ሲደርስ የከተማው በሮች ተዘግተው የሚወጣም ሆነ የሚገባ ሳይኖር ፀጥታ ሰፍኖ ጠበቀው::

ስምን እንደመጣም የሚጠይቀው ሰው አጣ ወደ ሠራዊቱም ተመለሰ ወደባሎ ሲመለስ አይሁድ ከበቡትና ይዘው ለማሠር ፈለጉ እሱ ግን እጁን ሳይሠጥ ተዋጋቸው ከባድ ጦርነትም ተካሄደ በሚቀጥለው ቀን ተመልሶ ወደ ቤተ መቅደስ ሄዶ ሠራዊቱም በደብረዘይት ተራራ ላይ እንዲመሽግ አደረገ እንዳይለያዩም ጥጦስ ሠራዊቶቹን ተማፀናቸው በማግሥቱ ጧት የቤተመቅደስ ሰዎች አሻግረው የሮምን ሠራዊት ተመለከቱ የሕዝቡ አለቆች በዚሁ ጊዜ ተሰበሰቡና በመካከላቸው ያለውን ጥላቻ አስወግደው ሮማውያንን እንከላከል አሉ::

ግንባር በመፍጠርም የሮምን ሠራዊት ጦርነት ገጠሙዋቸው ከአይሁዶችና ከሮማውያን ወገን ብዙ ሠራዊት አለቀ በመጨረሻ ግን አይሁድ ተቸንፈው ወደ ቦታቸው ወደ ቤተመቅደስ ተመለሱ:: ወድያውኑ ከከተማ በመውጣት ሮማውያንን በኋላ ገብተው ለመውጋት ወሰኑ በፊትና በኋላ በመሆንም አይሁድ ሮማውያንን በመካከላቸው አስገቡዋቸውና ብዙ ሮማውያንን ፈጁ ጥጦስ ራሱ ከአይሁድ እጅ ለጥቂት አመለጠ::

አይሁድ ጥቂት የሮማውያንን የመቻነፍ አዝማምያ ሲመለከቱ በመካከላቸው የሥልጣን ሽኩቻ ተፈጠረ ሐናን ለወደፊቱ የበላይ ባለሥልጣን መሆን ያለብኝ እኔ ነኝ አለ ግንባር ፈጥረው ጠላትን የመዋጋት ቃልኪዳኑንም አፈረሰ ስምዖንና አልአዛር በበኩላቸው የሐናን የበላይ ባለሥልጣን መሆንን አይቀበሉም ነበር በዚህ መካከል የቂጣ በዓል ደረሰ ሐናን በዓሉ ከመድረሱ አንድ ቀን ቀድሞ ወደቤተመቅደስ ገባ ተከታዮቹ የጦር መሣርያቸውን በየልብሳቸው ውስጥ ደብቀዋል ሌሎቹ ካህናት ሐናንና ተከታዮቹ ሰላማውያን ሁነዋል በማለትም እየተደሰቱ ወደቤተመቅደስ ገቡ የጦር መሣርያንም በእጃቸው ስላላዩ ጥርጣሬ አላደረባቸውም ሕዝቡ ለበዓሉ ገብቶ ግጥም እንዳለ ግን ማንንም ሳይለዩ የገባውን ሁሉ ጨፈጨፉ:: ስምዖንና አልዛር ነገሩን ሲረዱ በውጭ ያገኙዋቸውን የሐናንን ተከታዮች መጨፍጨፍ ጀመሩ ሐናን ከቤተመቅደስ ወጥቶ አልአዛርንና ስምዖንን ጦርነት ገጠማቸው በሁለቱ ወገን ከባድ ጦርነት ተከፈተ::

ስምዖን የነሱን የረሰበርስ ጦርነት ሲሰማ ሠራዊቱን ወደዚሁ ማዞር ጀመረ ከአይሁድ መካከልም ወደ ጥጦስ ሄዱና እኛ የቤተመቅደስን ቅፅር እንከፍትልሃለን አንተ ደግሞ አልአዛርን ስምዖንና ሐናን አስወግደህ በሰላም አኑረን አሉት ጥጦስ ግን አላመናቸውም አይሁዶቹ እንደገና ጥጦስ ይገባል በማለትና አይገባም በማለት ለሁለት ተከፈሉ::

ከሮማውያን ወታደሮች መካከል የአይሁድን መለያየት ሲረዱ ጥጦስ ሳያውቅ ወደ ቤተመቅደስ ቅፅር ተጠጉ የሐናን አልአዛርና ስምዖን ለአንድ አፍታ ግንባር ፈጥረው እነዚህን የሮማውያን ወታደሮች በዲንጋይ ወግረው አባረሯቸው ለሮማውያኑ በር ከፍተው ለማስገባት የተሰለፉትም አይሁድ አብረው ተደበደቡ ግማሾቹ ደግሞ ተመልሰው ሮማውያንን ደበደቡ የሮማውያኑም ወታደሮች ሸሹ ስለሸሹም አይሁድ እየተከታተሉ መጥፎ ስድብን ሰደቡዋቸው::

ጥጦስ እሱ ሳያዛቸው ሄደው ሽንፈትንና ውርደትን ተከናንበው የተመለሱትን ወታደሮቹ እጅግ ተቈጣቸው የአይሁድን ተንኮል ሳታውቁና



www.ethiopianorthodox.org

የኔንም ትእዛዝ ሳትቀበሉ በመሄዳችሁ ጥፋተኞች ናችሁ ትእዛዙን ያለከበረ ልጁን የገደለ ንጉሥ እንዳለ ታውቃላችሁ ስለዚህ እናንተም ትእዛዝ ባለማክበራችሁ ሞት ይገባችኋል አላቸው እነሱም በስሕተት ከባድ በደል መፈፀማቸውን አምነው ይቅርታን ጠየቁት።

## ምዕራፍ ፲፩

## የመጀመርያው የቤተመቅደስ ቅፅር መፍረስ ታሪክ

ጥጦስ የአይሁዶቹን መለያየት ሲሰማ ወታደሮቹ ከመጀመርያው ቅፅር ደርሰው እንዲያፈርሱት አዘዘ በየመንገዱም አደገኛ ጉድጓድን አስቆፈረ እንዳይታወቅም በቀላል ነገር ጉድጓዱን ሸፈነው አይሁድ በመካከላቸው ባለው ጠብ ደክመው ይህን የጥጦስን ተንኮል አልተከታተሉትም ባንድ በኩል ስምዖንና አልአዛር ሐናንን ለመውጋት ብቻ ግንባር ፈጥረው ነበር ሐናን ስድስት ሺ ወታደሮችንና አራት መቶ የጦር አዛገሮችን ይዞ ሀገረ ቆድሽን ሲገዛ ጀምሮ ነበር።

ስምዖን በበኩሉ መቶ ሺ አይሁዶችንና አምስት ሺ ሮማውያንን ይዞ ሉብቻ ነበር አብዛኞቹ ካህናት አልአዛርን በመደገፍ ነበሩ የቀሩት ደግሞ ሚናቸው ያልታወቀ በሦስቱ መካከል ሁነው ማሕል ሰፋሪዎች በመሆን ይገኙ ነበር አልአዛር ስምዖንና ሐናን ግን እንደመጀመሪያው ሮማውያንን ለመዋጋት ተሰለፉ ሮማውያን እንደተለመደው ሚናችንን እንለያለን ተባባሉ ጥጦስ ቤፋበር የተባለውን መልክተኛውን ልኮ ለአይሁዶች ሰላምን እንደሚፈልግ ይነግርለት ዘንድ ነገረው ቢፋቤር ከአይሁዶች ሲደርስ አንዱ አይሁዳዊ በጦር ወግቶ ገደለው። ጥጦስ በዚሁ እጅግ ተናደደ ትልልቅ የብረት መወጣጫንም በማበጀት ወደ መጀመሪያ ቅፅር አስጠጋ። አይሁድ ይህን ተመለከቱና ሕብረትን ፈጠሩ ሐናን ስምዖንና አልአዛርም በአንድነት ለመሰለፍ ተገደዱ የብረት መወጣጫውንም ለጥጦስ የሰሩለትን ሁሉ ገደሉ ጦርነትንም ከሮማውያን ጋር



በመግጠም ሮማውያንን ከቅጽረ ቤተ መቅደስ አራቋቸው። ይህን አድርገው ወዲያው አልአዛር ስምዖንና ሐናን መዋጋት ጀመሩ በዚህም ከሮማውያን ጋር ያላቸውን ጥላቻ ዘነጉት።

ጥጦስ ሁኔታቸውን አወቀ ያ የብረት ምስልን እንደገና ወደ መጀመሪያው የቤተመቅደስ ቅፅር አስጠጋው የመጀመሪያውንም ቅፅር ደርምሶ ገባ የተደረመሰውንም ቅፅር እንደልብ ለመግባት ያመች ዘንድ አሰፋው። ስምዖን፣አልአዛርና ሀናን ይህን ሲመለከቱ እንደገና ተባበሩ። ወታደሮቻቸውንም ለጥበቃ አሰማሩ፡ ጦርነት ተከፈተ ጥጦስ እጅግ ጨክኖ ተዋጋ ወታደሮቹ በጥብአት እንዲዋጉም ብዙ ገንዘብን ሰጣቸው ሦስቱ የአይሁድ አለቆች (ስምዖን ሃናንና አልአዛር ወታደሮቻቸውን በጥብአት አስከትለው ተዋጉ ‹‹ስምዖን ፈርቶ የሸሸ ወታደር ከተገኘ ንብረቱ ይዘረፋል›› በማለት አስጠነቀቀ።

የስምዖንን ማስጠንቀቂያ የሰማ ጥጦስ ሐናን መሽጎ ወደሚዋጋበት ቦታ ሄደ በዚሁም አቅጣጫ የተለየ ጥቃት ማድረስ ሞክሮ አልተሳካለትም አይሁድ ተባብረው በመውጋት መለሱት ይህንን ለማስገቢያ ሮማውያን ያፈረሱትን ቅጽርም በጥብቅጠበቁት ጦርነቱ ለአራት ቀን ቀጠለ በአራተኛውም ቀን ሌሎች አህዛብ ወደጥጦስ ተጨመሩ ጦርነቱንም አከበዱት አይሁዶችም በዚሁ ተቸንፈው ለመሸሸ ተገደዱ።

## ምዕራፍ ፲፪

## ጥጦስ አይሁድን ይታዘዙ ዘንድ እንደጠራቸው

አይሁድ አገራቸውን ጥለው የትም መሄድ እንደሌለባቸውና በሰላምም ለመኖር እንደሚችሉ ላከባቸው እንዲህም አላቸው «ለሮም መንግስት ታዛኘርነታችሁን ብቻ አረጋግጡ እንጂ በሰላም ለመኖር ትችላላችሁ አገራችሁም አትመዘበርም ቤተመቅደስም አትደመሰስም » እነሱ ግን አባባሉን አልተቀበሉም ጥጦሥ የነሱን ቁርጠኛ መልእክት ለመቀበል ለአምስት ቀን ያህል ጠበቃቸው በአምስተኛው ቀን ግን ለጦርነት ተዘጋጅቶ ወደ አገራቸው ተጠጋ ሲጠጋም



www.ethiopianorthodox.org

እነዋጋ ያሸነፈም ያሸንፍ የእግዚአብሔር ቤተመቅደሰን ግን አክብሩት የጦርነት አውድማም አታድርጉት ደምንም በማፍሰስ ቤተመቅደሱን የማድረግ ፈሊጣችሁ ይቁም የአምልኮቱንም መባ ከሱ አታጥፉ፡፡

እኛ ይህንን አልፈቀድንም ልንወጋችሁም አልመጣንም የምንዋጋችሁ ያለነው ለኛ የተለመደውን መታዘዛችሁ ስላቋረጣችሁ ብቻ ነው የኛን መዋጋቱ ከሰለቻችሁ ለኛ ተገዙና በሰላም ኑሩ ትእዛዛችንንም አክብሩ››

ሐናን በዚህ ጊዜ ለጥጦስ ገለፃ የሚከተለውን መልስ ሠጠ ‹‹ለዚህ ቤተመቅደስ ሌላ የከበረ መሥዋዕትነት ለማቅረብ ተዘጋጅተናል ለቤተመቅደስ መሥዋዕት የሚሆነው የኛ ደም ነው›› ጥጦስ ለሐናን የሚከተለውን መልስ ሠጠው እናንተ በዓመፅና በተንኮል የተሞላችሁ የገዛወገኖቻችሁን አይሁድ ደም በግፍ ያፈሰሳችሁ የለያላችሁ አረማውያን ናችሁ የናንተን ደም እግዚአብሔር በመሥዋዕትነት ይቀበለዋል እንዴት ትላለህ እግዚአብሔር ንፁሑን መሥዋእት ነውር የሌለው ቁርባንን እንደሚቀበል ተፅፏልና፡፡

በናንተ ሕይወት ላይ በዓለም አለ የተባለ ነውር ሁሉ ተጠራቅሟል ያልፈፀማችሁት ነውር የለም የመቅደስ ልዕልና በነውረኞችና ርኩሳን እናንተ ሊነገር አይገባውም ቤተመቅደሱን ያረከሳችሁ እናንተ ናችሁ አሁንም ጦርነታችሁ ስለቤተመቅደስ ሊሆን አይገባም ቤተመቅደስን ለማፍረስ እናንተ ተዘጋጅታቹኋል ስለቤተመቅደስ አይደለም መዋጋት ያለባችሁ ስለአገራችሁ ነው መዋጋት ያለባችሁ ይህ ከሆነ ከቤተመቅደስ ውጡና በሌላ ቦታ እንዋጋ፡፡

ብርቱ ሰው ደካማውን ይደግፋል ከሱም ችግርን ያስወግዳል እናንተ ግን በናንተ ሰበብ ቤተመቅደስ እንዲደመሰስ መጠጊያ አደረጋችሁት ከናንተ መካከል የቀረበለትን ማዕድ እሱ ሳይፈቅድ እንዲያነሱበት የሚወድ አለን የእግዚአብሔርን መባስ ለማጥፋት እንዴት ትዘጋጃላችሁ የእግዚአብሔርን



መባ ማጥፋት ማለት ቤተመቅደስን የጦር አውድማ ማድረግ ነው አሁንም ልንገራችሁ እኔ የመጣሁት ቤተመቅደስን ለማስፈረስ አይደለም አገራችሁንም ለማጥፋት አይደለም አመጣጤ ከናንተ ጋር ሰላምን ለመመሥረት ነው ለኛ አንታዘዝም ማለታችሁንም ለማስቀረት ነው የመጣሁት እኛ ከሌሎች አህዛብ ያላያችሁትን ትሕትና አሳይተናቹኋል በትሕትናም ሁሉን ከናንተ ጠይቀናል እናንተ ግን ለዚሁ ያልጠበቅነውን የጠላትነት መልስ ሠጣችሁን ጦርነትንም ገጠማቹን የኛ ባህል በጦርነት ያቸነፍነው ሁሉ በርሕራሄ እንክብካቤ ማድረግ ነው፡፡የናንተን ንጉስ የባቢሎኑ ነገስ ናቡከደነፆር በከበበው ጊዜ ቤተመቅደስን እንዳይደመስስበትና በሕዝቦቹም ላይ እልቂትን እንዳያደርስበት አስቦ እጁን ሠጠው በዚሁም ሕዝቦቹን ከእልቂት አዳነ ንጉስ ሴዴቅያስም ሕዝብን አታስጨርስ እጅህን ለናቡከደነፆር ሥጥ ስላሉት እጁን ሠጥቶ ሕዝቦቹን ከመጨፍጨፍ አድኗል እናንተም በነዚህ ሁለቱ ነገስታት መንገድ ልትሄዱ ይገባቹኋል ለራሳችሁና ለሕዝባችሁም እዘኑ፡፡

እንደተለመደው ለኛ ተገዢነታችሁን ከገለፃችሁ ሰላም ይሆናል እኔ እናንተን ከእግዚአብሔር ፊት ባዲስ ቃልኪዳን እማፀናችሁ አለሁ በእግዚአብሔር ስምም እለምናችሁ አለሁ በናንተ ላይ የተቃጣውን እልቂትም ሆነ እስካሁን በኛ ላይ የፈፀማችሁትን ክህደት ሳንቆጥር በሰላም እናንተን ለመቀበል ተዘጋጅተናል፡፡ሰላም ፈላጊ መሆኔን ለማረጋገጥ ዮሴፍ ወልደኮሪዮንን በካህንነት እሠጣችሁ አለሁ ሌሎችንም የናንተ ወገኖች ሁነው በወዳጅነት ከኔ ጋር ያሉትን ሁሉ ልሰጣችሁ፡፡

ንብረታችሁ ከውድመት ቤተመቅደሳችሁ ከመደምሰስ ዜጎቻችሁን ከእልቂት የምትታደጉበት ጊዜ አሁን ነው እኔ በምሠጣችሁ ምክር ከተመራችሁ ሥርዓተ ዓምልኮታችሁን በሥርዓት እየፈፀማችሁ በሰላም



www.ethiopianorthodox.org

ትኖራላችሁ፡፡ይህን ምክር እግዚአብሔርን ምሥክር በማድረግ ነው የምመክራችሁ›› እያለ ጥጦስ ብዙ ለመናቸው፡፡

ጥጦስ በላቲን ቋንቋ ይህን ሁሉ የማግባቢያ ቃል ሲገልፅ በእብራይስጢ እየተረጎመ ይገልፅላቸው የነበረው ዮሴፍ ወልደኮሪዮን ነበር፡፡ ዮሴፍ ወልደኮሪዮን ካህን ነበር የጥጦስን ገለፃ ሲተረጉሞላቸው አባባሉን እንደማይቀበሉት አስቀድሞ ሲረዳ በመቻሉ ያለቅስ ነበር፡፡ የራሱንም ወቀሳ እየጨመረ ‹‹እናንተ በዳንኤል የተነገረውን ትንቢት ፈፃሚዎች ልትሆኑ ነው በናንተ ሰበብ እቺ ቤተመቅደስ ለመጨረሻ ጊዜ ልትደመሰስ ነው ይህ ባይሆን ኑሮ እግዚአብሔር ምድራዊውን ሥልጣንና ሐይል ለሠጣቸው ኃያላን ተገገርነታችሁን ባረጋገጣችሁ ነበር›› አላቸው፡፡

እነዚህ ዓመፀኞችና ጨካኞች የአይሁድ ወገኖች ስምዖንና መሰሎቹ ከጥጦስና ከካህኑ ዮሴፍ ወልደኮሪዮን የተደረገላቸውን ገለፃና ልመና በምንም ዓይነት ለመቀበል ፈቃደኞች አልሆኑም ብዙዎች ከካህናትና ከአይሁድ ወገኖችግን አጋጣሚውን ተጠቅመው እጃቸውን ለጥጦስ ሠጡ ጥጦስም እነዚህን በፈቃዳቸው እጃቸውን የሠጡት በሮማውያን ወታደሮች የብቀላ እርምጃ እንዳይወሰድባቸው አስጠነቀቀላቸው በመልካም ሁኔታም እንክብካቤ ይደረግላቸው ዘንድ አደረገ፡፡ አመፀኞቹ እነስምኦን ሰው ሁሉ ሕይወቱን ለመታደግ ንቅንቅ ብሎ ሲወጣ መሆኑን ሲመለከቱ የቤት መቅደሱን በር ዘግተው እንዳይወጣ ከለከሉት፡፡



## ምዕራፍ ፲፯

## የኋለኛው አይሁድ ከሮማውያን ጋር ያደረጉት ጦርነት ታሪክ

ጥጦስ የብዙዎች ህይወታቸውን ካሰቃቂ ጦርነት ዕልቂት ለመታደግ መሽቀዳደምንና የዓመፀኞቹ የአይሁድ መሪዎች እንዳይወጡ እነሱን መከልከል ሲመለከት ወደ ፈረሰው የቤተ-መቅደስ ቅፅር ከዮሴፍ ወልደኮሪዮን ጋር በመጠጋት እንደገና ‹‹ባካችሁ እልቂትን አትፈልጉ ለመውጣት የሚፈልጉትንም አትከልክሉዋቸው›› በማለት ዓመፀኞቹን መሪዎች ለመናቸው ለመውጣት ፈልገው በሩ የተዘጋባቸው አይሁድ ዮሴፍ ወልደኮርዮንን አሻግረው እየተመለከቱ እኛ በሐጢአታችን ለዚሁ መከራ እግዚአብሔር እንዳዳረገን እናውቃለን ዐቅም ሳይኖረንም ሮማውያንን መክዳታችን በድለናል አሁንም አንተ ለጥጦስ ነግረህ ከሞት የምንድንበትን መንገድ ፈልግልን እኛ ወደሱ ለመግባት እንሻለን መሪዎቻችን ግን እንዳንወጣ በር ዘግተውብናል እያሉ አለቀሱ፡፡

ዐመፀኞቹ የአይሁድ መሪዎች የነሱን የጭንቀት ዋይታ ሲሰሙ ሊገድልዋቸው ተሽቀዳደሙ ሮማውያኑም የአይሁዶቹን በወገኖቻቸው ከማለቅ ለመታደግ እየዘለሉ ዓመፀኞቹን ጦርነት ገጠሙዋቸው ነገር ግን ዓመፀኞቹ የአይሁድ መሪዎች ሮማውያኑን አሸነፍዋቸው ሮማውያኑም ሸሽተው ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ገቡ፡፡ ቅድስተቅዱሳን ከዚሁ ዕለት በፊት ተደፍሮ አያውቅም አይሁድም ተከታለው በቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ ተዋጉዋቸው፡፡

ጥጦስ በዚህ ጊዜ ከአምባገነኖቹ አንዱ የሆነውን ዮሃናን አንተ ከሊቀ ካህናት በቀርለ ሌላ ያልተፈቀደውን ቦታ አስደፈርክ አሁንም ወደዚሁ

www.ethiopianorthodox.org

እናንተ እንደምታውቁት የአቤል እድሜ አጠረ።ወደዕረፍትም ሄደ ለዘለዓለምም ኖረ ከሓላፊው ዓለም ድካምም ተላቀቀ ቃየል ግን በዚህ ዓለም ብዙጊዜ ኖረ ነገር ግን ብዙ ዘመን መኖሩ አልጠቀመውም መላ ዕድሜውን በሌብነት በተሳዳቢነትና በፈሪነት ነው የፈፀመው ሲሞትም ወደ ኩነኔ ተወሰደ እንደዚሁም ሁሉ ለኛ መጥፎ አኗኗር የምንኖርበትን ዕድሜ አያስፈልገንም ተሎ ወደዘለዓለማዊ ሕይወት የምንደርስ ከሆነ ሞትን አንፈራም።

ነፍስ በሥጋ የታሠረች መሆንዋን እናውቃለን በአጥንትና ጅማቶች የተተበተበች መሆንዋንም እንረዳለን ነገር ግን በዚሁ አኳኋን መታሰርዋን ሥጋን ትመራውና ታስተዳድረው ዘንድ ነው። ሥጋ የነፍስን ምንነት አያውቅም መቼ ከሱ ዘንድ መጥታ እንዳደረችም አይረዳም ነፍስ ከሥጋ ልዩ ናት ከሱም ትከብራለች ከሱ መመሳሰልም እጅግ የራቀች ናት ነፍስ ልዕልናን የተጎናፀፈች ንእድ ክብርት ናት ሥጋ ግን ምድራዊ ነው ምድራዊ ደግሞ ያለነፍስ ሊኖር አይችልም ነፍስ ከሥጋ ጋር ባለችበት ሁሉ ደግሞ እስረኛ ናት ሥጋ ወደ ምግባረ ሐጢአት ስትወድቅ የነፍስ ፈቃድ ስላይደለ ነፍስ ትከፋለች።

ነፍስ የሥጋን ፈቃድ ለመፈፀም ከተሰለፈች ግን የመሞቻዋ ምክንያት ይሆናል በሚመጣው ዓለም የመጥፋቷ አቢይ ምክንያት ይሆናል ለሥጋ አልታዘዘም ካለች ግን ከሞት ወደ ህይወት ትሸጋገራለች በዚህም ነፍስ ደስ ይላታል ደገኛዋ ነፍስ ከሥጋ ስትለይ ከእሥር እንደተፈታች ያህል ትደሰታለች ከምርኮ የተለቀቀና ነፃ የሆነ ሰው ያህልም ደስ ይላታል። ከባርነት ነፃ እንደወጣ ባርያም ትደሰታለች ከሥጋ ጋር ታሥራ በነበረችበት ሁሉ ነፃነት አልነበራትምና።



የንጉሥ ባርያ እንደ እቃ አገሌን አገልግለው ተብሎ ለሌላ ይሰጣል የተፈቀደበትንም የአገልግሎት ዘመኑ ሲፈፅም ወደ ከበረው የጌታ ቤት በመመለሱም ደስ ይሰኛል ከጌታ ከራቀ ምንም ሥልጣን አይኖረውም እንደ ስድተኛ ይቆጠራልና የተላከበትንም አገልግሎት ዘመኑ ሲፈፅም ወደ ከበረው የጌታ ቤት በመመለሱም ደስ ይሰኛል ከፊቱ ከራቀ ምንም ሥልጣን አይኖረውም እንደስደተኛ ይቆጠራልና እንደዚሁ ሁሉ በግብዓተሥጋ የታሰረች ነፍስም የፈጠራት ጌታዋ ነይ ተመለሺ ሲላት ትደሰታለች በሞት ከሥጋ ስትለይ ወደ ብርሃን ትገባለች ይህ መኖሪያዋና መቀመጫዋ ነውና።

ነፍስ ወደ ብርሃን ስለምትሄድ ሰው ሲሞት የሕንድ ምሁራን አያለቅሱም በአንፃሩ ከባርነት ወደ ነፃነት ከድካም ወደ እረፍት ተሸጋገረች \ነፍስ\ ከሚያልፍ ዓለም ወደማያልፍ ዓለም ተሸጋገረች በማለት ይደሰታሉ እነዚህ በእግዚአብሔር የማያምኑ አሕዛብ ሞትን የማይፈሩ ከሆኑ እኛ ከነሱ የምንሻለውና እግዚአብሔርን የምናምን ነው የኋላኛውም ደስታ መኖሩን እየተረዳን ፈቃዱን ለመፈፀም ዋጋን እግዚአብሔር እንደሚከፍል እያወቅን እንዴት ሞትን እንፈራለን ለሮማውያንስ መገዛትን እንዴት ትሻላችሁ በሮማውያን ማመፁን በግሪክ ዘመን ብታደርጉት ኑሮ ለዚህ ውርደት ባልተጋለጣችሁ ነበር።

ከዚያ ወዲህ ሞተ ነፍስን አረፋችሁ ብዙ ጥፋትም በናንተ ላይ ደርሷል ጥጦስንም እንድትታዘዙት ጠርቷችሁ ነበር። ነገር ግን እምቢ አላችሁት መልካም ነገርንም ተናግራችሁ በክብር ሲጠራችሁ ብትታዘዙት ኑሮ ስህተት ባልሆናችሁ ነበር። እንደ ውርዴትም ባልተቆጠረባችሁ ነበር ምክንያቱም እሱ የንጉሥ ልጅ ንጉሥ ነውና። ነገር ግን ይህን ለመቀበል ፈቃደኞች አልሆናችሁም በሱ ባለመታዘዛችሁም የብዙ ህዝብ ደም ፈሰሰ አገር ጠፋ እንዳልነበረም ሆነ በሕዝበ አይሁድ ያልደረሰ አሰቃቂ መከራ

www.ethiopianorthodox.org

በክብር መሞትን እንመረጣለን አሉ።። ከዚህ በኋላ ሴሲቱን ሙሉ የመሰነባበቻ ልቅሶን ሲያለቅሱ አደሩ።ሲነጋ ወንዶቹ አይሁዶች ልጆቻቸውንና ሚስቶቻቸውን በገዛራሳቸው ገድለው ጨረሱዋቸውና በየጥልቅ ጉድጓዱ አስክሬናቸውን በመክተት አፈር አለበሱዋቸው ነፍሳችውን ለአህዛብ ከመስጠት ለእግዚአብሔር ሠጡ በመጨረሻም ወንዶቹ ከሮማውያን ጋር እየተዋጉ አንድም ሰው ከመካከላቸው ሳይማረክ በጦር ሜዳ አለቁ።

በዳግም ቤተ-መቅደስ ላይ ተመስርቶ የአይሁድን ታሪክ ዮሴፍ ወልደኮሪዮን የፃፈበት መፅሐፍ ከዚህ ላይ ተፈፀመ። ዮሴፍ ወልደኮሪዮን በኋላ ስለነሱ የአይሁድ ነገሥታት ስም ቅደም ተከተል ዳግማዊው ቤተ-መቅደስ ከተሠራ በኋላ ስለተፈፀሙ ታሪኮችና የአይሁድ ወደዚሁ መመለስንም ገልጿል ለልዑል እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይድረሰው አሜን።

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org